# ክርስቲያናዊ እምነት

shepherds
GLOBAL CLASSROOM

Shepherds Global Classroom የክርስቶስን አካል ለማነጽ በዓለም ዙርያ ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎች ሥርዓተ ትምህርትን ለመስጠት ያለመ ተቋም ነው። ዓላማችን አገር በቀል የኾኑ ማሠልጠኛ መርሓ ግብሮችን ለማብዛት 20 ትምህርቶች ያሉት ሥርዐተ ትምህርት መሣርያዎችን በማዘጋጀት በኹሉም አገራት ያሉ መንፈሳዊ አሰልጣኞች እጅ ላይ ተደራሽ ማድረግ ነው።

ይህ ትምህርት በነጻ በዚህ ማስፈንጠርያ ማግኘት ይቻላል https://www.shepherdsglobal.org/courses

ዋና ጸሐፊ፥ Dr. Stephen K. Gibson

በዚህ ትምህርት ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ሐሳቦች ኣምናለሁ፣ ኦሃዮ የሚገኘው የእግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እና ኮሌጅ መምዕራን፥ ከሚል መጽሐፍ ውስጥ የተወሰዱ ናቸው።

የቅጂ መብት © 2025 Shepherds Global Classroom

የተተረጎመው ከ4ኛ ቅጂ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ የተተረጎመ

መብቱ የተጠበቀ ነው።

**የፈቃድ መግለጫ**

ይህ ትምህርት በሚከተሉት መርሖች ሥር በወረቀትም ኾነ በዲጅታል በመልኩ ታትሞ መሠራጨት ይችላል፤ (1) የትምህርቱ ይዘት በምንም መንገድ መለወጥ የለበትም፤ (2) ቅጂዎች ለትርፍ መሸጥ አይችሉም ፤ (3) የትምህርት ተቋማት ይህን ትምህርት መጠቀም ሆነ ቅጂውን፥ የትምህርት ክፍያ ቢያስከፍሉም መጠቀም ይችላሉ፤ እና (4) ይህ ትምህርት ያለ Shepherds Global Classroom ፈቃድ እና ክትትል መተርጎም አይፈቀድም።

# ማውጫ


የትምህርቱ ጠቅላላ ዕይታ ........................................ 5

(1) የእግዚአብሔር መጽሐፍ ........................................ 9

(2) የእግዚአብሔር ባህሪያት ........................................ 23

(3) ሥላሴ ........................................ 31

(4) ሰው ........................................ 47

(5) ኃጥያት ........................................ 55

(6) መናፍስት ........................................ 63

(7) ክርስቶስ ........................................ 71

(8) ድነት ........................................ 85

(9) በድነት ዙርያ ያሉ ጉዳዮች ........................................ 95

(10) መንፈስ ቅዱስ ........................................ 107

(11) ክርስትናዊ ቅድስና ........................................ 117

(12) ቤተክርስቲያን ........................................ 129

(13) ዘላለማዊ እጣ ........................................ 137

(14) የመጨረሻ ሑነቶች ........................................ 143

(15) ጥንታዊ የእምነት መግለጫዎች ........................................ 151

የሚመከሩ ምንጮች ........................................ 159

የቤት ስራዎች መዝገብ ........................................ 163

# የትምህርቱ ጠቅላላ ዕይታ

**የትምህርቱ መግለጫ**

ይህ ትምህርት መሰረታዊ የሆኖ በክርስትና ስነመለኮት ምድብ ውስጥ እንደ እግዚአብሔር፥ ክርስቶስ፥ ሀጥያት ፥ ድነት እና ሌሎች ዋና አስተምሮዎችን ያስረዳል። ተማሪዎች በአስተምሮ ላይ ያሉ ስዕተቶችን ማስወገድን ይማራሉ። ተማሪዎቸ ሌሎችን ስለ ክርስቲያናዊ አስተምሮ ሌሎችን ለማስተማር ብቁ ይሆናሉ።

**የትምህርቱ አላማ**

(1) የክርስትና እምነት መሰረታዊ አስተምሮዎችን መማር

(2) መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ እንደ አስተምሮ ምንጭ እና ባለስልጣን በሚገባ ይጠቀማሉ

(3) በአስተምሮ ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ስዕተቶችን ያለያሉ

(4) ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማጣናከር የሚረዳ መረዳትን ይገበያሉ

(5) ሌሎችን ለማስተማር የሚረዳ ይዘት እና ቅርፅ ያገኛሉ

**ለክፍል መሪዎች የሚሆን መምሪያ**

እያንዳንዱ ትምህርት 90 ደቂቃ እንደሚወስድ እንገምታለን። ትምህርቶቹ በሁለት ክፍለ ግዜ ለቡድኑ መስጠት የተሻለ ነው። ቡድኑ ሁለት ግዜ ቢገናኝ፥ አንዳንድ መምሪዎች ሊስተካከሉ ይገባል። ለምሳሌ ሁለቱም ግዜ ፈተና መሰጠት የለበትም።

እያንዳንዱ ተማሪ ይህ መጽሐፍ በእጁ ላይ ሊኖር ይገባል።

ለክፍል መሪዎች የሚሆኑ ማስታወሻዎች ስለ ትምህርቶቹ የተወሰኑ ክፍሎች መመሪያዎችን በመያዝ በመላው ኮርሱ ውስጥ ተካተዋል።. እነሱ በኢታሊክ ተጻፈዋል።

በከፍለ ግዜው መጀመርያ ላይ - ያለፈውን ትምህርት መሰረት ፈተና ስጡ። እያንዳንዱ ተማሪ ያለምንም እርዳታ ፈተናውን መመለስ ያለበት የተማረውን በማስታወስ መሆን አለበት። ተማሪው ፈተናውን ማለፍ ካልቻለ፥ ሌላ ግዜ እንዲፈተን ዕድል መስጠት (በግምት የሚሰጥ ግዜ - 10 ደቂቃ)። የፈተና መልስ ቁልፍ ከ ShepherdsGlobal.org ማውረድ ይቻላል።

ከፈተናው በሓላ፥ ካለፈው ትምህርት አላማ ዝርዝር እንደ ማጥኛ ጥያቄዎች ተጠቀሙ። ከእያንዳንዱ አላማ ጥያቄ ተማሪዎችን በመጠየቅ ተማሪዎች እንዲያስረዱ ፍቀዱ (በግምት የሚሰጥ ግዜ ፤ 15 ደቂቃ)።

አዲስ ትምህርት የተሰጠውን ክፍል በማንበብ ጀመሩ፤ ተማሪዎችም ስለ ትምህርቱ ይዘት ክፍሉ የሚናገረውን እንዲወያዩ አድርጉ (በግምት የሚሰጥ ግዜ- 10 ደቂቃ)

*ትምህርቱ ማስተማርያ መፅሐፍ ውስጥ እያንዳንዱን ክፍል በማንበብ እና በማስረዳት ተመልከቱ። የክፍሉ አባላት አንዳንድ ዘርፎችን ማስተማር ይችላሉ ( በግምት የሚሰጥ ግዜ- 45 ደቂቃ)*

*በዚህ ትምህርት ውስጥ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ዘርፎች ጥቅም ላይ ውለዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ዘርፎች ማጣቀሻ በቅንፍ ውስጥ አንብብ ከሚለው ጋር ያሉት በክፍል ውስጥ ጮክ ተብሎ መነበብ አለበት። ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ዘርፎች ግን በማስተማርያው መጽሐፍ ውስጥ ያለውን ላለው ሃሳብ ድጋርፍ ሚሰጡ ናቸው። ሁል ግዜ በክፍል ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎቸን መመልከት እና ማንበብ አስፈላጊ አይደለም።*

***የውይይት ጥያቄዎች** እና **የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴዎች ►** በዚህ ምልክት ይለያሉ። አንዳዴ የውይይት ጥያቄዎች የትምህርቱን ክፍል ያስተዋውቃሉ፤ ሌላ ግዜ በክፍል ውስጥ የነበረውን ትምህርት ይከልሳሉ። የክፍሉ መሪ ጥያቄዎችን መጠየቅ አለበት እና ለተማሪዎችም መልሱ ላይ እንዲወያዩ ግዜ መስጠት አለበት። በዚህ ግዜ መልሱን ሙሉ ለሙሉ ማስረዳት አስፈላጊ አይደለም፥ በተለይ ጥያቄው ለክፍለ ግዜው መግቢያ ከሆነ።*

*በክፍለ ግዜው መጨረሻ ላይ ሙሉ ክፍሉ አብሮ ሁለት ጊዜ 'የእምነት መግለጫውን' ያንብብ።*

*በእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ ላይ- እያንዳንዱ ተማሪ ከተዘረዘሩት መካከል አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይመደባል። ከሚቀጥለውን ክፍለ ግዜ በፊት፤ ክፍሉን አንብቦ እና አንድ አንቀፅ ክፍሉ ስለ ትምህርቱ ርዕሰ ጉዳይ ስለሚናገረው ይፃፍ። የፃፉትንም አንቀፅ ለክፍሉ መሪ በሚቀጥለው ክፍለ ግዜ ያሳዩ።*

*ቢያንስ ለሶስት ግዜ ተማሪው ይህንን ትምህርት ወይም የትምህርቱን አንድ ክፈል በክፍል ውስጥ ለሌሉ ሰዎች ያስተምር። ይህም በቤተክርስቲያን ውስጥ ላለ ክፍል፥ ለቤት ለቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ወይም ሌላ ስብስብ ውስጥ መሆን ይችላል። በእያንዳንዱ ክፍለ ግዜ ማለቂያ ላይ ተማሪዎችን ስለ ቤት ስራ ማስታወስ እንዲሁም ካለፈው የትምህርት ግዜ በሓላ ያስተማሩት ቡድን ካለ ሪፖርት እንዲያደርጉ ጠይቁ።*

*በክፍለ ግዜው መጨረሻ ላይ ቀጣዩን ትምህርት ከሚቀጥለውን ክፍለ ግዜ በፊት አንብበው እንሚመጡ አስታውሷቸው (ለማሳሰቢያ እና ለቤት ስራ የሚያስፈልገው ግዜ በግምት - 10 ደቂቃ)*

*ተማሪዎች ክፍለ ግዜውን የመሳተፍ እና የቤት ስራቸውን በግዜ የመስራት ግዴታ አለባቸው። ተማሪ ክፍል ከቀረ፥ ያለፈውን ትምህርት ማጥናት፥ ፈተናውን መስራት እና የቤት ስራውን መፈፀም አለበት። በትምህርቱ መጨረሻ ላይ የተሰጡ እና የተጠናቀቁ የቤት ስራዎችን መመዝገቢያ ቅፅ አለ።*

***ለተማሪዎች መምሪያ***

*ለትምህርት ወደ ክፍል ከመምጣታችሁ በፊት በውይይቱ ላይ በተሻለ ግንዛቤ መሳተፍ እንድትችሉ የተሰጠውን መማርያ አንብባችሁ መምጣት አለባችሁ።*

*በእያንዳንዱ ክፍለ ግዜ መጀመርያ ላይ ያለፈውን ትምህርት መሰረት ፈተና ስለሚኖር በተሰጠው የማጥኛ ጥያቄዎች መሰረት ተዘጋጁ።*

*ወደ ክፍል ስትመጡ መጽሐፍ ቅዱስ፥ በታተመ የትምህርቱን ቅጂ እና የራሳችሁን ማስታወሻ መጨመር የሚያስችላችሁ እስኪብርቶ ይዛችሁ ወደ ክፍል መምጣት አለባችሁ።*

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎትን ለማጣቀስ፥ የውይይት ጥያቄዎችን ለመመለስ እና የክፍሉ መሪ በሚመራው መንገድ ለመሳተፍ ተዘጋጅታችሁ መምጣት አለባችሁ።

በእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ ላይ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይመደብላችሃል፤ ከሚቀጥለውን ክፍለ ግዜ በፊት ክፍሉን አንብባችሁ፤ በአንድ አንቀፅ ስለ ትምህርቱ ዋና ሃሳብ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉ የሚለውን በማስቀመጥ፤ ለክፍሉ መሪ ማሳየት።

ትምህርቱ በሚሰጥበት ወቅት ቢያንስ ሶስት ግዜ የተማሩትን ትምህርት ወይምን የተመረጠ ክፍል በመውሰድ በክፍሉ ውስጥ ለሌሉ ሰዎች ማስተማር አለባቹ። ይህንም የማስተማር ሀላፊነት በቤተክርስቲያን ውስጥ ላለ ክፍል፥ የቤት ለቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ወይን በሌላ መንገድ ሊሆን ይችላል። ባስተማራችሁ ግዜ ሁሉ ለክፍል መሪያችሁ አስታውቁ።

# ትምህርት 1

# የእግዚአብሔር መጽሐፍ

**የትምህርቱ አላማ**

(1) ተማሪው የሚከተሉትን ማስረዳት ይችላል

- የጠቅላላ መገለጥ እና የልዩ መገለጥ ሃሳቦችን
- መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ቃል መሆኑን ማስረጃዎችን
- ቅዱሳን መጽሐፍ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተጻፉ መሆናቸው
- ቅዱሳን መጽሐፍት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተጻፉ በመሆናቸውያለስዕተት መሆኑን እንዴት እንደሚያሳይ
- በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መፃፍ፥ የማይሳሳት እና ስዕተት አልባነት የሚሉትን ቃላት
- መጽሐፍ ቅዱስ ተፅፎ ማለቁን እና ከዚህ በላይ እንደማይጨመርበት
- መጽሐፍ ቅዱስ አስተምሮ ሁሉ ምንጭ እና ባለስልጣን እንደሆነ
- መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት በዕለታዊ የክርስትያን ህይወት ውስጥ ያለውን አስፈላጊነት
- ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያናዊ የእምነት መግለጫ

(2) ተማሪዎች ስለመጽሐፍ ቅዱስ ያሉ የተሳሳት ባለስልጣናትን ከመስማት ወይም መጽሐፍ ቅዱስን በተመጠነ ጥቅም ብቻ ከማንበብ ይቆጠባሉ።

**መግቢያ**

*ለክፍሉ መሪ ማስታወሻ- በተለምዶ ክፍለ ግዜው ያለፈውን ትምህርት እና የትምህርቱን አላማ በፈተና ከመከለስ ይጀመራል- ይህ ግን የመጀመርያ ትምህርት ስለሆነ የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በማንበብ ጀምሩ።*

► መዝሙር 119፥1-16 አብራችሁ አንብቡ። ይህ ክፍል ስለመጽሐፍ ቅዱስ ምን ይነግረናል?

እግዚአብሔር፥ የአለም ሁሉ ፈጣሪ፥ ተናግሯል። ራሱን እና የፈጠረውን አለም አላማ ገልጧል። እግዚአብሔር የገለጠው እውነት መገለጥ ይባላል።

► እግዚአብሔር እውነትን ለእኛ እውነትን የገለጠባቸው አንዳንድ መንገዶች ምንድን ናቸው?

**የተለያዩ የመገለጥ መንገዶች/ አይነቶች**

እግዚአብሔር እውነትን የገለጠበት መንገድ የተለያየ ስለሆነ በሁለት መደቦች ለያይተን እናወራል:- ጠቅላላ መገለጥ እና ልዩ መገለጥ።

## ጠቅላላ መገለጥ

**ጠቅላላ መገለጥ እግዚአብሔር ስለ ራሱ በፍጥረት ውስጥ ያሳየን ነው።** በዚህ ውስጥ የእግዚአብሔርን አስደናቂ አዋቂነት እና ሃይል በፍጥረተ አለሙ ንድፍ ውስጥ መመልከት እንችላለን።

የእግዚአብሔር ታላቁ ፍጥረት የሰው ልጅ ነው። የሰው ልጅ ፍጥረት ንድፍ ስንመለከት ስለ እግዚአብሔርን አንድ አንድ ነገሮች እንማራለን። ማገናዘብ መቻላችን፥ ውበትን ማድነቃችን እና በትክክለኛ እና ስዕተት መካከል መለየታችን (በፍፁም ባይሆንም) እነዚህ ክህሎቶች ተመሳሳይ የሆነ ነገር ግን በላቀ መንገድ ፈጣሪያችን እንዳለነው ማወቅ እንችላለን። እግዚአብሔር የሚያስብ እና የሚናገር መሆኑን እኛ ተመሳሳይ ክህሎቶች ስላሉን እናውቃለን።

ጠቅላላ መገለጥ እግዚአብሔር እንደሚናገር ያሳየናል፥ እንዲሁም ልዩ መገለጥ ሊኖር እንደሚችል ያስገነዝበናል። እግዚአብሔር ስለሚናገር ከእግዚአብሔር መልዕክት እንዳለ እና መጽሐፍም ሰጥቶናል።

ጠቅላላ መገለጥ በመኖሩ ሰዎች እግዚአብሔር እንዳለ ያውቃሉ፥ እርሱንም መታዘዝ እንዳለባቸው እና አሁን ባለመታዘዝ ውስጥ እንዳሉ ያውቃሉ። (ሮሜ 1፥20-21 ያንብቡ)። ጠቅላላ መገለጥ ግን ከእግዚአብሔር ጋር ጤናማ ወደ ሆነ ግንኙነት እንዴት መድረስ እንዳለባቸው አይናገርም። ጠቅላላ መገለጥ የልዩ መገለጥን አስፈላጊነት ያሳየናል ምክንያቱም ሰዎች ሃጥያተኛ እንደሆኑ እና ምንም ሰበብ ለፈጣሪያቸው መስጠት እንደማይችሉ ያሳያል፥ ነገር ግን ስለ መፍትሔው አይነግረንም።

## ልዩ መገለጥ

> ‘ህግን ሳይሰብክ ማንም ሰው ወንጌል መስበክ ይችላል ብዬ አላምንም። በህጉ ላይ ያለውን ብርሃን ስናጨለምን ሰው ስለ ጥፋተኝነቱን ያለውን ብርሃንም እናጨልምበታለን’
>
> -ቻርልስ ስፐርጀን

**እግዚአብሔር ልዩ መገለጥን የተገለጠው በመጽሐፍ ቅዱስ እና በእየሱስ፥ በእግዚአብሔር ልጅ ነው።** ልዩ መገለጥ በጠቅላላ መገለጥ ውስጥ ሰው ያለበትን ሁናቴ ያሳየናል፤ የወደቀ እና ጥፋተኛ። ልዩ መገለጥ እግዚአብሔርን ያስረዳል፥ ውድቀትን እና ሃጥያትን ያስረዳናል፥ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር መታረቂያውን መንገድ ያሳየዋል።

መጽሐፍ ቅዱስን እንዳለ አታውቁም ብለን እናስብ፥ እግዚአብሔር ግን እንዳለ ትረዳላችሁ- ከእግዚአብሔር ጋር ችግር ውስጥ እንደሆናችሁ ታውቃላችሁ። ከሞት በሓላ ያለውን ግን አታውቁም፥ የህይወትን አላማ አታውቁም፥ እግዚአብሔርን እንዴት መቅረብ እንደምትችሉ አታውቁም።

ቀጥላችሁ አንድ ሰው አንድን መጽሐፍ አስተዋወቃችሁ እንበል እንዲሁም መፅሐፉ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ለጥያቄያችሁም መልስ እንዳለነው ነገራችሁ- ይህ መጽሐፍ ምን ያህል ዋጋ እንዳለውን መገመት ትችላላችሁ?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ

► መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ራሱ ምን ይላል? ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ጥቅሶችን እንደ ምሳሌ በማምጣት ከእግዚአብሔር ስለ መሆኑ ማስረዳቱን አሳዩ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ራሱ የሚሰጣቸውን አስረጂዎች እናውራ። ቀጥለንም መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ስለመሆኑ ያሉንን ማስረጃዎች እንመለከታለን። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ይናገራል። በብሉይ ኪዳን፥ ከ3000

በላይ በሆኑ ንግግሮች ከእግዚአብሔር መልዕክት ናቸው፥ በአብዛኛው ግዜም ‘እግዚአብሔር እንደተናገረው’[1] በማለት ተቀምጠዋል፥ እየሱስ ብሉይ ኪዳን ከእግዚአብሔር የሆነ መልዕክት እንደሆነ ተናግሯል። (ማቴዎስ 5፥17-18፥ ዩሐንስ 10፥35፥ ማርቆስ 12፥36 አንብቡ)። የአዲስ ኪዳን ፀዓፍት የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ከእግዚአብሔር እንደሆኑ ያምናሉ (ሐዋርያት ስራ 3፥18፥ 2 ጢሞትዮስ 3፥16፥ 2 ጴጥሮስ 1፥20-21 አንብቡ)። የአዲስ ኪዳን ፀሓፍት የአዲስ ኪዳን መዐሐፍት ከእግዚአብሔር እንደሆኑ ያምናሉ (1 ቆሮንጦስ 14፥37፥ 2 ጴጥሮስ 3፥16 አንብቡ)።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለራሱ የሚያቀርበውን ሃሳብ የማይቀበል፥ የተሰጠውን መረጃ መመልከት አለበት። አሁንም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አታውቁም ብቻችሁ አስቡ፥ እግዚአብሔር ከፈለገ መናገር የሚችል አካል ነው፥ ስለዚህ ከእግዚአብሔር ዘንድ መጽሐፍ ሊኖር እንደሚችል ማወቅ እንችላለን። ቀጥላችሁ አንድ ሰው አንድን መጽሐፍ አስተዋወቃችሁ እንበል እንዲሁም መፅሐፉ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ነገራችሁ።

▶ መጽሐፍ ቅዱስ በእውነት የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን በምን ታውቃላችሁ? ምን ይመስላል ብላችሁ ታስባላችሁ?

> ህጉ በሽታውን ያመላክታል፤ ወንጌል ግን ፈውስን ይሰጣል
>
> ማርቲን ሉተር

በአለም ዙርያ ሁሉ ወንጌል በሚሰበክበት ቦታ ሰዎች ስለ እውነት ውስጣዊ የሆነ ጥፋተኝነት ይሰማቸዋል። ወንጌል አምነው ሃጥያታቸውን ሲናዘዙ፥ የእግዚአብሔርን ምዕረት እና የተለወጠ ህይወት ይለማመዳሉ። ለብዙዎች መጽሐፍ ቅዱስን የማመናቸው የመጀመርያው ምክንያት ይህ ነው (1 ተሰሎንቄ 1፥5 አንብቡ)

ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ላላቸው፥ እግዚአብሔር መንፍ በቃሉ በኩል ይናገራቸዋል- መረዳትን እና መወቀስን ይሰጣቸዋል። መንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስን የሚጠቀምበት መንገድ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ያረጋግጥልናል። (ኤፌ 6፥17 አንብቡ)።

ከእግዚአብሔር ጋር በግንኙነት ውስጥ ስንኖር፥ መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል ማንነቱን እና የሚሰራበትን መንገድ ይገልጥልናል። መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነትን የምንጀምርበትን እና የምንቀጥልበትን መንገድ ያስረዳናል። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን መረጃ ነው (መዝሙር 119፥1-2 አንብቡ)።

ነገር ግን ከራሳችሁ መንፈሳዊ ልምምድ ላይ የተመሰረተ መረጃ ባትፈልጉስ? በሌላ እምነት ውስጥ ያሉ ሰዎችም መንፈሳዊ ልምምድ አላቸው፥ ነገር ግን ልምምዳቸው በእውነት ላይ የተመሰረተ አይደለም፥ የእኛ ልምምድ በእውነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን በምን እናውቃለን?

▶ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚናገር ነገሮች እውነተኝነት መረጃ አለን?

መጽሐፍ ቅዱስ ከ40 በላይ የሆኑ ፀሃፊዎች በ1500 ዓመታት ግዜ ውስጥ ፅፈውታል፥ ብዙዎቹ እርስ በእርሳቸው የማይተዋወቁ ነበሩ። ከእንደዚህ አይነት መጽሐፍ በእውኑ ምን እንጠብቃለን? የተለያዩ ስዕተቶች እና ተቃርኖዎችን ይገኛሉ ብለን እናስባለን ነገር ግን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎችን ይህንን አስተውሉ፤ በሺህ የሚቆጠሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ መልከዓ ምድሮች ተገኝተዋል፥ በሺህ የሚቆጠሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ የታሪክ

[1] ለምሳሌ ዘኍልቍ 34፥1፤ ዘኍልቍ 35፥1፣ 9 ይመልከቱ።

ሑነቶች እና ሰዎች በታሪክ ትንክርት ውስጥ ተረጋግጠውልናል፥ አንድ ግኝት የመጽሐፍ ቅዱስ ሃተታት ተፃርሮ አያውቅም፥ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በራሱ ተቃርኖ የለውም። እነዚህ ሃሳቦች ለተፃፈ ሌላ የትኛውም መጽሐፍ እውነት አይደለም። ማስረጃዎች መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ራሱ በእግዚአብሔር እስትንፋስ በኩል መፃፉን የሚናገረውን እውነት የሚያረጋግጥ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለራሱ የእግዚአብሔር ቃል መሆን የሚናገረውን እውነት የሚደግፉንን ማስረጃዎቸን በስድስት ነጥብ ማጠቃለል ይቻላል። መጽሐፍ ቅዱስ በእውነት የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እናውቃለን ምክንያቱም

- በሺህ የሚቆጠሩ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎች ተረጋግጠዋል
- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ የትኛውን እውነት የተሳሳተ መሆኑ አልተረጋገጠም
- መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በእርሱ ተቃርኖ የለውም
- ወንጌል በሚያመጣው ተፅዕኖ እውነተኛነቱ የተረጋገጠ ነው
- የእግዚአብሔር መንፈስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይናገራል
- መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ይመራል

## ‘በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መፃፍ’ን መተርጎም

► መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ነው የተፃፈው ምን ማለት ነው?

በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መፃፍ ከተፈጥሮ በላይ በሆነ እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበት ስራ እና ይህም መገለጡን በጽሑፍ መልክ መቀመጡ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መፃፍ ውጤት ነው፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች ሁሉ በተለየ መልኩ ምሪት ያለበት ነው። **የመጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መፃፍ ማለት፣ ይህም ማለት ሙሉ በሙሉ የተጠቀማቸው ቃላት ሳይቀር የእግዚአብሔር ቃል ነው ማለት ነው።**

አንዳንድ ግዜ ሰዎች የሚያስደንቅ ሃሳብ ሲመጣላቸው ራሳቸውን በምሪት ውስጥ እንደሆኑ ያስባሉ፥ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የተፃፈ ነው ማለት ከዚህ በላይ ነው።

> ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ (2 ጢሞቴዎስ 3፥16)።

መጽሐፍ ቅዱስ ከሰዎች በሰዎች እጅ ካለ ብዕር የፈሰሰ ቢሆንም፥ የዚህ ክፍል አፅንዖት የሚሰጠው ግን መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ስለ ሆነ ለአስተምሮ አስተማማኝ ነው። በጣም ምርጥ የሆኑ ሰዎች እንኳን ከሚሰሩት የተሻለ ነው።

> ከሁሉ አስቀድሞ ይህን ልታውቁ ይገባችኋል፤ በመጽሐፍ ያለው የትንቢት ቃል ሁሉ ማንም ሰው በገዛ ራሱ መንገድ የሚተረጕመው አይደለም፤ ምክንያቱም ትንቢት ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የተናገሩት እንጂ ከቶ በሰው ፈቃድ የመጣ አይደለም (2 ጴጥሮስ 1፥20-21)።

ይህ በ2 ጴጥሮስ ላይ ያሉት ቁጥሮች ፀሐፊያን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ውስጥ እንደነበሩ ይናገራል። የመጽሐፍ ቅዱስ ፀሐፊያን ትክክለኛነት በእነሱ እውቀት ላይ የተመሰረተ አይደለም። በጸሐፊያኑ መንፈስ ቅዱስ የተመሩ ወይም

የተነዱ መሆናቸው የመፅሐፉ ተአማኝነት በእግዚአብሔር ላይ የሚመሰረት እንሆነ አመላካች ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደእግዚአብሔርን ያህል ተአማኝነት ያለው ነው።

### በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መፃፍ ምን ይመስላል?

► የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊያን የእግዚአብሔርን እውነት ከመፃፋቸው በፊት የተቀበሉባቸው ጥቂት መንገዶች ምንድን ናቸው?

አንዳንድ ግዜ ሰዎች በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መፃፍ እንዴት እንደሆነ ይጠይቃሉ። እግዚአብሔር እውነቱን ያስተላለፈበት መንገድ እንዲሁም ይህ እውነት በትክክል የተከተበበት መንገድን እንዴት ነው? መጀመርያ ስለ የእግዚአብሔር መገለጥ መንገድ ልናስተውለው የሚገባ እውነታ የመገለጡ መንገድ የተለያየ መሆኑ ነው፤ በአንድ ዘዴ ብቻ መገለጡ የተደገበ አይደለም (ዕብራውያን 1፥1 ይነበብ)።

አንዳንድ ግዜ እግዚአብሔር በድምፅ ይናገራል፥ ልክ ሙሴን እንዳናገረው (ዘፀአት 33፥11)። በሌላ ግዜ ህልም እና ራዕይን ይሰጣል፥ ፀሐፊያኑም ይገልጡት ነበር።[2] ምናልባትም ከእግዚአብሔር በቀጥተኛ ፀሑፍ መንገድ የመጣው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከእስራኤል ጋር የገባው ቃል ኪዳን በራሱ ጣት የተፃፈ ነበር (ዘዳግም 9፥10)። ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ዘርፎች ቃል በቃል ከእግዚአብሔር የተሰማው የተፃፈባቸው ናቸው፥ ዘፀአት፣ ዘሌዋውያን እና ዘኍልቍ ያሉ ዋና ዘርፎች "ከዚያም እግዚአብሔር ሙሴን አለው..." ከሚል አርፍተ ነገር ይቀጥላሉ።

በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መፃፍ ማለት እግዚአብሔር በሚሰማ ድምፅ ለሰዎች የሚፅፉትን ነግሯቸዋል ማለት አይደለም። የተለያዩ የፅሑፍ አይነቶችን እና ማንነቶችን በፀሐፊያኑ መካከል እንመለከታለን። ለምሳሌ የጳውሎስ የአፃፃፍ ዘይቤ ከጴጥሮስ ይለያል። ስለ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መፃፍ ያለን አለመካከት እግዚአብሔር የሰዎችን የተለያየ ማንነት፥ ስነ ቃላት፥ አፃፃፍ ስልት፥ የትምህርት ደረጃ እና ታሪካዊ ጥናት የተጠቀመ መሆኑን ያስተውላል።

በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መፃፍ ያለ ትክክለኛ አለመካከት እግዚአብሔር የጸሐፊያኑን ሁለንተና ይመራ እንደነበር ይህም የጸሐፊያኑን ምናብ እና ማንነት በመጠቀም መለኮታዊ እውነትን ለመግለጽ ተጠቅሞበታል፥ ይህ ማለት ግን እውነትን ለመግለጽ ብቻ ሳይሆን የጽሑፉን ሂደትም በመቆጣጠር ትክክለኛነቱን ያረጋግጥልናል።

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ሊያስተላልፍ የፈለገውን ሃሳብ ብቻ ነው የሰጠው፥ ይህንንም ሃሳብ ጸሐፊው ሰው ምርጥ በሚለው መንገድ አስረድቶታል- በመሆኑን ሰዎች በአፃፃፉ ላይ ያለውን ስዕተት ፈፅመዋል ብለው ያስባሉ። ይህ እሳቤ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን እግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መፃፍን አይገጥምም መጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፉያኑ በአፃፃፋቸው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ተነድተው እንደፃፉት ይገልጻል፤ ስለዚህ በራሳቸው ፈቃድ ስህተት እንዲሰሩ እንዳልተተዉ እናውቃለን።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ ምንም የተሳሳተ ነገር አይናገርም ምክንያቱም እግዚአብሔር ስለማይሳሳት። (ምሳሌ 30፥5 ይነበብ)። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተነገረው ታሪክ ውስጥ ራሱን ስለገለጠ፥ ዝርዝር ታሪኩም ትክክል መሆን አለበት፥ ምክንያቱን ትክክለኛ የእግዚአብሔር መገለጥን ሊኖረን

---

[2] ለራዕይ የመጣ መገለጥ ምሳሌ ዳንኤል 7 እና 8ትን እንዲሁም አብዛኛውን ራእይን መመልከት ይቻላል።

ስለሚገባ። በመሆኑም መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መፃፍ መግለጫ ምክንያት እግዚአብሔር አፃፃፉን እንደመራው እናውቃለን ስለዚህም ሙሉ በሙሉ ትክክለኛ ነው።

**የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛነት ለመከላከል የምንጠቀማቸው**

**በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መፃፍ**

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የተፃፈ ነው፥ ይህም ማለት ሙሉ በሙሉ የተጠቀማቸው ቃላት ሳይቀር የእግዚአብሔር ቃል ነው ማለት ነው፤ ይህ ሀረግ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ታማኝነት እና ትክክለኝነት በመጀመርያ በቂ ነበር፥ ነገር ግን አሁን አንዳንድ መፅሐፈር ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መፃፉን የሚያምኑ ሰዎች ሙሉ በሙሉ ትክክለኝነቱን ይክዳሉ። የሚቀጠሉት ቃላት/ ሀረጎች የእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መሰረት መፃፉን ለመከላከል ጥቅም ላይ ውለዋል።

**የማይሳሳት ነው**

ይህ ቃል "ሊያስት የማይችል" ማለት ሲሆን፥ መጽሐፍ ቅዱስ የማይሳሳት ነው ማለት ሙሉ ለሙሉ ልንታመንበት የምንችል እና በፍጹም ሊያሳሳተን የማይችል ነው ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የማይሳሳት ነው ስንል በአስተምሮ ብቻ ሳይሆን በውስጡ ያለው አርፍተ ነገር ሑሉ የማያሳሳት ነው።

**ስዕተት አልባ**

ይህ ቃል 'ስዕተት የሌለው ማለት' ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ሁሉም አርፍተ ነገር በሙሉ ትክክለኛ ነው። እግዚአብሔር የማይዋሽ እና የማይሳሳት (ቲቶ 1፥2ን ይነበብ) ስለሆነ፥ መጽሐፍ ቅዱስም የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ምንም ስዕተት የሌለበት መሆኑን እርግጠኛ መሆን እንችላለን። ማንም ሰው መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች በመፃፉ ውስጥ ስለተሳተፉ ስዕተት አለው ቢል በ 2 ጴጥሮስ 1፥21 ላይ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የሚለውን በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት እንደተፃፈ ያለውን መግለጫ ይረሳል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ታሪካዊ የሆነው በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መፃፍ የሚለው ሃሳብ ስለ ሙሉ፥ እያንዳንዱን ቃላት ጨምሮ የሚያመላክት ነው፥ ስለሆነም ከስዕተት ውጪ ነው (ማቴዎስ 5፥18ን ይነበብ)።

**በቅጂዎች ውስጥ ያለ ስዕተትስ?**

የማተሚያ መሳርያ ከመኖሩ በፊት፥ ሁሉም ፅሁፎች መጽሐፍ ቅዱስን ጨምሮ በእጅ ይገለበጥ ነበር። በጳውሎስ፥ በኢሳያስ ወይም በሙሴ የተፃፉት የመጀመርያዎቹ የፅሁፍ ስራዎች የሉንም። በሺህ ከሚቆጠሩ የጥንት በእጅ የተተለበጡ የግሪክ እና የዕብራይስጥ ስራዎች መካከል ትንንሽ ልዩነቶች አሉ፥ እንዲሁም የመጀመርያው ፅሁፍ በትክክል ምን እንደሆነ በሙሉ ልናውቅ አንችልን። ነገር ግን ልዩነቶቹ በጣም ትንንሽ ስለሆኑ ምንም አይነት የአስተምሮ ልዩነት ሆነ ጥያቄ ሊያነሱ አያስችሉም። የመጀመርያዎቹ ፅሁፎች ምንም አይነት ስዕተት እንደሌለባቸው እናውቃለን፤ እንዲሁም በተገለበጡት ውስጥም ኣለው ልዩነት አነስተኛ ነው ስለዚህም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን እያንዳንዱን አርፍተ ነገርን መተማመን እንችላለን።

► መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ግዜ በእጅ የተገለበጠ ሆኖ ትክክለኛ መሆኑን በምን ልናውቅ እንችላለን?

► ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስዕተት አለው ብለው የሚያምኑበት የተለያየ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

**አንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ስዕተት እንዳለው የሚያስቡት ለምንድን ነው?**

አንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ስዕተት እንዳለው ይናገራሉ- ይህም የሆነበት ምክንያት የመፀሐፍ ቅዱስን ባህሪ ስላልገባቸው ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የሰዎችን መደበኛ ተግባቦት መንገዶችን ተጠቅሟል። ለምሳሌ ፀሐይ በሰማይ ላይ እንደሚሄድ የሚገልፅ ጥቅስ አለ። አብዛኞቹ ሳይንቲስቶች ፀሐይ ከመጓዝ ይልቅ ምድር እንደምትሽከረከር ያምናሉ፤ ነገር ግን እነርሱ ራሳቸው እንኳ ስለ ፀሐይ መውጣትና መጥለቅ ይናገራሉ፤ የሚመለከቱትን በቀላሉ የሚገልጡበት መንገድ ነው።

እንዲሁም ቅኔያዊ የሆኑ ዓርፍተ ነገሮችን አሉ፥ ለምሳሌ "ኰረብቶችም እንደ ጠቦት ዘለሉ" (መዝሙር 114፥4) ወይም "የሜዳ ዛፎች ሁሉ፣ ያጨበጭባሉ" (ኢሳይያስ 55፥12)። ይህም የስነፅሑፍ መንገድ እንጂ ቀጥተኛ/ መደበኛ የሐነ ንግግር አይደለም።

አንዳንድ ግዜ ፀሐፊያኑ ይህም በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ውጪ የሆነ ሌሎች ሰዎች የተናገሩትን ይጠቅሳሉ (ለምሳሌ፥ እዮብ ወዳጆች ንግግሮች እግዚአብሔር ትክክል እንዳልሆኑ ቢናገርም ተፅፈውልናል (ኢዮብ 42፥7)።

ይህ ግን ምንም አይነት በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪነት መፃፍ የሚለው አስተምሮ ላይ ምንም አይነት ችግር አይፈጥርብንም። እግዚአብሔር የመጨረሻው ስራ የእርሱ ቃል ስለሆነ የፅሁፉን መንገድ በሙሉ ስዕተት እንዳይኖርበት መርቶታል።

አንዳንድ ግዜ ሰዎች በመፀሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተቃርኖዎችን እንደሚመለከቱ ያስባሉ፥ ነገር ግን በጥንቃቄ መመልከት አለባቸው። ለምሳሌ፥ ማርቆስ 5፥1-2 እና ሉቃስ 8፥26-27 ላይ እየሱስ ከአጋንንት እስራት ነፃ ስላወጣው ሰው ይናገራል። ማቴዎስ 8፤28 ደግሞ ሁለት ከአጋንንት እስራት ነፃ ስለወጡ ሰዎች ይናገራል። ይህ ግን ተቃርኖ አለው ማለት አይደለም ሉቃስ እና ማርቆስ አጋንንት የወጣለት ሰው አንድ ብቻ ነው አላሉም፥ ነገር ግን በአካባቢው ላይ ታሪክ ያለው አንዱ ሰው ላይ ብቻ ነው ያተኮሩት። አንድ ሰው በመፀሐፍ ቅዱስ ላይ እርስ በእርሳቸው ተቃርኖ እንዳላቸው የሚያስበው ዘርፎች ላይ ወደ መደምደሚያ ቶሎ መድረስ የለበትም፥ ነገር ግን ግዜው ወስዶ አውዱን መገንዘብ አለበት።

**መጽሐፍ ቅዱስ ለክርስቲያኑ**

► ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን መጠቀም ያለበት አንዳንድ መንገዶች ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

መፀሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ህግ ይሰጠናል። ህጉን መጠበቅ አያድነንም ነገር ግን ህጉ እግዚአብሔር በምን አይነት መንገድ እንድንኖር እንደሚፈልግ ያስረዳናል። የእግዚአብሔር ህግ የእግዚአብሔርን ማንንት ያሳየናል። ህጉን መከተል ያለብን እግዚአብሔርን መምሰል ስለምንፈልግ መሆን አለበት። እግዚአብሔር ስለምንወደው፥ ህፉን መውደድ አለብን። መዝሙር 119 እግዚአብሔርን የሚያመልኩት ሁሉ በእግዚአብሔር ህግ መደሰት እንዳለባቸው

ይነግረናል። እግዚአብሔርን የሚወደው ሰው ወደ እግዚአብሔር ፈቃድ ልቡን እንዲለውጥለት ይፀልያል። እግዚአብሔርን የሚወድድ ሰው እግዚአብሔርን ደስ ስለማሰኘት ግድየለሽ መሆን አይችልም።

> "በአሁኑ ስርዓት/ባህል ውስጥ የተዋሸናቸው ሑለት ውሸቶች ከፍጥረታችን መልካም ሰዎች እንደሆንን እና እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ስለሆነ ኃጥያትን እንደማይቀጣ ነው።"
>
> – ፍራንሲስ ቻን

የእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ነው፥ ሐዋርያው ጴጥሮስ አለም በመንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃልም በዚያ ውስጥ እንዴት መኖር እንዳለብን የሚያመራ መሆኑን ይነግረናል (2 ጴጥሮስ 1፥19-21 ይነበብ እንዲሁም መዝሙር 119፥105 ይመልከቱ)። ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚጋጭ ከሆነ በፍፁም የራሱን ሃሳብ ሆነ ስሜት መከተል የለበትም። መንፈስ ቅዱስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስዕተት ወደ ሚለው ሃሳብ በፍፁም አይመራም።

የእግዚአብሔር ቃል መንፈሳዉ ምግባችን ነው። መልካም ረሃብ የጤንነት ምልክት ነው፥ ክርስቲያንም የእግዚአብሔርን ቃል አንድ ልጅ ወተትን እንደሚጠማ መጠማት አለበት (1 ጴጥሮስ 2፤2)፤ ክርስቲያኑም ሲያድግ የበለጠ የእግዚአብሔርን ቃል የሚረዳ እና የሚገነዘብ መሆን አለበት ልክ አንድ ልጅ ሲያድግ ጠጣር ምግብ መውሰድ እንደሚጀምር (1 ቆሮንጦስ 3፥2)። አንድ ክርስቲያን በየዕለቱ ራሱን መንፈሳዊ ምግብ ከእግዚአብሔር ቃል መመገብ አለበት።

መጽሐፍ ቅዱስ ራሳችንን ከሰይጣን የምንጠብቅበት ነው። መንፈሳዉ የጦር ልብ በመልበስ ራሳችንን እንድንጠብቅ ታዘናል፥የተሰጠን የመንፈስ ቅዱስ ጦር የእግዚአብሔር ቃል ነው (ኤፌሶን 6፥17)፤ እየሱስ ከዲያቢሎስ ለመጣበት ፈተና መልስን ሰጠው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው (ማቴዎስ 4፥3-4)።

የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነው፤ ከእኛም ምላሽ ይፈልጋል። እየሱስም ከሚዘራ ዘር ጋር አወዳድሮታል (ሉቃስ 8፥11-15)። አንዳንዱ ዘር ባልተዘጋጀ መሬት ላይ ስለወደቀ ሊያፈራ አልቻለም፥ መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ ለህይወታችን ከቃሉ የተነሳ ፍሬን ለማፍራት ለሚናገረው እውነት ምላሽ መስጠት እና ወደ እግዚአብሔር መፀለይ አለብን።

## መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ…

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ …

- በፍፁም አሮጌ ሆነ የማይጠቅም አይሆንም። በሁሉም ቦታ እና ግዜ ውስጥ ላሉ ሰዎች ይሰራል።
- የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመለየት የሚመራ ነው፥ ይህም እግዚአብሔር ከራሱ ጋር የሚጋጭ ሆነ ሃሳቡን ስለማይቀይር ነው።
- ከህይወት ውስጥ ምርጡን የምናገኝበት መምሪያ ነው፥ ይህን እግዚአብሔር፥ ፈጣያችን አቅጣጫን ስለሰጠን ነው።
- ለመዳን እና ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖረን ግንኙነት ልናውቀው የሚገባንን ሁሉ የሚገኝበት ነው

ከመጋቢያን እና ከቤተክርስቲያን ወጎች ብንማርም- የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስን ሃሳብ የሚቃረን ሃሳብ ተቀባይነት የለውም ምክንያቱም የመጨረሻው ባለስልጣን ስለሆነ።

መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል እንድንረዳው ያበራልናል እንዲሁም ወደ መታዘዝ ይመራናል።

► እግዚአብሔር አሁንም ይናገራል ፥ ቢሆንም ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚጨመርን ሊኖር እንደሚችል ልንጠብቅ ይገባናል?

## መጽሐፍ ቅዱስ ተፅፎ አልቋልን?

በመጨረሻ ከሞተው ሐዋርያ በኃላ ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ ተፅፎ ያለቀ መጽሐፍ እንደሆነ ታምናለች። ቤተክርስቲያን ጽሑፎችን መርጣ ቅዱሳት መጻሕፍት ብላ እንዲሁ አልሰየመችም፥ ነገር ግን አንዳንድ ፅሁፎች በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት እንደተፃፉ እና ባለስልጣን እንደሆነ እውቅና ይሰጣሉ። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ፅሁፎች የሚያሟሉቱን መስፈርት ከዚያ በኃላ የተፃፉት የትኛውም ፅሁፍ ማሟላት አልቻለም።

ለብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ቤተክርስቲያን እስራኤላውያን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ የወሰዱትን ሙሉ በሙሉ ተቀብለዋል። በግዜው ውስጥ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት የሚከተሉትን መስፈርቶችን ሲያሟሉ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት ተቀባይነት አግኝተዋል

- ከሐዋርያት ጋር ያላቸው ታሪካዊ ትስስር
- የራሳቸውን እውነተኝነት የሚመሰክሩበት ጥራት
- በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለጥያቄ ተቀባይነት ማግኘት
- በብሉይ ኪዳን በአክብሮት በመጠቀም
- ከስዕተት ትምህርት ለመቋቋም ያላቸው ጠቀሜታ

እግዚአብሔር አሁንም ይናገራል፥ ስለሆነም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መጨመር ይቻል ይሆን? የትኛውንም አዲስ ፅሁፍ በዋነኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ስብስብ ውስጥ ለመካተት በሚያበቃ መልኩ መስፈርቱን አያሟላም። ለምሳሌ የትኛውም አዱስ ፅሑፍ ከሐዋርያት ጋር ሊተሳሰ አይችልም ምክንያቱም አሁን ከእኛ ጋር ማናቸውም ስለሌሉ። እንዲሁም የትኛውም አዲስ ፅሁፍ በአለም አቀፍ ደረጃ ባለችው ቤተክርስቲያንን በስምምነት ተቀባይነት ማግኘት አይችልም።

መፅሐፍ ቅዱስ ለመዳን እና ለክርስትና ህይወት ሙሉ እና በቂ ነው (2 ጢሞትዮስ 3፥14-17)። የሚያስፈልገን ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስላለ ምንም አስፈላጊ ሆነ ጠቃሚ የሆነ የሚጨመርበት የለውም። አዲስ መገለጥን እንደሚቀበሉ የሚያምኑ ሰዎች ግዜያቸውን እግዚአብሔር የገለጠውን ማትናት ማሳለፍ አለባቸው። በዚያም ውስጥ ከስዕተት የሚጠብቃቸው እና የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ያገኛሉ።

## ማስወገድ ያለብን ስዕተቶች

*ለክፍሉ መሪ ማስታወሻ- ሁለት የክፍሉ አባላትን ይህንን እና የሚቀጥለውን ክፍል ያስረዱ።*

### የመጽሐፍ ቅዱስ ባለስልጣንነትን ማላላት

በህይወታችሁ ላይ የመጨረሻው ባለስልጣን ማን ነው? ብዙ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ በህይታቸው ላይ ባለስልጣን እንደሆነ ይናገራለ ነገር ግን በዋናነት የሚያምኑት ስሜታቸውን ነው። አንድ ሰው ተግባሩ ትክክል መሆኑን የሚያምነው ፀፀት ካልተሰማው ነው፥ ነገር ግን ይህ ሰው ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ ስሜቱን ዋና ባለስልጣን ያደርጋል።

ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን አበክረው የማይወስዱበት የተለያየ ምክንያት ይኖራቸዋል፥ ምናልባትም የሚያከብሩት ሰው ግልጥ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ችላ ሲል እነሱንም እንዲሁ እንዲያደርጉ ያበረታታቸዋል። ምናልባትም መፅሐፍ ቅዱስ የሚከለክለውን በማድረግ ጥፋተኝነት ስለሚሰማቸው ራሳቸውን ለማስረዳት ይሞክሩ ይሆናል። ምናልባትም ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንዲሁ ችላ የሚሉ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት የምንችለውን ሁሉ ጥረት ማድረግ እና ራሳችንን ለስልጣኑ ማስገዛት ያስፈልገናል።

### መጽሐፍ ቅዱስን በተገደበ አላማ ማጥናት

መጽሐፍ ቅዱስ የአስተምሮ ዋነኛ ምንጭ ነው። ለሚነሳ የትኛውም የአስተምሮ ጥያቄ የመጨረሻ ባለስልጣን ነው። ነገር ግን ሰዎች ለራሳቸው አስተምሮ ማረጋገጫ ለማግኘት ብቻ ሲያጠኑት ችግር አለው። መጽሐፍ ቅዱስን ለመንፈሳዉ መብልነት ለማግኘት አይጠቀሙትም፥ ሌላው ሰው ስዕተት እንዳለበት ለማሳየት ብቻ ነው የሚጠቀሙት። አስተምሮን ለመስራት እና ለመከላከል መጽሐፍ ቅዱስን መጠቀም ትክክለ ነው። ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሙ ይህ ብቻ ከሆነ በግላችን ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖረን ግንኙነት ያለውን ጥቅም ውስጥ ያለውን ደስታ ያጡታል።

አንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለመበረታታት አላማ ብቻ ያነቡታል። መጽሐፍ ቅዱስ አላማ መምራት፥ ማነፅ እና ማስተካከል መሆኑን ማስታወስ አለብን (2 ጢሞትዎስ 3፥16)። የመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ራሳችን የተሻለ ስሜት የሚሰጡንን ተስፋዎችን ብቻ እያነበብን ትዕዛዛትን መዝለል/ መተው የለብንም፥ ምናልባትም እግዚአብሔር ሊመክረን ወይም ሊያስተካክለን ወይም ሊያስተምረን ፈልጎ ይሆናል።

## የአምልኮ ስርዓቶች ስዕተቶች

አንዳንድ የእምነት ቡድኖች መጽሐፍ ቅዱስን እናምናለን ይላሉ፥ ነገር ግን ሌላ ነገር የመጨረሻ ባለስልጣናቸው ያደርጋሉ። ያላቸውን መገለጥ ወይም ልዩ ስርዓት በመከተል እነሱ ብቻ መጽሐፍ ቅዱስን ማስረዳት እንደሚችሉ ያስባሉ፥ ያሏቸው መሰረታዊ አስተምሮዎች ግን በመጽሐፍ ቅዱስ መሰረት ማረጋገጫ የላቸውም።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆነ ሌላ እንደ ቅዱስ መጽሐፍ የሚጠቀሙት መጽሐፍም ይኖራቸዋል፥ መጽሐፍ ቅዱስም የትርጉም ሆነ ሲገለበጥ ስዕተት ስላለው ተአማኝ አይደለም ሊሉ ይችላሉ።

እነዚህ ሃሳቦች መጽሐፍ ቅዱስ ምኡሕ የእግዚአብሔር ቃል እንዳልሆነ ያመላክታሉ፥ ለእነዚህ ሰዎች ሌላ ነገር ዋና/ የመጨረሻ ባለስልጣናቸው ይሆናል።

► የእምነት መግለጫውን ቢያንስ ሁለት ግዜ አብራችሁ አንብቡ።

## የእምነት መግለጫ

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው። በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ስር ፀሐፊያኑን ስለፃፉት ያለ ምንም ስዕተት ነው የፃፉት። ከሀጥያት ለመዳን እና ከእግዚአብሔር ጋር ባለ ግንኙነት ለመኖር የሚያስፈልገን ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተካትቷል። መጽሐፍ ቅዱስ የአስተምሮ ዋና ምንጭ እና የመጨረሻም ባለስልጣን ነው። እግዚአብሔርን በሚገባ ለማወቅ፥ በእርሱን ለመመራት፥ መንፈሳዉ ምግብን ለማግኘት እና ትርጉም ያለው ደስተኛ ኑሮ ለመኖር ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን በየዕለቱ ማጥናት አለበት።

## የትምህርት 1 የቤት ስራዎች

(1) የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የቤት ስራ፡- ከታች ከተዘረዘሩት ዘርፎች መካከል እያንዳንዱን ተማሪ አንድ ይመደብ። ከሚቀጥለው ክፍለ ግዜ በፊት ክፍሉን አንብባችሁ በትምህርቱ ውስጥ ካለው ሃሳብ ላይ ምን እንደሚናገር በአንድ አንቀፅ ፃፉ።

- መዝሙር 119፥33-40
- መዝሙር 119፥129-136
- ምሳሌ 30፥5-6
- ማቴዎስ 5፥17-19
- 2 ጢሞትዎስ 3፥15-17
- 2 ጴጥሮስ 3፥15-16
- ራእይ 22፥18-19

(2) ፈተና፡- የሚቀጥለው ክፍለ ግዜ የምትጀምሩት በትምህርት 1 ፈተና ነው። ለፈተና ዝግጅት እንዲሆን የፈተና ጥያቄዎችን አጥኑ።

(3) የማስተማር የቤት ስራ፡- በዚህ ትምህርት ቢያንስ ሶስት ግዜ በዚህ ክፍል ውስጥ ላልተካተቱ ሙሉ ትምህርቱን ወይም በከፊል ታስተምራላችሁ። ይህ ትምህርት በቤተክርስቲያን ውስጥ ባለ የሰንበት ማስተማሪያ ክፍል፣ በቤት ውስጥ በሚደረግ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን፣ በቤተሰብ ስብስብ ወይም በማንኛውም ሌላ ቦታ ሊሰጥ ይችላል። የማስተማርያ መንገዱን ማዘጋጀት እና ማስተማር እናንተ ሃላፊነት ነው፥ ይህንን አድርጋችሁ ለክፍል መሪ ሪፖርት አድርጉ።

(4) ለሚቀጥለው ክፍለ ግዜ ቀጣዩን ትምህርት አንብባችሁ መምጣት አስታውሱ።

## ትምህርት 1 ፈተና

(1) ጠቅላላ መገለጥ ምንድን ነው?

(2) እግዚአብሔር ልዩ መገለጥን የሰጠበት ሑለት መንገዶችን ምንድን ናቸው?

(3) ልዩ መገለጥ ማድረግ የሚችለው በጠቅላላ መገለጥ ውስጥ መገኘት የማይችሉ ሦስት ነገሮች ምንድን ናቸው?

(4) መጽሐፍ ቅዱስ ስለራሱ የሚነግረን ምንድን ነው?

(5) መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለመሆኑን የምናውቅበት ስድስት ምክንያቶችን ዘርዝሩ።

(6) መጽሐፍ ቅዱስ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት በጽድቅም መንገድ ለመምከር የሚጠቅመው ለምንድን ነው? (2 ጢሞቴዎስ 3፥16)

(7) የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ስህተት እንዳይሠሩ ተጠብቀው እንደነበር የሚያረጋግጥልን ምን ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገለጻ አለ?

(8) እግዚአብሔር ጸሐፊያኑን ምሪት የሰጠበት አራት መንገዶችን ዘርዝሩ።

(9) መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ነው የተፃፈው ምን ማለት ነው?

(10) መጽሐፍ ቅዱስ የማይሳሳት ነው ማለት ምን ማለት ነው?

(11) መጽሐፍ ቅዱስ ስዕተት አልባ ነው ማለት ምን ማለት ነው?

# ትምህርት 2

# የእግዚአብሔር ባህሪያት

**የትምህርቱ አላማ**

(1) ተማሪው የሚከተሉትን ማስረዳት ይችላል

- የሰዎች ስለ እግዚአብሔር ያላቸው እሳቤ አስፈላጊነት
- እግዚአብሔር ፈጣሪ አምላክ መሆኑ ከሁሉም ነገር እንዴት የሚለይ እንደሚያደርገው
- የእግዚአብሔር ባህሪያት፤ እግዚአብሔር ሕላዌ፥ መንፈስ፥ ዘላለማዊ፥ ሥላሴ፥ ሁሉን ቻይ፥ በሁሉ ቦታ ይገኛል፥ የማይለወጥ፥ ሁሉን አዋቂ፥ ቅዱስ፥ ጻድቅ እና አፍቃሪ
- እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ባህሪ ከእርሱ ጋር ለሚኖረን ግንኙነት አስፈላጊ እንደሆነ
- የእግዚአብሔር ሉዋላዊነት መጽሐፍ ቅዱሳዉ እይታ
- ስለ እግዚአብሔር ክርስቲያናዊ የእምነት መግለጫ

(2) ተማሪው ስለ ተለያዩ የአምልኮ ቅርፆች ያሉ የተሳሳቱ መረዳቶችን ያስወድጋል።

**መግቢያ**

► ኢሳይያስ 40 አብራችሁ አንብቡ። ይህ ክፍል ስለ እግዚአብሔር የሚነግረንን ተወያዩ።

► ሰው ስለ እግዚአብሔር ትክክለኛ ሆነ እሳቤ መኖሩ ወይም አለመኖሩ ለምን አስፈለገ?

እግዚአብሔር ማን ነው? ኤ ደብልዩ ቶዘር የዚህ ጥያቄ አስፈላጊነት እንዲህ በማለት ያሳየናል “የትኛውም የአስተምሮ ስዕተት ሆነ ክርስቲያናዊ ስነ-ምግባርን የመተግበር ችግር ሁሉ ከጎዶሎ ወይም የማይገባ/ ስዕተተኛ የሆነ ስለ እግዚአብሔር ያለ እሳቤ ጋር አለመገናኘቱ በጣም ጠባብ ነው ብዬ አምናለው። ”[3] የሳምራውያን የተሳሳተ የአምልኮ ችግር የሚመነጨው የሚያመልኩትን ስለማያውቁነት እንደሆነ እየሱስ ሳምራዊቷን ሴት በውሃው ጉድጓድ ጋር ነግሯታል። የማንኛውም ሰው በጣም አስፈላጊው ማንነቱ/ ባህሪው ስለ እግዚአብሔር ያለው እሳቤ ነው። የሰው ስለ እግዚአብሔር ያለው አስተሳሰብ የሃይማኖቱ መሰረት ነው። ስለ እግዚአብሔር ከመሳሳት የባሰ የከፋ ስዕተት የለም።

እግዚአብሔር ከእኛ በላይ እጅግ የሚበልጥ እና የሚያይል ስለሆነ እግዚአብሔርን ለመግለጥ የሚሆን የትኛውም የሚመሳሰል የለም። መጽሐፍ ቅዱስ እንኳን እግዚአብሔርን የሚያስረዳ ትርጉም አይሰጠንም፥ ነገር ግን ማንነቱን እና ኃይሉን ሁሉም ቦታ ያስረዳል። ዘፍጥረት እግዚአብሔርን ሰማይ እና ምድርን፥ እፅዋትን፥ ፀሐይን፥ ጨረቃን እና ከዋክብትን እንዲሁም እንስሳትን በሙሉ በመጨረሻም የሰው ልጅን እንደፈጠረ ይነግረናል። የመጀመርያው

---

[3] A. W. Tozer, *The Knowledge of the Holy* (New York፥ Harper and Row, 1961), 10.

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ ነገር ፈጣሪ እንደሆነ ነው። ነገር ግን ካለው ነገር ሁሉ የተለየ ነው ፥ የፍጥረት አካል አይደለም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር የተለያዩ መግለጫዎች አሉት፥ የስነመለኮት ምሁራንም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ሃሳቦች በመለየት በጥንቃቄ የእግዚአብሔርን ባህሪያት ዘርዝረዋል። እነዚህን እውነቶችን ግን በእኛ ጎዶሎ/ ሙሉ ያልሆነ መረዳት መለየት አንችልም። ነገር ግን በአክብሮት እና በፈሪሐ የሆነ የእግዚአብሔርን ማንነት ጥናት ለመንፈሳዊ ልምምድ ታላቅ ዋጋ ያለው ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ራሱ የገለጠው እውነት ስለሆነ እውነት እንደሆነ እናውቃለን ስለዚህን የሚከተሉትን ስለ እግዚአብሔር ያሉትን መግለጫዎች እንመለከታለን።

## የእግዚአብሔር ባህሪያት

ሑሉንም የእግዚአብሔርን ባህሪያት ዘርዝረን መጨረስ መጨረስ ስለማንችል፥ ለማወቅ የሚያስፈልጉንን ባህሪያት ከዚህ በታች እንመለከታለን።

► የትኞቹን የእግዚአብሔር ባህሪያት መዘርዘር ትችላላችሁ?

### እግዚአብሔር ሕላዌ ነው

እግዚአብሔር እውነተኛ፥ ያለ ስሜት፥ ፈቃድ እና እውቀት ያለው ህያው እና እውን የሆነ አካል ነው።[4] የተፈጥሮ እውነታዎች ድምር ሆነ እንደ ኤሌክትሪክ ሆነ የመሬት ስበት አካል የሌለው ኃይል አይደለም። ይፈጥራል፥ ያደርጋል፥ ያውቃል፥ ፈቃድ አለው፥ ያቅዳል እንዲሁም ይናገራል።

► እግዚአብሔር አካል ባይሆን ምን ልዩነት ያመጣል?

እግዚአብሔር አንድ አካል መሆኑ ከእርሱ ጋር ግንኙነት እንዲኖረን ያስችለናል። እርሱ አካል ባይሆን ኖሮ ወደ እርሱ መፀለይ አንችንልም። እርሱ አካል ባይሆን ኖሮ እርሱን ደስ ማሰኘት ሆነ ማሳዘን አይቻለንም።

### እግዚአብሔር መንፈስ ነው

“እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባል” (ዮሐንስ 4፥24)።

እግዚአብሔር መንፈስ መሆኑ ከእርሱ ጋር መንፈሳዊ የሆነ ህብረት እንዲኖረን እና እርሱን እንድናመልከው መሰረት ይሰጠናል። ፀሎት እና አምልኮ ቁሳዊ የሆኑ ነገሮች ላይ፥ የተወሰኑ አካላዊ አቀማመጦች፥ የቀጠሮ ግዜ ሆነ ህንፃ ላይ ጥገኛ አይደሉም። እነዚህ ነገሮች ሃሳባችን ወደ አምልኮ እንዲሰበሰብ እረዱን ይሆናል እንጂ አምልኮ እነዚህ ላይ ጥገና አይደለም።

እግዚአብሔር መንፈስ መሆኑ ራሱ ለእርሱ ቁሳዊ የሆነ ምስል እንዳንሰራ ያዘዘው ለዚህ ነው። (ዘፀ 20፥ 4-6 ይነበብ)። እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ ራሱን በቁሳዊ መንገድ ለመግለጥ ካልፈለገ በስተቀር ለእኛ አይታየንም (1 ጢሞቴዎስ 1፥17)። (ዘፍጥረት 18፥1፤ ኢሳይያስ 6፥1 ይነበብ)። ስለ እግዚአብሔር ያለን እሳቤ/ እውቀት የተወሰነ

---

[4] ዘፍጥረት 6፥6፣ ኢሳይያስ 42፥21፣ ኢሳይያስ 46፥10-11፣ ናሆም 1፥2፣ ሶፎንያስ 3፥17፣ ያዕቆብ 5፥11፣ 1 ጴጥሮስ 5፥7

ስለሆነ፥ በሚታይ መንገድ እንኳን ቢገለጥም ግን ማንም እግዚአብሔር በሙሉ አይቶት አያውቅም (ዘፀአት 33፥ 20፤ ዮሐንስ 1፥18፤ ዮሐንስ 6፥46)።

### እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው

እግዚአብሔር ያልነበረበት ግዜ የለም ሆነ የማይኖርበት ግዜም አይኖረም፤ እግዚአብሔር መጀመርያ እና መጨረሻ የለውም። እግዚአብሔር ራሱን እኔ፣ ያለሁና የምኖር ነኝ (ዘፀአት 3፥14) በሚል ስም ገልጧል። በዮሐንስም እንዲህ ገልጦታል ያለውና የነበረው፣ የሚመጣውም፣ ሁሉን ቻይ ጌታ አምላክ (ራእይ 1፥8)። ከዘላለም እስከ ዘላለም እርሱ እግዚአብሔር ነው (መዝሙር 90፥2)። አንዳንድ ሃይማኖቶች አምላኮቻቸው ስለተወለዱበት ግዜ አፈታሪኮች አሏቸው ፥ እውነተኛው አምላክ ግን ዘላለማዊ ነው።

### እግዚአብሔር ሥላሴ ነው

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አንድ አምላክ እንዲሁም ስለሶስት የተለያዩ መለኮታዊ አካላትን ይናገራል። አንድ አምላክ ብቻ ነው ያለው ነገር ግን ሶስት አካላት አሉ። ሥላሴን በሙላት መረዳት ባንችልም ኢ-አመክኖአዊ አይደለም ምክንያቱን በአንድ ተመሳሳይ ሶስት እና አንድ የሆነ ነገር አለ እያልን ስላልሆነ። አንድ አምላክ አለ፥ ሶስት አካል ሆኖ ይኖራል። እግዚአብሔር አብ፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ሁላቸውም የመለኮትን ባህሪ ያላቸው ሲሆነ፥ ሁላቸውን እግዚአብሔር ይባላሉ እንዲሁም እንደ አምላክ ይመለካሉ። (ስለ ሥላሴ በሚቀጥለው ትምህርት ላይ በጥልቅ ይባላል)

### እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው

ማድረግ የሚፈልገውን ሁሉ ማድረግ ይችላል። “አምላካችንስ በሰማይ ነው፤ እርሱ ደስ የሚለውን ያደርጋል” (መዝሙር 115፥3)። ከራሱ መለኮታዊ ማንነት የማይፃረርን ነገር ሁሉ ያለመከልከል በሙሉ ኃይል የሚያደርግ እና ቃል የገባውን ሁሉ የሚፈፅም ነው። ምንም ነገር ለእርሱ ከባድ እና አስቸጋሪ አይደለም “ሁሉን ቻይ ጌታ አምላካችን ነግሷልና” (ራእይ 19፥6)።

► እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ አምላክ መሆኑን ማወቅ ምን ልዩነት ያመጣል?

ይህ ሃሳብ ያበረታታናል፥ ምክንያቱን በትግላችን ውስጥ “እንግዲህ በእኛ ውስጥ እንደሚሠራው እንደ ኀይሉ መጠን፣ ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ በላይ እጅግ አብልጦ ማድረግ ለሚቻለው፣” (ኤፌ 3፥20)። ነገሮች ከቁጥጥር ውጪ የሆኑ ቢመስለን እንኳ የእግዚአብሔር ታላቅ ዕቅድ ግን ሁልግዜ ወደ ፍፃሜ ይመጣል። እኛም እግዚአብሔር በነገሮቻችን ላይ ጣልቃ መግባት እንደሚችል በማመን በድፍረት እንፀልያለን።

### እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ ይገኛል

እግዚአብሔር የሌለበት ቦታ የለም፥ እርሱም ሳያየው የሚሆን አንዳች የለም። “ሰማይ ዙፋኔ ነው፤ ምድርም የእግሬ ማሳረፊያ ናት” (ኢሳይያስ 66፥1)። እርሱ የፍጥረተ አለሙ አምላክ ነው፥ እንዲሁም በቦታ የማይወሰን ሃይል አለው። “እኔ እንዳላየው፣ በስውር ቦታ ሊሸሸግ የሚችል አለን?” ይላል እግዚአብሔር። 'ሰማይንና ምድርንስ የሞላሁ እኔ አይደለሁምን' ይላል እግዚአብሔር” (ኤርምያስ 23፥24)። ይህም እግዚአብሔር ሁኔታችንን እና

> ‘በታላቅ እና ግዙፍ ህዋ ውስጥ ወደ ሌለ አምላክ አይደለም የምንጮሕው፥ እርሱ ከነፍሳችን ይልቅ ቅርብ ነው፥ ከምናስባቸው ጥልቅ ሚስጥሮቻችን ይልቅ ይጠጋናል”
>
> ኤ ደብልዩ ቶዘር

ችግሮቻችንነ ሁሉ እንደሚያውቅ ያስገነዝበናል። እንዲሁም ማንም ሰው ሆነ ኃጥያት ከእግዚአብሔር ሊደበቅ እንደማይችል ያስገነዝበናል። ሁሉን ነገር ለእርሱ እይታ የተገለጠ እና እርቃኑን ነው። (ዕብራውያን 4፥13 ይነበብ)።

**እግዚአብሔር አይለወጥም**

እግዚአብሔር አምላክ ካለመሆን ወደ መለኮትነት የመጣበት የትኛውም ግዜ አልነበረም እንዲሁም መለኮት ያልነበረበት ግዜ የለም። (ያዕቆብ 1፥17 ይነበብ)። አንዳንድ ሃይማኖቶች መለኮት በመለወጥ/ በማደግ ሂደት ውስጥ እንደሆነ ያምናሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እርሱ በማንነቱ፥ በስብዕናው፥ በባህሪው፥ እንዲሁም በአላማው የማይለወጥ አምላክ እንደሆነ ይነግረናል። (ሚልክያስ 3፥6 ይነበብ)። እርሱ ሁልግዜ ትክክል የሆነውን ይወዳል፥ እንዲሁም ትክክል ያልሆነውን ሁል ግዜ የሚጠላ አምላክ ነው። ራሱን 'እኔ ነኝ' ብሎ ለሙሴ የገለጠው ዘላለማዊው አምላክ ለዛሬም 'እኔ ነኝ' የሆነ አምላክ ነው። እርሱ በስብዕናው፥ በጥበቡ፥ በእውቀቱ፥ በቅድስናው፥ በፍትህ አሰጣጡ፥ በመልካምነቱ እና በእውነቱ ወሰን አልባ፥ ዘላለማዊ፥ እና የማይለወጥ ነው። እርሱ ሁል ግዜ ያው ነው፥ አመታቶቹም አያረጁም (መዝሙር 102፥27)።

**እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው**

"ለጥበቡም ወሰን የለውም" (መዝሙር 147፥5)። እግዚአብሔር ነገሮችን በመማር ሂደት ውስጥ የሚያልፍ አይደለም፥ እርሱ ሁሉን ያውቃል። እግዚአብሔር ምንም ነገር ከማንም ተምሮ አያውቅም፥ ማንምም ሊመክረው አይችልም። (ኢሳይያስ 40፥ 13-14 ይነበብ)። እግዚአብሔር ነገ የሚሆነውን ስለሚያውቅ በምንም አይደነቅም ወይም ሳይዘጋጅ አይገኝም (መዝሙር 139፥ 4)።

► እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ መሆኑን ማወቅ ለእኛ ምን ልዩነት ያመጣልናል?

ከእግዚአብሔር እውቀት ጋር በፍጥረት እና በድነት ዕቅድ ውስጥ የታየው የእግዚአብሔር ጥበብ ይተሳሰራል። (መዝሙር 104፥24፤ ሮሜ 11፥33 ይነበብ)። እግዚአብሔር ሁሉን የሚያውቅ እና የሚረዳ ስለሆነ ሁል ግዜ መደረግ ያለበትን ትክክለኛ ነገር ያውቃል። የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁል ግዜ ለእኛ የተሻለ የሆነው እርሱ ሁሉንም ሁኔታ እና የተግባሮችን ውጤቱን በሚገባ ስለሚያውቅ ነው።

**እግዚአብሔር ቅዱስ ነው**

እግዚአብሔር ራሱን በዋናነት ቅዱስ በማለት ነው የገለፀው። ነብዩ ኢሳይያስ በተደጋጋሚ እግዚአብሔርን "የእስራኤልን ቅዱስ። " በማለት ይገልፀዋል። መላዕክትም በፊቱ ያለማቋረጥ "ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ" እያሉ ይጮሃሉ (ራእይ 4፥8፣ ኢሳይያስ 6፥3)። የእግዚአብሔር ቅድስና የአምልኮ መሰረታዊ ሃሳብ ነው "ታላቁንና አስፈሪውን ስምህን ይወድሱ፤ እርሱ ቅዱስ ነው" (መዝሙር 99፥3)። እርሱ የሞራላዊ ፍፅምና ሁሉ መለኪያ ነው። ተግባሮቹም በመልካምነት ሁሉ የታወቁ እና ክፋት ምንም የሌለባቸው ናቸው፤ እንዲሁም ከዚህ የተለዩ ሊሆኑ አይችሉም። የእግዚዓብሔር ቅድስና የሰው ልጅ ለማገልገል ሆነ ለማምለክ በመጀመሪያ በጸጋ ሳይለወጥ ብቁ አለመሆኑን ያሳየናል። (ኢሳይያስ 6፥5ን ይነበብ።) እግዚአብሔር እንደ እርሱ ቅዱሳን እንድንሆን ይፈልጋል። "ነገር ግን የጠራችሁ እርሱ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተም በኑሯችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ፤ ምክንያቱም 'እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ' ተብሎ ተጽፏል" (1 ጴጥሮስ 1፥15-16)።

**እግዚአብሔር ጻድቅ ነው**

እግዚአብሔር ስራዎች ሁል ግዜ ትክክል ናቸው። ተግባሮቹም ሁሉ ከቅዱስ ማንነቱ የሚፈሱ ናቸው (ዘዳግም 32፥4 ይነበብ)። እርሱ በማንነቱ የትክክለኝነት ሁሉ መለኪያ ነው። ቃሉን ሁል ግዜ የሚጠብቅ እና የማይዋሽም ነው (ዘኍልቍ 23፥19፤ 2 ሳሙኤል 7፥28)።

► *እግዚአብሔር ጻድቅ መሆን ለእኛ ምን ልዩነት ያመጣል?*

*ፅድቁ የህጉ መሰረት ነው፥ ህጉም ለእርሱ እና ለሌሎች ያለን ሃላፊነቶቻችን ሁሉ ፍፁም የሆነ መለኪያ ነው። ህጉን በፅድቅ ያስተዳድራል፥ የሚታዘዙትን ይባርካል፥ ህጉን የሚተላለፉትን ይቀጣል። ይህ የሚሰቃዩትን እና ለተጨቆኑት መፅናናትን ሲሰጥ፤ ማንም ስዕተትን በመፈፀም ከእርሱ ቅጣት እንደማያመልጥ ያስጠነቅቃል "የ እግዚአብሔር ፍርድ የታመነ፣ ሁለንተናውም ጻድቅ ነው" (መዝሙር 19፥9)። እያንዳንዱን ሰው እንደ ስራው ይከፍለዋል። (ሮሜ 2፥6)። "ሁላችንም በእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለንና" (ሮሜ 14፥10)።*

**እግዚአብሔር ፍቅር ነው**

*ይህ የእግዚአብሔር ባህሪ እጅግ አስፈላጊ ነው፤ እስቲ አስቡት ሁሉን ቻይ እና ሁሉን አዋቂ የሆነ እግዚአብሔር ባይወደን ምን ያህል አስፈሪ እንደሆነ! ምን ይመስል ነበር ቅዱስ እና ጻድቅ ሆኖ ባይወደን ኖሮ? ከፍፁም ከሆነ ሃይሉ እና ቅድስናው ጋር እግዚአብሔር ይወደናል። (ሮሜ 5፥8 ይነበብ)። እግዚአብሔር የፈጠረውን ሁሉ ይባርካል (ዘፍጥረት 1፥22፥28)፥ የሰውን ልጅ ደግሞ በተለየ በህይወት ባሉ መልካም ነገሮች ሁሉ እባርካል፥ ይህንን አለም ሰዎች በደስታ የሚኖሩበት አድርጎ ለይቶለታል። [5] ለሚወዱት እና ለሚያገለግሉ ደግሞ ህይወትን በሙሉ በረከት ያደርግላቸዋል (ሮሜ 8፥28)። ፀጋው፥ ምዕረቱ፥ ትዕግስቲ እና ሰላሙ ከፍቅሩ የተነሳ በረከታችን ናቸው። (ዘፀአት 34፥6፣ ኤፌሶን 1፥7፣ ኤፌሶን 2፥4-5ን አንብብ።)*

> "እግዚአብሔር ስለ እኔ ያለኝን መጥፎ ማንነት ሁሉ አስቀድሞ አውቆ እንደሚወደኝ ማወቁ ትልቅ እፎይታ ነው። እኔ በራሴ ድክመት ደጋግሜ ተስፋ ብቆርጥም፣ እርሱ ግን ሁሉን አስቀድሞ ስለሚያውቅ በእኔ አዲስ ስህተት ተገርሞ ፍቅሩ አይቀንስብኝም፤ እኔን ለመባረክ ያለው ውሳኔም በምንም አይናወጥም።"
>
> - ጄ.አይ. ፓከር ፣ *እግዚአብሔርን ማወቅ*

"በርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወድዷልና" (ዮሐንስ 3፥16)። *ሃጥያታችንን እና አመፃችንን ሳይቆጥርብን ሁልግዜ በምዕረት ስለ ሀጥአታችን ማስተሰረያ ባደረገው በልጁ በኩል ወደ እኛ ይቀርባል።* (1 ዩሐ 2፤2)። *በመስቀል ላይ እግዚአብሔር በእኛ በልቡ የሚፈሰውን ጥልቅ ፍቅር እና ሃዘኔታ ማየት ችለናል "ፍቅር ይህ ነው፤ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው ሳይሆን እርሱ እንደ ወደደንና ስለ ኀጢአታችን ማስተስረያ ይሆን ዘንድ ልጁን መላኩ ነው"* (1 ዮሐንስ 4፥10)። *እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ያለ ዘራቸው፥ ያላቸው ተፈጥሮአዊ ተሰጥኦ፥ ወይም ምድራዊ ቦታ ተፅዕኖ ይወዳል እንዲሁም ለሁሉ ይቅርታን አቅርቧል* (ሮሜ 2፥11፤ ያዕቆብ 2፥1-5 ይነበብ)። *ስለዚህም እግዚአብሔር ሁሉም ሰው እንድንወድድ እና የበደሉንን ሁሉ*

---

[5] *መዝሙር* 8፥4-6፤ *መዝሙር* 23፤ *መዝሙር* 36፥5-10፤ *መዝሙር* 103

ይቅር እንድልን ይፈልግብናል። ፍቅር እና ይቅርታ የእግዚአብሔር ልጆች መገለጫዎች ናቸው (ማቴዎስ 5፥43-45 ይነበብ)።

> "ጌታ ሆይ! አንተ ለእራስህ ፈጥረኸናል፤ ልባችንም በአንተ ውስጥ ዕረፍት እስኪያገኝ ድረስ ዕረፍት የለውም።"
> - ቅዱስ አውግስጢኖስ

እግዚአብሔር በራሱ መልስ ነው የሰራን፤ እኛ ውስን ሆነን እርሱ ግን ወሰን የሌለው/ማለቂያ የሌለው ቢሆንም ከፍጥረት ሁሉ እርሱን የምንመስለው እኛ ነን። እርሱን እናውቀው፣ እንናመልከውና እንወደው ዘንድ በዚህ መንገድ ሰርቶናል። እርሱ ለራሱ ፈጥሮናል አገስቲን እንደሚያስታውሰን፥ በእርሱ እስክናርፍ ድረስ እረፍት የለንም። ከእግዚአብሔር ጋር ሲስተያይ በምድር ያለ ሁሉ አላስፈላጊ የሆነ እና ያልንን ሁሉ መሰጠት መውሰድ ያለበት እግዚአብሔር ብቻ ነው። ዘለቄታዊ የሆነ እርካታን ከእግዚአብሔር ውጪ የትም ማግኘት አይቻልም። በእርሱ ምዕረት የዳንን እና ከሁሉ በላይ አድርገን እንድናመልከው እና እንደ ሰማያዊ አባታችን እንድናምነው እና በሁሉን የህይወት መንገድ ላይ የእርሱን ፈቃድ እንድናደርግ ተደርገናል።

## እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው

*ለክፍሉ መሪ ማስታወሻ- የክፍሉ አባል ይህንን ክፍል ማስረዳት ይችላል።*

እግዚአብሔር ፍፁም ስልጣን እና ፍፁም ሃይል አለው። እንደ ፍጥረተ አለሙ ገዢ የፈለገውን ማድረግ ይችላል (መዝሙር 115፥3፣ መዝሙር 135፥5-6)

ሁሉን ነገር እንደ ፈቃዱ ለማንም መገዛት ሳያስፈልገው ያደርጋል (ኤፌሶን 1፥11)። እንዲሆን የወሰነው ሁሉ ይሆናል ማንን ሊያስቆመው ሆነ የትኛውም ሁኔታ ለእርሱ የማይቻል ሊያደርገው አይችልም (ኢሳይያስ 46፥9-11 ይነበብ)። እርሱ በፈለገ ግዜ የምድር መሪዎችን ተግባራትን ሁሉ ይቆጣጠራል ( ዘፍጥረት 50፥20፥ ሐዋርያት ሥራ 4፥27-28)።

እግዚአብሔር ግን ለሰዎች የሚመርጡበትን አቅም ሰጥቷቸዋል፤ መልካም ከሆኑ ነገሮች መካከል መምረጥ ይችላሉ እንዲሁም ከመልካም እና ክፉ መካከል መምረጥ ይችላሉ። እግዚአብሔር መታዘዝ ሆነ አለመታዘዝ መምረጥ ይችላሉ። ከሰው ሁሉ መጀመርያ የፈጠራቸው ሰዎች ኀጥያትን መስራት መርጠዋል። ከእነሱ በኃላ የተፈጠረው ሰው ሁሉ ምርጫ መርጧል፥ አንዳንዶች መልካምን ቢመርጡም ሁሉም ግን ኀጥያተኞች ናቸው።

እግዘአብሔር የሁሉ ጌታ ከሆነ- በቢሊየን የሚቆጠሩ ፍጥረታት የራሳውን ምርጫ በሚመርጡበት ምድር ላይ ፈቃዱን እንዴት ይከውናል?

ፍጥረት የራሳቸውን ምርጫ እንዲመርጡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፥ ይህም ማለት ሁሉንም ምርጫቸውን እርሱ አይወስልናቸውም ማለት ነው። ይህም ለሚያደርጉት ነገር እውን የሆነ ውጤት አለው ማለት ነው፤ ካልሆነማ እውነተኛ ምርጫ እያደረጉ አይደለም ማለት ነው። እግዚአብሔር በሆነ መንገድ ክፋት እንዳይከሰት የሰዎችን ተግባር የሚቆጣጠር ከሆነ ከሰዎች ክፊትን የመምረጥን ዕድል ይወስድባቸዋል ማለት ነው።

የእግዚአብሔር ፍትሕ እውነተና ፍትሕ ነው ምክንያቱም ሰዎች በፈቃዳቸው ለወሰኑት እና ላደረጉት ተግባር እየፈረደባቸው ስለሆነ (ራእይ 20፥12-13 ይነበብ)። እግዚአብሔር ሁሉንም ተግባር ከተቆጣጠረ እንግዲያው ለመቅጣት ሆነ ለመሸለሙ ትርጉም የለሽ ይሆናል።

እግዚአብሔር ሰዎች መልካም የሆነውን እንዲመርጡ ይሻል፤ ከሁሉ በበለጠ ግን ምርጫቸው የእውነት/ እውን እንዲሆን ይፈልጋል። ለዚህ ነው አሁን ያለችን አለም እንዲህ የሆነችው። ምድር ከእግዚአብሔር የሆኑ መልካም ነገሮች ፥ ከሰው መልካም ተግባር ውጤቶች፥ የሰው ክፉ ተግባር ውጤቶች እንዲሁም እግዚአብሔር ከሰው ክፉ ተግባው የሚያመጣው መልካም ውጤት ስብስብ ነች።

እግዚአብሔር ቅድሚ የሚሰጠውን ነገር በመዳን ዕቅድ ውስጥ እንመለከተዋለን፥ እርሱ ለሰዎች ሁሉ መዳንን ያቀርባል፤ ሁሉም እንዲድኑም ይፈልጋል (1 ጢሞትዎስ 2፥3-4)። ለእያንዳንዱ ሰው ለወንጌል ምላሽ የመስጠትን አቅም ይሰጣል እንጂ ማንንም አያስገድድም። ለዚህ ነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥሪ እና ማሳመኛ ቃላት ጥቅም ላይ የዋሉት፥[6] እግዚአብሔር ለሰዎች ምርጫን እና ውጤታቸውን ገልጦላቸዋል።

ወንጌል በሙሉ ድፍረት የምንሰብከው ሁሉም ሰው እንዲድን ነው። አላማችን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመሆን ሰዎች ለእግዚአብሔር እንዲገዙ ማሳመን ነው (2 ቆሮንቶስ 5፥11 ይነበብ)።

► የእምነት መግለጫውን ቢያንስ ሁለት ግዜ አብራችሁ አንብቡ።

### የእምነት መግለጫ

ፍጥረተ-አለምን ሁሉ የፈጠረ እና የሁሉ ጌታ የሆነ አንድ አምላክ አለ። እርሱን ዘላለማዊ፥ የማይለወጥ፥ መንፈስ ነው። እርሱ ሁሉን ቻይ፥ ሁሉን አዋቂ፥ በሁሉም በሆታ የሚገኝ ነው። እርሱ በባህሪው እና በፅድቅ በሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ፍጹም ቅዱስ ነው። ፍጥረቱን የሚባርክ እና ሁሉንም ሰዎች የሚወድድ፥ ይቅርታን የሚሰጥ እና ከእርሱ ጋር ግንኙነት እንዲኖራቸው የሚጋብዝ ነው።

---

[6] ዘዳግም 30፥15፣ 19፤ ኢያሱ 24፥15፤ ኢሳይያስ 1፥18፤ ኢሳይያስ 55፥1፤ ሕዝቅኤል 18፥31፤ ራእይ 3፥20

## ትምህርት 2 የቤት ስራዎች

(1) የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የቤት ስራ፡- ከታች ከተዘረዘሩት ዘርፎች መካከል እያንዳንዱን ተማሪ አንድ ይመደብ። ከሚቀጥለው ክፍለ ግዜ በፊት ክፍሉን አንብባችሁ በትምህርቱ ውስጥ ካለው ሃሳብ ላይ ምን እንደሚናገር በአንድ አንቀፅ ፃፉ።

- መዝሙር 139፥ 1-4
- ምሳሌ 9፥10
- ኢሳይያስ 46
- ራእይ 4፥9-11

(2) ፈተና፡- የሚቀጥለው ክፍለ ግዜ የምትጀምሩት በትምህርት 2 ፈተና ነው። ለፈተና ዝግጅት እንዲሆን የፈተና ጥያቄዎችን አጥኑ።

(3) የማስተማር የቤት ስራ፡- ከክፍል ውጪ የማስተማርያ ግዜን ቀጠሮ መያዝ እና ማስተማራችሁን ሪፖርት ማድረግ አስታውሱ።

## ትምህርት 2 ፈተና

(1) የአንድ ሰው በጣም አስፈላጊ የሆነውን ማንነቱ/ባህሪው ምንድን ነው?

(2) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው የመጀመርያው ትምህርት ምንድን ነው?

(3) ከእያንዳንዱ አርፍተ ነገር ጋር የሚዛመደውን የእግዚአብሔርን ባህሪ/ማንነት ጻፉ።

- እግዚአብሔር ምን አይነት ገጽታ እንዳለው መግለጽ አንችልም
- እግዚአብሔር ሑል ግዜ ያለ እና የነበረ ነው
- እግዚአብሔር እውቀት፥ ስሜት እና ፈቃድ አለው
- እግዚአብሔር አይቀያየርም
- የፈቀደውን/የመረጠውን ሑሉ ማድረግ የሚችል ነው
- ሑሉም መመልከት የሚችል ነው
- እግዚአብሔር ምዕረትን እንድናገኝ ልጁን ላከልን
- እግዚአብሔር በሦስት አካል በአንድ ሕላዌ አለው
- እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ የሆነ ሞላዊ ፍጽምና አለው
- እግዚአብሔር ምንም የሚማረው ነገር የለም
- የእግዚአብሔር ተግባራት ሑሉ ግዜ ፍትሓዊ እና ስርዓት የጠበቀ ነው

# ትምህርት 3

# ሥላሴ

## የትምህርቱ አላማ

(1) ተማሪው የሚከተሉትን ማስረዳት ይችላል

- "እግዚአብሔር ማን ነው?" የሚለውን ጥያቄ ሥላሴ እንዴት እንደሚመልሰው
- ስለሥላሴ ያለን እምነት ጸሎታችንን እና አምልኳችንን እንዴት ጥልቅ እንደሚያደርገው
- ሥላሴ በወንጌል ውስጥ እንዴት እንደተገለጠ
- ስለሥላሴ አስተምሮ ያሉ ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች
- ስለሥላሴ ስናወራ የምንጠቀማቸው የተወሰኑ ቃላት አስፈላጊነት እና የትኞቹን ቃላት መጠቀም እንዳለብን
- ሥላሴ እግዚአብሔር በፍጥረት፣ ድነት እና በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ያለውን አላማ እንዴት እንደሚያስረዳ
- ስለ ሥላሴ ክርስቲያናዊ የእምነት መግለጫ

(2) ተማሪዎች እግዚአብሔር እንደተከፋፈለ ወይም የተለያዩ ክፍሎች እንዳሉት የሚናገሩ እንዲሁም በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን ማንነት መለየት የማይችሉ የስህተት ትምህርቶችን መለየት ይችላሉ።

## መግቢያ- እግዚአብሔር ማን ነው?

አንድን ሰው ለመጀመርያ ግዜ እንዳገኛችሁት አስቡ[7] "ማን ነህ/ሽ?" ብለው ሲጠይቁ ምላሻችሁ "እኔ ጠንካራ፣ ብልህ እና መልካም ነኝ" ወይስ "እኔ የሰው ልጅ ነኝ- አካል እና ነፍስ አለኝ" ብላችሁ ነው የምትመልሱት? በእርግጥ እንዲህ አይደለም! እነዚህ መልሶች **ምን** እንደሆናችሁ ነው የሚናገሩት (ጠንካራ፥ መልካም፥ ብልዕ ሰው) ነገር ግን **ማን** እንደሆናችሁ አይናገሩም። አንድ ሰው ማን እንደሆንን ሲጠይቀን የምንሰጠው ምላሽ ስማችንን ነው፤ ለምሳሌ "እኔ ዮሐንስ ነኝ" ወይም "እኔ ማርያም ነኝ"'።

አሁን ይህንን ጥያቄ ተመልከቱ፥ "እግዚአብሔር ማን ነው?" ብዙ ሰዎች የሚሉት "እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ፥ ፍጹም መልካም እና ጥበበኛ ነው" ወይም "እግዚአብሔር መለኮት ነው፤ መንፈስ ነው"። እነዚህ ነገሮች ሁሉ እውነትና አስፈላጊ ናቸው። እነዚህ ምላሾች ሁሉ እግዚአብሔር **ምን** (ሁሉን ቻይ፥ መልካም እና ጥበበኛ መንፈስ) እንደሆነ የሚነግሩን ናቸው። ይህንን ጥያቄ የምንመልስበት ምርጥ መንገድ "እግዚአብሔር አብ፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ነው" በማለት ነው። ይህ እግዚአብሔር **ማን** እንደሆነና ይህንንም መረዳት ከእግዚአብሔር ጋር በተሻለ መንገድ ግንኙነት እንድንፈጥር ይረዳናል። በእግዚአብሔር ማንነት ውስጥ ሦስት የሆነ ነገር አለ። የላቲኑ ቃል *trinitas* (ሥላሴ) ሦስት ማለት ነው። ሥላሴ "እግዚአብሔር ማን ነው?" የሚለውን ጥያቄ መልስ ነው።

---

[7] በዚህ ትምህርት ውስጥ ያለው ሃሳብ የተሰጠው በ Johnathan Arnold ከ Dr. Tom McCall እና Dr. David Fry ጋር በመተባበር ሲሆን በ Dr. Stephen Gibson ዋና ጸሐፊነት ነው።

"በእግዚአብሔር አምናለው" ማለት ወይም "እግዚአብሔር ሆይ እርዳኝ" ብሎ መጸለይ ጥሩ ነው። ነገር ግን አይሁድ ወይም ሙስሊም እንዲሁ ሊናገሩ እና ሊጸልዩ ይችላሉ። ነገር ግን ክርስቲያኖች ብቻ ናቸው "በእግዚአብሄር አብ፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ አምናለው" ማለት የሚችሉት። እንዲሁም ክርስቲያኖች ብቻ ናቸው "አባት ሆይ የምለምንህን ስጠኝ፥ እየሱስ ማረኝ፥ መንፈስ ቅዱስ ምራኝ" ብለው መጸለይ የሚችሉት። ክርስቲያኖች ብቻ ናቸው እግዚአብሔር ማን እንደሆነ የሚያውቁት፥ ለዚህም ነው ስነመለኮታዊው ጎርጎርዮስ " እኔ 'እግዚአብሔር' ስል 'አብ፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ' ማለቴ ነው። "[8]

## የመግቢያ ጸሎት

"እግዚአብሔር ማን ነው?" ለሚለው ጥያቄ ምላሹ ሥላሴ ከሆነ ይህን አስተምሮ ማጥናታችን እግዚአብሔርን እንድናውቀው እና እንድናከብረው ሊረዳን ይገባል። የሥላሴ አስተምሮ ለጸሎት ሕይወታችን ጥልቀት ይሰጠዋል ምክንያቱም እግዚአብሔርን በማንነቱ እንድናመልከው ስለሚረዳን። በመቀጠል ከሥላሴ ጋር ባለን የግል ግንኙነት ማደግ እንድንችል ልንጸልየው የሚገባ አይነት ጸሎት ምሳሌ ነው።

►ጸሎቱን በክፍል ውስጥ በጋራ አንብቡት[9]። ይህንን ትምህርት የምታጠኑት ከሰዓት በሗላ ወይም ምሽት ላይ ከሆነ የሚከተለውን ተናገሩ "ሰማያዊ አባት ሆይ፤ እንደምን ዋልክ" ወይም "ሰማያዊ አባት ሆይ፤ እንዴት አመሸህ።"

*መልካም ማለዳ፥ ሰማያዊ አባት፣*

*መልካም ማለዳ፤ ጌታ እየሱስ፣*

*መልካም ማለዳ፥ መንፈስ ቅዱስ፣*

*ሰማያዊ አባት፤ የፍጥረተ አለሙ ፈጣሪ እና ጠባቂ ስለሆንክ አመልክሃለው።*

*ጌታ እየሱስ፥ የምድር አዳኝ እና ጌታ ስለሆንክ አመልክሃለው።*

*መንፈስቅዱስ፥ የእግዚአብሔር ህዝብ የምትቀድስ ስለሆንክ አመልክሃለው።*

*ክብር ለአብ፣ ለወልድ እና ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን።*

*ሰማያዊ አባት፥ በአንተ መገኘት ውስጥ እንድኖር እና ሁልግዜ በበለጠ እንዳስደስትህ እጸልያለው።*

*ጌታ እየሱስ፥ ዛሬ መስቀሌን ተሸክሜ እንድከተልህ እጸልያለው።*

*መንፈስ ቅዱስ፥ ዛሬ በራስህ ትሞላኝ ዘንድ እንዲሁም በሕይወቴ ፍሬህን፤ ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግስት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ ታማኝነት፥ ገርነት እና ራስን መግዛት ማፍራት እንድትችል እጸልያለው።*

---

[8] *ንግግር 38። ጎርጎርዮስ ዘነገረ መለኮት (በተጨማሪም ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ በመባል የሚታወቀው) ከአሁኗ ቱርክ የተገኘ ታላቅ ክርስቲያን ምሁር ነበር።*

[9] ይህ የጆን ስቶት በየቀኑ ማለዳ ከእንቅልፉ ሲነሳ የሚጸልየው ጸሎት ነበር። ጆን ስቶት በእንግሊዝ ከ1921-2011 ይኖር የነበረ የስነመለኮት ምሁር ነው።

ቅዱስ፥ የተባረክህ እና ባለግርማ ሥላሴ፥ ሶስት አካል አንድ አምላክ፥ ምህረት በእኔ ላይ እንዲሆን እለምንሃለው፤ አሜን።

## አንድ እና አንድ ብቻ አምላክ

በብሉይ ኪዳን፤ እግዚአብሔር ህዝቡን አንድ አምላክ ብቻ እንሆነ እንዲናገሩ አዝዟል "እስራኤል ሆይ ስማ፤ እግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) አምላካችን፣ እግዚአብሔር (ያህዌ) አንድ ነው" (ዘዳግም 6፥4)። ይህ እምነት እስራኤላውያንን ከሌሎች ብዙ አማልክትን ከሚያመልኩ ሕዝቦች የሚለያቸው ነበር። እየሱስ እና ሐዋርያትም እግዚአብሔር አንድ አምላክ እንደሆነ በማስተማር ቀጥለዋል (ማርቆስ 12፥29፣ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፥5)። ሦስት አማልክት ሆነ 10 አማልክት የሉም። የማይታይ፥ ኃያል መንፈስ የሆነ "እግዚአብሔር" የሚባል አንድ ብቻ አለ።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ በተመሳሳይ ግዜ በአንድ አምላክ ውስጥ ሦስትነት ወይም ብዝሓነትን የሚጠቁሙ ሀሳቦች አሉ። እግዚአብሔር አዳም እና ሔዋንን ሲፈጥር እንዲህ አለ "እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ "ሰውን በመልካችን፣ በአምሳላችን እንሥራ..." (ዘፍጥረት 1፥26)። እግዚአብሔር ከማን ጋር እየተነጋገረ ነው? "በመልካችን" (በብዙ ቁጥር) የሚለው ለምንድን ነው? ኢሳይያስ በራዕይ እግዚአብሔርን በመቅደሱ ሲያየው፥ መላዕክት "ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ..." (ኢሳይያስ 6፥3) ሲሉ ሲሰማቸው እና እግዚአብሔርም አለ "...ማንስ ይሄድልናል?" (ኢሳይያስ 6፥8)። በመዝሙረ ዳዊት 110፥1 ላይ ያሕዌ ሌላ የዳዊት ጌታ ተብሎ ከሚጠራ ጋር ይነጋገራል፤ እንዴት ጌታ ከጌታ ጋር ያወራል?

ለእነዚህ ጥያቄዎች ምርጥ የሆነው ምላሽ የሚገኘው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ታላቅ ታሪክ ነው። ጸሓፊውም ታሪኩን ለመቀበል ዝግጁ እስክንሆን ድረስ እስከመጨረሻው ሊገልጣቸውን ያልወደዳቸው አንዳንድ እውነቶች አሉ። እግዚአብሔር ስለራሱ ያለውን ጥልቅ እውነት የገለጠው እግዚአብሔር አብ ልጁን ተሦዕን እንዲሆን በላከ ጊዜ እና በኋላም በጴንጤቆስጤ ቀን መንፈስ ቅዱስን በላከ ጊዜ ነው። ወንጌላት አንድ በሆነው አምላክ ውስጥ በእርግጥ ሦስትነት እንዳለ ያመላክታል። ሥላሴ እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጆች የገለጠበት ታላቅ መገለጥ ነው። ይህን በክርስትና እምነት ውስጥ ማዕከላዊ የሆነ ነው።

## ተሦዕን፤ የእግዚአብሔር ልጅ መገለጥ

እግዚአብሔር ራሱን በበለጠ የገለጠው ግዜው በደረሰ ግዜ "...እግዚአብሔር...ልጁን ላከ" (ገላትያ 4፥4)[10] ፤ "...እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወድዷልና" (ዮሐንስ 3፥16)። እግዚአብሔር ልጁን ከላከ፤ እንግዲያው አንዱ እግዚአብሔር ልጅ ያለው አባት ነው ማለት ነው። ልጅ ወደ ምድር ከተላከ፤ እንግዲያው ከመምጣቱ በፊት የእግዚአብሔር ልጅ ነበር ማለት ነው።

እየሱስ ልዩ በሆነ መንገድ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ መናገሩ ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩልነቱን መሆኑን ያሳያል ያደርገዋል። ዮሐንስ 5፥18 ሲናገር "እንግዲህ አይሁድ፣ ኢየሱስ ሰንበትን ስለ ሻረ ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን አባቱ በማድረግ፣ ራሱን ከእግዚአብሔር እኩል በማድረጉ፣ ሊገድሉት አጥብቀው ይፈልጉት ነበር። " እየሱስም "...አብርሃም ከመወለዱ በፊት እኔ፣ እኔ ነኝ" (ዮሐንስ 8፥58) ሲል ያህዌ (ዘፀአት 3፥14) ነኝ ማለቱ

[10] ዕብራውያን 1፥2 እና ማቴዎስ 16፥16 ንም ይመልከቱ

ነበር። በ1ኛ ቆሮንቶስ 8፥6፤ ጳውሎስ በዘዳግም 6፥4 ("...እግዚአብሔር አንድ ነው") በማለት ያረጋግጥልናል፤ ነገር ግን የጌታችን የእየሱስ ክርስቶስን ማንነት በአንዱ ፈጣሪ አምላክ ውስጥ በማካተት ነው።

### "አብ ከእኔ ይበልጣል"

በዮሐንስ 14፥28 ላይ እየሱስ "...አብ ከእኔ ስለሚበልጥ። " በማለት ተናግሯል። ይህ ቁጥር የሚናገረው ወልድ ከእግዚአብሔር ያንሳል ማለት አይደለም፤ ጠቅላላው የዩሐንስ ወንጌል የወልድን እና አብን[11] እኩልነት በማስረገጥ የሚናገር ነው። ዮሐንስ 14፥28ም በአውዱ ውስጥ ነው መነበብ ያለበት። እየሱስ ደቀመዛሙርቱን "...ብትወድዱኝስ አብ ከእኔ ስለሚበልጥ ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር። " ብሏል። ይህን ሲል እየሱስ በምድር ላይ የሰው ልጅ (በመከራው ሁሉ) መሆኑን በሰማይ ካለው አባቱ (ከነሙሉ ክብሩ) ጋር በማነጻጸር ነው። እየሱስ ደቀመዛሙርቱ የሚወዱት ከሆነ፤ አለም ሳይፈጠር በፊት በአባቱ ዘንድ ባለው ክብር እንዲከብር እንደሚፈልጉ ይነግራቸዋል። (ዮሐንስ 17፥5 ይመልከቱ)። አስታውሱ፥ እየሱስ ፍጹም መለኮት እንዲሁም ፍጹም ሰው ነው። እንደ አምላክ (በመለኮታዊ ማንነቱ በኩል) ወልድ ከአብ ጋር እኩል ነው። እንደ ሰው (በሰዋዊ ማንነቱ በኩል)፤ በስጋ የተገለጠው ወልድ ከአባቱ በታች እና ለአባቱ የሚገዛ ነው። አገስቲን እንደሚያስረዳው "የእየሱስን ሁለት ማንነቶች እውቅና መስጠት አለብን- መለኮት፤ ከአባቱ ጋር እኩል የሚሆንበት፤ እንዲሁም ሰው፤ አባቱ ከእርሱ የሚበልጥበት"።

### ተሦዕን፤ የእግዚአብሔር ልጅ መገለጥ (የቀጠለ)

የእግዚአብሔር አብ ልጅ እንደመሆኑ፥ እየሱስ አባት አይደለም። ልጅ አባቱ ጋር አንድ አካል አይደለም። በዮሐንስ 1 እየሱስ "እግዚአብሔር" (1፥1) እንዲሁም "ከቶውንም እግዚአብሔርን ያየ ማንም የለም ... አንድያ ልጁ..." (1፥18) ተብሏል፥ እንዲሁም "ከእግዚአብሔር [አብ] ጋራ" (1፥1) እንዲሁም "ከአባቱ ዘንድ የመጣውን የአንድያ ልጅን" (1፥14) ተብሏል። ወልድ ከአባቱ ተልኳል (ዮሐንስ 5፥23)፥ ወደ አባቱ ጸልዩል (ማቴዎስ 26፥39) እንዲሁም አብን እንዲከብር ራሱ አብ ወልድን እንዲያከብረው ጠይቋል (ዮሐንስ 17፥1)። ወልድ አባቱን ቢሆን ኖሮ፥ ወልድ ራሱን ነው የሚልከው፥ ከራሱ ጋር ነው የሚያወራው፥ እንዲሁም ራሱ ራሱን እንዲያከብረው ነው የሚጠይቀው። ይህ ምንም ትርጉም አይሰጥም!

በአብ እና ወልድ መካከል እውን የሆነ ልዩነት አለ፥ ነገር ግን በአንድ መለኮትነት ፍጹም የተጣመሩ ናቸው። በዮሐንስ 14፥11 እየሱስ እንዲህ ሲል ተናገረ "እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ ስነግራችሁ እመኑኝ..."። አብ እና ወልድ አንዳቸው በሌላቸው ውስጥ ፍጹም በአብሮነት ይኖራሉ ምክንያቱም አንድ ዘላለማዊ መንፈስ ስለሆነ። ሁለት የተለያዩ መናፍስት አይደሉም እንዲሁም ሁለት የተለያዩ አማልክት አይደሉም።

የሥላሴ አስተምሮ ከእነዚህ የእየሱስ ትምህርቶች እንዲሁም ስለመንፈስ ቅዱስ ያስተማራቸው ትምህርቶች ላይ ትኩረት ያደረገ ምልከታ ውጤት ነው።

---

[11] ዩሐንስ 1፥1፣ 18፤ ዩሐንስ 5፥18፤ ዩሐንስ 8፥58፤ ዩሐንስ 10፥30፤ ዩሐንስ 14፥9፤ ዩሐንስ 17፥5፤ ዩሐንስ 20፥28

## ጴንጤቆስጥ፤ የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ


እየሱስ ስለአባቱ ሁልግዜ?? ተናግሯል፥ ነገር ግን ስለ ሌላም እንዲሁ ተናግሯል- መንፈስ ቅዱስ። እየሱስ አብ መንፈስን እንዲልክ እንደሚለምነው ቃል ገብቷል (ዮሐንስ 14፥16–17)። እየሱስ ከአብ የሚሰርጸውን መንፈስ እንደሚልክ ቃል ገብቷል (ዮሐንስ 15፥26)። አብ መንፈስ ቅዱስን በእርሱ ስም እንደሚልክላቸው እየሱስ አስረግጦ ነግሯቸዋል (ዮሐንስ 14፥26)። ከትንሳኤው እና ዕርገቱ በኋላ እየሱስ ከአብ ቃል የተገባውን መንፈስ ቅዱስ ተቀብሏል፤ ይህንንም መንፈስ ቅዱስ በደቀመዛሙርቱ ላይ በጴንጤቆስጥ ቀን አፍስሷል (ሐዋርያት ሥራ 2፥33)።

እንደ እግዚአብሔር መንፈስ፥ መንፈስ ቅዱስ ከአብ እና ወልድ ጋር እኩል ነው። አንድ ሰው ሲዋሽ ጴጥሮስ እንዲህ ሲል ጠየቀው "ሐናንያ ሆይ፤ መንፈስ ቅዱስን ትዋሽና ... ሰይጣን ልብህን ለምን ሞላው? የዋሸኸው እኮ እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አይደለም" (ሐዋርያት ሥራ 5፥3–4)። መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው። እርሱ ዘላለማዊ (ዕብራውያን 9፥14) እና ሁሉን አዋቂ (1ኛ ቆሮንቶስ 2፥10–11) ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ መንፈስ ቅዱስ አብ ወይም ወልድ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ሌላ አካል ነው፥ ልክ ወልድ ሌላ አካል እንደሆነ (አብን እንዳልሆነ)። መንፈስ ቅዱስ በአብ እና ወልድ የተላከ ነው፥ የሚናገረውም ከአብ እና ከወልድ የሰማውን ነው (ዮሐንስ 16፥13) እንዲሁም ልጁን ሊያከብር ነው የመጣው (ዮሐንስ 16፥14)። መንፈስ ቅዱስ አብና ወልድ ቢሆን ራሱን ነበር የሚልከው፥ ከራሱ የሰማውን ነበር የሚናገረው እንዲሁም ራሱን ለማክበር ነው የሚፈልገው። ይህ ምንም ትርጉም አይሰጥም!

## ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

ማቴዎስ 3፥13–17 በአብ፥ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለው መስተጋብር የሚያስረዳ አስፈላጊ ክፍል ነው። እየሱስ ሲጠመቅ፥ አብ ከሰማይ ተናገረ ("በርሱ ደስ የሚለኝ የምወድደው ልጄ ይህ ነው") እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ የማይታይ ቢሆንም በእርግብ መልክ ተገልጦ በእየሱስ ላይ አረፈ። አብ ወልድ ነው ማለትም ሆነ መንፈስ ቅዱስ ወልድ ነው ማለት ምንም ትርጉም የማይሰጥ ነው። ይህ እውነት ቢሆን ኖሮ እየሱስ የራሱን ድምጽ ወደ ሰማይ ልኮ፤ በራሱ እንደተደሰተ እየተናገረ እንዲሁም በራሱ ላይ እያረፈ ይሆናል ማለት ነው! በእየሱስ ጥምቀት ላይ ሦስት ነበሩ።




በማቴዎስ 28፥19 ላይ ያለውን የጥምቀት ስርዓት ለሥላሴ ክርስቲያናዊ አስተምሮ ማዕከላዊ ነው፤ "ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። " በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ስሙን (ያሕዌ) በህዝቡ ላይ አደረገ፥ እንዲሁም ስሙን በአሕዛብ መካከል እንዲሸከሙ ጠራቸው (ዘኍልቍ 6፥27፤ ዘዳግም 28፥10)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ የአብ፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስን ስም በማድረግ ለተልዐኮ ወደ አለም ልኳቸዋል። ይህም አብ፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዳቸው እግዚአብሔር መሆናቸውን ነገር ግን እንደሚለያዩ

ያሳያል። የሥላሴ አስተምሮ ደቀ መዛሙርቱን በሥላሴ ስም መጠመቅ ምን ማለት እንደሆነ ያስረዳቸዋል። ሁሉም ክርስቲያናዊ ስነመለኮት የሚገነባው ከዚህ ሃሳብ በመነሳት ነው።

► በዚህ ገጽ ላይ ያለው ምስል "የሥላሴ ጋሻ" በመባል ይታወቃል፤ እስካሁን የተማርናቸውን አስፈላጊ የሆኑ የተወሰኑ እውነቶችን ያጠቃልላል - ምስሉን በድጋሚ ስሩት፤ ይህም እንድታስታውሱት ይረዳቿል።

### ቃላት ዋጋ አላቸው፡- በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ያሉ ቁልፍ ቃላት

ወንጌል **በአንዱ** መለኮት ውስጥ **ሦስትነት** እንዳለ ያሳያል። ነገር ግን የእግዚአብሔር ሦስትነት እና አንድነት በአንድ አይነት መንገድ አይደለም። ሦስት አማልክት እና አንድ አምላክ አይደለም ያለው። ይህ የሚጣረስ ሃሳብ (እንዲሁም ግልጽ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ክህደት) ነው። ይህንን እግዚአብሔር ሶስት የሆነበትን እና "...እግዚአብሔር አንድ ነው" (ዘዳግም 6፥4) የሚለውን ለማስረዳት ቃላት ያስፈልጉናል።

በመጀመርያዋ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ብዙዎች ግሪክ ወይም ላቲን ቋንቋ ነበር የሚናገሩት፤ ስለዚህም ምን ቃል መጠቀም እንዳለባቸው ለብዙ መቶ አመታት ይነጋገሩ ነበር። ስለ እግዚአብሔር ለመናገር የሚበቃ ቋንቋ ማግኘት አስቸጋሪ መሆኑ ሊያስደንቀን አይገባም። የሰው ቋንቋ እግዚአብሔርን በሚገባ ሊገልጸው አይችልም። ነገር ግን፥ ስለ እግዚአብሔር ከምናምነው ነገር በላይ ምንም አስፈላጊ ነገር ስለሌለ ሌሎችን ላለማሳትም ሆነ በማይገባ መንገድ ላለመምራት ቃላቶቻችንን በጥንቃቄ በመምረጥ ያስፈልጋል።

*Ousia* (ግሪክ) እና *substantia* (ላቲን) የሚሉት ቃላት **ስለእግዚአብሔር አንድነት** ለመግለጥ ምርጥ ሆነው የተገኙ ቃላት ነበሩ፤ ለ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የጋራ የሆነ ቃል ነው። ጌታ በ *ousia* እና *substantia* አንድ ነው። እነዚህ ቃላት አንድ ነገር **ምን** እንደሆነ የሚጠቁሙ ናቸው (በዚህ ትምህርት መጀመርያ ላይ ያለውን ምስል ይመልከቱ)። እግዚአብሔር አንድ የማይታይ፥ ዘላለማዊ፥ በኃይል፥ በእውቀት እና በመልካምነት ፍጹም ነው። ስብዕና/ መለኮታዊ ማንነት የሚለው ቃል (ከላቲኑ *substantia*) የምንጠቀመው እግዚአብሔርን አንድ ስለሚያደርገው ነገር ነው። ማንነት፥ ስብዕና፥ እና ህልውና የሚሉትን ቃላትም ጥቅም ላይ ውለዋል። አንድ ብቻ መለኮታዊ ህልውና ወይም ማንነት አለ።

*Hypostasis* (ግሪክ) እና *persona* (ላቲን) የሚሉት ቃላት **የእግዚአብሔርን ሦስት** ለመግለጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላት ናቸው። አብ፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ሦስት እውነት እና የተለያዩ *hypostases* or *personae* ናቸው። እነዚህ ቃለት **ማንነትን** የሚያመላክቱ ናቸው። በድጋሚ፥ ሥላሴ "እግዚአብሔር ማን ነው?" ለሚለው ጥያቄ መልስ ነው። አካል (ከላቲኑ *personae*) ጥቅም ላይ የሚውለው የእግዚአብሔርን ሦስትነት ለመግለጥ ነው። *ሰዎች* ወይም *ግለሰቦች* የሚሉትን ቃላት አንጠቀምም፥ ምክንያቱም የተለያዩ ማንነቶችን ወይም ህልውናን ስለሚያመላክት።

እነዚህ ቃላቶች በራሳቸው ድካም እና ገደብ አለባቸው፥ ስለሆነም ያልተገባ ትርጉም እንዳይኖር በጥንቃቄ ማስረዳት ይኖርብናል። በየትኛውም ቋንቋ የሚጠቀሙ የስነመለኮት ሰዎች የትኛውን ቃላት መጠቀም እንዳለባቸው በጥንቃቄ ማሰብ አለባቸው። አንዳንድ ግዜ ቋንቋ ልንጠቀመው የሚችለው ጥሩ ቃላት አይኖሩትም። ነገር ግን በሰፊት የሚታወቅ እና የምንረዳውን ቃላል መጠቀም ይጠቅማል። ለምሳሌ እነዚህ ቃላት ዮሐንስ 10፥30 ምን ማለት እንደፈለገ እና እንዳልፈለገ ለማስረዳት ይጠቅመናል። እየሱስ "እኔና አብ አንድ ነን" ሲል እያለ ያለው "እኔ እና አብ በማንነት ወይም በህልውና አንድ ነው " ሲሆን "እኔና አብ አንድ አካል ነን" ግን እያለ አይደለም። ዮሐንስ

*"…ቃልም ከእግዚአብሔር ጋራ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ" (ዮሐንስ 1፥1) ለማለት የፈለገው "ወልድ ከእግዚብሔር አብ ህላዌ/አካል ጋር ነበር እና ወልድ እንደ አብ ያለ መለኮታዊ ማንነት (ተመሳሳይ ህልውና) ነበረው" ለማለት ነው።*

### *ለመረዳት ለምንድን ነው የሚያስቸግረን*

እነዚህ ልዩነቶች ለመረዳት የሚረዱን ቢሆኑም፥ ሥላሴ ግን ለመረዳት አስቸጋሪ ነው። በአንድ ክፍል ውሰን አልባ የሆነውን እግዚአብሔር ወሰን እና ገደብ ባለው የሰው አዕምሮ በፍጹም በሙላት መረዳት አንችልም። ይህም የሆነበት ሌላኛው ምክንያት በፍጥረት ሁሉ መካከል ሦስት አካላት በአንድ ማንነት ሆኖ የሚገኝ ስለሌለ ነው። ስለነገሮች ብዙ ግዜ የምንማረው አዳዲስ ነገሮችን ከምናውቃቸው ጋር በማወዳደር ሲሆን ከእግዚአብሔር ጋር የሚወዳደር ምንም ስለሌለ ነው፤ ማንም በሦስት አካላት ያለ አንድም ፍጥረት የለም።

የሰው ልጅን አስቡት፤ በእያንዳንዱ የሰው ሰውነት ውስጥ ቁሳዊ አካል እና ነፍስ ይኖራል፥ አንድ አካል ብቻ ነው- "ዮሐንስ" ወይም "ማርያም"። አንድ ሰው ከአንድ አካል በላይ እንደሆነ ከተናገረ ምንም ትርጉም አይሰጥም ምክንያቱም የሰው ልጆች የሚኖሩት እንዲህ ስላልሆነ። ነገር ግን እግዚአብሔር ሰው አይደለም። የእግዚአብሔር ማንነት ልንመለከት ከምንችለው ማንነት ሁሉ የተለየ አይነት ነው። እግዚአብሔር የገለጠልን አንድ መለኮታዊ ማንነት ሲሆን በዚያም ሦስት አካላት አሉ። እግዚአብሔር የገለጠውን እውነት በእምነት እንዲሁ እንቀበለዋለን። አዕምሮአችን እግዚአብሔርን በሙሉ ሊረዳው ባይችልም፤ በእግዚአብሔር መገለጥ እየተደሰትን እና በመንግስተ ሰማያት እርሱን የበለጠ እናውቀው ዘንድ እንጠብቃለን።

### *ማስወገድ ያለብን ስዕተቶች፤ ስለ ሥላሴ ያለ የስዕተት አስተምሮ*

አንዳንድ ሰዎች በፍጥረት ውስጥ በሚመለከቱት ላይ በመመስረት ሥላሴን በራሳቸው መረዳት ለማስቀመጥ ይሞክራሉ፤ የሥላሴ አማንያን የሚከተሉትን ላለማድረግ ጥንቁቅ ናቸው፤ (1) አንዱን የእግዚአብሔር ሕልውና አይከፋፍሉም፥ (2) የእግዚአብሔር ሦስት አካላት አንዱን ከሌላው በሚገባ አይለዩም/ አያመሳስሉም፥ (3) ማንኛውንም መለኮታዊ አካል ከሌላው በስብዕናው አያሳንሱም ወይም እኩልነቱን አይክዱም።

1. **ሕልውና አይከፋፍሉም-** አብ፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ የአንድ ምሉዕ ሦስት አካላት አይደሉም። እግዚአብሔር ክፍፍል የለውም። እግዚአብሔር እንደ እንቁላል ሦስት ክፍሎች ያሉት አይደለም (ቅርፊት፥ አስኳል፥ እና ነጭ ክፍል). እግዚአብሔር ሦስት ክፍል ያሉት አበባ አይነት አይደለም፤ ይህ ምሳሌ *'partialism'* የሚለውን የስዕተት ትምህርት ያመላክታል።

2. ***ሦስቱን አካል መለየት አለመቻል-*** *አንዳንድ ሰዎች ወልድ በተለየ መልክ አብ እንደሆነ ይናገራሉ ወይም መንፈስ ቅዱስ ወልድ በተለየ መንገድ እንደተገለጠ ይናገራሉ። ነገር ግን አብ፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ* እያንዳንዳቸው እንደተለያዩ አካላት ሆነው እርስ በእርሳቸው መስተጋብር እንዳላቸው ተመልክተናል። አብ ወልድ አይደለም፤ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አይደለም፥ እግዚአብሔር አንድ እንደ ውሃ በሦስት የተለያየ *መንገድ የሚገለጥ አይደለም (እንደ በረዶ ጠጣር፤ ፈሳሽ ወይም እንፋሎት)። እግዚአብሔር ሰው አይደለም ሦስት የተለያየ ኮፍያ/ የፊት ጭብል አድርጎ የሚንቀሳቀስ። እግዚአብሔር ሦስት ሚና የሚጫወት ተባዕት* አይደለም (አባት፥ ባል እና ሰራተኛ)። እነዚህ ምሳሌዎች ሞዳሊዝም/ *modalism* የተባለ ወልድ እና

መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካል መሆናቸውን የሚክድ የኑፋቄ አስተምሮ ነው። *Modalism* ሌላኛው መጠርያ *Sabellianism* (በሦስተኛው ክፍለ ዘመን የነበረ *Sabellius* (ሳቤልየስ) የተባለ የስዕተት ትምህርት አስተማሪ ስም ተከትሎ የተሰጠ ስያሜ)ነው።

3. **የትኛውንም አካል ያነሰ ወይም ከሌላው የሚቀንስ ህላዌ እንዳለው አድርጎ መቁጠር-** ሌላኛው የተለየ ትምህርት ወልድ ከአብ ያነሰ እንደሆነ የሚያስተምር ነው። አንዳንድ ሰዎች ወልድ የአብ የመጀመርያው እና ታላቁ ፍጡር እንደሆነ አንስተው ያስተምራሉ። እየሱስን እንደ "መለኮት" ቆጥረው ያከብሩት ይሆናል እንጂ ከአብ ጋር እኩል እንደሆነ ሆነ ሑልግዜ ኗሪ እንደሆነ ኤአምኑም። ይህ ኑፋቄያዊ ትምህርት አርዮሳዊ/ *Arianism* (በአራተኛው ክፍለ ዘመን የነበረ *Arius* (አርዮስ) የተባለ የስዕተት አስተማሪ ተከትሎ የተሰጠ ስያሜ) ነው። የዚህ አስተምሮ ተከታዮች ወልድ ከአብ ጋር በሕልውናው ተመሳሳይ ሆኖ ነገር ግን ከእርሱ የሚያንስ እንደሆነ ያስተምራሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለወልድ የሚያስተምረን "በህልውናው ከአብ ጋር አንድ የሆነ፤" (በኒቅያ ጉባኤ እንደተጻፈው)። ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ከአብ ጋር በኃይል፥ በክብር፥ እና በዘላለማዊነት እኩል ናቸው። አምልኮ የሚገባቸው እና በሙሉ ኃይል ሊያድኑን የሚችሉ ናቸው።

► ሥላሴ የሚብራራባቸው ሌላ ምሳሌዎች/ምስላዊ ማብራርያዎችን ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ችግር ያለባቸው ወይም ሊያሳስቱ የሚችሉት ለምንድን ነው?

## እያንዳንዱ ስም የተሰጠበት ምክንያት

የሥላሴን ትምህርት በሚገባ ለመረዳት ሦስቱን አካላት በጥንቃቄ መመልከት አለብን። የመጀመርያው እና ሁለተኛው አካል 'አባት/አብ' እና 'ልጅ/ወልድ' የተባሉት ለምንድን ነው? እንዲሁም ሦስተኛው አካል 'መንፈስ ቅዱስ' የተባለው ለምንድን ነው? ስሞቹ ትርጉም አልባ አይደሉም። ስሞቹ ስለ እውተኛው እና ዘላለማዊ የሆነው እግዚአብሔር የሚነግሩን ነገር አለ። አለም ከመፈጠሩ በፊት እግዚአብሔር አብ፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ነበሩ።

### "አብ" እና "ወልድ"

እግዚአብሔር አብ በሰማይ ይሁን እንጂ (ማቴዎስ 6፥9)፥ የመጀመርያው የሥላሴ አካል "አብ/ አባት" የሚባለው በዚህ ምክንያት አይደለም። የመጀመርያው አካል "አብ/ አባት" የተባለው ለወልድ የዘላለም አባት ስለሆነ ነው። እንዲሁም ሁለተኛው አካል "ወልድ" የተባለውም ለአባቱ ዘላለማዊ ልጅ ስለሆነ ነው። አብ እና ወልድ የሚለው መጠርያ አንዳቸው ከሌላቸው ጋር ባላቸው ዘላለማዊ ግንኙነት ውስጥ ነው። አብ እና ወልድ ሁለቱም ዘላለማዊ እና ያልተፈጠረ፤ እግዚአብሔር ብቻ ያለው ሕያውነት ያላቸው ናቸው፤ ነገር ግን ይህ ሕይወት ለወልድ የተሰጠው ከአብ ነው (ዮሐንስ 5፥26)።

አብ እና ወልድ ሁለቱም ዘላለማዊ ናቸው፥ አብ ለወልድ ሕይወትን "የሰጠው" የሆነ ግዜ ላይ አይደለም፥ አብ ወልድን አልፈጠረውም። ወልድ ከአብ ከዘላለም ጀምሮ "የተገኘ" ወይም ወልድ የተገኘው ከአብ ሆኖ አብ ብቻ በሚያውቀው መንገድ ነው። ይህ የኒቅያ ጉባኤ ማዐከላዊ አስተምሮ ነው "እርሱ ብቻ የአብ ልጅ በሚሆን፤ ዓለም ሳይፈጠር ከአብ በተወለደ፤ ከአምላክ በተገኘ አምላክ፤ ከብርሃን በተገኘ ብርሃን፤ ከእውነተኛ አምላክ በተገኘ እውነተኛ አምላክ፤ በህልውናው ከአብ ጋር አንድ የሆነ፤ በተፈጠረ ሳይሆን በተወለደ፤... እናምናለን። "

ይህ ታላቅ ሚስጥር ነው- የሰውን ልጅ ውልደት እንኳን በሚገባ አልተረዳንም! እንዴት አድርገን የወልድን ከአብ ለዘላለም መገኘት ምን ማለት እንደሆነ ልንረዳ እንችላለን? የቤተ-ክርስቲያን አባቶች ስለወልድ የሚከተውን የሚለውን ዕብራውያን 1፥3 "…የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅና የባሕርዩ ትክክለኛ ምሳሌ ሆኖ…" ይጠቁሙናል። ብርሃን ሁልግዜ ነጸብራቅ አለው[12]። ሻማ እስካበራ ድረስ ብርሃን ያንጸባርቃል። አብ ዘላለማዊ ብርሃን ስለሆነ ልጁን ሁልግዜ ያንጸባርቀዋል። አብ ወልድን ማንጸባረቅ የጀመረበት ግዜ የለም። ማንጸባረቅም የሚያቆምበት ግዜ የለም። አብ እና ወልድ "በማንጸባረቅ" እና "በመንጸባረቅ" ዘላለማዊ ግንኙነት ውስት ይኖራሉ። እየሱስ "ከአምላክ በተገኘ አምላክ፣ ከብርሃን በተገኘ ብርሃን፣" ነው (የኒቅያ ጉባኤ)።

**"መንፈስ ቅዱስ"**

መንፈስ የሚለው ስም ስለ ሦስተኛው የሥላሴ አካል ዘላለማዊ እውነት የሆነውን ነገር የሚያመላክት ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ የሚለው ሀረግ *የሙሴ መንፈስ* ወይም *የአብረሃም መንፈስ* ከሚለው በሰው ዘንድ ያለውን መንፈሳዊ ወይም የማይዳሰሰውን የሰው አካል ጋር ተመሳሳይ አይደለም። እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የተለያዩ አካላት ያሉት ግን አይደሉም። ነገር ግን "የእግዚአብሔር መንፈስ" የሚለው ቃል መንፈሱ ከእግዚአብሔር እንደሆነ የሚያመላክት ነው - ልክ ወልድ ከአብ እንደሆነ። *መንፈስ* የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል "እስትንፋስ" ተብሎ ተጠቅሷል። አንድ ሰው ትንፋሹን እንደሚተነፍስ መንፈስ ከአብ "ወጣ" (ዮሐንስ 15፥26)። ብዙ ክርስቲያኖች መንፈስ ከዘላለም ጀምሮ የወጣው ከእየሱስ እንደሆነ ያምናሉ[13]።

መንፈስ ዘላለማዊ መሆኑ በግዜ ውስጥ የተላከ እንዳልሆነ ያሳያል፤ መንፈስ በአብ የተፈጠረ አይደለም። አብ በዘላለም ውስጥ መንፈስን እፍ ብሎታል። መንፈስ ከዘላለም ጀምሮ ከአብ "ወጣ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ በእርግጥ አናውቅም ነገር ግን "መገኘት" ማለት እንዳልሆነ እናውቃለን። ይህ ባይሆን አብ ሁለት ወልድ ይኖረው ነበር ማለት ነው።

**የቁልፍ ሃሳቦች ማጠቃለያ**

አማኞች ሁሉ ሊያውቁት የሚገባ ቁልፍ እውነቶችን በአትናትዮስ የእምነት መግለጫ መሰረት እንደሚከተለው ተጠቃለዋል

1. አብ ከማንም የተገኘ አይደለም። አልተፈጠረም እንዲሁም አልተገኘም (ከሌላ የማይገኝ ነው)
2. ወልድ ከአብ ብቻ ነው። አልተሰራም እንዲሁም አልተፈጠረም። በዘላለም ውስጥ ግን ከሌላ ተገኝቷል
3. መንፈስ ቅዱስ ከአብ [ከወልድ] ነው። አልተሰራም፥ አልተፈጠረም፥ አልተገኘም። በዘላለም ውስጥ ወጥቷል

---

[12] "ማንም መቼም ቢሆን ብርሃንን ያለ ብራማ አንጸባራቂነቱ ተመልክቶ አያውቅም፥ ስለወልድን 'ያልነበረበት ግዜ ነበር' ወይም ከትውልዱ በፊት አልነበረውም"? ማለትስ የሚችል አለ" (አትናትዮስ፥ *Discourse I Against the Arians* 14.12)

[13] በስድስተኛው ክፍለ ዘመን በምዕራብ ባለችው ቤተ-ክርስቲያን "እና ወልድ" ( በላቲኑ *filioque*) የሚለውን ቃል በኒቅያ ጉባኤ ላይ፤ " መንፈስ ቅዱስ… ከአብ [ ከወልድ] በሚሥርጽ" በማለት ጨመረች።*filioque*ን በመደገፍ ከተሰጡ አብዛኛው ክርክሮች መካከል "የእግዚአብሔር መንፈስ" በሮሜ 8፥9ላይ "የክርስቶስ መንፈስ" በማለት ተጠቅሷል፤ ወልድም በራሱ ግዜ መንፈስ ቅዱስን እንደላከው (ዮሐንስ 15፥26) እና እፍ እንዳለባቸው (ዮሐንስ 20፥22) ዘላለማዊ ግንኙነት አንዳላቸው አመላካች ነው፤ ይህም ልክ አብ ወልድን መላኩ ዘላለማዊ ግንኙነታቸውን እንደሚያመለክተው ነው።

4. ስለዚህ፥ አንድ አብ/ አባት አለ፤ ሦስት አቦች/አባቶች አይደለም። አንድ ወልድ/ልጅ አለ፥ ሦስት ወልዶች/ልጆች የለም። አንድ መንፈስ ቅዱስ አለ፥ ሦስት መንፈስ ቅዱሶች አይደለም።

## የማስረዳት ኃይል

ይህ ትምህርት በንግግራችን አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ (በዚህ ስድር) የምንልበት እና መንፈስ ቅዱስ፥ ወልድ እና አብ (ወይም በሌላ በየትኛውም ስድር) የማንልበትን ምክንያትን ያስረዳናል። በኃይል እና ስልጣን ሦስቱም አካላት እኩል ናቸው ምክንያቱም አንድ እግዚአብሔር ነው፤ ነገር ግን አብ የወልድ ዘላለማዊ ምንጭ ነው፥ እንዲሁም አብ [እና ወልድ] የመንፈስ ቅዱስ ዘላለማዊ ምንጭ ናቸው። ስለዚህ አብ፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ በሚለው ስድር መናገራችን ትክክል ነው።

ትምህርቱ መጽሐፍ ቅዱስ "እግዚአብሔር ወልድ" እና "እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ" ሳይል"የእግዚአብሔር ልጅ" እና "የእግዚአብሔር መንፈስ" ያለበትን ምክንያት ያስረዳናል። ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ስለሆኑ በዚህ መንገድ ስለእነሱ ማውራት ይገባናል። ነገር ግን ይህ የንግግር መንገድ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር ያላቸውን ግንኙነት በትክክል ያሳያል። "የእግዚአብሔር ወልድ" የሚለው ሀረግ የእየሱስን መለኮትን ያመላክታል ፥ "የእግዚአብሔር ልጅ" የሚለው ቃል እየሱስ "ከመለኮት የሆነ መለኮት" ማለት ነው። (በኒቅያ ጉባኤ)

በመጨረሻም ይህ ትምህርት ወንጌልን የበለጠ እንድረዳው ይረዳናል። ከሥላሴ አካል መካከል ማናቸውም ሰው በመሆን ሊያድንን ይችል ነበር። ነገር ግን ከአብ የተገኘው ወልድ በአብ ተልኮ ሊመጣ የተገባው ሆነ። ከአብ ያለእናት ከዘላለም ጀምሮ የተገኘው ወልድ በሴት/ እናት በግዜ ውስጥ ያለአባት ሊወለድ የተገባው ሆነ። ከአብ [እና ወልድ] የወጣው መንፈስ ቅዱስ ሕይወትን ይሰጠን ዘንድ ከአብ እና ወልድ ተላከ። ወንጌል ስለእግዚአብሔር ዘላለማዊ የሆነን እውነት ያመላክታል።

## የሥላሴን ፍቅር ማካፈል

የሥላሴን አስተምሮ ስንማር እግዚአብሔር የበለጠ ማን እንደሆነ እና ያደረጋቸውን ነገሮች ለምን እንዳረጋቸው መረዳት እንችላለን። በሦስት ቁልፍ ነጥቦች እናጠቃልላለን-

1. ***ሥላሴ "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያስረዳናል-*** አንድ ሰው በምድረበዳ በአንድ ቤት ውስጥ ብቻውን ቢኖር እና ከማንም ጋር ባይነጋገር ብላችሁ አስቡ፤ ቀጥላችሁ ከ20 ዓመት በኃላ ይህ ሰው ከቤቱ ወጥቶ "የምወድ ሰው ነኝ" ቢል ታምኑታላችሁ? ላታምኑት ትችላላችሁ! የሚወድድ ሰው ከሌሎች ጋር በግንኙነት የሚኖር ነው። ከሌሎች ራሱን ለይቶ አይኖርም። መጽሐፍ ቅዱስ "...እግዚአብሔር ፍቅር ነው" (1ኛ ዮሐንስ 4፥8) ይላል። እግዚአብሔር አንድ አካል ብቻ ቢሆን አለምን ከመፍጠሩ በፊት ማንን ይወድድ ነበር? እግዚአብሔር ግን ሦስት አካል ስለሆነ እግዚአብሔር ፍቅር ነው ማለት ትርጉም ይሰጣል። እየሱስ ወደ አብ ሲጸልይ እንዲህ አለ "...ዓለም ሳይፈጠር ስለ ወደድኸኝ..." (ዮሐንስ 17፥24)። ከዘፍጥረት 1፥1 በፊት ወደ ነበረው ዘላለም ወደኃላ ከሄድን አንድ ነገር ብቻ ነው የሚቀረው - እግዚአብሔር እየወደደ። አብ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስን ይወድዳል፤ ወልድም አብ እና መንፈስ ቅዱስን

ይወድዳል እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ አብ እና ወልድን ይወዳል። እንዴት የሚያምር ምስል ነው። እግዚአብሔር ማንነት ውስጥ የሚወዋደዱ አካላት ህብረት አለ። እግዚአብሔር ፍቅር ነው።

2. **ሥላሴ እግዚአብሔር አለምን ለምን እንደፈጠረ እና እንደሚያድነው ያስረዳናል-** እግዚአብሔር አለምን የፈጠረው ብቸኝነት ስለተሰማው አይደለም፥ እግዚአብሔር የሚወደውን ሰው መፈለግ አላስፈለገውም። ነገር ግን የእውነተኛ ፍቅር ባህሪ ራሱን ማጋራት እና አዲስ ሕይወትን ማምጣት ነው። እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው ከንጹሕ ፍቅርና በጎነት የተነሳ ነው። ይህንን ፍቅሩን ለማካፈል የሰው ልጆችን ፈጠራቸው። አዳም እና ሔዋን በኤደን ገነት ውስጥ በአመሻሹ ቅዝቃዜ አብረው ከእግዚአብሔር ጋር ይራመዱ ነበር (ዘፍጥረት 3፥8)። የሰው ልጆች እግዚአብሔር አብ፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስን እንዲያውቁ፥ እንዲወዱ እና በእርሱ ደስ እንዲሰኙ ተፈጥረዋል። የተፈጠርነው ለሥላሴ ነው! የሰው ልጆች እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ሲመርጡ በኃጥያት ወደቁ፥ እግዚአብሔር ግን ብቻችንን አልተወንም። አብ ሊያድነን እና ወደ ተፈጠርንበት አላማ ሊመልሰን ስለወደደ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስን ላከ። የድነት አላማ ወደ መጀመርያው ቤታችን ወደ ሥላሴ ሊመልሰን ነው!

3. **ሥላሴ የቤተ-ክርስቲያንን አላማ እና የመጨረሻ እጣ ፈንታ ያስረዳናል-** እግዚአብሔር የሰው ልጅን በመልኩ እና በአምሳሉ ፈጠረው (ዘፍጥረት 1፥26)። ቀጥሎም ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አለመሆኑን ተናገረ (ዘፍጥረት 2፥18)። አንዳችን ከሌላችን ጋር ፍቅር ባለበት ግንኙነት ስንኖር የሥላሴን ፍቅር እናሳያለን። አንዳንዶች ብቻቸውን በመሆናቸው ኩራት ይሰማቸዋል፤ "ማንም አያስፈልገኝም" ይላሉ፥ ይህ ግን የውድቀት አሳዛኝ ውጤት ነው። ምናልባት በሌሎች ተጎድተው ራሳቸውን ለመጠበቅ ስለሚፈልጉ ይሆናሉ። እግዚአብሄር እንዲህ እንድንኖር አልፈለገም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ሥላሴ ስለሆነ ከሌሎች ጋር በህብረት የመኖርን አስቸጋሪ እርምጃ መውሰድ አለብን። በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔርን በኃጥያት የተከፋፈለውን ሰዎችን እያስታረቀ ነው። በዮሐንስ 17፥22 እየሱስ እርሱ እና አብ አንድ እንደሆኑ ቤተ-ክርስቲያን አንድ እንድትሆን ጸለየ። በእርግጥ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሰዎች አንድ የሰው ልጅ አይሆኑም። ነገር ግን በህብረት እና በሰላም ስንኖር በሥላሴ መካከል ያለውን ፍጹም ህብረት ያሳየናል። በመንግስተ ሰማያት ቤተ-ክርስቲያን ከአብ፥ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ጋር በፍጹም ህብረት አብረን እንኖራለን። ይህ እንዴት የሚገርም ቀን ይሆናል።

## ማጠቃለያ

ይህንን ትምህርት በምስጋና እና በአምልኮ አጠቃልሉ። ክርስቲያናዊ አምልኮ ከመጀመርያው እስከ መጨረሻው ሥላሴያዊ ነው፤ ምክንያቱም የምናመልከው ሥላሴን ነው።

► የሚከተለውን የምስጋና ጸሎት አብራችሁ ጸልዩ። ይህ የጥንት ለሥላሴ የሚደረግ የምስጋና ጸሎት ዛሬም በብዙ አማኞች ዕለታዊ ጸሎት እና የቤተ-ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ጥቅም ላይ ይውላል።

> ከመጀመርያ እንደነበረው፥ አሁን እንዳለው እና ሁል ግዜ እንደሚሆነው ክብር ለአብ፥ ለወልድ እና ለመንፈስ ቅዱስ ለዘለዓለም፥ አሜን።

► 2ኛ ቆሮንቶስ 13፥14 አብራችሁ በሉት፥ ይህ ባርኮት በብዙ የክርስቶስ ተከታዮች ዕለታዊ ጸሎት እና የቤተ-ክርስቲኣን ስርዓቶች ላይ ጥቅም ላይ ይውላል።

የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት [ከእኛ] ጋራ ይሁን።

► የእምነት መግለጫውን ቢያንስ ሁለት ግዜ አብራችሁ አንብቡ።

## የእምነት መግለጫ

በአንዱ እውነተኛ እና ኗሪ አምላክ ሦስት መለየት የሚገባን አካላት አሉ፤ አብ፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ። ሁላቸውም ሊከፋፈል የማይችል አንድ ሕልውና፥ ኃይል እና ዘላለማዊ ናቸው። ወልድ ለዘላለም ከአብ የተገኘ ነው፥ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ ከአብ [እና ወልድ] የወጣ ነው።

## የአትናትዮስ የእምነት መግለጫ

*ለክፍሉ መሪ ማስታወሻ- ይህንን በክፍለ ግዜው አብራችሁ ማንበብ አስፈላጊ አይደለም*

*አትናትዮስ የእምነት መግለጫ በአራተኛው ክፍለ ዘመን Arius (አሪዮስ) ከተባለ የስዕተት አስተማሪ የክርስትና እምነትን የተከላከለ የአሌክሳንድሪያውን Athanasius አትናትዮስን ለማክበር በስሙ የተሰየመ ነው። እምነትን 'የማይጠብቁትን' በማስጠንቀቅ የሚጀመር ነው፤ ይህም እውነተኛውን ወንጌል ተቀብለው መካድን ለመረጡት ነው። ብዙ ቤተ-ክርስቲያናት ውስጥ ይህንን የእምነት መግለጫ ከጴንጤቆስጥ እሁድ ቀጥሎ ባለው የሥላሴ እሁድ ላይ በጉባኤ የሚነበብ ነው።*

ለመዳን የሚፈልግ ሁሉ ከሁሉም ነገር አስቀድሞ የሁሉ የሆነች የቤተ ክርስቲያንን ሃይማኖት እውነተኛ አድርጎ ሊቀበል ያስፈልገዋል። ንጹሕና ሙሉ አድርጎ ያልጠበቀው ሁሉ ያለ ጥርጥር የዘላለም ጥፋት ይደርስበታል።

በሦስትነቱ አንድነቱን፥ በአንድነቱም ሦስትነቱን አምነን አንድ አምላክን እናመልካለን። ይህም እውነተኛ የክርስትና ሃይማኖት ነው። ይህንንም የምናደርገው አካላቱን ሳንደባልቅ መለኮታዊ ህልውናውንም ሳንከፍል ነው።

ምክንያቱም የአብ አካል ለብቻው የወልድ ለብቻው፥ የመንፈስ ቅዱስም ለብቻው ስለሆነ ነው።

ሆኖም፥ የአብ፥ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ መለኮት አንድ ነው፥ ክብሩ ሥልጣኑም እኩል ሆኖ ይኖራል።

ወልድ በህልውናው እንደ አብ ነው፥ መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ ነው።

አብ አልተፈጠረም፥ ወልድ አልተፈጠረም፥ መንፈስ ቅዱስም አልተፈጠረም።

አብ ወሰን የለውም፥ ወልድ ወሰን የለውም፥ መንፈስ ቅዱም ወሰን የለውም።

አብ ዘላለማዊ የሚሆን አንድ እንጂ ሦስት አይደሉም።

ቢሆንም ዘላለማዊ የሚሆን አንድ እንጂ ሦስት አየደሉም።

ያልተፈጠና ወሰን የሌለው ሦስት እንዳልሆነ እንደዚሁም ያልተፈጠረና ወሰን የሌለው አንድ ነው።

እንዲሁም አብ ሁሉን የሚችል ነው፥ ወልድ ሁሉን የሚችል ነው፥ መንፈስ ቅዱስም ሁሉን የሚችል ነው።

ቢሆንም፥ ሁሉን የሚችል አንድ አንጂ ሦስት አይደለም።

ስለዚህ አብ አምላክ ነው፥ ወልድ አምላክ ነው፥ መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው።

ሆኖም አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አይደሉም

ስለዚህ አብ ጌታ ነው፥ ወልድ ጌታ ነው፥ መንፈስ ቅዱስም ጌታ ነው።

ሆኖም አንድ ጌታ እንጂ ሦስት ጌቶች አይደሉም።

ምክንያቱም የክርስትና እምነት እውነተኛነት እያንዳንዱ አካል አምላክና ጌታ መሆኑን እንድናምን እንደሚያስገድደን ሁሉ የክርስትና ሃይማኖት ሦስት አማልክት ወይም ሦስት ጌቶች እንዳንል ይከለክለናል።

አብ በማንም አልተሠራም፥ አልተፈጠረም፥ አልተወለደምም።

ወልድ ከአብ ተወለደ እንጂ አልተሠራም አልተፈጠረምም።

መንፈስ ቅዱ አልተሠራም፥ አልተፈጠረም፥ አልተወለደምም፥ ነገር ግን ከአብና ከወልድ የሚሠርጽ ነው።

ስለዚህ አብ አንድ ስለሆነ ሦስት አብ አይደለም፥ ወልድም አንድ አንጂ ሦስት ወልድ አይደለም፥ መንፈስ ቅዱስም አንድ እንጂ ሦስት አይደለም።

ከሦስቱ አካላት አንዱ ከሌለው ቀዳሚነት ወይም ደኃሪነት የለውም፥ አንዱም ከሌላው የሚበልጥ ወይም የሚያንስ አይደለም።

ስለሆነም፥ ሦስቱ አካላት በእኩልነትና በዘላለማዊነት አንድ ናቸው። ከዚህ የተነሣም ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ሦስቱ አካላት በአንድ መለኮት አንድ አምላክም በሦስት አካላት ይመለካል።

ለመዳን የሚፈልግ ሁሉ ስለ ሥላሴ እንደዚህ ማሰብ ይገባዋል።

ስለዚህ ሌላ የዘላለምን ደኅንነት ለማግኘት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋ መገለጽ በእውነት ማመን አስፈላጊ ነው።

ምክንያቱም ትክክለኛው እምነት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ አምላክም ሰውም መሆኑን ማመን አስፈላጊ ነው።

እርሱም ከዘመናት አስቀድሞ ከአብ የተወለደ አምላክ ከእናቱም በሥጋ በዓለም የተወለደ ሰው ነው።

የሚያስብ ነፍስ ያለችውና የሰውን ሥጋ የለበሰ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው።

በአምላክነቱ ከአብ ጋር የተካከለ፥ በሰውነቱም ከአብ ያነሰ ነው፥

አምላክም ሰውም ቢሆንም አንድ ክርስቶስ እንጂ ሁለት ክርስቶስ አይደለም።

አንድ ነው ስንል ግን የሰውን ሥጋ ለበሰ እንጂ መለኮት ወደ ሥጋ አልለወጠም።

በእርግጥ አንድ የሆነውም በባሕርያት መደባለቅ ሳይሆን በአካል አንድ በመሆኑ ነው።

ምክንያቱም የሚያስብ ነፍስና ሥጋ አንድ ሰው እንደሆኑ ሁሉ አምላክና ሰው በክርስቶስ አንድ ናቸው።

እርሱም ለደህንነታችን ሲል መከራ ተቀበለ፥ ወደ ሲኦል ወረደ፥ ከሙታን ተነሣ።

ወደ ሰማይ የወጣ፥ በአብ ቀኝ የተቀመጠ፥ በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ከዚያ የሚመለስ፥

በመምጣቱ ጊዜም ሰዎች ሁሉ በሥጋ ተነስተው ስለ ሥራቸው መልስ ይሰጣሉ።

መልካም የሠሩ ወደ ዘላለም ሕይወት ክፉ የሠሩም ወደ ዘላለም እሳት ይገባሉ።

ይህ እውነተኛው የክርስትና እምነት ነው። ይህን የሚያምንና አጥብቆ የማይዝ ሊድን አይችልም።

## ትምህርት 3 የቤት ስራዎች

(1) የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የቤት ስራ፡- ከታች ከተዘረዘሩት ዘርፎች መካከል እያንዳንዱን ተማሪ አንድ ይመደብ። ከሚቀጥለው ክፍለ ግዜ በፊት ክፍሉን አንብባችሁ በትምህርቱ ውስጥ ካለው ሃሳብ ላይ ምን እንደሚናገር በአንድ አንቀፅ ፃፉ።

- ዮሐንስ 17፥1-5
- ኤፌሶን 1፥3-14
- ኤፌሶን 1፥15-23
- ቈላስይስ 1፥9–19
- ዕብራውያን 1

(2) ፈተና፡- የሚቀጥለው ክፍለ ግዜ የምትጀምሩት በትምህርት 3 ፈተና ነው። ለፈተና ዝግጅት እንዲሆን የፈተና ጥያቄዎችን አጥኑ።

(3) የማስተማር የቤት ስራ፡- ከክፍል ውጪ የማስተማርያ ግዜን ቀጠሮ መያዝ እና ማስተማራችሁን ሪፖርት ማድረግ አስታውሱ።

(4) የአትናትዮስን እምነት መግለጫ በጥንቃቄ አንብቡ።

## ትምህርት 3 ፈተና

(1) “እግዚአብሔር ማን ነው?” ለሚለው ጥያቄ ምርጡ መልስ ምንድን ነው?

(2) የሥላሴ አስተምሮ የጸሎት ሕይወታችንን የሚያጠናክርልን እንዴት ነው?

(3) በየትኞቹ ሑለት ዋና የሐዋ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ውስጥ ነው እግዚአብሔር ሥላሴ ራሱን የገለጠው? በእያንዳንዱ ክስተት የትኛው የሥላሴ አካል ነው የተገለጠው?

(4) እግዚአብሔር እንደ እንቁላል ነው? ለምን ነው ወይም አይደለም?

(5) እግዚአብሔር እንደ ሦስት የፊት ጭብሎችን እንዳደረገ ሰው ነው? ለምን ነው ወይም አይደለም?

(6) የሥላሴ የመጀመርያ እና ሑለተኛ አካላት ለምንድን ነው “አብ/አባት” እና “ወልድ/ልጅ” በመባል የሚታወቁት?

(7) የሰው ልጅ ለምን አላማ ነው የተፈጠረው?

# ትምህርት 4

## ሰው

**የትምህርቱ አላማ**

(1) ተማሪው የሚከተሉትን ማስረዳት ይችላል

- በሰዎች ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር መልክ አካላዊ መመሰል እንዳልሆነ እንዴት እንደሚያውቁ
- በሰዎች ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር መልክነት ስምንት ባህሪያት
- ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት እንዲኖራቸው በልዩነት መሰራታቸው
- ሰዎች ነፃ ፈቃድ በምን መንገድ እንደሆነ
- ሰዎች ከምድራዊ ህይወታቸው ውስጥ ያለ ተግባራዊ ዋጋ በላይ ጥልቅ ዋጋ እንዳላቸው

ስለ ሰው ልጅ ክርስቲያናዊ የእምነት መግለጫ

(2) ተማሪዎች ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ከሌለቸው እንደ ሰው በምንም መርካት እንደማይችሉ ይረዳሉ።

**የሰው ልጅ - በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሯል**

► መዝሙር 8 አብራችሁ አንብቡ። ይህ ክፍል ስለ ሰው ልጅ ምን ይነግረናል?

► በምድር ላይ ያለ ሰው በሙሉ የሚመሳሰልባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

ማንነትን ስለሚሰጡን ነገሮች አስቡ፤ ሰው መሆን ማለት በእውነት ምን ማለት ነው?

► ዘፍጥረት 1፥26-27 አብራችሁ አንብቡ።

በማንነታችን እግዚአብሔርን የሚመስል ነገር አለን፥ እግዚአብሔርን አይደለንም ነገር ግን ከእንስሳት የሚለየን እና ልዩ የሚያደርገን ነገር አለ። በመዝሙር 8፥5 ላይ ፀሐፊው ከመላዕክት በትንሹ አንሰን እና የክብር እና የምስጋና ዘውድን ተሸልመን ስለተፈጠርን ይደሰታል።

እግዚአብሔር ሰዎች አለምን እና በውስጧየሚኖሩ ፍጥረትን የሚያስተዳድሩበትን ልዩ ኃላፊነት ሰጥቷቸዋል (መዝሙር 8፥6)። ሰዎች ምድርን በጥንቃቄ ማስተዳደር አለባቸው፥ ህያው የሆኑ ፍጥረታት እንዳይጠፉ መከላከል፥ ሃብትን በጥበብ መጠቀም እና ለሚቀጠለው ትውልድ ምድሪቱን በጥሩ ሁኔታ ትተው ማለፍ አለባቸው።

ይህ ለሰው ልጅ ያለው ትልቅ እሳቤ ለራስ ላለን አክብሮት ከዝግመተ ለውጥ በእርግጥ የተሻለ ነው። በዝግመተ ለውጥ ውስጥ የሰው ህይወት ከሌላው የተለየ ምንም አስፈላጊነት፥ አላማ፥ ትርጉም ሆነ ምንም ሰው በመሆኑ ልዩ የሆነ ነገር የለውም።

አንዳንድ የጥንት አፈ ታሪኮች ሰዎች በድንገት ያለ ምንም አላማ ሆነ በፈጠራቸው የሚወደዱ ሳይሆኑ ተፈጥረዋል ይላሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚዓብሔር አምሳል የተፈጠርን ልዩ ፍጥረት መሆናችን ይነግረናል። ይህ ምን ምን ማለት ነው?

ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል ተፈትረዋል ማለት ግን ከእርሱ ጋር አካላዊ መመሳሰል አለን ማለት አይደለም

► ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረዋል ስልን አካላዊ መመሳሰልን አለመሆኑ በምን ይታወቃል?

(1) **እግዚአብሔር መንፈስ ነው** (ዩሐንስ 4፥24)-ሰለሞን እግዚአብሔርን ሰማይ እና ምድር ሊይዙት እንደማይችሉ ተገንዝቧል (1 ነገስት 8፥27)። እግዚአብሔር ራሱን በወደደው መልክ ሊገልፅ ይችላል፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር መልክ ሆኖ እርሱን የሚመስል ማንም የለም። ይህን በእርሱ አምሳል ለማምለክ ምንም ምስል ማስቀመጥ ሆነ መቅረፅ የሌለብን ለዚህ ነው።

(2) **በሰው አምሳል የሆነ የትኛውንም ምስል/ ቅርፅ በእግዚአብሔር መልክ መስራት ጣኦት አምልኮ ነው** (ሮሜ 1፥23 ይነበብ)።

(3) ለመራመድ እግሮች፥ ነገሮችን ለማንቀሳቀስ እጆች፥ ለመገንዘብ ማየት እና መስማት ኖሮት **ሰው የተሰራው በምድር ላይ ላለ ህይወት ነው**። እግዚአብሔር በምድር ላይ ላለ ህይወት ነው የሰራን፥ ነገር ግን አግዚአብሔር በህዋ ውስጥ ሁሉ አለ። ነገሮች የፈጠረው እና የሚያንቀሳቅሰው በቃሉ ነው። ምንም የሚገድበው ነገር የለውም። በሰው አይነት አካላዊ በሆነ ቅርፅ እንደሚኖር የሚነግረን ምንም ምክንያት የለም።

## የሰው ልጅ በእግዚአብሔር መልክ ሲፈጠር ያለው ዘርፎች

► የእግዚአብሔርን መልክ የሚያመላክቱ የሰው ልክ ባህሪያት ምንድን ናቸው?

የስነመለኮት ምሁራን ከብዙ ጥናት በኃላ ሰዎች እግዚአብሔርን መልክ ነው የሚለው ሃሳብ ላይ የተመስማሙባቸው የሚከተሉት ማንነቶች ላይ ነው

### የፈጠራ ልብ

በእኛ ውስጥ ካለው የእግዚአብሔር መልክ የተነሳ ሰዎች የፈጠራ ልብ ያለን ነን። ፈጣሪያችን የፈጠራ ችሎታ ያላቸው አድርጎ ሰርቶናል። አንዳንድ ግዜ እንስሳት ሰዎች የጥበብ ስራ ብለው የሚያምኑትን ምልክቶችን አስቀምጠዋል፤ ነገር ግን ይህ ሰዎች ሃሳባቸውን ለመግለጥ ከሰሩት የጥበብ ስራ የተለየ ነው። ጥንታዊ የሆኑ ስዕሎች በዋሻዎች ውስጥ ይገኛሉ፥ ስለሳሉት ሰዎች ብዙ እውቀት የለምን ነገር ግን የስዕል ስራዎች በሰዎች እንጂ በእንስሳት እንዳልተሰሩ ምንም ጥርጥር የለም።

የፈጠራ ስራ ሙዚቃን ጭምር ይገልጣል። ሙዚቃ ስሜታችንን እና ሃሳብችን በሚያስገርም መንገድ የመግለጥ አቅም አለው። ሃሳባችን በሙዚቃ መግለጥ የእግዚአብሔር መልክ በእኛ ውስጥ ስላለ ያለን አቅም ነው።

### የማሰብ ችሎታ

የማሰብ ችሎታችን ሌላ እንደ እግዚአብሔር አይነት የሆነ ችሎታ ነው። እንስሳት እውቀት አላቸው፥ ነገር ግን የእንስሳት የእውቀት ስራ ከደመነፍስ እና በስሜት መነዳት ያለፈ አይደለም። ሰዎች ብቻ ናቸው የማስተዋል፥ የመመዘን፥ እና የምልከታ እንዲሁም ይህንን ከሌሎች ጋር የመግባባት ችሎታ ያላቸው።

ማሰብ ብቻ ሳይሆን የምንችለው፤ ስለማሰባችን እንኳን ማሰብ የምንችል ነን። የምናሰባቸውን ሃሳብ መንገዶች ማሰላሰል የምንችል እና ምክንያታዊ በመሆን ስለምክናታዊነት ማሰብ እንችላለን።

### የተግባቦት ችሎታ

ሰዎች የተግባቦት ችሎታ አላቸው። ቋንቋን የመጠቀም ችሎታን ያመላክታል፥ ይህም ሃሳባችንን በምልክቶችን እና በድምፅ በመጠቀም ሃሳባችንን ለሌሎች ሰዎች የምናስረዳበት መንገድ ነው። እንደ ውሻ እና አዕዋፋት ያሉ እንስሳት ድምፅን በመጠቀም ይግባባሉ ነገር ግን በምንም መንገድ የሰዎች ንግግር ያዕል ውስብስብ የሆነ የእንስሳት መግባቢያ የለም። እንስሳት ሌሎችን የሚያስፈራሩበት መንገድ አለ፥ የራሳችን ወሰን የሚወስኑበት፥ ምግብ የሚጋሩበት ነገር ግን ስለ ህይወት ትርጉም እርስ በእርሳቸው አይነጋገሩም።

የተግባቦት ችሎታ በማሰብ እና በማስተዋል ክህሎት ላይ የተመሰረተ ነው። እንስሳት ቃላትን መናገር አይችሉን፤ ቢችሉ ኖሮ እንኳን ብዙ የሚናገሩት አይኖርም።

### የማህበራዊ የሆነ ፍጥረት

ሰዎች ማዕበራዊ የሆነ ተፈጥሮ አለው። እኛ ከሌሎች ሰዎች ጋር መስተጋብር እንዲኖረነው ተደርገን ተሰርተናል፤ ይህም ሌሎች ሰዎች መሰጠት እንዲኖረን እና እኛም ሌሎች ላይ በመደገፍ የምንኖር ነን። ህይወትን የምንጀምረውን ሙሉ በሙሉ ሌሎች ላይ ተደግፈን ነው፥ ከዚያም በኃላ ከልጅነት ወደ አዋቂነት ለመድረግ ብዙ ዘመን ይፈጅብናል። ይህ የሆነው ግንኙነት ለእግዚአብሔር አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

እግዚአብሔር የሰዎችን ህይወት የነደፈው አብረው የሚሰሩ እና ለዕለታዊ የሆነ ፍላጎቶቻቸው መሳካት የእርስ በእርስ ግንኙነታቸው ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ሆኖ ነው። አንድ ሰው ምግብ እና መኖርያን ያለ ሌላ ሰው እርዳታ ማግኘት ቢችል እንኳን ከሌሎች ጋር ግንኙነት በማድረግ ብቻ የሚሟሉ አስፈላጊ ፍላጎቶች አሉት። የሰው ማዕበራዊ የሆነ ማንነት የእግዚአብሔር ማንነት ያሳየናል፤ እግዚአብሔር ሥላሴ በመሆን ለዘላለም በግንኙነት ውስጥ ይኖራል።

በሰዎች መካከል ያለው ግንኙነት ብዙ ችግሮች አሉበት፤ በእነዚህ ችግሮች ምክንያት አንዳንድ ሰዎች ግለኛ እና ብቻቸው ሆነው መኖር እንደሚችሉ ይመስላቸዋል። ሌሎች ላይ መደገፍ የማያስፈልጋቸው ይመስላቸዋል። ብቻችን መኖር መፍትሔም ሆነ እግዚአብሔር ህይወትን የቀየሰልን መንገድ አይደለም። ነገር ግን በግንኙነት ውስጥ የምንኖርበትን መርህ ሰጥቶታል፤ ችግሩ የእግዚአብሔር ሃሳብ መከተል ሲያቅተን ነው።

### ስነ ምግባራዊ እይታ

በተፈጠሯችን ስነ ምግባራዊ እይታ ያካተተ ነው። ነገሮች ትክክል ወይም ስዕተት እንደሆኑ የሚነግረን በእኛ ውስጥ ያለ አንድ ነገር አለ። (ሮሜ 1፥20፣ ሮሜ 2፥15 ይነበብ)። ይህን ስሜታችን መከተል መች ትክክል እንደሆን እና

*መች መከተል እንደሌለብን ይነግረናል። አዳም እና ሔዋን ቅዱስ እና ፍፁም በሆነ መንገድ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈፅሙ ተደርገው ተፈጥረዋል።*

> *"በዘመናችን ያሉ ሰዎች አሁንም የሰውን ክብርን ለመያዝ ይሞክራሉ፥ ነገር ግን እንዴት እንደሚይዙት አያውቁም ምክንያቱን የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩን ረስተዋል .... ያለንበት ባህል ሰዎችን ለረጅም ግዜ መሳርያዎችን መሆናቸውን እያወራላቸው በመቆየቱ ይህም በተግባራቸው መታየት መጀመሩን የምናስተውልትን ሑነት እውን እየሆነ ነው።"*
>
> *— -ፍራንሲስ ኤ ሻፍነር*

*ሰው በኃጥያት ስለወደቀ እና መሰረታዊ የሆነ የስነምግባር እሳቤውን ስለተበላሸበት፤ ይህ የስነምግባር እይታ አሁን ሙሉ በሙሉ ትክክል አይደለም ነገር ግን በእያንዳንዳችን ውስጥ ትክክል እና ስዕተትን በሚገባ የሚረዳ ችሎታ አለ።*

*ይህ የስነ ምግባር እይታ ስላለን ትክክል የሆነው የማድረግ ግዴታ እንዳለንብ ይሰማናል እንዲሁም ለምንሰራው ኃጥያት ጥፋተኛ እንሆናለን። በደመ ነፍስ ተመርተው ያለ ጥፋተኝነት ስሜት እንደሚኖሩ እንስሳት አይደለንም።*

### *የመምረጥ ችሎታ*

*ሰው የመሆን ባህሪ ነፃ ፈቃድ ወይም የመምረጥ ችሎታ ያካትታል። በተቃራኒው የእንስሳት ምርጫ በግዜያዊ ስሜታዊነት እና ደመ ነፍስ ላይ የተመሰረተ ነው። እንስሳት ተግባሮቻቸው ጥንቃቄ የተሞላ፥ ግዜ በመውሰድ የታሰበበት ሆነ ስነ ምግባራዊ ሆነ ተግባራዊ የሆነ ውጤቱን በማስተዋል የተመራ ውሳኔ ላይ አይመሰረተም። ሰዎች ግን ትርጉም ያለው እና ህይወት ቀያሪ የሆነ ምርጫዎችን የማድረግ ችሎታ አላቸው* (*ኢያሱ* 24፥15 *ይነበብ*)።

► *ነፃ ፈቃድ በሰውነት ውስጥ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?*

*ምክንያቱም እውን የሆኑ ምርጫዎችን ስለምንመርጥ ነው፥ ለእግዚአብሔርም ተጠያቂነት አለብን። እርሱን ኃጥያትን ይቀጣል እንዲሁም ጽድቅን ይሸልማል* (*ራእይ* 20፥12-13)።

*ስንወለድ ጀምሮ ኃጥያተኛ የሆነ ማንነት ስላለን፤ እግዚአብሔርን በሚያከብር መንገድ አሁን እንዲሁ ማድረግ አንችልም፤ የሰው ፍጥረት አሁን ለኃጥዓት ባርያ ነው* (*ሮሜ* 6፥16-17፣ *ኤፌሶን* 2፥1-3 *ይነበብ*)፥ *ትክክል የሆነውን ማድረግ ለማይችል ሰው እግዚአብሔር በፀጋው ወደእያንዳንዱ ሰው ይደርሳል፤ ይህን ለወንጌል ምላሽ የሚሰጥን ፍላጎት እና ችሎታን ይሰጠናል። ለዚህም ነው ሰዎች ንሰሃን የመግባት እና ወንጌልን ማመን የሚችሉት* (*ማርቆስ* 1፥15 *ይነበብ*)።

### *ህያውነት - የማይሞት ማንነት/ ተፈጥሮ*

*ህያውነት የእግዚአብሔር መልክ የመሆን አስፈላጊ ክፍል ነው። በህይወት ያልኖርበትን ዘመን ነበር፥ ነገር ግን ከተፀነሰበት ግዜ ጀምሮ ግን ሰው ለዘላለም እንኖራለን። ቁሳዊ የሆነው አካል ብቻ ሳንሆን ነገር ግን ለዘላለም የምንኖር መንፈሶች እንዲሁም በአዲስ አካላት በትንሳኤ ለዘላለም የምንኖር ነን* (1 *ቆሮንቶስ* 15፥16-22፣ 52-54 *ይነበብ*)። *እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን በዘላለማዊ የሆነ አላማ ፈጥሮናል። ህያውነት እያንዳንዱን ውሳኔዎቻችንን ዘላለማዊ የሆነ ተፅዕኖ እንዲኖራቸው ያደርጋል ምክንያቱን ዘላለምን ወይ በገነት አለበለዚያ በሲኦል እናሳልፋለን።*

**የመውደድ ችሎታ**

የሰዎች የመውደድ ችሎታ የእግዚአብሔር መልክ መሆን አካል ነው። በእንስሳት መካከል ግንኙነቶች በደመነፍስ የተገደቡ እና ደመነፍስ የሚቆጣጠራቸው ናቸው።

ሌሎቹ የሰው ባህሪያት ለዚህ አስፈላጊ ናቸው። የተግባቦት፥ የመምረጥ እና ለምንወዳቸው የመስጠት እና ከሌሎች ፍቅርን ስንቀበል በሚገባ በመረዳት የምንመልስበት ችሎታ ከሌለን እንወዳቸዋለን ለምንላቸው መውደድ የምንለው ምንድ ትርጉም አይኖረውም።

የሰዎች ፍቅር በግንኙነት ውስጥ ባለ ደስታ፥ ቃልን የመስጠት እና በመጠበቅ፥ መስዋትነት ያለበት መስጠት እና ሌሎችን ማገልገል እና በይቅርታ ይገለጣል። ይህም የእግዚአብሔር ፍቅር መገለጫም ናቸው።

**የማምለክ አቅም**

በጣም አስፈላጊ የሆነው ባህሪያችን የማምለክ አቅማችን ነው። በጣም የምትወዱትን የአምልኮ መዝሙር አስቡ፤ 'አምላካችን ድንቅ አምላክ ነው' ' እንዴት ድንቅ አምላክ ነው' የሚሉ ግዜ የማይሽራቸው ጥልቅ አምልኮ ያላቸው ዝማሬዎችን እንዘምራለን። የመጽሐፍ ቅዱስ ዘማሪው "ነፍሴ ሆይ፤ እግዚአብሔርን ባርኪ፤ የውስጥ ሰውነቴም ሁሉ ቅዱስ ስሙን ባርኪ" (መዝሙር 103፥1) በማለት ይዘምራል። ይህም እውን የሆነው በእኛ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር መልክ በእርሱ መልክ የተሰራነውን እግዚአብሔርን ስለሚያውቅ እና ምላሽ መስጠት ስለሚችል ነው።

## በሰው ልጆች መካከል የእግዚአብሔር መልክነት አላማ

እግዚአብሔር በራሱ መልክ ለምን እንደፈጠረን ቆም ብሎ ማሰብ አስፈላጊ ነው። ከሌለው ፍጥረት በጣም የምንለየው ለምንድን ነው? መልሱም ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት እንዲኖረን እና እንድናመልከው ስለተሰራን ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ፍጥረት በሙሉ ለእግዚአብሔር እንደሚያከብር ይናገራል። የእግዚአብሔርን ትልቅነት በፈጠረው አለም ውስጥ መመልከት እንችላለን። ሌሎች ፍጥረታት ግን እግዚያብሔርን ያለማስተዋል ያከብሩታል፤ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ለማወቅ የሚረዳቸው ማንነት/ ፍጥረት ስለሌላቸው እግዚአብሔር መረዳት አይችሉም።

በእኛ ውስጥ የፈጠራ ችሎታ ስላለን የእግዚአብሔርን ወደር የሌለውን ፈጣሪነት ማድነቅ እንችላለን። ትክክሉን ከስዕተት መለየት ስለምንችል ቅዱስነቱን እና ፅድቁን እናመልካለን። የመውደድ አቅም ስላለን ወደር በሌለው ፍቅሩ እንደነቃለን።

በእውቀት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን እርሱን በግንኙነት ውስጥ እግዚአብሔእን በተሻለ ባወቅነው መጠን፥ በበለጠ እንወደዋለን እና እናመልከዋለን። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ለሆነ ግንኙነት ስለሰራን፤ ከእርሱ ጋር በሆነ ግንኙነት ውስጥ ደስታን እና እርካታን እናገኛለን።

**ሌሎች አስፈላጊ ሃሳቦች**

**(1) *ሁሉም ሰዎች በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠሩ ናቸው*** (ዘፍጥረት 1፥27) - አንዳንድ ሰዎች በእውቀት ውስንነት ምክንያት ራሳቸውን በፈጠራ መግለጥ ሆነ ነፃ ፈቃዳቸውን ከመጠቀም የተወሰኑ ይሆናሉ። የእግዚአብሔር መልክ በውስጣቸው ቢኖርም ግን በዚህ ምድራዊ ህይወታቸው ውስጥ ግን በሙላት መኖር አይችሉም።

**(2) *የሑሉም ሰው ህይወት ዘላለማዊ እና ትልቅ ዋጋ አለው*** - አንዳንድ ግዜ የሰዎችን ተግባራዊ ዋጋ እንመለከታለን- ከእውቀታቸውን፥ ከትምህርታቸውን፥ ከችሎታቸውን እና ከጥንካሬያቸውን ጋር የተገናኘ ዋጋቸውን እንመለከታለን። ነገር ግን ሁሉም ሰው ከተግባራዊው ዋጋ ያለፈ አስፈላጊ ዋጋ አለው ምክንያቱም በእግዚአብሔር አምሳል ስለተፈጠሩ። ለዚህም ነው ሁሉም ሰው፤ ምናልባትም ተግባረዊ የሆነ ዋጋ የሚያሰጠው ምክንያት ባይኖረውም ሆነ ክፉ ሰው ቢሆንም ግን ሰው በመሆኑ አክብሮት የሚገባው። የእግዚአብሔር መለክ መሆን ሁሉም ልጅ በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ የሚያሰጣቸው ሲሆን፤ ለዚህም ነው ውርጃ ክፉ ሃጥያት የሆነው (ዘፍጥረት 9፥6፣ መዝሙር 139፥13-14፣ ኢሳይያስ 44፥24)።

**(3) *መላዕክት በፍጥረታቸው ልዩ ናቸው*** - ጥለቅ የሆነ እውቀት ያላቸው፥ የአመክኖ ችሎታ፥ የተግባቦት ክህሎት፥ እና የማምለክ አቅም አላቸው። በመሆኑም እነሱም በሆነ በኩል የእግዚአብሔር መልክ በእነሱ ውስጥ አለ። አሁን መላዕክት በኃይል ከእኛ ይበልጣሉ (መዝሙር 8፥5) ነገር ግን እኛን ያገለግሉናል (ዕብራውያን 1፥14)። በዘላለም ውስጥ ግን እኛ ከመላዕክት በስልጣን በልጠን ከክርስቶስ ጋር እንመራለን (1 ቆሮንቶስ 6፥3 ይነበብ)። ይህም ሰዎች ከመላዕክት በላይ በእግዚአብሔር መልክ መፈጠራቸውን አመላካች ነው።

**(4) *አለም በተፈጠረበት ቅርፅ/ሁኔታ ውስጥ አይደለም***- በጎበዝ ሰዓሊ የተሳለ ውብ የሆነ ስዕል አስቡ፥ ይህ ስዕል ግን በመሬት ላይ ተጥሎ ሰዎች በጨቀየ ጫማቸው የተረማመዱበት ቢሆን ብላችሁ አስቡ። አሁን ስዕሉን ስትመለከቱት የሰዓሊውን ትልቅ ችሎታ መታየት ቢችልም ስዕሉ ግን በመጀመርያ ሰዓሊው እንደሳለው አይደለም። ፍጥረት እንደዚህ ነው - እግዚአብሔር መጀመርያ እንደፈለገው ሆነ አንደፈጠረው አይደለም ነገር ግን የእርሱ ክብር ግን አሁምን ይታያል።

**(5) *ኃጥያት 'የእግዚአብሔር አይነት' የሆነ በሰዎች ውስጥ ያለውን አቅም አበላሽቷል*** - ለምሳሌ ስነ-ፈጠራዊ የሆኑ ስራዎች ከእግዚአብሔር ስጦታ ከክፉ ልብን የሚገልጡ እና ለሰይጣን መሳርያ መሆን ይችላል። ነገር ግን በፀጋ ጣልቃ በመግባቱ ኃጥያት ከእኛ ውስጥ የእግዚአብሔር መልክ ከእኛ ውስጥ ሙሉ በሙሉ አላጠፋውም። በፀጋ የእግዚአብሔር መልክ በእኛ ውስጥ ይታደሳል፥ ይጎለብታል፥ እንዲሁም ለፈጣሪያችን ክብር መገለጥ ይሆናል (ቈላስይስ 3፥10፤ ኤፌሶን 4፥22-24፤ 2 ቆሮንቶስ 3፥18ን አንብብ)።

**(6) *እኛ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር መልክ በእኛ ውስጥ ያለው እጅግ አስፈላጊው ነገር ነው***- በእኛ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር መልክ ለወንጌል ምላሽ እንድንሰጥ ያደርገናል። በውስጣችን ያለውን ሞራላዊ አስተሳሰብ በፀጋ በኩል ህሊናችንን እንዲነቃ እና ለኃጥያት ጥፋተኝነት እንዲሰማን ያደርገናል። በፀጋ ምክንያት በነፃ የመምረት አቅማችንን በማደስ የምናገለግለውን የመምረጥ ችሎታችንን መልሶልናል፤ በፈጠራ ክህሎታችምን ለእግዚአብሔር ክብር እና አምልኮ እናቀርብበታለን። አመክንዮን በመጠቀም የተደበቀውን እውነት መፈለግ እንችላለን፥ እንዲሁም ስለ

እግዚአብሔር እና መንገዱ በሚገባ እንረዳለን። እግዚአብሔርን ለመረዳት የምናደርገው ፍለጋ በክብር የሸለመንን የፈጠሪያችንን አስደናቂነት ስናውቅ ወደ አምልኮ ይመራናል።

## ማስወገድ ያለብን ስህተት

አንዳንድ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት የሚያስፈልገው ከሞት በኃላ ላለው ህይወት ብቻ ነው ብለው ያስባሉ፥ አንድ ሰው በምድር ላይ መልካምን ህይወት ከኖረ ክርስቲያን መሆን ሆነ አለመሆኑ ምንም ልዩነት የለውም። ነገር ግን የሰውን በተፈጥሮ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት እንዲኖረው ሆኖ እንደተሰራን ስናስብ ህይወታችን እግዚአብሔርን ካላወቅን ብኩን ነው። እንዲመራን፥ ያልንን አቅምን ሙሉ በሙሉ እንድንጠቀም እና ዘላለማዊ የሆነ ህይታን እንዲሰጠን የእግዚአብሔር መንፈስ ያስፈልገናል።

► የእምነት መግለጫውን ቢያንስ ሁለት ግዜ አብራችሁ አንብቡ።

## የእምነት መግለጫ

ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል እግዚአብሔር ለመውደድ እና ለማምለክ ተፈጥረዋል፥ እግዚአብሔርም ሰዎችን የማሰብ፥ የተግባቦት እና የማፍቀር ችሎታን በመስጠት ፈጥሯቸዋል። ሰው ሞራላዊ እሳቤ፥ የግል ነፃ ፈቃድ እና ዘላለማዊ መንፈስ ተሰጥቶታል። የእግዚአብሔር ፀጋ ለሰዎች በፈቃዳቸው ውሳኔ የማድረግን ኃይል ይሰጣል። እያንዳንዱ የሰው ህይወት ዘላላማዊ እና ታላቅ የሆነ ዋጋ አለው።

## ትምህርት 4 የቤት ስራዎች

(1) የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የቤት ስራ፡- ከታች ከተዘረዘሩት ዘርፎች መካከል እያንዳንዱን ተማሪ አንድ ይመደብ። ከሚቀጥለው ክፍለ ግዜ በፊት ክፍሉን አንብባችሁ በትምህርቱ ውስጥ ካለው ሃሳብ ላይ ምን እንደሚናገር በአንድ አንቀፅ ፃፉ።

- ዘፍጥረት 3፥1-6
- ኢያሱ 24፥14-18
- ሮሜ 6፥12-23
- ሮሜ 8፥22-26
- ኤፌሶን 2፥1-9
- 1 ተሰሎንቄ 5፥23
- ያዕቆብ 1፥12-15

(2) ፈተና፡- የሚቀጥለው ክፍለ ግዜ የምትጀምሩት በትምህርት 4 ፈተና ነው። ለፈተና ዝግጅት እንዲሆን የፈተና ጥያቄዎችን አጥኑ።

(3) የማስተማር የቤት ስራ፡- ከክፍል ውጪ የማስተማርያ ግዜን ቀጠሮ መያዝ እና ማስተማራችሁን ሪፖርት ማድረግ አስታውሱ።

## የትምህርት 4 ፈተና

(1) በዘፍጥረት 1፥26-27 መሰረት የሰው ልጅ ከተቀረው ፍጥረት ሑሉ ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው?

(2) ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠራቸው ቁሳዊ/ አካላዊ መመሳሰል ስለአለመሆኑ ሦስት ምክንያቶችን ዘርዝሩ።

(3) የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አምሳል በመፈጠሩ ያሉትን ሰባት ክፍሎችን ዘርዝሩ።

(4) በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርንበት ሑለት ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

(5) ከስነ ምግባራዊ እይታ ውስጥ የሚገኝ ችሎታ ምንድን ነው?

(6) ሰዎች ትክክለኛ/እውነተኛ ምርጫን የማድረግ ችሎታ መኖሩ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ያለው አስፈላጊነት ምንድን ነው?

# ትምህርት 5

# ኃጥያት

**የትምህርቱ አላማ**

(1) ተማሪው የሚከተሉትን ማስረዳት ይችላል

- የኃጥያት መነሻ / ምንጭ
- ስለኃጥያት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ቃላትን
- የተወረሰ ውድቀት ትርጉም እና መግለጫ
- በፈቃድ የሚሰራ ኀጥያት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሃሳብ
- ስለ ኃጥያት ክርስቲያናዊ የእምነት መግለጫ

(2) ተማሪዎች በፈቃድ ስለሚሰራ ኀጥያት ጥርት ያለ ትርጉም በመያዝ መለወጥን በሚገባ መረዳት ይችላሉ።

**መግቢያ**

► ዘፍጥረት 3 አብራችሁ አንብቡ። ይህ ክፍል ኃጢአት ምን ይነግረናል?

► ለምንድን ነው ስለ ኃጥያት መረዳት የሚያስፈልገን?

*ኃጥያትን መረዳት ያለብን -*

1. **የአለምን ሁኔታ ለመረዳት-** መጽሐፍ ቅዱስ ኃጥያት የሰው ልጅ መከራ ምንጭ እንደሆነ ይነግረናል። በኃጥያት ምክንያት ሞት ወደ አለም ገባ (ሮሜ 5፥12 ይነበብ)። በኃጥያት እርግማን ውስጥ በሽታ፥ ማርጀት፥ እና ህመም አለ። መዋሸት፥ መስረቅ፥ መግደል፥ ዝሙት፥ ስካር ፥ እና ግፍ የመሳሰሉ ኃጥያት ያለባቸውም ተግባራት ምድር በመከራ ሞሏት። ጥላቻ፥ የአይን አምሮት፥ ቅናት፥ ኩራት እና ራስወዳድነት ከሚመሳሰሉ በልብ ውስጥ ካለ ኃጥያት ነው ተግባራቱ የሚመነጩት።

2. **ፀጋን እና ድነትን ለመረዳት-** እግዚአብሔር ከኃጥያት የሚያድነን ፀጋን ሰጥቶናል (ማቴዎስ 1፥21፤ ሮሜ 5፥20-21)

3. **ቅድስናን ለመረዳት-** ኃጥያተኝነት የቅድስና ተቃራኒ ነው - ለእግዚአብሔር ያለ መሰጠትም ይቃረናል። እግዚአብሔር በሚጠብቅበት መንገድ ለመቀደስ ሰው ከኃጥያት መራቅ ያስፈልገዋል (1 ጴጥሮስ 1፥15-16)።

## የኃጥያት መነሻ

እግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ ፍፁም ነበር ፤ እርሱ የፈጠረው ሁሉ ያለ ግድፈት ነበር። እግዚአብሔር ፈጥሮ ሲጨርስ፤ ሁሉም መልካም እንደሆነ አየ (ዘፍጥረት 1፥31)፤ በመሆኑም ኃጥያት በእግዚአብሔር ምክንያት የመጣ አይደለም።

አዳም እና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ነበራቸው፥ እግዚአብሔር ለማስደሰት ይሹ እና ትክክል የሆነውን ሁሉ የማድረግ አቅም ነበራቸው። ሰይጣንም ሔዋን እግዚአብሔር እንዳትታዘዘው ሊያታልላት መጣ፤ በዚህም ኃጥያት በምድር በልዕለ አለሙ ውስጥ እንደነበረ መረዳት እንችላለን። ሰይጣን ቀድሞንን በኃጥያት ወድቋል- ነገር ግን ኃጥያት ወደ ሰው ልጆች እና በሰው ልጆች አስተዳዳሪነት ውስጥ ወዳለው ፍጥረት አልገባም ነበር።

አዳም እና ሔዋን ነፃ ፈቃድ ነበራቸው። ኃጥያት እውን መሆን የቻለው ሰዎች እውነተኛ የሆነ ምርጫ ማድረግ ስለቻሉ ነው። የእግዚአብሔር ህግ መተላለፍን መረጡ፥ ይህም የሰው ልጅ ኃጥያት ጅማሬ ነው።

የመጀመርያው የኃጥያት ተግባር ሰውን ከእግዚአብሔር ለየው፥ ኃጥያትም የሰውን ልጅ ፍጥረት አበላሸው (መዝሙር 51፥5 ይነበብ)። ከዚህ በኃላ የሚወለዱ ልጆች በሙሉ በኃጥያት ህይወታቸው የተበላሸ እና ኃጥያትን የሚያደርጉ ሆኖ (ሮሜ 5፥12፣ 14፣ 18-19 ይነበብ)።

ኃጥያት በፍጥረት ሁሉ ላይ እርግማ አመጣ (ዘፍጥረት 3፥16-19)። ህይወትም ከኃጥያት የተነሳ ተለወጠ- ህመም፥ ማርጀት፥ እና ሞት ጀመሩ (1 ቆሮንቶስ 15፥22 ይነበብ )። ስራ እና ኑሮ ከባድ ሆነ፥ የሰዎች ግንኙነት በግጭት የተሞላ ሆነ፥ አመታት በጨመሩ እና ሰዎች በበዙ ልክ፥ የኃጥያትም መዘዝ አዳም እና ሔዋን ከገመቱት በላይ የበዛ ሆነ።

## ለኃጥያት የዕብራይስጥ እና የግሪክ ቃላት

ብዙ ቋንቋዎች ለኃጥያት የተለያዩ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት አሏቸው። የመጀመርያዎች መጽሐፍ ቅዱስ የተፃፈባቸው የዕብራይስጥ እና የግሪክ ቋንቋዎችም፥ ከታች እንደተብራራው፥ በተለያዩ ቃላት ኃጥያትን ለመግለይ እና ለመተርጎም ይጠቀማሉ- እነዚህ ቃላት ስለ ኃጥያት ሙሉ የሆነ ስዕል ይሰጡናል

> "ኃጥያት እና እግዚአብሔር ልጅ በፍጹም አብረው መሄድ የማይችሉ ናቸው። አንዳንድ ግዜ ይገጣጠማሉ ነገር ግን አብረው በስምምነት መኖር አይችሉም።"
>
> – ጆን ስቶት

- **ኃጥያት እንደ ስልጣንን አለመቀበል- አመፅ** (መዝሙር 51፥1) ያዕቆብ ይህንን የዕብራይስጥ ቃል ከላባ ጋር ያደረገው ንዴት በተሞላ ንግግር ውስጥ በእርሱ ላይ የፈፀመው ወንጀል ምን እንደሆነ ሲጠይቅ ይጠቀመዋል (ዘፍጥረት 31፥36)። ይህም ቃል የሞኣብ ንጉስ በንጉስ እዩርብኣም ላይ ፈፀመውን ተግባር ለመግለፅ ጥቅም ላይ ውሏል (2 ነገሥት 3፥7)።
- **ኃጥያትን እንደ ጠማማነት ወይም መዛባት-** የታጠፈ ወይም የተጣመመ (መዝሙር 51፥2a)- ሰይጣን ምንም መፍጠር አይችልም፥ በመሆኑም ኃጥኣት እግዚአብሔር የፈጠረውን መልካም ነገር ሁሉ ማጣመም/ ማዛባት ነው።

- ***ኃጥያት የሚፈለገውን መሳት ወይም ከግብ መጉደል ነው*** - በመዝሙር 51፥2b ላይ ለኃጥያት ጥቅም ላይ የዋለው ቃል ይህንን ትርጉም ይይዛል። በመሳፍንት 20፥16 ላይም ደግሞ ስለ ስነምግባር ጉድለት ተመሳሳዩ ቃል በገለልተኛ መንገድ ስለ700 ግራኝ የሆኑ ወንጭፍ ወርውረው በአናት ላይ ያለ ፀጉር የማይስቱ ተዋጊዎች ይገልጣል። ኃጥያት እግዚአብሔር ስለ እውነት፥ ቅድስና፥ እና ፅድቅ ያደረውን ምልክት መሳት ነው።

  በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለው ቃል ተመሳሳይ ትርጉም አለው። ቃሉ ለመላው አለም ኃጥያት መጠቀም ይቻላል (ማቴዎስ 1፥21) ፥ ወይም የአንድን ሰው ኃጥያት ለመግለጥ መጠቀም ይቻላል፥ ለምሳሌ የእየሱስን እግር እንዳጠበችው ሴት ኃጥያት (ሉቃስ 7፥48-50) ወይም አንድን ኃጥያት ለመግለጥ ሊሆን ይችላል እንደ እስጢፋኖስ መግደል ኃጥያት (ሐዋርያት ሥራ 7፥60)። ኃጥያት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ዞር ማለት ነው።

- ***ኃጥያት እንደ መጥፎ*** - የመልካም ተቃራኒ (መዝሙር 51፥4)- ይህ ተመሳሳይ ቃል በእብራይስጥ ፈርኦን በህልሙ ያያቸውን ሰባት ከሲታ ላሞችን (ዘፍጥረት 41፥19) እንዲሁም መበላት የማይቻለውን በለስ ኤርምያስ 24፥2 ለመግለጥ ጥቅም ላይ ውሏል።

- ***ኃጥያት እንደ ውድቀት ወይም ለመስማት ፈቃደኛ እንዳለመሆን፥ በንቃት ለሚደረግ አለመታዘዝ ውጤት*** ነው (ሮሜ 5፥19) - በሐዋርያት ሥራ 7፥57፤ ላይ እስጢፋኖስ ሲወገር ጆሯቸውን የደፈኑ ሰዎችን ባህሪ የሚያመላክት ነው። አለመታዘዝ የሚለው ቃል በግሪክ ያለውን ሃሳብ በሚገባ የሚያስረዳው ቃል ነው።

- ***ኃጥያት የተሰጠን የተወሰነን ህግ መጣስ ነው - እግዚአብሔር ከሚደነግገው በተቃራኒው ማድረግ ነው-*** (1 ዮሐንስ 3፥4)። ሁለት የግሪክ ቃላት በመጣመር 'ህግ አልባ' ወይም "ዐመፅ" የሚል ትርጉም ይሰጡናል።

- ***ኃጥያት አውቆ ከትክክለኛው መንገድ ዞር ማለት ወይም ከሚታወቀው ወይም በእግዚአብሔር ከሚጠብቀው መንገድ አልፎ መሄድ ነው*** (ዘፀአት 32፥7-8) በዚህ ክፍል ውስጥ ሰዎች ሙሴ ሲና ተራራ ላይ ሆኖ ከእግዚአብሔር መንገድ ዞር ማለት ነው።

- ***ሳናውቅ የሚደረጉ ኃጥያቶች*** (ዘሌዋውያን 4፥2)- ይህ አይነት ኃጥያት በሁለቱን ብሉይ እና ዐዲስ ኪዳናት ውስጥ ተጠቅሷል። ዕብራውያን 9፥7 ላይ የተጠቀሰው የግሪክ ቃል 'አላዋዊ መሆን' ወይም 'አለመረዳት' ከሚለው ግስ ሲሆን- ትርጉሙም 'ኃጥያትን ያለማወቅ ማድረግ' ፤ **ይህም ጥቅስ ሊቀ ካህኑ ባለማወቅ ስለተሰራ ኃጥያት የሚያደርገው የስርየት ስርዓትን የሚገልፅ ነው።**

ከእነዚህ ቃላት ውስጥ ኃጥያት ዘርፈ ብዙ የሆነ ችግር እንዳለበት አመላካች ነው። አንዳንድ ቃላት ኃጥያትን በጠቅላላው ሑነቱ የሚገልጡ ሲሆን፤ ሌሎች ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ባለመስማት ምክንያት ለተቀመጠ ህግ በመጠበቅ መኖር ሲያቅታቸው፥ ሆነ ቀድሞ የታሰበበት ኃጥያት ወይም ባለማወቅ ወይም በስዕተት የሚሰራ ኃጥያት ነው። የትኛውም ኀጥያት ይሁን ግን እየሱስ በመስቀል ላይ ሰዎችን ከኃጥያታቸው ለማዳን እንደሞተ ማወቅ የተባረከ ሃሳብ ነው (ማቴዎስ 1፥21)።

### በፈቃድ የሚሰራ ኃጥያት

► በፈቃድ የሚሰራ ኃጥያት ምንድን ነው?

*በፈቃድ የሚሰራ ኃጥያት ማለት ለተገለጠው የእግዚአብሔር ፈቃድን አውቆ መጣስ ነው።* (1 ዮሐንስ 3፥4፤ ያዕቆብ 4፥17 ይነበብ)። *ሰዎች ስዕተት መሆኑን እያወቁ ማድረግ መቀጠል ወይም ትክክል የሆነውን ነገር ላለማድረግ መምረጥ ነው። አውቆ የሚደረግ የስዕተት ስራ ነው።*

በ1 ዮሐንስ 3፥5-6 ላይ ሐዋርያው ዩሐንስ እንዲ ብሎ ይፅፋል

> እርሱ እየሱስ ኀጢአትን ሊያስወግድ እንደ ተገለጠ ታውቃላችሁ፤ በርሱም ኀጢአት የለም። በርሱም የሚኖር ኀጢአትን አያደርግም፤ ኀጢአት የሚያደርግ ግን እርሱን አላየውም ወይም አላወቀውም።

በዚህ ክፍል የሚያወራው አውቀን በተደጋጋሚ የሚደረግ ኃጥያት ነው። የዚህ ክፍል ሲብራራ የሚለው ሃሳብ፤ ማንም **በ**ክርስቶስ **የሚኖር** ቢሆን **በተደጋጋሚ እና ተለምዶዓዊ ኃጥያት** አይሰራም፤ እንዲሁም **በተደጋጋሚ እና በተለምዶ** ኃጥያትን የሚሰራ ሰው እንዲሁ እየሱስን አላየውም ፥ አያውቀውም።

አንድ ሰው ኃጥያትን በዚህ በጠቅላላው መተርጎም የሚፈልግ ከሆነ (ያለማወቅ ወይም በስዕተት የሚሰራን ኃጥያት ጨምሮ)፥ ይህ አርፍተ ነገር ትርጉም አይሰጠውም። ክርስቲያኖች ከፈቃዳቸው ባለፈ ውድቀት አለባቸው፤ ነገር ግን ማንም *ኃጥያት* (በዚህ ክፍል ውስጥ እንዳለው) ሲረዳው "የእግዚአብሔርን ህግ በፈቃደኝነት መካድ" በሚል ከሆነ ይህ ክፍል ትክክለኛ ትርጉም ይሰጠናል።

### የተወረሰ ውድቀት

► ሰዎች ይዘውት ስለሚወለዱት ኃጥያተኛ ማንነት ምን ትላላችሁ?

***የተወረሰ ውድቀት*** የሰው ልጅ ከተወለደ ጀምሮ ወደ ኃጢአት እንዲያዘነበል የሚያደርግ የተፈጥሮ ሞራል መበላሸት ነው። አንዳንዴ የሰው የውርስ ኃጥያት ነውም ተብሎ ይጠራል። ይህም በአዳም በሰራው ኃጥያት ምክንያት ያለን ኃጥያተኛ ማንነት ነው።

ሁሉም ሰው ከውልደቱ ጀምሮ ወደ ክፋት ያዘነብላል። (መዝሙር 58፥3 ይነበብ)። የሰው ማንነት ከውልደቱ ጀምሮ ኃጥያተኛ ዝንባሌ ስላለው ከመጀመርያ ፍጥረቱ የተዛባ ኃጥያተኛ ዝንባሌን ሰው ከአካባቢው የሚማረው አይደለም ነገር ግን ምርጫን በራሱ መምረጥ ከሚጀምርበት ግዜ ጀምሮ ከፍጥረቱ ኃጥያትን መስራት ይጀምራል።

ዳዊት ሲናገር በአመፅ ተፀነስኩ፤ በኃጥያትንም ተወለድኩ ብሏል (መዝሙር 51፥5 ይነበብ)። እናቱ ስዕተት ሰርታለች ለማነት ሳይሆን ነገር ግን አንድ ሰው በእናቱ ማዕፀን ውስጥ ገና ሲበጅ ከፍጥረቱ በኃጥያት የተበላሸ ማንነት ይዞ እንደሚሰራ ለማለት ነው።

በተበላሸ ማንነቱ ምክንያት በሰዎች ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር መልክ ተጎድቷል። ሁሉም ሰው ራሱን በሚወድ እና ለኃጥያት በተሰጠ ማንነት ይዞ ይወለዳል (ሮሜ 3፥10-12)። እግዚአብሔር መሻቱን እና ጉልበትን ካልሰጠን በቀር ሰው በራሱ መልካምን የመምረጥ ነፃነት የለውም።(ሮሜ 6፥16-17 ይነበብ።)

**የተወረሰ ውድቀት** እንደ ኩራት፥ ቅናት፥ ጥላቻ እና ይቅርታ አለማድረድ የመሳሰሉ ነገሮችን እንድንፈልግ ያደርገናል። ኃጥያትያዉ የሆኑ ተግባራትን እንድንመርጥ ያነሳሳናል።

ሰዎች የእግዚአብሔርን ባለስልጣንነት ላይ የሚያምፅ ተፈጥሮዓዊ አመለካከት እና በሰጠው ህግ ላይ ቁጣ አለባቸው። ኃጥያተኞች ስለ ኃጥያተኛ ተግባራቸው ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ስላለው የአመፅ አመለካከታቸውም ይቀጣሉ (ይሁዳ 1፥15 ይነበብ)።

ኃጥያተኛ ማንነት ያለው ሰው በተፈጥሮ ራስ ወዳድ ነው። ለእግዚአብሔር እና ሌሎች ፈቃድ ራሱን ከማስገዛት በላይ ለራሱ ፈቃድ ለመፈፀም የተሰጠ ነው። እግዚአብሔርን ከማስደሰት ይልቅ የራሱን ፍላጎት ለማሟላት የሚፈልግ ነው። በእግዚአብሔር ላይ የሚተማመን ሳይሆን በራሱ የሚተማመን ነው፥ ለእርሱ ዋነው ነገር የራሱ ስኬት እንጂ የእግዚአብሔር ክብር አይደለም።

የሰዎች እውቀት ስለጨለመ ትክክለኛውን ከስዕተቱ በሚገባ መለየት አይችሉም (ኤፌሶን 4፥17-18 ይነበብ)። ሰዎች በተፈጥሯቸው የአለምን አመፀኛ ፈቃድ የሚከተሉ፥ በሰይጣን ቁጥጥር ውስጥ እና በራሳቸውን ኃጥያተኛ ፍላጎት የሚከተሉ በመሆን ራሳቸውን በእግዚአብሔር ቁጣ ስር ያውላሉ (ኤፌሶን 2፥2-3 ይነበብ)። በእያንዳንዱ ደቂቃ የሰዎች ተፈጠሯዊ ዝንባሌ ወደ ኃጥያት ነው (ዘፍጥረት 6፥5)።

ሰዎች የእግዚአብሔር ፀጋ በህይወታቸው የሚያመጣው ለውጥ ካልሆነ በስተቀር መልካም ማድረግ ሆነ መልካምን መሻት አይችሉም። በንሰዓ መመለስ ሆነ እግዚአብሔርን መፈለግ አይችሉም (ዮሐንስ 6፥44 ይነበብ)። በኃጥያታቸው እና በበደላቸው የሞቱ ናቸው (ኤፌሶን 2፥1)። የስነ መለኮት ምሁራን ይህንን ‘ፍጹም ውድቀት’ ይሉታል።

የእግዚአብሔር ፀጋ እንዴት ለሚወረስ ኃጥያት የሚሰጠውን ምላሽ መገንዘብ አስፈላጊ ነው። በመጀመርያ የእግዚአብሔር ኃይል ከወንጌል ጋር አብሮ በመምጣት ለወንጌል ምላሽ ለመስጠት ፍላጎት እና አቅም ይሰጣል። (ይነበብ ሮሜ 1፥16.) በመቀጠልም የዳነው ሰው ከኃጥያት ቁጥጥር ስር ነፃ ይወጣል (ሮሜ 6፥11-14)፤ ነገር ግን አዲስ የዳነ ሰው ከተወረሰ ኃጥያት ተፅዕኖ ስር መሆኑን ይቀጥላል።

የተወረሰ ኃጥያት ተፅዕኖ በክርስቲያን ውስጥ በተለያዩ መንገድ ይገለጣል።

1. አዲስ ክርስቲያን በሚፈተን ግዜ በራሱ ፈቃድ ይታገላል
2. አዲስ ክርስቲያን ሊቃወማቸው የሚገቡ የተሳሳቱ መገፋፋቶች ይሰሙታል
3. አዲስ ክርስቲያን ማድረጉን ሳያስተውል የተሳሳተ ምላሽ እና እሳቤ ይኖረዋል

አዲሱ ክርስቲያን ኃጥያት ያለባቸውን ዝንባሌዎች ገና ስላሉት እምነቱን እንዳይተው ሊበረታታ ይገባል። በእግዚአብሔርን መንፈስ የሚመገኘውን ኃይል እና ለውይ ሁል ግዜ መሻት አለበት።

መጋቢው ከአዲሱ ክርስቲያን ጋር ትዕግስት ሊኖረው ያስፈልጋል፤ በሚለው እና በሚያደርጉት ሁሉ ወጥነት አይኖራቸውም እንዲሁም ችግራቸውን ወድያው መለየት አይችሉም።

### ባለማወቅ የሚሰሩ ስህተቶች

አንዳንድ ግዜ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል **ባለማወቅ ወይም በስዕተት ሊያፈርሱ/ ሊጥሱ** ይችላሉ፥ በዘሌዋውያን 4፥2-3 ውስጥ አንድ ሰው ይህ አይነት ስዕተት እንደተሳሳተ ባወቀበት ቅፅበት ወድያው መስዋትን ማቅረብ እንዳለበት

እንመለከታለን። የክርስቶስ ሞት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ይቀርቡ የነበሩ መስዋቶችን ሁሉ ስለሚተካ፤ ክርስቲያኖች ባለማወቅ ለሚሰሩ ስህተቶች ሁሉ ድነት አላቸው።

መረዳታችን የተወሰነ ስለሆነ ባለማወቅ የሚሰሩ ስህተቶች አይቀሬ ናቸው፤ ለእግዚአብሔር ያልንን ፍቅር ላይ ስለማይጋጩ ከእርሱ ጋር ያልንን ግንኙነት አይነኩብንም። እግዚአብሔር ለእርሱ ያለን ፍጹም ፍቅር እርሱ ከእኛ የሚፈልገውን ሁሉ እንደሚያሟላ ተናግሯል። (ማቴዎስ 22፥37-40፤ ሮሜ 13፥8-10 ይነበብ)፥ ለማናውቀው ነገር ተጠያቂዎች መሆን አንችልም (ያዕቆብ 4፥17 ይነበብ)።

> በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ያለ ትልቅነት የሚለካው በመታዘዝ ነው።
>
> ጆን ስቶት

በብርሃን ስንመላለስ (በምናውቀው እውነት ውስጥ ስንመላለስ) ከኃጥያት ሁሉ እንነፃለን (1 ዮሐንስ 1፥7 ይነበብ)። በክርስቶስ የማዳን ስራ ስለምንታመን ባለማወቅ የሰራናቸው ስዕተቶች ከእግዚአብር ጋር ያልንን ግንኙነት ያፈርሱብናል ብለን አንፈራም።

ዘሌዋውያን ባለማወቅ ስዕተት መስራታችንን ስንገነዘብ ንሰሓን እንድንገባ እና እግዚአብሔር ምዕረት እንድንለምን እንዲሁም እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ህይወታችንን እንድናስተካክል ያስተምረናል።

የእግዚአብሔርን ቃል ስናጠና፥መንፈስ ቅዱስን ስንከተል፥ ከሌሎች አማኞች ጋር ህብረትን ስናደርግ እና በብስለት ስናድግ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚጣረሰውን ባለማወቅ የምንሰራውን ስዕተት እንቀንሳለን።

► የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሚገባ ማወቅ እና ማድረግ ያለብን ለምንድን ነው?

የእግዚአብሔር ፈቃድ የበለጠ ማወቅ እና መከተል የምንፈልግበት ምክንያቶች

1. እግዚአብሔር የሚያሳዝን ምንም ማድረግ ስለማንፈልግ።
2. የትኛውም ስዕተት፥ ባለማወቅም የተሰራ ቢሆንም፥ መጥፎ ውጤት አለው።
3. እንደ ክርስቲያን መልካም ምሳሌ መሆን አለብን።
4. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስናስወግድ ባለማወቅ በሚሰራ ኃጥያት ጥፋተኛ ነን።

ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ያለን እውቀት ሲጨምር በህይወታችን ያለውን ስዕተቶች ማስተዋል እንጀምራለን። የምናደርገው ነገር ስዕተት መሆኑን ስንገነዘብ ነገር ግን ማድረጋችንን ስንቀጥል፤ ስዕተቱ ባለማወቅ መሆን ያቆማል። መለወጥ ሲያቅተን ስዕተቱ በፍላጎት የሚሰራ ኃጥያት ይሆናል።

## መደምደምያ

አንዳንድ ግዜ የስነመለኮት ምሁራን ኃጥያቶችን በራሳቸው ጎራ አያስቀምጡም፤ ከፍፅምና የጎደለ ነገር ሁሉ ወይም በማወቅ የሚደግ ስዕተት ሁልግዜ ኃጥያት በማለት ይፈርጃሉ። የኃጥያት በራሳቸው ጎራ ስንረዳ የእግዚአብሔር ፀጋ በእኛ ምን መስራት እንደሚፈልግ እንረዳለን።

- **በፈቃድ የሚሰራ ኃጥያት** ሁሉ ሰው ዳግም ሲወለድ ማሸነፍ ይችላል። ዮሐንስ ዳግም የተወለደ ሰው ኃጥያትን መደበኛ ተግባር አያደርግም (1 ዮሐንስ 3፥4-9)። በፈቃድ የሚሰራ ኃጥያት በክርስቶስ ካለን

እምነት ጋር አብሮ የሚሄድ አይደለም። በማወቅ የሚደረግ አመፅ የአንድ ክርስቲያን የተለመደ ባህሪ አይደለም።

- መቀደስ ሰዎች ፍፁማን ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር **በሰዎች ህይወት ውስጥ ያለውን ኃጥያት** ለማጥፋት የሚሰራው ስራ ነው (1 ተሰሎንቄ 5፥23)። የሰዎች ሁሉ መንፈስ፥ ነፍስ እና አካል ሁሉን እንከን አልባ ማድረግ ነው። ቅድስና የሰውን ኃጥያተኛ የሆነ ማንነቱን የሚያሸንፍ ነው።
- **ያለማወቅ ኃጥያቶች** በአላማ የሚደረግ አለመታዘዝ አይደለም፤ ከኃጥያተኛም ማንነት የሚወጣ አይደለም ነገር ግን ከወደቀ አካል እና እውቀት የሚመነጭ ነው። ከዚህ አይነት ኃጥያት ሰው በምድራዊ ህይወቱ መላቀቅ አይችልም። በትንሳኤ ግን የከበሩት ቅዱሳን ሙሉ በሙሉ እና ለዘላለም ( በቋሚነት) ከሁሉም አይነት ኃጥያቶች ነፃ ወጥተዋል።

► የእምነት መግለጫውን ቢያንስ ሁለት ግዜ አብራችሁ አንብቡ።

**የእምነት መግለጫ**

የሰው ኃጥያት ከሚመነጨው በመጀመርያ የተፈጠሩት ሰዎች እግዚአብሔር ካለመታዘዛቸው ነው። ሑሉም ሰው፤ ከእየሱስ ክርስቶስ በስተቀር፥ ከአዳም የተወረሰ ውድቀት እና የኃጥያት ተግባራት ጥፋተኝነት አለበት። የሰው ስዕተቶች የእግዚአብሔርን ህግ ሊጥሱ ይችላሉ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት አያፈርስብንም። ሁሉም ኃጥያተኛ ከመጨረሻው ፍርድ በፊት ከእግዚአብሔር ምዕረትን ካላገኘ ለዘላለም የተፈረደበት ይሆናል።

## ትምህርት 5 የቤት ስራዎች

(1) የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የቤት ስራ፡- ከታች ከተዘረዘሩት ዘርፎች መካከል እያንዳንዱን ተማሪ አንድ ይመደብ። ከሚቀጥለው ክፍለ ግዜ በፊት ክፍሉን አንብባችሁ በትምህርቱ ውስጥ ካለው ሃሳብ ላይ ምን እንደሚናገር በአንድ አንቀፅ ፃፉ።

- ሮሜ 1፥21-32
- ሮሜ 3፥10-20
- ገላትያ 5፥16-21
- ኤፌሶን 5፥1-8
- ቲቶ 1፥10-16
- ያዕቆብ 4፥1-4
- 2 ጴጥሮስ 2፥9-17

(2) ፈተና፡- የሚቀጥለው ክፍለ ግዜ የምትጀምሩት በትምህርት 5 ፈተና ነው። ለፈተና ዝግጅት እንዲሆን የፈተና ጥያቄዎችን አጥኑ።

(3) የማስተማር የቤት ስራ፡- ከክፍል ውጪ የማስተማርያ ግዜን ቀጠሮ መያዝ እና ማስተማራችሁን ሪፖርት ማድረግ አስታውሱ።

## የትምህርት 5 ፈተና

(1) ኃጥያትን መረዳት ያልብን ሦስት ዋና ምክንያቶች ዘርዝሩ።

(2) ኃጥያት በእግዚአብሔር ምክንያት የሖነ እንዳልሆነ በምን እናውቃለን?

(3) ለሚከተሉት ለእያንዳንዱ በአንድ አርፍተ ነገር ትርጉም ጻፉ፤ በፈቃድ የሚሰራ ኃጥያት፥ የተወረሰ ውድቀት፥ ባለማወቅ የሚሰሩ ስህተቶች።

(4) የእግዚአብሔርን ፈቃድ አብዝተን መፈለግ እና ማድረግ ያለብን ለምንድን ነው?

# ትምህርት 6

# መናፍስት

## የትምህርቱ አላማ

(1) ተማሪው የሚከተሉትን ማስረዳት ይችላል

- ስለ መላዕከት ማንነት የሆነ ያህል መረጃ ይኖራቸዋል
- መላዕክት በአማንያን ህይወት ውስጥ ያለው ተሳትፎ
- የሰይጣን መውደቅ እና ሌሎች ክፉ መናፍስት
- በመንፈሳዊ አለም ያለው መንፈሳዊ ውጊያ
- የእግዚአብሔር እና አማንያን በክፉ መናፍስት ላይ የሚቀናጁት የመጨረሻ ድል
- ስለ መናፍስት ክርስቲያናዊ የእምነት መግለጫ

(2) ተማሪዎች ስለ መንናፍስት አለም የተሳሳተ አይነት ፍላጎትን ያስወግዳሉ።

## መላዕክት ምን አይነት ናቸው

► ማቴ 4፥1-11 አብራችሁ አንብቡ። ይህ ክፍል ስለ ስለክፉ መናፍስት ምን ይነግረናል?

ሰዎች ስለመላዕክት ሲናገሩ ብዙ ግዜ ጥያቄው የሚጀምረው "መላዕክት ምን ይመስላሉ?" ከሚለው ነው፤ ብዙም አርቲስቶስ ሊገልጧቸው ሞክረዋል።

► መላዕክት ምን ይመስላሉ?

መላዕክት ክፍ አላቸውን? ኢሳይያስ ሱራፌል ስድስት ክንፎች እንዳሉት ተመልክቷል (ኢሳይያስ 6፥2)። እግዚአብሔር ሙሴን በታቦቱ ላይ እንዲያስቀመጥ ያዘዘው የኪሩቤል ምስል ክንፎች ነበሩት (ዘፀአት 25፥20)። ሕዝቅኤል ያየው ኪሩቤል ደግሞ አራት ክንፎች ነበሩት (ሕዝቅኤል 1፥6፣ ሕዝቅኤል 10፥15)።

መላዕክት በጠቅላላው ክንፍ ይኖራቸው ወይም አይኖራቸው በእርግጥ አናውቅም። ለመንቀሳቀስ ክንፍ አያስፈልጋቸውም፥ መንፈስ ስለሆኑ በክንፍ ከሚበሩበት ፍጥነት በላይ ይጓዛሉ። መንፈስ ስለሆኑ ቁሳዊ የሆነ አካል የላቸውም። ለመላዕክት ክንፎች ብዙውን ግዜ አላስፈላጊ ናቸው።

ብዙ ግዜ የምናያቸው ምስሎች በተቃራኒ፤ መጽሐፍ ቅዱስ መላዕክትን በሴቶች ሆነ ዕጻናት አይመስላቸውም። እንደ ወንድ ቢገለጡም ነገር ግን ሰዎች እንደሆኑት አይነት ፆታ የላቸውም። የትዳር ሆነ ቤተሰባዊ የሆነ ግንኙነት የላቸውም። (ማቴዎስ 22፥30 ይነበብ)። እያንዳንዱ ለየብቻው ነው የተፈጠረው።

መላዕክት ለሰዎች ብዙ ግዜ ለሰዎች አይታዩም፥ ነገር ግን አላማ ሲኖራቸው ሊገለጡ ይችላሉ። አንዳንድ ግዜ መላዕክት ሲገለጥላቸው ሰዎች በመጀመርያ ሰው ያዩ ይመስላቸዋል (ዘፍጥረት 19፥1-2)። በሌላ ግዜ መላዕክት

በታላቅ ግርማ ስለሚገለጡ ሰዎች በፍርሓት መሬት ላይ ይወድቃሉ (ማቴዎስ 28፥2-4)። መላዕክት ለሰዎች ብቹ ግዜ ሲገለጡ የሚያቀርቡት ሰላምታ “አትፍራ” የሚል ነው (ሉቃስ 1፥13፣ 30፤ ሉቃስ 2፥10 ይነበብ)።

መላዕክት መናፍስት ናቸው (ዕብራውያን 1፥14)፣[14] በዚህ ምክንያት ግን እውን ከመሆን ያነሱ እንደሆኑ ማሰብ የለብንም። መጽሐፍ ቅዱስ መናፍስት ከየትኛው ቁሳዊ በላይ የበለጡ ሓያላን ናቸው (ኢሳይያስ 31፥1፣ 3 ይነበብ)።

መላዕክት የሆነ ያህል የእግዚአብሔርን ስብዕና እንደ ሰው ባልሆነ መንገድ ይጋራሉ። መላዕክት ከሰዎች በኃይህ እና ጥበብ ይበልጣሉ፤ ነገር ግን ሰዎች ከመላዕክት የሚበልጡበት ግዜ ይመጣል (1 ቆሮንቶስ 6፥3 ይነበብ)።

በዘፍጥረት ውስጥ የመላዕክት አፈጣጠር አልተፃፈም፤ ምድር ከመፈጠሯ በፊት መላዕክት ተፈጥረዋል፤ እግዚአብሔርም ምድርን ሲፈጥር መላዕክት የፈጠረውን አይተው አክብረዋል (ኢዮብ 38፥4-7 ይነበብ)።

መላዕክት አይሞቱም (ሉቃስ 20፥36)። መላዕክት አለም ከመፈጠሩ በፊት ስለተፈጠሩ እጅግ ብዙ ሺ ዓመታት ኖረዋል እንዲሁም የምድርን ታሪክ በሙሉ ተመልክተዋል።

መላዕክት የራሳቸው ስብዕና አላቸው። መናገር እና ከሌሎች ጋር ተግባቦት ማድረግ ይችላሉ (ሉቃስ 1፥18-20)። እግዚአብሔርን ያመልካሉ፥ ይህም ማለት የእርሱን ማንነት እና ለትልቅነቱ ምላሽ መስጠት ይችላሉ (ዕብራውያን 1፥6)። በኃጥያተኛው መመለስ ይደሰታሉ፤ ይህም ስሜት እንዳላቸው አመላካቸው ነው (ሉቃስ 15፥10 ይነበብ)። የመዳን ዕቅድ ምን እንደሆነ ለመረዳት አብዝተው የሚሹ በመሆናቸው የመገንዘብ ችሎታ እንዳላቸው ያመላክታል (1 ጴጥሮስ 1፥12 ይነበብ)። የእየሱስን መወለድ ሲያበስሩ በብዙ ምስጋና ያከበሩ ናቸው (ሉቃስ 2፥13-14)።

መላዕክት ተመሳሳይ አይደሉም፤ ምክንያቱም አንዳንዶች ኪሩቤል ተብለዋል (መዝሙር 80፥1)፤ ሌሎች ሱራፌል (ኢሳይያስ 6፥2)። እንዲሁም መላዕክት የተለያየዑ ደረጃዎች አሏቸው፥ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መላዕክትም እንዲሁም ቢያንስ ስለአንድ ሊቀ-መላዕክት እና እንዲሁም “ዲያብሎስና መላእክቱ” (ማቴዎስ 25፥41) ተገልጠዋል። የስልጣን ተዋረድ በመካከላቸው አለ፥ ይህም ዙፋናት፥ አለቆች እና ስልጣናት ተብለው ተገልጠዋል (ኤፌሶን 6፥12፤ ቈላስይስ 1፥16 ይነበብ)።

በአይሁድ ሆነ ክርስቲያን ትውፊት ውስጥ ስለ መላዕክት ምናልባትም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተፃፈው በላይ ብዙ ጽሑፎች አሉ።


በመላዕክት መካከል ስላለ ልዩነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ አልተገለጠም። *መላእክት አለቃ* የሚለው ቃል ሑለት ግዜ ብቻ ተፅፏል። ሚካኤል መላእክት አለቃ፣ ይባላል፤ እንዲሁም የክርስቶስ ዳግም ምፅዓት መላእክት አለቃ ድምፅ አለው (1 ተሰሎንቄ 4፥16፤ ይሁዳ 1፥9)። *መላእክት አለቃ* የሚለው ሃሳብ ቀጥተኛ ትርጉም ‘የመላዕክት ዋና/ሊቀ መላዕክት’ ነው። ምን ያህል መላእክት አለቆች እንዳሉ በቁጥር አናውቅም።

ሱራፌል የሚለው ቃል በኢሳይያስ 6 ላይ ብቻ ነው የተጠቀሰው። ስድስት ክንፍ አላቸው፤ ከክንፎቻቸው ውጪ መልካቸው ሁሉ የሰውን በሚመስል እጆች፥ እግሮች እና ፊት አላቸው።

---

[14] አጋንንትም ‘መናፍስት’ ተብለው በማቴዎስ 8፥16፣ ማቴዎስ 12፥45፤ ሐዋርያት ሥራ 19፥12፤ እና በሌሎች ዘርፎችም ላይ ተገልጠዋል።

ኪሩቤል እና የሚነደው ሰይፍ በኤደን ገነት መግቢያ ላይ አዳም እና ሔዋን መባረርን ተከትሎ የተቀመጠ ነው (ዘፍጥረት 3፥24) አላማውን ወደ ኤደን ገነት መግቢያውን መከልከል ነው። የሕዝቁል ስለ ኪሩቤል ያለውን መግለጫ ከሌላው የተፈጠረ ፍጥረት ሁሉ የተለየ ነው። አራት ክንፍ፥ አራት የተለያዩ ፊቶች፥ ብዙ እጆች ያላቸው፥ እንደ እሳት የቀላ መልክ ያላቸው፥ እንደ መብረቅ የሚያበሩ እና የፈጠኑ ናቸው (ሕዝቅኤል 1፥5-14፤ ሕዝቅኤል 10፥15)።



[15]በታቦት ማዕከል ላይ የምህረት መቀመጫ ኖሮ በጫፎች ላይ ሁለት ኪሩቤሎች ይቀመጣሉ ፤ እግዚአብሔርም በተደጋጋሚ በኪሩቤል ላይ የምትቀመጥ[16] ተብሎ ተጠርቷል። ይህም እግዚአብሔር በቤተ-መቅደስ ውስጥ የሚመለክ ፤ እርሱ ባዘዘው መልኩ ብቻ የሚቀረብ የእስራኤል አምላክ እንደሆነ ያሳያል።

የእግዚአብሔር ኃይል እና ግርማ በሚያገለግሉት ሰራተኞቹ መካከል ይታያል። ኪሩቤሎች የሚመለከታቸው ሰው እግዚአብሔርን ራሱ እንዳየ ያስባል፥ እናም እነርሱን ለማምለክ ሊቃጣው ይችላል ይሁን እንጂ ኪሩቤል የእግዚአብሔር አገልጋይ ብቻ ነው።

ብዙ መላዕክት በእግዚአብሔር ዙርያ መሆናቸው ታላቅ ግርማውን ያመላክታል። ሐዋርያው ዮሐንስ በራዕይ በእግዚአብሔር ዙፋን ዙርያ እልፍ የሆኑ መላዕክት መከበቡን እንዲህ ይገልጠዋል "ሺሕ ጊዜ ሺሕና እልፍ ጊዜ እልፍ" (ራእይ 5፥11)።

የመላዕክት ኃይል ያልተወሰነ አይደለም፤ ዳንኤልን ስናነብ አንድ መላዕክት ለዳንኤል መልዕክት ለማድረስ መንገድ ላይ መቋቋም ገጥሞት ነበር (ዳንኤል 10፥12-13 ይነበብ)። እግዚአብሔር ግን ለሚሰጣቸው የትኛውም ስራ የሚያስፈልጋቸውን ያህል ኃይል ይሰጣቸዋል፤ ለምሳሌ 185፣000 ወታደሮችን እንደገለው መላዕክት (2 ነገሥት 19፥35)።

መላዕክት የሚመደቡበት ስራ አለ። መጽሐፍ ቅዱስ ድነትን የሚቀበሉትን ለማገልገል እንደሚላኩ ይነግረናል (ዕብራውያን 1፥14 ይነበብ)። እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ሰዎችን ይከባሉ እና ይጠብቃሉ (መዝሙር 34፥7)። በሁሉም ግዜ ብዙ መላዕክት ከእኛ ጋር እንዳሉ መገንዘብ እንችላለን። እየሱስም ለልጆችን የሚመደቡ መላዕክት እንዳሏቸው ተናግሯል (ማቴዎስ 18፥10 ይነበብ)። መላእክት አለቃ ሚካኤል የእስራኤል እንደ ሀገር የሚጠብቅ ልኡል እንደሆነ ተፅፏል (ዳንኤል 12፥1)።

መጽሐፍ ቅዱስ ለመላዕክት እንዳንፀልይ ያስተምረናል፤ ከእነሱ ጋር መነጋገር እንድንሞክር እንኳን አይነግረንም። በሰዎች እና እግዚአብሔር መካከለኛም አይደሉም። መላዕክት ለሚያመልኩ እና በሚገባ ባልተረዱት የመናፍስት አለም ውስጥ ለሚሳተፉ ታላቅ ማስጠንቀቂያ አለ (ቈላስይስ 2፥18 ይነበብ)። እግዚአብሔር በማይፈልገው መንገድ

---

[15] ምስል፡-"Ark of the Covenant engraving", *Illustrated Bible Dictionary* (1893), የተወሰደ https://commons.wikimedia.org/wiki/File:Ark_of_the_Covenant_engraving.jpg, public domain.

[16] ለምሳሌ፤ 2 ነገሥት 19፥15፣ 1 ዜና መዋዕል 13፥6፤ ኢሳይያስ 37፥16

ከመላእክት ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ከሞከርን፤ ምናልባትም ከእግዚአብሔር መላዕክት ይልቅ ክፉ መናፍስት ምላሽ ይሰጡናል።

## ሰይጣን እና የወደቁ መላእክት

► የክፉ መናፍስት ምንጭ/ መገኛ ከየት ነው?

ክፉ መናፍስት እግዚአብሔር ላይ ያመፁ መላዕክት ነው። ይህ የሆነው ሰዎች ከመፈጣቸው በፊት ነው፥ እንዴት እንደሆነም መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ አይገልጠውም። ሰይጣንም የአመፁ መሪ ነበር፥ አንድ ሶስተኛ የሆነውን መላዕክት ተከተለው (ራእይ 12፥4)። ይሁዳ ሲናገርም ቦታቸውን ስለተዉ መላዕክት ይናገራል (ይሁዳ 1፥6)። አሁን እግዚአብሔር ፈርዶባቸዋል (ዮሐንስ 16፥11፤ 2 ጴጥሮስ 2፥4 ይነበብ)።

በትንቢት መጽሐፍት ውስጥ ሁለት ቦታዎች ላይ ስለ ሰይጣን መውደቅ ሊናገሩ ይችላሉ (ኢሳይያስ 14፥12-17 እና ሕዝቅኤል 28፥12-19)። እያንዳንዱ ክፍል ስለ ምድራዊ ንጉስ የሆነ ሰው ነው የሚናገረው ነገር ግን ይህ የነገስታቱ መውደቅ ከሰይጣን መውደቅ ጋር እያነጻጸሩ ሊሆን ይችላል።

ሰይጣን በኩራት በመያዝ ከእግዚአብሔር አገዛዝ ነፃ ለመውጣት የሞከረ ይመስላል። ሐዋርያው ጳውሎስ ሰዎች ኩራተኛ በመሆናቸው እንደ ሰይጣን ባለ ቅጣት ውስጥ ሊወድቁ እንደሚችሉ ያስጠነቅቃል (1 ጢሞቴዎስ 3፥6 ይነበብ)። ዲያቢሎስ ለአዳም እና ሔዋን "እንደ እግዚአብሔር እንደምትሆኑ" (ዘፍጥረት 3፥5) በማለት ያቀረበላቸው ፈተና ይህ ነበር። ይህ ፈተና የእግዚአብሔርን ገዥነት በመካዳት ለራሳችን አማልክት እንዲሆን የቀረበ ፈተና ነው።

► ስለሰይጣን የምናውቃቸው አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው?

> ሰይጣን ራሱን የኃጥያተኞች ልብ፥ የአይኖች እና ምላስን ጌታ ያደርጋል። ልቡን በኃጥያት ፍቅር ይሞላዋል፥ አይኖቹ ጥፋተኝነቱን እና የሚጠብቀውን ቅጣት እንዳያዩ ያሳውራል እንዲሁም ምላሱን እንዳይፀልይ ይከለክለዋል።
>
> አደም ክላርክ
> ክርስቲያን ስነ-መለኮት
> 'መልካም እና ክፉ መላዕክት'

ሰይጣን አሁንም እግዚአብሔር ላይ ያለውን አመፅ የሚመራ ነው። በአየር ላይ ላሉት መንፈሳውያን ኀይላት ገዥ (ኤፌሶን 2፥2) ይባላል። የዚህ ዓለም ገዥ በመባል ይታወቃል ምክንያቱም በዚህ ምድር ላይ ያሉ ብዙዎቹ ሰዎች እግዚአብሔር ላይ በአመፅ ውስጥ ስለሚኖሩ ነው (ዮሐንስ 12፥31)። የዚህ አለም መንግስት ባለቤት እንደሆነ በመውሰድ በግዜያዊነት የፈለገው ይሰጠዋል (ሉቃስ 4፥4-6)። ወንጌልን እንዳይቀበሉም የኃጥያተኞችን እውቀት ያሳውራል (2 ቆሮንቶስ 4፥4 ይነበብ)። ንስሃ ያልገቡ ሀጢአተኞች በእውነት የእርሱ እስረኞች ናቸው (2 ጢሞቴዎስ 2፥26)። የእግዚአብሔርን ቃል ከእውቀትዓቸው በማውጣት ተፅዕኖ እንዳይኖረው ያደርጋል (ማርቆስ 4፥15 ይነበብ)። በሐናንያ እና ሰጲራ ልብ ውስጥ ቤተክርስቲያንን እና መንፈስ ቅዱስን የመዋሸትን ሃሳብ አስቀመጠ (ሐዋርያት ሥራ 5፥3)፥ በይሁዳ ውስጥም እየሱስን የመካድን ሃሳብ አኖረ (ሉቃስ 22፥3)፥ የስዕተት ሃይማኖታዊ አስተምሮዎችን በመፍጠር ሰዎች እንዲያስተምሯቸው ያበረታታል (1 ጢሞቴዎስ 4፥1 ይነበብ)።

ሰይጣን እግዚአብሔር ይጠላል እንዲሁም ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል ስለተፈጠሩ እና ከእግዚአብሔር ታላቅ ሞገስን ስላገኙ እነሱንም ይጠላቸዋል። ሰዎችን በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምፁ በማድረግ እርሱ ወዳለበት ኩነኔ ብዙዎችን ለማምጣት ይፈልጋል።

በራሳቸው ሃሳብ ሰይጣንን ለማገልገል የሚፈልጉ ሰዎች በምድር ላይ በሚገባ የተታለሉ ሰዎች ናቸው ምክንያቱም ድል በሌለበት አመፅ ውስጥ ናቸው። የማይወዳቸው እና መጥፋታቸውን ብቻ የሚፈልግ ጌታን እያገለገሉ ናቸው (1 ጴጥሮስ 5፥8)። መጠበቅ እንደማይችል እያወቀ ቃልኪዳንን ይገባላቸዋል (ዮሐንስ 8፥44)።

ሌሎች በኃጥያት ውስጥ ለመኖር በመወሰን ባለማስተዋል ሰይጣንን ይከተሉታል (ኤፌሶን 2፥2-3)። ለዚህ ነው ብዙ ግዜን እና አቅምን በመፈተን እና በማሳት ላይ የሚያጠፋው (2 ቆሮንቶስ 4፥4፣ 2 ቆሮንቶስ 11፥3፣ 14)። ከተፈጠሩ ነገሮች ውስጥ ጣኦታትን በመስራት፥ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲክዱ ይፈልጋል (ሮሜ 1፥25)። ፈተናዎቹ አሳች ናቸው ምክንያቱን እግዚአብሔር የፈጠረውን ከማበላሸት ውጪ ሌላ መስጠት የሚችለው ነገር የለውም። ሰይጣን ምንም ደስታን ሆነ ሃሴትን መፍጠር አይችልም፤ እግዚአብሔር ነው ሁሉንም የፈጠረው። ሰይጣን ማድረግ የሚችለው ብቸኛ ነገር ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ በሆነ መልክ የተበላሸን ደስታን ማቅረብ ብቻ ነው። ሰይጣን ምንም ነገር መፍጠር አይችልም፥ ማድረግ የሚችለው ብቸኛ ነገር እግዚአብሔር የፈጠረውን መልካም ነገር ማበላሸት ብቻ ነው።

አንዳንድ ክፉ መናፍስት የተለየ ቦታ ወይም ሰዎች ጋር ያተኩራሉ። መላዕኩ ሚካኤል እስራኤልን የሚጠብቅ አለቃ ተብሎ ተጠርቷል፤ የፐርሽያ እና የግሪክ ልኡላን ተብለው የተጠሩም ክፉ መናፍስትም አሉ (ዳንኤል 10፥13፣ 20)። አንዳንድ መናፍስትም የሀገራት አማልክት ይሆናሉ።

ሰይጣን አምልኮን ይፈልጋል (ማቴዎስ 4፥9 ይነበብ)። ክፉ መናፍስት በተሳሳቱ ኃይማኖቶች ውስጥ ይሰራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ጣኦትን ሲያመልኩ አጋንንትን እያመለኩ እንደሆነ ይነግረናል (ዘዳግም 32፥17፤ 1 ቆሮንቶስ 10፥20-21 ይነበብ)። የሚያመልኩትን በማያውቁ ሰዎች አምልኮን አጋንንት ይቀበሉታል። እግዚአብሔር የሚያመልኩ ሰዎች እግዚአብሔር እየመሰሉ እና በቅድስናው ሀሴትን እንደሚያደርጉ፥ የክፉ አምላኪዎች እንዲሁ በክፋት እየጨመሩ እና ደስ እየተሰኙ ይሄዳሉ። ምናልባትም በጣም የከፋው አምልኮ ሰዎች ልጆቻውን ለአጋንንት መሰዋትን ያቀረቡበት አምልኮ ነው (መዝሙር 106፥37-38 ይነበብ)።

ሰይጣን እና አንዳንድ አጋንንት የሰዎችን እውቀት እና ባህሪ ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ይሞክራሉ። ይህን "በአጋንንት መያዝ" ይባላል። አንዳንድ ሰዎች በፈቃዳቸው ለእንደዚህ አይነት አጋንንታዊ ቁጥጥር ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋለ፥ ሌሎች ግን ምናልባትም የሚያደርጉትን ነገር ባለማስተዋል በህይወታቸው ይህ እንዲሆን ፈቅደዋል። አንዳንዶች ለራሳቸው አላማ ኃይልን የሚያገኙ መስሏቸው ወደዚህ ሁኔታ ውስጥ ቀስ በቀስ ገብተዋል። በአጋንንት የተያዘ ሰው ለክፉ መናፍስት ባርያ በመሆን ለራሳቸው ጥፋት ወደሚሆንባቸው እና በእውቀት እና ስሜታቸው የከፋን መከራን ወደሚቀበሉበት ሁኔታ ውስጥ ይገባሉ (ማርቆስ 5፥2-5 ይነበብ)። ከዚህ እስር ማላቀቅ የሚችለው እየሱስ ብቻ ነው።

**የእግዚአብሔር ድል**

ወንጌል በሚገባ የተንሰራፋቸው ሀገራት ውስጥ የአጋንንት እንቅስቃሴ በብዛት በተለያየ ሽፋን ውስጥ ነው የሚሰራው። በሚገርም ሁኔታ፥ እነዚህ 'ዘመኑ' በሚባሉ ሀገራት ዓለማዊነት ገኖባቸው የትኛውንም ልዕለ-ተፈጥሮዓዊ የሆነ ነገር ላይ የሚቀልዱ እና የመናፍስትን መኖር የሚክዱ ናቸው። በዚህ አይነት ሁኔታዎች ውስጥ ክፉ መናፍስት በግልፅ አይሰሩም ምክንያቱም ወንጌል የሰሙ ሰዎችን ቢያስፈራሩ ከእነዚህ ብዙዎች ነፃ ለመውጣት እና ለጥበቃው ወደ እግዚአብሔር ይመለሳሉ።

ወንጌል በሚገባ ያልተሰማባቸው ሀገራት ውስጥ ግን ክፉ መናፍስት በግልፅ ይሰራሉ። በእነዚህ ሀገራት ያሉ ሰዎች ነፃ ለመውጣት ወደ ክርስቶስ መዞር እንደሚችሉ አያውቁም፥ ስለዚህ የመናፍስት ኃይላት በማስፈራራት ይገዟቸዋል። ሰዎቹ መናፍስቱን በፈቃደኝነት እና በደስታ ሳይሆን በፍርሃት ያገለግሏቸዋል። ወንጌል የነፃ መውጣት እና የአርነት መልካም የምስራች ነው።

> "መቃወምህን ከቀጠልክ ዲያብሎስ ሊያሸንፍህ አይችልም። ምንም ያህል ኃይለኛ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር እርሱን መቃወም የሚቀጥልን ሰው ዲያብሎስ እንዲያሸንፈው ፈጽሞ አይፈቅድለትም። እርሱ የሰውን ፈቃድ በግድ ሊያስገድድ አይችልም።"
>
> አደም ክላርክ
> ክርስቲያን ስነ-መለኮት
> 'መልካም እና ክፉ መላዕክት'

ሁልግዜ ካለው የአጋንንት ውጊያ የተነሳ አሁን በመንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ ነው ያለውን። መዋጋታችን አካል ከለበሱ ጠላቶች ጋር ሳይሆን ከመናፍስቱ አለም ጋር መሆኑን እንድናስታውስ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል (ኤፌሶን 6፥12 ይነበብ)። ራሳችንን በሚገባ ለመከላከል እንድንችል መንፈሳዊ የጦር ዕቃችንን እንድንለብስ ታዘናል (ኤፌሶን 6፥13)። የእግዚአብሔርን ኃይል መቋቋም ስለማይችል እኛም የዲያቢሎስ ስንቋቋም ከእኛ ይሸሻል በዚህም ድል እንደምናደርግ ልበ ሙሉዎች ነን (ያዕቆብ 4፥7)።

► ሰይጣን የእግዚአብሔር ተቃራኒ ነውን?

ዲያቢሎስ ያለው ኃይል አሁን ሰዎች በሚሞት ማንነታቸው ውስጥ ካለው ሁሉ በላይ ነው። ነገር ግን አቅሙ ከእግዚአብሔር ጋር ሲስተካተከል ምንም ነው። ከእግዚአብሔር ጋር በኃይል እኩል አንደ ሆነ ያህል የእግዚአብሔር ተቃራኒ ተደርጎ መታየት የለበትም። አንዳንድ ፈላስፎች የመልካም እና ክፉ ኃይላት እኩል ናቸው ብለው ያስባሉ፥ ይህ ግን ከእውነት የራቀ ነው። ሰይጣት በሑሉም ቦታ አይገኝም፥ ሑሉንም ነገር አያውቅም እንዲሁም ስዕተቶችን ይሰራል። እግዚአብሔር መናፍስትን ሁሉ ፈጥሯል፥ እነሱም ሊያሸንፉት አይችሉም። የሰው ልጅ የተወሰነለት ግዜ ሲያበቃ ሑሉም ክፉ መናፍስት ከኃጥያተኛ ሰዎች ጋር ለፍርድ ይቀርባሉ፥ ይታሰራሉ እንደሁም ይቀጣሉ።

የሰይጣት መሸነፍ ለረጅም ግዜ ጀምሮ ቃል የተገባ ነው። እግዚአብሔር አዳኝ በመላክ የእባቡን አናት እንደሚቀጠቅጠው ቃል ገብቶልናል (ዘፍጥረት 3፥15)። እየሱስ የመጣው የሰይጣንን ስራ ለማደምሰስ እና በኃጥያት ላይ ድልን ሊሰጠን ነው (1 ዮሐንስ 3፥8 ይነበብ)። እየሱስ በሞቱ እና በትንሳኤው ሰይጣን በሞት ላይ ኃይል እንዳይኖረው አድርጎታል (ዕብራውያን 2፥14፤ ራእይ 1፥18)። የሰይጣን እና የሌሎች ክፉ መናፍስት መጨረሻ የእሳት ባህር ነው (ማቴዎስ 25፥41 ይነበብ)።

እግዚአብሔር ሰይጣን ሊያደርገው የሚችለው ላይ ገደብ አበጅቶለታል (ኢዮብ 1፥12፣ ኢዮብ 2፥6)። ይህም ማለት ሰይጣን ምን ያደርገኛል በሚል ፍርሃት መኖር የለብንም፥ እግዚአብሔር ካልፈቀደ ምንም አይሆንም፥ እርሱን ልንሸከመው የምንችለውን ምን ያህል እንደሆነ ያውቃል (1 ቆሮንቶስ 10፥13)።

ከሰይጣት ጥቃቶች የተከለልን ብቻ ሳንሆን ነገር ግን የእግዚአብሔርን መንግስት በሰይጣን ግዛት ውስጥ የማስፋት ኃይል አለን። እየሱስ ለሐዋርያት ብቻ ሳይሆን ለደቀ መዛሙርቱ ሁሉ መናፍስትን የማስወጣት ኃይልን ሰጥቷል (ሉቃስ 10፥17 ይነበብ)። ወንጌልን ስንሰብክ እግዚአብሔር ለእውነቱ ብርታትን ይሰጣል እንዲሁም ለወንጌል ምላሽ የሰጡትን ከሰይጣን እስራት ነፃ ያወጣቸዋል።

## ማስወገድ ያለብን ስህተት፥ ስለመንፈሳዊ አለም ያለ የተሳሳተ አይነት ፍላጎት

*ለክፍሉ መሪ ማስታወሻ- የክፍሉ አባል ይህንን ክፍል ማስረዳት ይችላል።*

አንዳንድ ሰዎች ስለመንፈሳዊ አለም በብዙ ይደነቃሉ፥ ስለመላዕክት ማጥናት ይጀምራሉ ፤ ከእነሱም ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ይሞክራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ለመላዕክት እንድንፀልይ ሆነ ከእነሱ ጋር ግንኙነት እንዲኖረን አያስተምረንም። መላዕክትን እንዳናመልካቸው እና ከሚገባን በላይ ስለ እነሱ ለማወቅ እንዳንጥር መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል (ቈላስይስ 2፥18)።

ሰዎች በክፉ መንፈስ ላይ ደግሞ ፍላጎት ሲያሳድሩ የበለጠ አደገኛ ነው። አንዳንድ ሰዎች ባላቸው ኃይል እና በሚያደርጉት ነገር ይደነቃሉ። ከመናፍስት ጋር ለመነጋገር የሚጠቀሙት ጨዋታዎች አሉ፥ እንዲሁም ከመናፍስቱ መረጃን የሚቀበሉበት መንገዶች አሏቸው። እኛ ግን በእግዚአብሔር ኃይል ከመቋቋም ውጪ በምንም መንገድ ከክፉ መናፍስት ጋር ግንኙነት ማድረግ የለብንም (ያዕቆብ 4፥7፣ 1 ጴጥሮስ 5፥8-9)።

አንዳንድ ሰዎች ስለ መናፍስቱ አለም እና እንዴት እንደሚሰራ የተወሳሰብ እና ዝርዝር የሆነ ማብራርያ አላቸው። ነገር ግን እግዚአብሔር ስለ መናፍስቱ አለም ልናውቀው የሚያስፈልገው መገለጥ በሙሉ ሰጥቶናል።

► የእምነት መግለጫውን ቢያንስ ሁለት ግዜ አብራችሁ አንብቡ።

## የእምነት መግለጫ

ሑሉንም መናፍስት የፈጠረው እግዚአብሔር ነው። ቅዱስ መላዕክት እግዚአብሔር የሚያመልኩ እና አማኞችን የሚጠብቁ ናቸው። መላዕክት የማይሞቱ፥ መናገር፥ ማምለክ እና አመክንዮን ማድረግ የሚችሉ ግላዊ ፍጡራን ናቸው። ሞራላዊ የሆነ ውሳኔን ማድረግ የሚችሉ ናቸው። ሰይጣን እና ሌሎች መላዕክት በኃጥያት ወደቁ እንዲሁም ከእግዚአብሔር እና የሰው ልጅ ጠላቶች ሆኑ። እግዚአብሔርም የሰይጣንን አቅም ወስኖታል እንዲሁም ለዘላለም ቅጣት ወስኖታል።

## ትምህርት 6 የቤት ስራዎች

(1) የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የቤት ስራ፡- ከታች ከተዘረዘሩት ዘርፎች መካከል እያንዳንዱን ተማሪ አንድ ይመደብ። ከሚቀጥለው ክፍለ ግዜ በፊት ክፍሉን አንብባችሁ በትምህርቱ ውስጥ ካለው ሃሳብ ላይ ምን እንደሚናገር በአንድ አንቀፅ ፃፉ።

- ማቴዎስ 12፥43-45
- ሉቃስ 8፥27-35
- ሐዋርያት ሥራ 12፥7-11
- 2 ቆሮንቶስ 11፥13-15
- 1 ጴጥሮስ 5፥8-9

(2) ፈተና፡- የሚቀጥለው ክፍለ ግዜ የምትጀምሩት በትምህርት 6 ፈተና ነው። ለፈተና ዝግጅት እንዲሆን የፈተና ጥያቄዎችን አጥኑ።

(3) የማስተማር የቤት ስራ፡- ከክፍል ውጪ የማስተማርያ ግዜን ቀጠሮ መያዝ እና ማስተማራችሁን ሪፖርት ማድረግ አስታውሱ።

## የትምህርት 6 ፈተና

(1) መላዕክት በአብዛኛው ግዜ አካላዊ/ቁሳዊ የሆነ አካል እንደሌላቸው በምንድን ነው የምናውቀው?

(2) መላዕክት መች ተፈጠሩ?

(3) መላዕክት ይሞታሉን?

(4) መላዕክት ስብዕና እንዳላቸው የምናውቅበትን አራት መንገዶች ጥቀሱ?

(5) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መላዕከትን ለመግለጥ የተጠቀማቸው አራት ቃላትን ጥቀሱ።

(6) እግዚአብሔር ለሚያገለግሉ ሰዎች መላዕክት የሚያደርጉት ነገር ምንድን ነው?

(7) የክፉ መናፍስት ምንጭ ምንድን ነው?

(8) ጣኦት አምላኪ በእውን የሚያመልከው ምንድን ነው?

(9) የሰይጣን እና የሌሎች ክፉ መናፍስት የመጨረሻ መገኛ የት ነው?

(10) አማኞች ራሳቸውን ከመንፈሳዉ ጥቃት ለመከላከል ምን ማድረግ አለባቸው?

# ትምህርት 7

# ክርስቶስ

**የትምህርቱ አላማ**

(1) ተማሪው የሚከተሉትን ማስረዳት ይችላል

- እየሱስ መሲህ ነው ማለት ምን ማለት ነው
- "የጌታችን የእየሱስ ክርስቶስ" በሚለው ሀረግ ውስጥ ያለውን የእምነት መግለጫ
- ስለእየሱስ ሰው መሆን ያለው ማስረጃ እና አስፈላጊነት
- ስለእየሱስ መለኮት መሆን ያለው ማስረጃ እና አስፈላጊነት
- የእየሱስ ሞት ለኃጥያት ይቅርታ በቂ መሆን
- ትንሳኤ ለክርስቲያን እምነት ያለው አስፈላጊነት
- ስለ ክርስቶስ ክርስቲያናዊ የእምነት መግለጫ

(2) ተማሪዎች በሌላ እምነት ውስጥ ያሉ ሰዎች ስለ ክርስቶስ ምን እንደሚሉ ይማራሉ።

**መግቢያ**

ራእይ 5፥11-14 አብራችሁ አንብቡ። ይህ ክፍል ስለ እየሱስ ምን ይነግረናል?

**ሀሰተኛ ክርስቶሶች**

መጽሐፍ ቅዱስ ስለመጨረሻዎቹ ቀናት ብዙዎችን የሚያስቱ ሀሰተኛ ክርስቶሶች እና ሀሰተኛ ነብያት እንደሚነሱ ይናገራል። ብዙ ሰዎች ሊያድኑ በማይችሉ ሀሰተኛ ወይም በእውቀትዓቸው የሳሏቸውን ክርስቶሶች ላይ እምነታቸውን ያደርጋሉ። በሞርሞኖች እና በይሖዋ ምስክሮች የሚነገርላቸውን ሑለቱን ሀሰተኛ ክርስቶሶችን ተዋወቋቸው።

**የሞርሞኑ ክርስቶስ**

አንድ ሞርሞን በራችሁን ቢያንኳኳ፥ የሉሲፈር የመንፈስ ወንድም የሆነን እየሱስ ይዞላችሁ ይመጣል። ሞርሞኖች እየሱስ 'መንፈሳዊ አባት' እና 'መንፈሳዊ እናት' ወደ ልዕለ አለሙ ካመጧቸው ብዙ ቢልዬን ከሚቆጠሩ መናፍስት-ዕፃናት መካከል አንዱ ነው ብለው ያስተምራሉ። እየሱስ በምድር ላይ ሲኖር ብዙ ሚስቶች የነበሩት እና ከእነሱ መካከል መቅደላዊት ማርያም አንዷ እንደነበረች ሞርሞኖች ያስተምራሉ። ከሞቱ እና ከትንሳኤው በኃላ እየሱስ ወደ አሜርካ በመሄድ ለቀደምት አሜርካውያን ሰበከላቸው።

**የይሖዋ ምስክሮች ክርስቶስ**

የይሖዋ ምስክሮች እየሱስ ሊቀ-መልዓኩ ሚካኤል ሲሆን ከፍጥረት ሁሉ መጀመርያ የተፈጠረ እና ሰው የሆነ እና በመስቀል ላይ ሳይሆን በእንጨት ላይ የሞተ እንደሆነ ይነግሯችሃል። እየሱስ መንፈስ ሆኖ ተነስቶ ሊቀ መላዕክ ሚካኤልን ሆነ፥ ስጋዊ አካሉ ግን ወደ ጋዝነት ተለወጠ።

**ትክክለኛው እየሱስ**

በእርግጠኝነት እነዚህ የመናፍቃን እምነት ተከታዮች የሚያስተምሩት እየሱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለው እየሱስ የተለየ ነው፤ ነገር ግን ጥያቄው እውነተኛውን፥ የመጽሐፍ ቅዱስን እየሱስን መግለጥ ትችላላችሁ? በሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በአዕምሯቸው ውስጥ ሀሰተኛ የሆነ የክርስቶስ ሃሳብ አላቸው፤ ይህም ክርስቶስ ሊያድናቸው አይችልም።

ስለእየሱስ ያላችሁን እምነት ትክክለኛ መሆኑ አስፈላጊ ነው፤ ይህም እናንተ እንዳትሳሳቱ እና ለሌሎችም እርሱን ማስተዋወቅ እንድትችሉ ነው።

*ለክፍሉ መሪ ማስታወሻ- ሌሎች እምነቶች ስለእየሱስ ስለሚያስተምሩት ትምህርት የበለጠ መረጃ ለማግኘት፤ በዚህ ክፍል መጨረሻ ላይ "ሌሎች ሃይማኖቶች ምን ይላሉ" የሚለውን ክፍል ተመልከቱ።*

**እየሱስ መሲሑ**

► በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ መሲሕ ያሉትን ትንቢቶች ምንድን ናቸው?

አራቱም ወንጌላት እየሱስን እስራኤል የምትጠብቀው መሒህ አድርገው ያቀርባሉ። ስለ መሲሑ ብዙ ትንቢቶች አሉ። የንጉስ ዳዊት ትውልድ ሀረግ ውስጥ ስለሆነ ለንግስና ብቁ ነው። ህዝቡንም ከእስራት እና ቀንበት ነፃ ያወጣቸዋል። ለተላከበት ተልዕኮ እንዲያሳካ በእግዚአብሔር በልዩነት ተቀብቶ የሚላክ ነው። *መሲሕ* ማለት "የቀባኸው" ማለት ሲሆን ይህን የእስራኤል ነገስታት ስም ነው።

አዲስ ኪዳን እስከተፃፈበት ግዜ ድረስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉ ስለ መሲሑ ያሉ አስፈላጊ ዝርዝር መረጃዎች በሚገባ አልተብራሩልንም። ቅድሚያ የሚሰጠው ህዝቡን ከኃጥያታቸው ማዳን ነው። (ማቴዎስ 1፥21፤ ሉቃስ 1፥74-75 ይነበብ)። መንግስቱ ምድራዊ ሳይሆን መንፈሳዉ እና ሰማያዊ ነው (ዮሐንስ 18፥36 ይነበብ)፣ ነገር ግን በመጨረሻ መንግስቱ ምድርን ሁሉ የሚወርስ ነው (ፊልጵስዩስ 2፥10-11፤ ራእይ 19፥11-16፤ ራእይ 20፥6)።

*መሲሕ* የሚለው ቃል የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን፥ የግሪክ አቻ ቃሉ *ክርሲቶስ* ነው፥ ከዚህም ቃል ክርስቶስ የሚለው እናገኛለን። "እየሱስ ክርስቶስ" የሚለውን ሀረግ ስንጠቀም እየሱስ መሲሕ ነው የሚለውን መግለጫ እየሰጠን ነው።

**እየሱስ ጌታ ነው**

የጥንቷ ቤተክርስቲያን *ጌታ* የሚለውን ቃል ሲጠቀሙ እየሱስ ለእርሱ መገዛት ያለብን ሓያሉ ባለስልጣን ነው ማለታቸው ነው። "እየሱስ ጌታ ነው፣" ሲሉ እየሱስ የሁሉም ጌታ፥ ፈታሪ እና የልእለ አለሙ አምላክ ነው ማለታቸው ነው። ይህ የእምነት መግለጫ ክርስቲያኖችን ሌላው የሚለይ ነው፤ ምክንያቱም በምድር ላይ ሰው ሆኖ የተራመደው እየሱስ ራሱ የሑሉም አምላክ እንደሆነ ስለሚያምኑ ነው።

“ጌታ እየሱስ ክርስቶስ” የሚሉት ቃላት ታላቅ የሆነ መግለጫ ነው። እየሱስ መሲሕ እና መለኮት ነው ብለው እያወጁ ነው። ሶስቱም ቃላት በፊልጵስዩስ 2፥10-11 ውስጥ ይገኛሉ። እነዚህ ዘርፎች በምድር ላይ ያለ ሰው ሁሉ እየሱስ ክርስቶስ መሆኑን የሚያውጅበት ግዜ እንደሚመጣ ይነግሩናል።

> “እርሱ ብቻ የአብ ልጅ በሚሆን፣ ዓለም ሳይፈጠር ከአብ በተወለደ፣ ከአምላክ በተገኘ አምላክ፣ ከብርሃን በተገኘ ብርሃን፣ ከእውነተኛ አምላክ በተገኘ እውነተኛ አምላክ፣ በህልውናው ከአብ ጋር አንድ የሆነ፣ በተፈጠረ ሳይሆን በተወለደ፣ ሁሉ በእርሱ በሆነ”
>
> - የኒቅያ ጉባኤ

### ሶስት ልዩ ቀናት

ስለ እየሱስ ያለን መሰረታዊ አስተምሮ በሶስት ምድቦች መከፈል ይችላሉ፤ ሶስቱም ምድቦች ከሶስት ልዩ ቀናት ጋር ይገናኛሉ።

### ልደትን የምናከብረው በተስፅነ ምክንያት ነው

የልደት በኃል የምናከብረው በመንፈስ ቅዱስ የተፀነሰው እና ከድንግል ማርያም መወለዱን በማስመለክት ነው (ሉቃስ 1፥34-35 ይነበብ)። እየሱስ ከሴት በመወለዱ ሰው ሲሆን ነገር ግን ወደ ፈጠረው አለም የገባ መለኮትም ነው። ይህ የሚገርም እውነት ነው፤ እየሱስ ልጅ እያለ እናቱ ማርያም የፈጠራትን እርሱን ይዛዋለች።

*የእግዚአብሔር ልጆች* የሚለው ቃል ለአማንያን ጥቅም ላይ ውሏል (ዮሐንስ 1፥12)፥ ነገር ግን የእየሱስ የእግዚአብሔር ልጅነት በልዩ መንገድ ነው (ዮሐንስ 3፥16)። የአባቱን ማንነት በሙላት ብቻውን የሚጋራው እየሱስ ብቻ ነው። እርሱ የአባቱ መልክ በሙላት ያለበት ሲሆን፥ ልክ እንደ አባቱ መለኮት ነው (ዕብራውያን 1፥2-3 ይነበብ)።

በእየሱስ ህላዌ ውስጥ የመለኮት ማንነት እና የሰው ማንነት አብረው ኖረዋል። ይህም *ተስፅነ* ይባላል፤ ይህም ማለት እግዚአብሔር የሰውን ስጋ በመጨመር ሰው ሆኗል ማለት ነው። እየሱስ ሰው እና መለኮት በመሆኑ እርሱ ብቻ ነው አዳኛችን መሆን የሚችለው።

### እየሱስ ሰው ነው

አዲስ ኪዳን ውስጥ የምንመለከተው እየሱስ ሰው እንደሆነ መገንዘብ ከባድ አይደለም። በእናቱ ማፅጸን ውስጥ የተፀነሰ፥ ያደገ፥ የተመረ፥ እና እንደ ሰው የጎለመሰ ነበር (ሉቃስ 2፥52 ይነበብ)። ደክሞታል፥ ተኝቷል፥ ተፈትኗል፥ ሰዎች ሊያደርጉት የሚችሉትን ከኃጥያት በቀር አድርጓል (ዕብራውያን 4፥14-15)፥ ሞቷልም፤ ሰው በመሆን ራሱን ከእኛ እንደ አንዱ ሆኗል (ዮሐንስ 1፥14 ይነበብ)።

► እየሱስ ሰው መሆኑ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

እየሱስ ሰው ስለሆነ

1. **እንደ መሰዋት መሰቃየት እና መሞት ይችላል** (ኤፌሶን 5፥2፣ ዕብራውያን 7፥26-27)። መለኮት ብቻ ቢሆን እና ሰው ባይሆን ኖሮ በአካል መሰቃየት እና መሞት አይችልም ነበር።

2. **ጽድቁ ሊያጸድቀን እና ሕይወት ሊሰጠን ይችላል** - የመጀመርያው አዳም ኃጥያት ሲሰራ እና ከእግዚአብሔር ጋር ሲለያይ ሰውን ሁሉ ወክሎ ነው፤ ይህም በሰው ልጆች ሁሉ ላይ ሞትን አመጣባቸው። እየሱስ ያለኃጥያት ህይወቱን የኖረ እና የእግዚአብሔርን መስፈርቶች ሑሉ አሟልቷል። የእርሱ ነን ለሚሉ ሑሉ የዘላለምን

ሕይወት ይሰጣቸዋል፥ በመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ የመጨረሻው አዳም የሚል ስም ተሰጥቶታል (1 ቆሮንቶስ 15፥22፣ 45-49፤ ሮሜ 5፥17-19)።

3. **በእግዚአብሔር ዘንድ የሚወክለን ካህናችን ሆኖልናል-** እንደ አማላጃችን ለእኛ ብቻ የሚናገርልን ሳይሆን በእውነት ይወክለናል። በእኛ እና በእግዚአብሔር መካከለኛ ለመሆን ሰው መሆኑ አስፈላጊ ነበር (ዕብራውያን 2፥17 ይነበብ)። የእርሱ የክህነት ሚና የዘላለም ድነትን ይሰጠናል (ዕብራውያን 5፥9፣ ዕብራውያን 10፥5-7)። የእየሱስ ሰውነት የወንጌል አስፈላጊ ነው (1 ዮሐንስ 5፥1 ይነበብ)።

*ለክፍሉ መሪ ማስታወሻ- ስለ እየሱስ ሰውነት የበለጠ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ ለማግኘት "ስለ እየሱስ ሰውነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ" የሚለውን በዚህ ትምህርት ላይ መጨረሻ ላይ ያለውን ክፍል ይመለከቱ።*

**እየሱስ መለኮት ነው**

***እየሱስ መለኮት እንደ ሆነ ተናግሯል***

> "አብ 'እኔ ነኝ' የሚለውን መግለጫ እንደሚጠቀመው፤ ክርስቶስን ይጠቀመዋል፥ ምክንያቱን ግዜ የማይበግረው ብቸኛ ኗሪ ህላዌ እርሱ ብቻ ነው።"
>
> ዩሐንስ አፈወርቅ

የመጽሐፍ ቅዱሱ እየሱስ ሰው ነው፤ ነገር ግን ሰው ብቻ አይደለም። እርሱ ወሰን የሌለው የልዕለ አለሙ አምላክ ጭምር ነው። እየሱስ ራሱ ይህንን እውነት ስለራሱ ተናግሯል። "እኔና አብ አንድ ነን" (ዮሐንስ 10፥30) ብሏል። ይህንን በመናገሩም አይሁዳውያን በድንጋይ ሊወግሩት ጀመሩ፤ ምክንያቱን ይህንእ በማለቱ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል እያደረገ መሆኑን ስለተገነዘቡ ነው። እየሱስ ይህንን ሲሆን 'አይ፥ አልተረዳችሁኝም፥ እኔበእውነት እግዚአብሔር ነኝ አላልኩኝም" አላለም፤ ነገር ግን ቃላቱን የተረጎሙበትን መንገድ ተቀብሎታል። ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩል እንደሆነ አስተምሯል።

እየሱስ "አብርሃም ከመወለዱ በፊት እኔ፣ እኔ ነኝ፣" (ዮሐንስ 8፥58) ሲል በዘፀአት 3፥14 ላይ ራሱን እኔ ነኝ ብሎ የተገለጠውን ራሱን ችሎ ያለውን የልዕለ አለሙን አምላክ ነኝ እያለ ነው። አይሁዳውያኑም ይህን ስለ ራሱ ስላለ ነው ሊወግሩት የሞከሩት (ዮሐንስ 8፥59)።

***እየሱስ በምድር ላይ መለኮታዉ ተግባራትን ከውኗል***

እየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ግዜ መለኮታዊ የሆኑ ተግባራትን አድርጓል። የዘላለም ህይወት ሰጥቷል (ዮሐንስ 10፥28 ይነበብ)። ለኃጥያት ምህረትን አድርጓል (ማርቆስ 2፥10)። እግዚአብሔር ብቻ ማድረግ የሚችላቸው ነገሮች አሉ።

የእየሱስ የሽባውን ኃጥያት ሲምረው አብሮ በሽታውን በመማር በምድር ላይ ኀጢአትን ለማስተስረይ ሥልጣን (ማርቆስ 2፥5፣ 10-12) ስልጣን እንዳለው አስመስክሯል። ተግባራቱ እንዳቸው ለሌላው ምስክር በመሆን እየሱስ ተአምራቶቹን የከወናቸው እንደ አንድ በእግዚአብሔር እንደተቀባ ነብይ ብቻ እንዳለሆነ ምስክር ናቸው። እየሱስ ኃጥያትን ለመማር እና በሽታን ለመፈወስ መለኮታዊ ስልጣን እና ኃይል አለው።

እየሱስ “ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ” (ዮሐንስ 11፥25) ብሎ ከተናገረ በኃላ አላዛርን ከሞት አስነስቶታል። ይህም መለኮታዊ ስራ መለኮታዊ የሆነ ንግግር ጋር አብሮ የተሰራ ነው። እግዚአብሔር ብቻ ነው ትንሳኤ ነኝ ብሎ መናገር የሚችለው ይህም ማንንም ከሞት ማስነሳት የሚችል ኃይል ያለው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ነው። እየሱስ ስለራሱ ሕይወት ሰጭነቱ ከተናገረ በሓላ ለአላዛር ሕይወቱን ሰጥቶታል፤ ይህም ስልራሱ የሚናገረው እውነት መሆኑን አሳይቷል። እነዚህ ሁነቶች እየሱስ ሰዎችን በእግዚአብሔር ሀይል ከሞት ካስነሱ ከሌሎች ነብያት እና ሐዋርያት ራሱን የለየበት መንገድ ነው። ከእነዚህ መካከል ማናቸውም በራሳቸው ተአምራቱን ለማድረግ ኃይል እንዳላቸው አልተናገሩም፤ የእግዚአብሔር መጠቀሚያ እቃዎች ብቻ ነበሩ። በዮሐንስ 5፥21 ላይ እየሱስ አባቱ ከሞት እንደሚያስነሳ እርሱን እንደዚያው ሕይወትን እንደሚሰጥ ተናግሯል።

እየሱስ ተእምራቱን ባደረገ ግዜ ክብሩንም ገልጧል (ዮሐንስ 2፥11) ይህን ክብር ልጅ ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር ነው፥ ጸጋ እና እውነት የተሞላ ነው (ዮሐንስ 1፥14)። እነዚህ ተአምራቶች የእግዚአብሔር ልጅ ታላቅ ክብር መገለጫ ናቸው፥ ይህም መለኮትነቱን ያመላክታል።

### *እየሱስ ፈጣሪ እና ጠባቂ ነው*

እንደ ሐዋርያቱ ጳውሎስ እና ዩሐንስ መሰረት እየሱስ ሑሉን የፈጠረ እና ሑሉን የሚይዝ እንዲሁም ሑሉም ለእርሱ የሆነ ነው (ዮሐንስ 1፥3፤ ቈላስይስ 1፥17 ይነበብ)። በእርግጥም ይህ ለእግዚአብሔር ብቻ ካልሆነ ለማንም ሊባል አይቻልም።

► እየሱስ መለኮት መሆኑን ማወቅ የሚያስፈልገን ለምንድን ነው?

ምክንያቱን እየሱስ አምላክ ስለሆነ-

1. የመስዋትነት ሞቱ ዋጋ እጅግ ታላቅ እና የማይቆጠር ነው- ለአለም ኃጥያት ሑሉ ምህረትን ማድረግ የሚችል ነው (1 ዮሐንስ 2፥2)።
2. እኛን ለማዳን ኃይል አለው፤ መንገድ፥ እውነት እና ሕይወት ነው (ዮሐንስ 14፥6)።
3. አባትን እንደምናመልከው እርሱን ማምለክ አለብን (ዮሐንስ 5፥23 ይነበብ)።

እየሱስን እንደ መለኮት እግዚአብሔር መመልከት ካልቻልን፤ እንደ እግዚአብሔር አናከብረውም። እግዚአብሔር አብ እና ወልድ በሚገባ ካላከበርናቸው ድነትን ማግኘት አንችልም።

ክርስትና የሚመሰረተው በእየሱስ አስተምሮ እና ተግባር ላይ ብቻ ሳይሆን ልዩ በሆነው የእየሱስ ማንነት ላይ ነው። እየሱስ የድነት መልዕክት አስተማሪ ብቻ ሳይሆን እርሱ ራሱ አዳኝ ነው፥ እርሱ ሰው የሆነው መለኮት- ብቻ ነው አዳኝ መሆን የሚችለው።

*ለክፍሉ መሪ ማስታወሻ- ስለ እየሱስ መለኮትነት የበለጠ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ ለማግኘት “ስለ እየሱስ መለኮትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ” የሚለውን በዚህ ትምህርት ላይ መጨረሻ ላይ ያለውን ክፍል ይመለከቱ።*

### እየሱስ አንድ ህላዌ ነው

እየሱስ ፍጹም የሆነ ሰው እና ፍጹም የሆነ አምላክ ቢሆንም ግን ሑለት ሕላዌ ተጣምሮ አይደለም። ሑለቱ ማንነቶች በፍጹም መስማማት አንድን ሕላዌ ይፈጥራሉ። እየሱስ አንድ መለኮት-ሰው ነው፥ የሰራቸውን ተግባራት ሁሉ በፍጹም ሰውነቱ እና መለኮትነቱ መታየት አለበት። ቤተክርስቲያን በዘመናት ውስጥ የእየሱስ ሑለት ማንነቶች አንዳቸው ከሌላቸው እንደማይለያዩ ታስተምራለች፥ እነዚህ ማንነቶች አንዱ የሌላውን ባህሪ በሚያጠለሽ መልኩ በፍጹም አይደባለቁም። [17]

የእየሱስን ማንነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንነት ጋር ማወዳደር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፤ እንደ እየሱስ መጽሐፍ ቅዱስ ፍጹም መለኮታዊ እና ፍጹም ሰዋዊ ነው። የሰው መጽሐፍ ስለሆነ፤ ሌሎች በሰው የተጻፈ መጽሐፎች ባህሪያት አሉት ነገር ግን ከሌሎች የሚለየው ግን ምንም አይነት ስዕተት ስለሌለበት ነው። መለኮታዊ ስለሆነ ደግሞ ሌላ ምንም መጽሐፍ ሊያሳየው የማይችለውን ባህሪ ማሳየት ይችላል። በተመሳሳይ መንገድም፤ እየሱስም መለኮታዊ እና ሰዋዊ ባህሪያትን ያሳያል። መጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ ባህሪ ማሳየቱ በሰው የሆነ መጽሐፍ መሆንን አይቀንስበትም። እንዲሁም እየሱስ መለኮታዊ በሆነ መንገድ መስራቱ በምንም ሰውነቱን አይቀንሰውም። እንዲሁም እየሱስ በሰውነቱ መስራቱ በምንም መለኮታዊነቱን አይቀንሰውም።

### የተለመዱ የአስተምሮ ስህተቶች

ሰዎች ስለ ክርስቶስ ሲናገሩ የሚፈጽሟቸው ተደጋጋሚ ስዕተቶች መካከል በጣም የተለመዱት

- እየሱስ መለኮት መሆኑን መካድ
- እየሱስ ሰው መሆኑን መካድ
- መለኮቱን ወይም ሰውነቱን እንደአላስፈላጊ በመቁጠር ማሳነስ
- የክርስቶስን አካልነት አንድነት መካድ

ከእነዚህ መካከል የትኛውም ስዕተት የክርስቶስን ስጋ መልበስ መካድ ነው። የክርስቶስ ስጋን መልበስ ለድነት አስፈላጊ ነው፤ ስለዚህ ሰው የክርስቶስ ስጋ መልበስ የካደ ሰው በተሳሳተ ወንጌል የሚያምን እና በተሳሳተ የድነት መንገድ የሚሄድ ነው።

### ሌሎች ሃይማኖቶች ምን ይላሉ

*ለክፍሉ መሪ ማስታወሻ- የክፍሉ አባል ይህንን ክፍል ማስረዳት ይችላል።*

የይሖዋ ምስክሮች እየሱስ ሰው ነው ይላሉ፤ በምድር ላይ ከኖሩት ሰዎች ሁሉ የተበለጠ ግን ሰው ብቻ እንደሆነ ያምናሉ። በዚህ ምክንያትን ነው ሞቱ ለድነት በቂ የሆነ መስዋትን እንዳልሆነ የሚያምኑት። መዳን በስራ እንደሆነ በሚያስተምር ወንጌል ያምናሉ፤ ክርስቲያን እንደሆኑ ቢናገሩም ነገር ግን የተለየ ሀይማኖት ነው ያላቸው።

---

[17] በትምህርት 15 ውስጥ የተካተተው የኬልቄዶን የሃይማኖት መግለጫ (451 ዓ.ም)፤ ሁለቱ የክርስቶስ ባሕርያት የማይለወጡ፣ የማይከፈሉ፣ የማይለያዩ እና የማይቀላቀሉ እንደሆኑ ይናገራል።

ሞርሞኖች እየሱስ በእግዚአብሔር በመጀመርያ የተፈጠረ መንፈስ እንደሆነ ያምናሉ፥ ለሉሲፈርም ወንድም እንደሆነ ያህል። ወደ ምድር እየሱስ የተባለ ሰው ሆኖ እንዲወለድ የተላከ መሆኑን እና እየሱስ መለኮት እንዳልሆነ ያምናሉ።

ሙስሊሞች እየሱስ በአምላክ የተላከ ነብይ እንደሆነ ያምናሉ፤ መለኮት እንዳልሆነ እንዲሁም ሥላሴ የሚባል ነገር እንደሌለ ያምናሉ። እንደተሰቀለም ሆነ ከሞት እንደተነሳ አያምኑም።

የሒንዱ እና የቡዲዝም አማንያን እየሱስ ተአምራትን ያደረገ ቅዱስ ሰው እንደሆነ ያምናሉ፤ ለሀይማኖታቸው ግን አስፈላጊ ነው ብለው አያምኑም። ፈጣሪ እና ጌታ በሆነ መለኮት አያምኑም ስለዚህ እየሱስ ስጋን የለበሰ መለኮት እንደሆነ አያምኑም።

## ስቅለት አርብ የምናከብረው በስርየት ምክንያት ነው

የስቅለት አርብ ቀን እየሱስ የተሰቀለበት ቀን ነው፤ በዚህ ክፉ እና አስደናቂ ቀን ላይ ኃጥያታችንን በመስቀል ላይ ተሸከመ። በመስቀል ላይ ለኃጥያታችን የሞተልን ምህረትን እንድናገኝ ነው።

### መስዕዋት አስፈላጊ ነው

ቅዱስ እና ጻድቅ የሆነ እግዚአብሔር ለኃጥያታችን ምህረትን የሚያደርግልን መስዕዋት ሲከፈል ነው። ይህ መርህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር በፈለገው መስዋት ውስጥ የተደነገገ ነው (ዕብራውያን 9፥22)። እግዚአብሔር ኃጥያትን ያለምንም መሰረት ዝም ብሎ ምህረትን ቢያደርግ ጻድቅ እንዳልሆነ እና ኃጥያትም ያን ያህል ከቁም ነገር የሚቆጠር አይሆንም። ነገር ግን ማንም የክርስቶስን በመስቀል ላይ የሞተውን ተመልክቶ የኃጥያትን ቀላል ማድረግ አይችልም፤ መስዋትነቱ ለይቅርታችን መሰረት ይሰጠናል።

### እየሱስ ብቻ ነው በቂ መስዋዕት መሆን የሚችለው

► ለምንድን ነው ለኃጥያታችን መስዕዋት መሆን የሚችለው እየሱስ ብቻ የሆነው?

የእግዚአብሔር ጽድቅ እና የኃጥያት ትልቅ ችግርነት ከእርሱ የበለጠ ለፍጥረት ሐሉ በላይ የላቀ መስዋዕትን ይፈልጋል (ዕብራውያን 10፥4 ይነበብ)። ታላቅ እና ወሰን የሌለውን አምላክ በድለናል፥ በዚህም ምክንያት ጥፋተኝነታችን ታላቅ እና ወሰን የለሽ ነው ሰስለዚህ ምክንያት መስዕዋት መሆን የሚችለው እየሱስ ብቻ ነው። እርሱ ፍፁም ሰው እና ፍፁም አምላክ ስለሆነ እርሱ ብቻ ነው ለመስዋዕትነት በቂ መሆን የሚችለው። መለኮት ስለሆነ ኃጥያት አልባ ስለሆነ የመስዋትነቱን ዋጋ ማለቂያ እና ማብቂያ የሌለው ነው። በሰውነቱ ምክንያት ደግሞ ሑላችንንም መወከል እና በእኛ ቦታ መተኛት ይችላል።

### የእየሱስ ደም መስዋትነት ያለውን ሞቱን ይወክልናል

እግዚአብሔር ለሰዎች መስዕዋት የሚለውን ስርዓት በመስጠት ስለስርየት አስተምሮናል። ካህኑ እንስሳቱን በመግደል እና ደማቸውን በማቅረብ ሞታቸውን ወክሏል። የዕብራውያን መጽሐፍ ደም ሳይፈስስ ስርየት የለምና (ዕብራውያን 9፥18-22) የለም ይላል።

እግዚአብሔር ህዝቡን ህይወት የሚገኘው በደም ውስጥ እንደሆነ በማስተማር ደምን በተለየ መንገድ እንዲመለከቱት አዟል (ዘሌዋውያን 17፥11፣ 14)። ደም ማስፍሰስ ማለት መግደል ማለት ነው (ዘፍጥረት 9፥5-6)። በቤተ መቅደስ ውስጥ ደም ጥቅም ላይ ውሏል ማለት አንድ እንስሳ ሞቷል ማለት ነው።

የክርስቶስ ሞት የመጨረሻው መስዕዋት በመሆን ድነትን በግዜ ውስጥ ላሉ ሰዎች በሙሉ እንዲገኝ አስችሏል (ዕብራውያን 10፥4፣ 12 ይነበብ። ) ደሙን በመንግስተ ሰማይ መስዋዕት የሆነ ሞቱን በመወከል አቅርቧል (ዕብራውያን 9፥12፣ 24 ይባላል)። እየሱስ የሞተው መስዕዋት ሆነ እኛን ሊያድነን ስለሆነ የእየሱስ ደም ሞቱን በመወለክ ድነትን ይሰጠናል።

እየሱስ በመስቀል ላይ መሞት ያስፈለገው ለምንድን ነው፥ ለምን በሌላ አይነት ሞት አልሞተም። በብሉይ ኪዳን መሰረት በእንጨት ላይ ተሰቅሎ የሚሞት ሑሉ የተረገመ ይሁን ይላል (ዘዳግም 21፥23)። ሐዋርያው ጳውሎስም እየሱስ በእንጨት ላይ በመሰቀል ከእግዚአብሔር የሆነውን እርግማን በራሱ ላይ እንደወሰደ ጽፎልናል (ገላትያ 3፥13)።

**እየሱስ ሰውን እና እግዚአብሔር አስታርቋል**

እየሱስ ሑለት የተለያዩ አካላትን አስታርቋል- እግዚአብሔርን እና ሰውን። እንደ መካከለኛ- ሑለቱንም በሚገባ በተመሳሳይ ሰዓት ወክሎናል። እንደ መለኮት፥ እግዚአብሔርን በሰዎች መካከል አድሯል። ሰው በመሆን፥ ሰዎችን ለእግዚአብሔር ወክሏል። ሑለቱንም በፍፁም በመወከል እየሱስ እግዚአብሔር እና ሰዎችን ማስታረቅ ችሏል። ዕርቅን ለማምጣት እንዲቻል በሑለቱን አካላት መደረግ ያለበትን ሑሉ አድርጓል።

## ፋሲካን/ትንሳኤን የምናከብረው ክርስቶስ ከሞት ስለተነሳ ነው

ሰዎች መካከል ፋሲካን/ትንሳኤን የሚያከብሩበት የተለያየ አይነት ባህል እና ወግ አላቸው ነገር ግን ብዙዎች ግን የሚያደርጉትን ተግባራት ትርጉም ሆነ የክርስቶስን ትንሳኤ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ሳይረዱ ነው የሚያደጓቸው። እየሱስ ከሞተ በሶስተኛው ቀን በትንሳኤ ማለዳ ከመቃብር ተነሳ ይህንን በማድረጎ በኃጥያት፥ በሞት እና በሰይጣን ላይ ኃይል እንዳለው አሳይቷል። ሞታችንን ብቻ ሳይሆን የወሰደው ነገር ግን ህይወትን በመስጠት ድል ነስቷል። እርሱ ድል ስለነሳ እኛም ድል እንነሳለን።

**እየሱስ በአካል ተነስቷል**

እየሱስ ለአይሁዳውያን “ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፤ እኔም በሦስት ቀን መልሼ አነሣዋለሁ። ” ብሏቸዋል። አይሁዳውያን ሔሮድስ ስለገነባው ቤተ-መቅደስ የሚያወራ መስሏቸው ነበር የዩሐንስ ወንጌል ግን እየሱስ ስለ ራሱ አካል እንደሚያውራ ያስረዳናል (ዮሐንስ 2፥19-21)። ሑሉም ወንጌላት እየሱስ የተቀበረበት መቃብር በሶስተኛው ቀን ባዶ እንደነበር ጽፈውለናል። “ደግሞም ንኩኝና እዩ፤ በእኔ እንደምታዩት መንፈስ ሥጋና ዐጥንት የለውምና” (ሉቃስ 24፥39) በማለት ከትንሳኤ በኃላ ራሱን ለደቀ መዛሙርቱ አሳይቷል። ይህም በማለቱ በአካል ከሞት መነሳቱን ለማሳየት እና ማረጋገጥ ነው።

► እየሱስ ከሞት ባይነሳ ምን ልዩነት ይመጣል?

1. **የእየሱስ አካላዊ ትንሳኤ በኃጥያት እና ሞት ላይ የክርስቶስን ድል የሚያሳይ ነው** (ቈላስይስ 2፥12-15፤ ራእይ 1፥17-18 ይነበብ)።

2. **እየሱስ በአካል መነሳቱ ስለራሱ ማንነት የነገረን እውነተኛ እንደሆነ ማስረጃ ነው** (ማቴዎስ 17፥22-23፣ ዮሐንስ 2፥16-22) ይህም ወንጌል እውነት መሆኑንም ያሳየናል፤ እየሱስ ከሞት እንደተነሳ የሚክዱ ሰዎች ወንጌልንም ይክዳሉ (1 ቆሮንቶስ 15፥17 ይነበብ)።

3. **የእየሱስ በአካል ከሞት መነሳት እኛም ከሞት እንደምንነሳ የሚያስረግጥልን ነው።** እየሱስ ለሞቱን ትንሳኤን እንደሚሰጥ ቃል ገብቶልናል። ይህንን ቃል የምናምነው እርሱ ራሱ ከሞት ስለተነሳ ነው (ዮሐንስ 5፥28-29)። በትንሳኤ እንደእየሱስ ባለ የከበረ አካል እንነሳለን (1 ዮሐንስ 3፥2 ይነበብ)።

**እየሱስ አሁንም ሰው ነው**

የእየሱስ ትንሳኤ ሰው መሆኑ ፍጹም እና ዘላቂ እንደሆነ ማሳያ ነው። እየሱስ ለዘላለም ፍጹም መለኮት እና ሰው ነው። እየሱስ፥ መለኮት የሆነው ሰው ስለእኛ በአባቱ ፊት ሁልግዜ ይማልድልናል (ሮሜ 8፥34) እንደሁም አንድ ቀን ተመልሶ መጥተ ወደ መንግስተ ሰማያት ይወስደናል (1 ተሰሎንቄ 4፥16-17)።

**ለእየሱስ የምንገዛለት ስለማንነቱ እና ስለሰራው ስራ ነው**

እንደአማኞች ከክርስቶስ ጋር ዕለታዊ ግንኙነት ያላቸው ናቸው። በታሪክ ውስጥ የነበረ ሰው ሆነ በሰማይ ያለ አምላክ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ከሑላችንም ጋር አለ። ለደቀ መዛሙርቱ ሁል ግዜ አብሯቸው እንደሚሆን ቃል ገብቶላቸዋል (ማቴዎስ 28፥20)።

በቤተክርስቲያንም ውስጥ ልዩ በሆነ መንገድ አብሮነቱ አለ፤ የቤተክርስቲያን ራስ ነው እና ቤተ-ክርስቲያኑን አካሉ እንሆነች ተናግሯል (ኤፌሶን 1፥22-23)። ቤተክርስቲያንን ይመራል፥ አንድ አድርጎ ይጠብቃል፥ እንዷሂም የሚያስፈልጋትን ያደርግላታል (ቈላስይስ 2፥19 ይነበብ)።

ስለእየሱስ ያለውን እውነት በትክክል የተቀበለ ሰው ምላሹ እምነት እና መታዘዝ መሆን አለበት። ሌሎችም ይህንን እውነት እንዲያምኑ እንደሚከተለው በመጸለይ መርዳት ትችላላችሁ

> አባት ሆይ፥ ስለወደድከኝ እና ልጅህ እየሱስን ወደ አለም ለእኔ ስትል ስለላክኽልኝ አመሰግናለሁ። እየሱስ ኃጥያት የሌለበት መለኮት እና ሰው እንደሆነ፥ እንደሞት እና እንደተነሳ በዚህም ለኃጥያቴ ይቅታን እና ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅን አግኝቻለሁ። ስለሰራሁት ኃጥያት ሁሉ ይቅር በለኝ፥ ኃጥያቴ እየሱስን በመሰቀል ላይ እንደቸነከረው አውቃለው። በአሁኑ ሰዓት ይህ ስዕተት እንደሆነ አውቃለው ስለዚህም ከዚህ ራሴን እመልሳለው፤ እየሱስንም እንደ ጌታዬ እና መድኃኔቴ አድርጌ እቀበላለው። ከዚህ ቀን ጀምረህ ምራን፥ ለአንተ ለዘላለም እኖራው! ስለማርከኝ አመሰግናለሁ፤ እወድሃለሁ፥ አሜን።

► የእምነት መግለጫውን ቢያንስ ሁለት ግዜ አብራችሁ አንብቡ።

### የእምነት መግለጫ

እየሱስ የሑሉም መሲህ እና ጌታ ነው፥ ከድንግል የተወለደው የእግዚአብሔር ልጅ ሰዋዊ እና ለመለኮታዊ የሆኑት ሁሉ ስብዕናዎች በአንድ አካል ውስጥ አሉት። ከኃጥያት የነፃን ህይወት ኖሮ፥ እንደ መስዕዋት በመሞቱ ለኃጥያታችን ይቅርታን አገኘን። እርሱ ከሞት ተነስቷል፥ በመመለሱም ሑሉንም አማኞች ከሞት ያስነሳቸዋል። መንግስቱ ልዕለአለማዊ እና ማለቂያ የሌለው ነው።

### ስለ እየሱስ ሰውነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ

*ለክፍሉ መሪ ማስታወሻ- ይህም ክፍል እና የሚቀጥለውን መጠቀም ምርጫችሁ ነው። ተማሪዎች የበለጠ መጽሐፍ ቅዱሳዉ ማስረጃ ካስፈለጋቸው ብቻ ይህንን መሸፈል ይቻላል።*

እየሱስ የሔዋን ልጅ ነው (ዘፍጥረት 3፥15)፥ የአብረሃም ዘር (ዘፍጥረት 22፥18 ከ ሐዋርያት ሥራ 3፥25 ጋር በማነጻጸር ተመልከቱ)፥ ከሴት የተወለደ (ገላትያ 4፥4)፣ ከማርያር የተወለደ (ማቴዎስ 1፥21-25)፥ የሰው ልጅ የተባለ (ማቴዎስ 13፥37)፥ እንዲሁም እንደማንናውም ሰው በዕድገት ውስጥ ያለፈ ነው (ሉቃስ 2፥40፣ 52)።

የዕድገቱ ሁናቴ ከሌሎች የተለየ እንዳልነበረ ወደ ተወለደበት እና አደገበት አካባቢ ለመጎብኘት ሲመጣ፥ የአካባቢው ሰዎች የነበራቸው ምላሽን በመመልከት ማስተዋል እንችላለን (ማቴዎስ 13፥54-56)።

እንደ ሰው እንዲታዘዝ የሰውን አካል ነበረው (ዕብራውያን 10፥5-9)፤ ስጋ እና ደም ለበሰ (ዕብራውያን 2፥14)፤ እንደእኛ መሰቃየት እንዲችል እንደኛው ሰው ሆነ (ዕብራውያን 2፥10-18)፤ በመከራ ውስጥ ፍጹም ሆነ (ዕብራውያን 2፥9-10)፤ እንደሰውም ተፈትኗል (ዕብራውያን 4፥15)።

በሰው አምሳል ተገኝቷል (ፊልጵስዩስ 2፥6-8)።

አላለማዊ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ሲሆን በምድር ላይ ለመኖር ስጋ ለብሷል (ዮሐንስ 1፥14)።

ስለእየሱስ ሰው መሆን ያለው የእምነት መግለጫ ለክርስትና እምነት አስፈላጊ ነው (ዮሐንስ 1፥14፤ 1 ዮሐንስ 4፥2-3)።

### ስለእየሱስ መለኮትነት መጽሐፍ ቅዱሳዉ ማስረጃ

እየሱስ መለኮትነት በሶስት መንገድ ማስረጃን መስጠት እንችላለን

1. እግዚአብሔር ተብሎ ተጠርቷል።
2. መለኮታዊ ባህሪያት እንዳሉት ታይቷል።
3. የእግዚአብሔርን አይነት ሚና ሲጫወት ይታያል።

**እየሱስ አምላክ ተብሏል**

- ዮሐንስ 1፥1፣ 14 - ከዘላለም የነበረው ቃል እግዚአብሔር እንደሆነ ይናገራል።

- ዮሐንስ 12፥41 ኢሳዕያስ እየሱስን እንዳየው ይነግረናል።
- ሐዋርያት ሥራ 20፥28 - የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን በእርሱ ደም እንደተገዛች ይነግረናል።
- ሮሜ 9፥5 - ክርስቶስ፥ ለዘላለም የተባረከው እግዚአብሔር እንደመጣ ይናገራል።
- ቲቶ 2፥13 - የአምላካችንና የአዳኛችንን የእየሱስ ክርስቶስን ብሎ ይጠራዋል።
- ማቴዎስ 1፥23 (ኢሳይያስ 7፥14 በመጥቀስ) ስሙ "እግዚአብሔር ከእኛ ጋራ" ማለት እንደሆነ ይነገረናል።
- ኢሳይያስ 9፥6 ስሙ ኀያል አምላክ ተብሎ እንደሚጠራ ይነግረናል።
- 1 ጢሞቴዎስ 3፥16 እግዚአብሔር በስጋ እንደተገለጠ፥ በአህዛብ መካከል እንደተሰበከ እና ክብር እንዳረገ ይነግረናል።
- በዮሐንስ 10፥30፣ 33 እየሱስ ከአባቱ ጋር አንድ እንደሆነ ተናግሯል።
- በዮሐንስ 5፥17-18፣ ላይ አይሁዳውያን እየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ነኝ እንዳለ ተረግተዋል።
- በዮሐንስ 14፥9 ላይ "እኔን ያየ አብን አይቷል" ብሏል።
- በዮሐንስ 20፥28-29 ውስጥ ቶማስ የእየሱስን ቁስል ተመልክቶ "ጌታዬ፤ አምላኬም፣" ሲል እየሱስም የሚያምኑ ብጹዓን ናቸው ብሏል።
- በዮሐንስ 8፥58 ላይ ራሱን እኔ ነኝ ብሏል፤ አይሁዳውያኑም ይህን ማለቱ እግዚአብሔር ነኝ ማለቱ እንደሆነ ተረድተዋል።
- በራእይ 1፥17፣ ራእይ 2፥8፣ እና ራእይ 22፥13 ውስጥ መጀመርያ እና መጨረሻ እንደሆነ ተናግሯል፤ በኢሳይያስ 44፥6 ውስጥ ይህ ስም ለእግዚአብሔር የተነገረ እንደሆነ እንመለከታለን።
- ዕብራውያን 1፥2-3 እየሱስ ፍጹም የሆነ የእግዚአብሔር መልክ እንደሆነ ይናገራል።
- ዕብራውያን 1፥8 ላይ እግዚአብሔር ተብሎ ተጠርቷል።

**እየሱስ የእግዚአብሔር ባህሪያት አሉት**

**በሁሉም ቦታ ይገኛል** - በማቴዎስ 18፥20 ላይ ሑለት እና ሶስት አማኞች በሚሰበሰቡበት በዚያ እንደሚገኝ ተናግሯል። በማቴዎስ 28፥20፣ ከአማኞች ጋር እስከአለም ፍጻሜ ድረስ አብሮ እንደሚሆን ቃል ገብቶላቸዋል።

**ሁሉን ቻይ** - ዕብራውያን 1፥3 አለሙን በስልጣኑ ቃል እየደገፈ እንደሚይዝ ይናገራል። ፊልጵስዩስ 3፥21 ደግሞ ሑሉን ከእርሱ በታች እንደሚያስገዛ ይናገራል።

**ዘላለማዊ** - ዕብራውያን 13፥8 በዘላለም ውስጥ እርሱ የማይለዋወጥ እንደሆነ ይናገራል፤ ዕብራውያን 1፥12 ደግሞ ለዘላለም የማይለዋወጥ መሆኑን ይነግረናል ይህም መዝሙር 102፥25-27 ስለ እግዚአብሔር የሚናገረውን በመጥቀስ ነው።

**ሁሉን አዋቂ ነው-** ዮሐንስ 2፥24-25 ላይ ሑሉንም ሰው የሚያውቅ እና በልባቸው ያለውን ሑሉ የሚያውቅ እንደሆነ ተናግሯል። ዮሐንስ 10፥15 ውስጥ ደግሞ እርሱ አባቱን እንደሚያውቀው እንዲሁ አባቱም እርሱን እንደሚያውቀው ተናግሯል።

**እየሱስ የመለኮትን ሚና ይጫወታል**

- እየሱስ ፈጣሪ ነው (ቈላስይስ 1፥16፤ ዕብራውያን 1፥10)።
- እየሱስ ኃጥያትን ይምራል (ሉቃስ 5፥20-24፣ ሉቃስ 7፥48)
- እየሱስ በታላቁ ፍርድ ግዜ ዳኛ ሆኖ ይፈርዳል (ማቴዎስ 25፥31-46፤ 2 ቆሮንቶስ 5፥10)
- እየሱስ እንደ አባቱ ይመለካል (ዮሐንስ 5፥22-23፤ ዕብራውያን 1፥6፤ ራእይ 5፥12-13)።

## ትምህርት 7 የቤት ስራዎች

(1) የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የቤት ስራ፡- ከታች ከተዘረዘሩት ዘርፎች መካከል እያንዳንዱን ተማሪ አንድ ይመደብ። ከሚቀጥለው ክፍለ ግዜ በፊት ክፍሉን አንብባችሁ በትምህርቱ ውስጥ ካለው ሃሳብ ላይ ምን እንደሚናገር በአንድ አንቀፅ ፃፉ።

- ማርቆስ 1፥1-12
- ዮሐንስ 5፥19-26
- ዮሐንስ 6፥44-51
- ዮሐንስ 8፥51-59
- ሐዋርያት ሥራ 2፥22-36
- ራእይ 1፥12-18

(2) ፈተና፡- የሚቀጥለው ክፍለ ግዜ የምትጀምሩት በትምህርት 7 ፈተና ነው። ለፈተና ዝግጅት እንዲሆን የፈተና ጥያቄዎችን አጥኑ።

(3) የማስተማር የቤት ስራ፡- ከክፍል ውጪ የማስተማርያ ግዜን ቀጠሮ መያዝ እና ማስተማራችሁን ሪፖርት ማድረግ አስታውሱ።

## የትምህርት 7 ፈተና

(1) የመሲሑ ዋና ትኩረት ምን ነበር?

(2) የጥንቷ ቤተ-ክርስቲያን 'እየሱስ ጌታ ነው' ስትል ምን ማለቷ ነው?

(3) የእየሱስ ልጅነት ልዩ የሆነው እንዴት ነው?

(4) ተስዕጎ ማለት ምን ማለት?

(5) እየሱስ ሰው መሆን ያስፈለገበትን ሦስት ምክንያቶች ዘርዝሩ።

(6) እየሱስ መለኮት መሆኑን ማወቅ ያለብን ሦስት ዋና ምክንያቶችን ዘርዝሩ።

(7) መስዕዋት ያስፈለገበት ሑለት ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

(8) እየሱስ በሌላ መንገድ ሳይሆን በመስቀል ላይ ለምን መሞት አስፈለገው?

(9) እየሱስ አካላዊ የሖነ ትንሳኤ አስፈላጊ ለመሆኑ ሦስት ምክንያቶችን ዘርዝሩ።

# ትምህርት 8

# ድነት

## የትምህርቱ አላማ

(1) ተማሪው የሚከተሉትን ማስረዳት ይችላል

- ብዙዎች በመስቀሉ ለምን እንደሚበሳጩ
- የኃጥያተኛው ያለበት ሁናቴ
- ስርየት ለይቅርታ ያለው አስፈላጊነት
- የንሰሓ ትርጉም
- ደሕንነት ያለበት እምነት ክፍሎች
- ስርየት ለሑሉም ሰዎች እና ላለው ኃጥያት ሁሉ በቂ መሆኑ
- ለግላዊ ድነት እርግጠኝነት ያለው መሰረት
- የፍጥረት ሁሉ ድነት
- ስለ ድነት ክርስቲያናዊ የእምነት መግለጫ.

(2)ተማሪዎች ከንሰሓ ውጪ የሆነ ኃይማኖት ስዕተትን ይረዳሉ።

## መግቢያ

► መዝሙር 85 አብራችሁ አንብቡ። ይህ ክፍል ስለ ድነት ምን ይነግረናል?

## መስቀል

በክርስትና ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆነው ምልክት መስቀል ነው፤ የታሪክ ሁሉ ማዕከል የሆነው ሁነት መስቀል ነው። ይህ በክርስትና እና በሌሎች መካከል ያለው ዋነኛ ልዩነት ያመላክታል።

መስቀል ለብዙዎች ሚስጥር ነው፤ እየሱስ ለምን እንደሞተ አይረዱም። ስለሚወደን እና ሊያድነን ስለሚፈልግ እንደሞተልን ቢሰሙም ነገር ግን መስቀሉ መሆን የነበረበት ለምን እንደሆነ አይረዱም። ብዙዎችን “እግዚአብሔር ሊምረን ከፈለገ፥ ለምን እንዲሁ አልማረንም?” በማለት ይጠይቃሉ።

የመጀመርያዎቹ ክርስቲያኖች ወንጌልን መስበክ ሲጀምሩ ስለመስቀል ውዥንብር መፈጠር የጀመረው (1 ቆሮንቶስ 1፥22-23 ይነበብ)። አይሁዳውያን እግዚአብሔር ራሱን የሚያሳየው በታላቅ ኃይል እንደሆነ ያስቡ ነበር። ከነበሩበት ጭቆና የሚያወጣቸው ድነትን ነበር የሚጠብቁት ነገር ግን መስቀሉ ድካምን እና ውድቀትን የሚያሳይ የመሰላቸው።

ግሪኮች ደግሞ አምላክ ራሱን የሚገልጠው በጥበብ እንደሆነ ያስቡ ነበር። የሚያስፈልጋቸው ድነት የተሻለውን ሕይወት ለማግኘት መምራት የሚችሉበትን መረዳት እንዲሰጣቸው ነበር፥ ነገር ግን መስቀሉ ለእነሱም ሞኝነት እና ድካም ነበር።

► አንዳንድ ሰዎች በመስቀሉ ለምንድን ነው የሚበሳጩት?

መስቀሉ ለብዙዎች ብስጭትን የሚፈጥር ነው፤ ብዙዎች ኃይማኖተና ለመሆን ፈቃደኛ ናቸው። አንዳንድ ነገሮችን ለማመን፥የኃይማኖት ስርዓትን እና ምክሮችን ለመቀበል ፈቃደኛ ናቸው። ነገር ግን ኃጥያተኝነታቸው በጣም የከፋ ሆኖ መስቀልን የሚያህል ክፍያ መጠበቁ ያበሳጫቸዋል። እግዚአብሔር ተግበራቸውን ሆነ ባህሪያቸውን መቃወም እንዳለበት አያስቡም። መስቀል የሚያበሳጫቸው ምህረት የሚያስፈልጋቸው ኃጥያተኞች እንደሆኑ ስለሚናገር ነው።

የእየሱስን በመስቀል ላይ የሆነውን የመስዋትነት ሞት ለመረዳት፤ የሰውን ኃጥያተኛተንነት እና የእግዚአብሔርን ቅዱስ የሆነ ማንነት መረዳት ምን ያህል ትልቅ አጣብቂኝ እንደፈጠረ መረዳት ያስፈልጋል። ስርየት እግዚአብሔር ይቅርታን እንዲያደርግልን እንዴት ማድረግ እንደቻለ መረዳት አስፈላጊ ነው።

## የሰው ሁናቴ

በአዳም ኃጥያት ምክንያት ሑሉም ሰው ከውልደቱ ጀምሮ ከእግዚአብሔር ጋር ይለያያል (ሮሜ 5፥12)። ይህም ማለት ሑሉም ሰው ራስ ወዳድ እና በራሱ መንገድ የሚሄድ ነው።

አንድ ሰው በራሱ ውሳኔን መወሰን ከጀመረበት ግዜ ጀምሮ ኃጥያትን መስራት ይጀምራል። **ሑሉም ኃጥያተኛ እጅግ ብዙ የኃጥያት ተግባራት ጥፋተኛ ነው** (ሮሜ 3፥23 ይነበብ)።

ኃጥያት የእግዚአብሔር ህግ መጣስ ነው (1 ዮሐንስ 3፥4፤ ያዕቆብ 2፥10-11)። እግዚአብሔርም ፍጹም ጻድቅ ስለሆነ ምንም አይነት ኃጥያት አይታገስም ሆነ ምክንያት አይፈልግም፤ ሑሉም ሰው ስለሰራው ይፈረድበታል (2 ቆሮንቶስ 5፥10፤ ራእይ 20፥12-13)። ስለማንኛውም ሰው ጥፋተኝነት ሆነ የተወሰነበት ፍርድ ምንም ጥያቄ የለም። የማያምን ሰው ሁሉ አሁን ተፈርዶበታል (ዮሐንስ 3፥18-19 ይነበብ)።

**ንሰሓ ያልገባ ኃጥያተኛ የእግዚአብሔር ጠላት ነው** (ሮሜ 5፥10)። ኃጥያተኛ በእግዚአብሔር ላይ የፈፀመው ኃጥያት እስካልተማረ ድረስ ምንም አይነት ግንኙነት ሊኖራቸው አይችልም።

> "ኃጥያተኛ በእግዚአብሔር ዘንድ እንዴት እንደሚጸድቅ ለሑሉም ሰው አስፈላጊ ጥያቄው ነው፤ ከእግዚአብሔር ጋር ጥል ውስጥ እስከሆንን ድረስ አሁንም ሆነ ለዘላለም እውነተኛ ሰላም ሆነ ሀሴትን ማግኘት አንችልም።"
>
> - ጆን ዊስሊ-
>
> "በእምነት መጽደቅ" ከሚል ስብከቱ

ኃጥያተኛው ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ሊኖረው በሚችልበት ሁኔታም ውስጥ አይደለም። **ኃጥያተኛው ምኞቶቹ የተበላሹ ናቸው** (ኤፌሶን 2፥3) ምክንያቱን ለኃጥያት ባርያ ስለሆነ **ኃጥያተኛው ያለበትን ሁናቴ ለመለወጥ አቅመቢስ ነው** (ሮሜ 6፥20፣ ሮሜ 7፥23 ይነበብ)።

ስለዚህ ኃጥያተኛው የሚያስፈልገው ድነት ምንድን ነው? ኃጥያተኘው ጥፋተኛ ስለሆነ ይቅርታ ያስፈልገዋል። የእግዚአብሔርም ጠላት ስለሆነ ድነት ማለት እርቅ ማለት ይሆናል። የተበላሸም ስለሆነ፥ ድነት ማለት መንጻት ማለት ይሆናል። አቅመ ቢስም ስለሆነ ድነት ነፃ መውጣት ማለት ይሆንለታል። እነዚህ ኃጥያተኛው የሚያስፈልጉት የድነት ገጽታዎች መካከል ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው።

## አጣብቂኙ

ሰዎች ለራሳቸው ኃጥያት መክፈል አይችሉም። አንዱ ምክንያት ያለን ሑሉ የእግዚአብሔር መሆኑ ነው። ከዚህ የሚበልጠው ምክንያትም ግን ኃጥያት ታላቅ እና ወሰን የሌለው እግዚአብሔርን በመበደል ነው፤ ሰዎችም እግዚአብሔር ሊከፍሉት የሚችሉት ያን ያህል ዋጋ ያለው ነገር የላቸውም።

ሰዎች ስለሚያስፈልጋቸው ነገር ሊያደርጉት የሚችሉት ነገር የለም ስለዚህ ድነታቸውን ለመፈጸም የሚቀመጥላቸው ምንም መስፈርት የለም (ገላትያ 3፥21 ይነበብ)። ሰዎች የራሳቸውን ድነት መፈፀም የሚችሉበትን መንገድ ቢኖር ኖሮ እየሱስ በመስቀል ላይ መሞት አያስፈልገውም ነበር (ገላትያ 2፥21 ይነበብ)።

► እግዚአብሔር ሊምረን ከፈለገ፥ ለምን እንዲሁ ያለመስቀል ድነትን አይሰጥም ነበር?

እግዚአብሔር ቅዱስ እና ጻድቅ ስለሆነ በእውነት እና ፍትሓዊ የሆንን ፍርድ መስጠት አለበት (ሮሜ 2፥5-6)። ስርየት የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእየሱስ መስዋትነት ከእግዚአብሔር ጋር የምንታረቅበት መንገድ ነው።

የእየሱስ መስዋትነት ባይኖር ኖሮ ብላችሁ አስቡ፥ እግዚአብሔር ያለ ስርየት ኃጥያትን ይቅር ቢልስ?

እግዚአብሔር ያለስርየት ኃጥያትን ይቅር ቢል፤ ኃጥያትን አላስፈላጊ ያደርገዋል፥ እግዚአብሔርም ጻድቅ ሆነ ቅዱስ አይደለም። በእግዚአብሔር አይን ትክክል ሆነ ስዕተት በሚያደርግ መካከል ልዩነት የሌለ ይመስላል።

ምህረት ከስርየት ውጪ ከሆነ እግዚአብሔር እንደ ቅዱስ እና ጻድቅ አምላክ ሆኖ የሚመለክ አይሆንም። ከስርየት ውጪ ሆነ ምህረት እግዚአብሔርን አያከብርም ስለዚህ ይህም አይሆንም።

እግዚአብሔር የሚወደን እና ሊምረን ይፈልጋል፤ የሰውንም ልጅ ቢገባውም በኃጥተኛነቱ ውስጥ፥ ለዘላለም የጠፋ ሆኖ ሊተወው አልፈለገም።

በመስቀል ላይ የሆነው የክርስቶስ መስዋትነት የሚያስፈልግንን ዋጋው ታላቅ እና ማብቂያ የሌለው መስዋትነት ሰጥቶናል። እየሱስም (1) **ኃጥያት የሌለበት በመሆኑ** (ፍጹም እና ራሱ ድነት የማያስፈልገው፤ 2 ቆሮንቶስ 5፥21) እና (2) **እግዚአብሔር እና ሰው በመሆን** ብቁ ሆኖ ተገኝቷል።

ስርየት ለይቅርታ የሚያስፈልገውን መሰረት ሑሉ ይሰጠናል። ንሰሓን የገባ እና በሰጠው ተስፋ የሚያምንን ሰው እግዚአብሔር ይቅር ይለዋል። በመስቀል ላይ የነበረውን መስዋትነት በሚገባ የተረዳ ሰው ኃጥያት በእግዚአብሔር ምን ያህል ከባድ እንደሆነ መረዳት ይችላል።

ስርየት ጻድቅ የሆነ አምላክ በተስፋው ላይ የሚያምነውን ኃጥያተኛ ጻድቅ አድርጎ የሚቆጥርበት መንገድ ነው (ሮሜ 3፥26 ይነበብ)። ሮሜ 3፥20-26 ስርየት እንዴት እንደሚሰራ አመክኖያዊ ማስረጃን ይሰጠናል።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ያዘጋጀው የድነት መንገድ ብቸኛው መንገድ እንደሆነ ይነግረናል። ሰው ከእምነት በፀጋ ያለውን ድነት የማይቀበል ከሆነ መዳን አይችልም (ማርቆስ 16፥15-16፤ ሐዋርያት ሥራ 4፥12፤ ዕብራውያን 2፥3 ይነበብ)።

ለዚህ ነው ድነት እምነት እና ጸጋ ብቻ የሚለውን አስተምሮ ማወቅ አስፈላጊ የሆነው፤ ድነት በጸጋ ብቻ ስለሆነ ድነት እንዲገባን ሆነ እንድናገኝ ልናደርግ የምንችለው ምንም ነገር የለም። በእምነት ብቻም የሆነውም ምንም ብንሰራ ልናገኝው የምንችል ስላልሆነ ነው። የእግዚአብሔርን ተስፋ ብቻ ነው ማመን የምንችለው።

## የመጀመርያው ጸጋ

► ወደ ድነት የመጀመርያውን እርምጃ የሚያደርገው ማን ነው፤ እግዚአብሔር ወይስ ሰውየው ራሱ?

እግዚአብሔር ኃጥያተኛውን ወደ ድነት ለማምጣት የመጀመርያውን እርምጃ የወሰደው እግዚአብሔር ነው። ይቅርታን የማድረግ ፈቃደኝነቱን ያሳየው እየሱስ በመስቀል ላይ መስዕዋት እንዲሆን በማድረግ ነው። አሁን የእግዚአብሔር ጸጋ ወደ ኃጥያተኛው ልብ በመድረስ ስለኃጥያተኝነቱ በመኮነን ይቅርታን እንዲፈልግ ያደርገዋል (ቲቶ 2፥11፤ ዮሐንስ 1፥9፤ ሮሜ 1፥20 ይነበቡ)። ሰዎች ከእግዚአብሔር እርዳታ ውጪ ኃጥያትን ለመተው አቅመቢስ ናቸው (ዮሐንስ 6፥44)። እግዚአብሔር ኃጥያተኞ ለወንጌል ምላሽ እንዲሰጡ አቅም ይሰጣል። ሰው ካልዳነ፥ ጸጋ ስናነሰው ሳይሆን ነገር ግን እግዚአብሔር ለሰጠው ጸጋ ምላሽ መስጠት ስላልቻለ ነው።

እየሱስ ለአለም ሑሉ ኃጥያት ሞቷል እንዲሁም እግዚአብሔር ሑሉንም ሰው ማዳን ይፈልጋል (2 ጴጥሮስ 3፥9፤ 1 ዮሐንስ 2፥2፤ 1 ጢሞቴዎስ 4፥10 ይነበቡ)። የእግዚአብሔር ጸጋ ሑሉም ሰው ምላሽ እንዲሰጥ አቅም ይሰጣል ነገር ግን ማንንም ሰው አያስገድድም። ለዚህ ነው እግዚአብሔር ኃጥያተኞችን ወደ ንሰሓ እና እምነት እንዲመጡ የሚጋብዘው (ማርቆስ 1፥15)።

## ንሰሓ

► ንሰሓ ምንድን ነው?

ንሰሓ መግባት ማለት መመለስ እና በሌላ አቅጣጫ መሄድ ማለት ነው። በስነ-መለኮት አረዳድ ይህ ማለት ኃጥያተኛ ራሱን እንደ ጥፋተኛ እንደሆነ ያስተዋለ እና ቅጣት እንደሚያስፈልገው የተረዳ ቢሆንም ግን ከኃጥያቱ ለመመለስ ፈቃደኛ የሆነ ነው።

> ክፉ ሰው መንገዱን፣ በደለኛም ሐሳቡን ይተው። ወደ እግዚአብሔር ይመለስ፤ እርሱም ምሕረት ያደርግለታል፤ ወደ አምላካችን ይመለስ፤ ይቅርታው ብዙ ነውና (ኢሳይያስ 55፥7)።

ንሰሓ ማለት እግዚአብሔር ይቅርታን ከማድረጉ በፊት ኃጥያተኛ ሕይወቱን ማስተካከል እና ራሱን ጻድቅ ማድረግ አለበት ማለት አይደለም። ይህ በፍጹም ሊሆን አይችልም። ነገር ግን ኃጥያተኛ እግዚአብሔር ከኃጥያቱ ነፃ እንዲያወጣው ፈቃደኛ መሆን አለበት።

► ድነት የሚገኘው በጸጋ ነው፤ ስለዚህ ንሰሓ ለምን አስፈላጊ ሆነ?

ለይቅርታ የሚያስፈልገው ብቸኛ ነገር እምነት ብቻ ነው፤ ነገር ግን ለድነት የሚሆን እምነት ከንሰሓ ውጪ ሊሆን አይችልም። አንድ ሰው ለንሰሓ ፈቃደኛ ካልሆነ ከኃጥያቱ መዳን አይችልም።

እግዚአብሔር በኃጥያታቸው የፀኑ እና ለመመለስ ፈቃደና ያልሆኑ ሰዎችን ይቅር ካለ፤ በምድር ላይ ያለውን ጻድቅ ፈራጅነቱን ያዋርደዋል። ንሰሓ አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱን አንድ ሰው ንሰሓ ካልገባ የኃጥያትን ክፋት በሚገባ አላመነም ማለት ነው። ከኃጥያት መመለስ ያለበት ለምን እንደሆነ በሚገባ ካልተረዳ ምህረት ለምን እንደሚያስፈልገው አይመለከትም።

አንድ ሰው ራሱን ያለ ምንም ሰበብ ጥፋተኛ የሆነ እና ቅጣት እንደሚያስፈልገው እንደሆነ ካልተሰማው፤ በትክክል ንሰሓ አልገባም። ኃጥያተኛ እንደሆነ ካመነ ነገር ግን በኃጥያቱ መቀጠል ከፈለገ ንሰሓው ጎዶሎ ነው፥ ምክንያቱም ክጀዋለው ያለውን ኃጥያት ማድረግ ስለቀጠለ ነው።

## የሚያድን እምነት

► አንድ ሰው የሚያድን እምነት ካለው ምንድን ነው የሚያምነው ማለት ነው?

አንድ ሰው የሚያድን እምነት ካለው የሚያምነው፤

**(1) ራሱን ለማጽደቅ ምንም ማድረግ አይችልም**

> በእምነት፣ በጸጋ ድናችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ በሥራ አይደለም (ኤፌሶን 2፥8-9)።

ምንም የሚያደርገው ነገር ሆነ ስራ ድነትን ለመቀበል በሙሉ ሆነ በጥቂቱ እንኳን በቂ እንደማያደርገው ሲረዳ ነው።

**(2) የእየሱስ መስዕዋትነት ለሚሰጠው ይቅርታ በቂ ነው**

> እርሱም የኀጢአታችን ማስተስረያ ነው፤ ይኸውም ለዓለም ሁሉ ኀጢአት እንጂ ለእኛ ብቻ አይደለም (1 ዮሐንስ 2፥2)።

ማስተሰርያ ማለት ይቅርታን እውን የሚያደርግልን መስዋትነት ሲሆን፥ ለዚህም ይቅርታ ከክርስቶስ መስዕዋትን ውጪ ምንም አስፈላጊ አይደለም።

> "የሚያድን እምነት የሚያሳርፍ እምነት ነው፥ እምነቱን የሚጣለው ሙሉ በሙሉ በአዳኙ ስለሆነ ነው።"
>
> ጆን ስቶት

**(3) እየሱስ ከሞት በመነሳቱ ኃጥያትን እና ሞትን ድል ነሳ**

> "እየሱስ ጌታ ነው" ብለህ በአፍህ ብትመሰክር፣ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን፣ ትድናለህ (ሮሜ 10፥9)።

ሞት እና ኃጥያት ድል የሚነሱበት ብቸኛው መንገድ በክርስቶስ ትንሳኤ ብቻ ነው። እየሱስ ከሙት በመነሳቱ በሑለቱም ላይ ያለውን ፍጹም የሆነ ድል ያስረግጥልናል።

**(4) እግዚአብሔር የማረው በእምነቱ ብቻ ነው**

> ኀጢአታችንን ብንናዘዝ ኀጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከዐመፃም ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው (1 ዮሐንስ 1፥9)።

ማንም ሰው ለድነት ሌላ ነገሮች እንደሚያስፈልጉት ካመነ፤ በጸጋ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በግማሽ በስራ እንደሚድን ያሰባል ማለት ነው።

**ዋስትና**

► ሰዎች ለመዳናቸው እንዴት እርግጠኞች መሆን ይችላሉ?

አንዳንድ ሰዎች በስሜታቸው ላይ ይደገፋሉ፥ ስሜት ግን የሚቀያየር እና ሊያሳስት ይችላል።

መጽሐፍ ቅዱስ ለመዳናችን እርግጠኞች እንድንሆን ይነግረናል (1 ዮሐንስ 5፥13)። እግዚአብሔር እንደተቀበለን እርግጠኞች መሆን እንችላለን። በፍርሃት መኖር አይጠበቅብንም ምክንያቱንም የእግዚአብሔር መንፈስ የእግዚአብሔር የማደጎ ልጆች መሆናችንን ያስረግጥልናል። ሐዋርያው ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ለመንፈሳችን የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንን ምስክር እንደሚሆነን ይነግረናል (ሮሜ 8፥15-16)።

ይህ ዋስትና ሙሉ ስለሆነ በመጨረሻ ሑነቶች መፍራት የለብንም (1 ዮሐንስ 4፥17 ይነበብ)። አንዳንድ ሰዎች ወደ መንግስተ ሰማያት ተቀባይነት እንደሚያገኙ ተስፋን እንደሚያደርጉ ይናገራሉ ነገር ግን ከዚህ የተሻለ ዋስትና አለን። ድነት ለሑሉም ሰው በጅምላ እንደተሰጠ ማመን በቂ አይደለም፤ አንድ ሰው ራሱ እንደዳነ ማወቅ አለበት።

የተለወጠ ሕይወት አንድ ሰው እንደዳነ ማስረጃ ነው፤ ነገር ግን ይህ ማስረጃ የሚገኘው በድነት የመጀመርያ ግዜያቶች ላይ አይገኝም። የድነት ውጤቶች የመገለጫ ግዜ ገና የላቸውም። ስለዚህ በንሰሓ ግዜ የተለወጠ ሕይወት የድነት ዋስትና አይደለም።

አማኝ ስለድነቱ እርግጠኛ መሆን የሚችለው መጽሐፍ ቅዱስ ለድነት ያስቀመጠውን መንገድ መከተሉን እርግጠኛ ከሆነ ብቻ ነው። አንድ ሰው በእውነት ንሰሓ ገብቶ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያዘው ካመነ እግዚአብሔር እንደማረው ማመን እና የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን መብት አለው።

በእውነት ንሰሓ ሳይገባ እንደዳነ እንዲሰማው ቢሞክር ግን ግራ በመጋባት ውስጥ ይኖራል እንዲሁም ራሱን ያስታል።

አንድ ሰው (1) በእውነት ንሰሓ ቢገባ፥ (2) እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰጠውን ቃልኪዳን ቢያምን እና (3) የመንፈስ ቅዱስን ምስክርነት ቢቀበል ግን አይስትም። ይህ ዋስትና በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሰረተ እና ሊተማመኑበት የሚያስችል ነው። እግዚአብሔር ሁልግዜ ቃሉን የሚጠብቅ አምላክ ነው።

## የድነት ገጽታዎች የሚያሳዩን 10 ቃላት

**መታረቅ** - ይህ ቃል በፊት ጠላቶች የሆኑ አሁን በሰላም ይኖራሉ ማለት ነው። በድነት ውስጥ እግዚአብሔር ከራሱ ጋር ያስታርቀናል እንዲሁም ከእርሱ ጋር ሰላም አለን (2 ቆሮንቶስ 5፥19፤ ሮሜ 5፥1 ይነበብ- እነዚህ ጥቅሶች ስለመጽደቅ እና መታረቅ ይናገራሉ)።

**የዕዳው ጽዕፈት መሰረዝ-** ይህ ሀረግ የጽዕፈቱን መሰረዝ የሚያሳይ ሲሆን፥ በድነታችን የዕዳችን ጽዕፈት ተሰርዞልናል (ዕብራውያን 8፥12 ይነበብ)።

***ማስተሰረያ***- ይህ ቃል የሚያሳየው አንድ አካል ከቁጣው ለመመለስ የሚሰጥ እንደሆነ ማሳያ ነው። በድነታችን ውስጥ የእየሱስ መስዕዋትነት በእኛ ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን የጽድቅ ቁጣን ዞር ያደረገ ነው (1 ዮሐንስ 2፥2 ይነበብ)።

***ነጻ መውጣት*** - ይህ ቃል ከሌላ ኃይል አንድን አካል ማዳን ነው። በድነት ውስጥ ከሰይጣን እና ኃጥያት ኃይል ተላቀናል (ሉቃስ 1፥74፤ ሮሜ 6፥6፣ 12-18 ይነበብ)።

***ቤዛነት***- ይህ ቃል አንድ አካል ነጻ እንደሆን የሚያስፈልገው ዋጋ ተከፍሏል ማለት ነው። በድነት ውስጥ የእየሱስ ሞት ከኃጥያት ቀንበር እና ቅጣትን ዋጋ በእየሱስ ደም ተከፍሏል (ኤፌሶን 1፥7፤ ቲቶ 2፥14 ይነበቡ)።

***መጽደቅ***- ይህ ቃል አንድ ሰው ጻድቅ ወይም ያለ ጥፋት ነው ተብሎ ታውጇል ማለት ነው። በድነት ውስጥ ጥፋተኛ የነበረው ኃጥያተኛ እየሱስ በእርሱ ቦታ ስለተሰቃየለት እንደጻድቅ ተቆጥሯል (ሮሜ 5፥1፤ 2 ቆሮንቶስ 5፥19 ይነበብ እነዚህ ጥቅሶች ስለመጽደቅ እና መታረቅ ይናገራሉ)።

***መቀደስ***- ይህ ቃል አንድ አካል ቅዱስ ሆነ ማለት አለበት። በድነት ውስጥ ጥፋተኛ የነበረው ኃጥያተኛ ወደ ቅዱስ የሆነ የእግዚአብሔር ልጅነት ተለወጠ ማለት ነው። ብዙ መልዕክታት አማንያንን ‘ቅዱሳን’ ብለው ይጠሯቸዋል (ኤፌሶን 1፥1፣ ፊልጵስዩስ 1፥1፣ ቈላስይስ 1፥2 ይነበብ)።

***የማደጎ ልጅነት*** - ይህ ቃል አንድ ሰው በህጋዊ መንገድ ልጅ እንደሆነ ይናገራል። በድነት ውስጥ የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል (ዮሐንስ 1፥12፤ ሮሜ 8፥15 ይነበብ)።

***ዳግም ልደት/ አዲስ ውልደት*** - ይህ ቃል አንድ ሰው አዲስን ሕይወት ዳግመኛ መጀመሩን ያሳያል። በድነት ውስጥ አማኙ አዲስን ሕይወት በውስጡ በሚሆነው የመንፈሳዊ ሕይወት ትንሳኤ ምክንያት ይጀምራል (ኤፌሶን 2፥1፤ ዮሐንስ 3፥3፣ 5 ይነበቡ)።

***መታተም***- ይህ ቃል አንድ ሰው የማን ንብረት እንደሆነ ማሳያ ምልክት ነው። በድነት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ የእግዚአብሔር እንደሆንን ያስረዳናል (ኤፌሶን 1፥13-14 ይነበብ)።

### ***ማስወገድ ያለብን ስህተት፥ ያለንሰሓ የሆነ ኃይማኖት***

*ለክፍሉ መሪ ማስታወሻ- የክፍሉ አባል ይህንን ክፍል ማስረዳት ይችላል።*

ድነት በእምነት በኩል በጸጋ እንደሆነ ሲሰማ እንደዳነ የሚያስብ ሰው ሊኖር ይችላል፤ ይህ ማለት እንደሚያስፈልገው ስላላሰበ በሚገባ ንስሓን አልገባም ማለት ነው። የእግዚአብሔር ፍርድ የሚገባው ኃጥያተኛ እንደሆነ በፍጹም እንደሆነ በሚገባ ስላልተመለከተ ነው ስለዚህ ጸጋ ማለት እንዲሁ በራሱ መንገድ እንደወደደ መሄድ እንደሚችል ያስባል። የክርስትናን እውነት ስላወቀ ብቻ የሕይወት ለውጥ ሳይኖር ክርስቲያን እንደሆነ ያስባል። ይህ አይነት ሰው የራሱን ፈቃድ ለእግዚአብሔር በሙሉ ሳያስገዛ እግዚአብሔርን እንደ አንድ የሕይወት አካሉ ብቻ በመመልከት ሕይወቱን በራሱ ፈቃድ የሚመራ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስተምረን መሰረት መሰረት ግን ይህ ድነት የሚገኝበት ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ግንኙነት የሚጀመርት መንገድ አይደለም።

► የእምነት መግለጫውን ቢያንስ ሁለት ግዜ አብራችሁ አንብቡ።

**የእምነት መግለጫ**

የእየሱስ ክርስቶስ ሕይወት፥ ሞት እና ትንሳኤ ለአለም ሑሉ ኃጥያት ስርየትን የሚሰጥ ነው። ሑሉም ሰው በኃጥያት ምክንያት በደለኛ የሆነ እና ራሱን የሚያድንበት አቅም የሌለው ነው። ኃጥያቱን የሚናዘዝ ሑሉ ግን የእግዚአብሔር ጸጋ በእምነት መቀበል ይችላል። አማኙም ከኃጥያት ኃይል እና ቅጣት ይቅርታን ያገኛል እንዲሁም ነጻ ይወጣል። መንፈስ ቅዱስ አማኙነት በኃጥያት ምክንያት ከነበረበት ጥፋተኝነት ወደ ቅዱስ እግዚአብሔርን የሚያመለክ ሰው ይለወጣል። ከዚህ ውጪ ሌላ ምንም የድነት መንገድ የለም። ፍጥረት ሑሉ ድነትን ያገኛል እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር ተሓድሶ ይሆንለታል።

**ድነት በብሉይ ኪዳን ውስጥ**

*ለክፍሉ መሪ ማስታወሻ- ይህም ክፍል እና የሚቀጥለውን መጠቀም ምርጫችሁ ነው። የክፍሉ አባላት ፍላጎት ላይ በመመስለት ይህንን ክፍል መሸፈን ትችላላችሁ።*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር በመስዕዋት ውስጥ የአምልኮ ስርዓትን ሰጥቷል። ይህ መስዕዋት በእየሱስ ሞት በኩል እንደሆነው አይነት ድነትን አያስገኝም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይነግረናል “የኰርማዎችና የፍየሎች ደም ኀጢአትን ማስወገድ አይችልም” (ዕብራውያን 10፥4)። ስለዚህ መስዕዋት ያስፈለገው ለምንድን ነው? ምክንያቱን ይህ የአምለኮ ስርዓት በወደ ፊት በክርስቶስ እየሱስ የሚሆነውን የመስዕዋትነት ምልክት እንዲሆን ነው (ዕብራውያን 10፥1)።

ይህ ማለት ግን ድነት አዲስ ኪዳን ግዜ ድረስ አልነበረም ማለት አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስ የጸጋ በኩል በእምነት ስለመጽደቅ ያለውን አስተምሮን ሲያስረዳ አብረሃምን እና ዳዊትን እንደምሳሌ አድርጎ መጠቀሙ ድነት አዲስ ሃሳብ እንዳልሆነ ያሳያል (ሮሜ 4፥1-8)። እየሱስም ኒቆዲሞስ ጋር ሲያወራ የብሉይ ኪዳን አስተማሪ መሆኑን በመጥቀስ ስለ አዲስ ልደት ማወቅ እንደነበረበት ይናገረዋል (ዮሐንስ 3፥10)። ጳውሎስም ለጢሞትዮስ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን መጽሐፍት ድነት ስለሚገኝበት መንገድ ጠቢብ እንደሚያደርጉት ነግሮታል (2 ጢሞቴዎስ 3፥15)። ስለዚህ ወንጌል በብሉይ ኪዳን ውስጥ የነበረ ሲሆን ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንዳለው ግልጽ በሆኑ ቃላት አልተቀመጠም።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ውስጥ ጸጋን የተረዱ ሰዎች ነበሩ፤ የስርየት ዝርዝር መንገዱ ሆነ እንዴት ስርየት እንደሚሆን ግልጽ ባይሆንላቸውም ነገር ግን እግዚአብሔር የይቅርታን መንገድ እንዳዘጋጀ ግን አምነው ነበር። መስዕዋቶች እግዚአብሔር ላይ ያለ እምነታቸው መገለጫዎች ሲሆን እኛ ዛሬ የምናደርገው አይነት አምልኮ ነው (ለምሳሌ የጌታ ዕራት)። መስዕዋቶቹ በእምነት እና መታዘዝ ካለቀረቡ፤ ልክ ያለ ልብ እና ሕይወት ለእግዚአብሔር እንደምናቀርበው አምልኮ ረብ የሌላቸው ይሆናሉ። መዝሙር 51 እና ኢሳይያስ 1፥11-18 ንሰሓ እና እምነት በብሉይ ኪዳን ግዜ አስፈላጊ እንደሆኑ ያሳዩናል።

በክርስቶስ የተደረገው ስርየት ከመፈጸሙ ከብዙ ዘመናት በፊት የተጻፈው መዝሙር 85 የእግዚአብሔርን ጸጋ እና ኃጥያትን እንዴት እንደሚምር ውብ በሆነ መንገድ ያስቀምጥልናል። የእግዚአብሔር ቁጣ እንዴት እንደቆመ

ይናገራል። መዝሙር 85፥10 እንዲህ ይላል፣ “ምሕረትና ታማኝነት ተገናኙ፤ ጽድቅና ሰላም ተቃቀፉ። ” በስርየት ውስጥ ውብ የሆነ የድነት ምስል አለ። ስርየት ከሌለ የእግዚአብሔር ምሕረት በጥፋተኝነታችን እውነት ውስጥ ይወሰናል። የእግዚአብሔር ጽድቅ ሰላም የሚሰጠን ሳይሆን ጠላቶቹ ያደርገን ነበር፤ በስርየት ውስጥ ፍትሕ ተፈጸመ እንዲሁም ምሕረትም ታየ።

## የፍጥረት ሑሉ ድነት

መዳን እና ድነት የሚሉት ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስፋት ጥቅም ላይ ውለዋል፤ በዚህ ትምህርት ውስጥ ይህ ሃሳብ የምንመከለተው ከግላዊ ከሆነ ድነት በላይ ነው መሆኑን ነው። እነዚህ ቃላት በፊት የተሰራውን (ኤፌሶን 2፥8)፥ አሁን እየሆነ ያለውን (1 ቆሮንቶስ 1፥18)፣ እንዲሁም ወደፊት የሚሆነውን (ማርቆስ 13፥13) የሚያመላክቱ ናቸው። ሃሳቡ እያንዳንዱ ሰው ላይ የሚሆነውን (በዚህ ትምህርት ላይ እንደተብራራው) የሚያመላክት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን እንደአይሁዳውያን (ሮሜ 1፥16)፥ አህዛብ (ሮሜ 11፥11)፥ አንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ (ሉቃስ 19፥9)፣ ወይም ቤተሰቦችን (ዕብራውያን 11፥7)፣ ያሉ የማህበረሰብ ዘርፎችንም የሚያመላክት ሊሆን ይችላል እንዲሁም አንድ ሰው ከአካላዊ አደጋ የሚድንበትን መንገድ የሚያመላክት መሆን ይችላል (ማቴዎስ 14፥30)።

የመጀመርያዎቹ ሰዎች ኃጥያትን ሲሰሩ ፍጥረት ሑሉ ከእርግማ ስር ሆነ (ዘፍጥረት 3፥17)። ድነት ፍጹም ሲሆን ግን ፍጥረት ሑሉ ይታደሳል።

ድነት ከመንፈሳዊ መታደስ ይጀመራል፤ አማንያን ከኃጥያት ድነው በእግዚአብሔር በረከት ውስጥ ይገኛሉ። ነገር ግን በኃጥያት የሆነው እርግማን ምክንያት ቁሳዊ/አካላዊ ከሆነው የእርግማን ችግር ግን ገና ነጻ አልወጡም፤ ገና የሚያረጅ እና የሚሞት አካል አላቸው።

ፍጥረትንም እንዲሁ ገና በኃጥያት እርግማን ስር ነው። እግዚአብሔር መጀመርያ የፈጠረውን አለም ምን እንደሚመስል አይነት አናውቅም፤ የምናየው ፍጥረት በአደገኛ እና እርስ በእርሳቸው ግጭት ውስጥ በሆኑ ፍጡራን የተሞላ ነው። በዚህ አለም ውስጥ ብዙ ፍጡራን ሌሎች እንዲኖሩ መሞት አለባቸው።

ፍጥረት ሑሉ የሚታደስበት ግዜ እየመጣ ነው (ራእይ 21፥1፤ ዕብራውያን 1፥10-12)። ሮሜ 8፥18-25 ለክርስቲያኖች ከኃጥያት እርግማን ነጻ የሖነ አለም ተስፋን ይናገራል።

## ትምህርት 8 የቤት ስራዎች

(1) የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የቤት ስራ፡- ከታች ከተዘረዘሩት ዘርፎች መካከል እያንዳንዱን ተማሪ አንድ ይመደብ። ከሚቀጥለው ክፍለ ግዜ በፊት ክፍሉን አንብባችሁ በትምህርቱ ውስጥ ካለው ሃሳብ ላይ ምን እንደሚናገር በአንድ አንቀፅ ፃፉ።

- መዝሙር 51
- ኢሳይያስ 1፥11-18
- ሮሜ 3፥20-26
- ሮሜ 8፥19-25
- ኤፌሶን 2፥1-10

(2) ፈተና፡- የሚቀጥለው ክፍለ ግዜ የምትጀምሩት በትምህርት 8 ፈተና ነው። ለፈተና ዝግጅት እንዲሆን የፈተና ጥያቄዎችን አጥኑ።

(3) የማስተማር የቤት ስራ፡- ከክፍል ውጪ የማስተማርያ ግዜን ቀጠሮ መያዝ እና ማስተማራችሁን ሪፖርት ማድረግ አስታውሱ።

## የትምህርት 8 ፈተና

(1) መስቀል ብዙዎችን የሚያበሳጨው ለምንድን ነው?

(2) ንሰሓ ስላልገባ ኃጥያተኛ ስለሆነ ሰው ያሉ አራት እውነቶችን ዘርዝሩ።

(3) ያለ ስርየት የሖነ ይቅርታ እግዚአብሔርን የማያከብረው ለምንድን ነው?

(4) እየሱስን ብቻ መስዕዋት ለመሆን በቂ የሚሆንበትን ሑለት መንገዶችን ዘርዝሩ።

(5) የተመለሰ/ንሰሓ የገባ ኃጥያተኛ አመለካከት ምንድን ነው?

(6) አንድ ሰው ድነት የሚሰጥ እምነት ካለው፥ ምንድን ነው የሚያምነው?

(7) አንድ ሰው እንደዳነ በምን እርግጠኛ መሆን ይችላል?

# ትምህርት 9

# በድነት ዙርያ ያሉ ጉዳዮች

## የትምህርቱ አላማ

(1) ተማሪው የሚከተሉትን ማስረዳት ይችላል

- አማኙ በኃጥያት ላይ ያለው ድል አስፈላጊነት እና መብት
- እግዚአብሔር ጸጋ የድልን ሕይወት እንደሚሰጠን
- ከክርስቶስ ጋር ባለን ግንኙነት የሚገኝ መንፈሳዊ ሕይወት
- ከጸጋ የመጉደል መጽሐፍ ቅዱሳዉ ማስጠንቀቂያ
- ስለ ድነት ጉዳዮች ክርስቲያናዊ የእምነት መግለጫ

(2) ተማሪው በድል አድራጊነት ከኃጢአት ተላቅቆ ለመኖር ይጠብቅበታል።

## መግቢያ

► ሮሜ 6 አብራችሁ አንብቡ። ይህ ክፍል ስለ ድነት ውስጥ ያሉ ውጤቶች ምን ይነግረናል?

## የድነት ማስረጃዎች

የ1 ዮሐንስ ደብዳቤ ዋና ሃሳቦች መካከል የግል ድነት እርግጠኝነት አንዱ ነው። ዩሐንስ ይህንን ደብዳቤውን የጻፈበትን አላማ እንዲህ በማለት ያስቀምጣል "በእግዚአብሔር ልጅ ስም የምታምኑ እናንተ፣ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ ይህን እጽፍላችኋለሁ" (1 ዮሐንስ 5፥13)።

► ሰው ስለድነቱ ምንም አይነት ጥርጣሬ ቢኖርበት ምን ማድረግ አለበት?

ሐዋርያው አማንያን ስለድነታቸው ማረጋገጫ የሚፈልጉበት ግዜ እንዳለ ያውቅ ነበር፤ ለዚህም አንድ አማኝ ትክክለኛ ማድረግ ያለበት ነገር ስለድነቱ ማስረገጫ መሰረት የሚሆንለትን ማስረጃዎች መፈለግ እንደሆነ ያሳያል። በመልዕክቱም ውስጥ ከማስረጃዎች መካከል አንዳንድ ምሳሌዎችን "በዚህ እናውቃለን"[18] በማለት አስቀምጦልናል። ይህንንም ማስረጃ በመጠቀም አማንያን ልባቸውን ማሳረፍ እንደሚችሉ ይናገራል (1 ዮሐንስ 3፥19)።

በኃጥያት ላይ ያለን ድል 1 ዮሐንስ ላይ ከአማንያን ማንነት መካከል አጽንኦት የተሰጠው ነው፥ ሐዋርያው ዩሐንስም እንዲህ ብሎ ጽፏል "ልጆቼ ሆይ፤ ይህን የምጽፍላችሁ ኀጢአት እንዳትሠሩ ነው" (1 ዮሐንስ 2፥1)። በዚህ አርፍተ ነገር ውስጥ ሐዋርያው አማንያን በፈቃድ የሚደረግ ኃጥያት ነጻ የሆነ ሕይወት መኖር እንዳለብ ያስተምረናል[19]። ይህንን የሚጽፈው በድል የመኖርን አስፈላጊነት ሊያሳያቸው ነው።

---

[18] 1 ዮሐንስ 2፥3፣ 5፣ 29፤ 1 ዮሐንስ 3፥10፣ 14፣ 19፣ 24፤ 1 ዮሐንስ 5፥2፣ 18

[19] በፈቃድ ስለሚሰራ ኃጥያት በትምህርት 5 ላይ ተምረናል።

*ነገር ግን ማንም ኀጢአት ቢሠራ፣ በአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፤ እርሱም ጻድቁ እየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም የኀጢአታችን ማስተስረያ ነው፤ ይኸውም ለዓለም ሁሉ ኀጢአት እንጂ ለእኛ ብቻ አይደለም* (1 ዮሐንስ 2፥1-2)።

*በዚህ ክፍል ላይ ዩሐንስ ኃጥያት ሊከሰት እንደሚችል ነገር ግን መሆን አለበት ማለት እንዳልሆነ ይመለከታል። አንድ አማኝ በኃጥያት ከወደቀ የክርስቶስ መስዋትነት ለኃጥያቱ ማስተሰረያነት በቂ እንደሆነ ያስረግጥልናል። ነገር ግን ይህ ማለት አማኝ ወደ ኃጥያት ገብቶ ወድያው ያለንስሓ ምህረትን ያገኛል ማለት አይደለም። ይህ ቁጥር የሚያሳየን መስዕዋትነቱ አሁንም ለሑሉም ሰው እና ኃጥያት በቂ በሆነ መንገድ እንዳለን የሚያሳይ ነው። መላው አለም እንዲሁ ድነትን የሚያገኝ እንዳልሆነ እናውቃለን፥ አንድ አማኝ ግን ኃጥያትን ቢሰራ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት በማስተዋል ንሰሓን መግባት አለበት።*

1 ዮሐንስ *ውስጥ ያሉት የሚከተሉነት ቁጥሮች የአማንያን ታላቁ መለያቸው ኃጥያትን ለማድረግ በሚገፋፉቸው ፈቃዳቸው ላይ ያላቸው ድል ነው። በቅንፍ ውስጥ ያሉት ሀረጎች የተጨመሩ አስተያየቶች ናቸው*

*ትእዛዞቹን ብንፈጽም እርሱን ማወቃችንን በዚህ ርግጠኞች እንሆናለን [እግዚአብሔርን የማይታዘዝ ሰው ይህንን ምስክርነት የለውም] "እርሱን ዐውቃለሁ" እያለ ትእዛዞቹንም የማይፈጽም ግን ሐሰተኛ ነው፤ እውነቱም በርሱ ውስጥ የለም።* (1 ዮሐንስ 2፥3-4)።

*ኀጢአት የሚያደርግ ሁሉ ዐመፅን ያደርጋል፤ ኀጢአትም ዐመፅ ነው። እርሱ ኀጢአትን ሊያስወግድ እንደ ተገለጠ ታውቃላችሁ፤ በርሱም ኀጢአት የለም። በርሱም የሚኖር ኀጢአትን አያደርግም፤ ኀጢአት የሚያደርግ ግን እርሱን አላየውም ወይም አላወቀውም* (1 ዮሐንስ 3፥4-6)።

*ልጆች ሆይ፤ ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤ እርሱ ጻድቅ እንደ ሆነ፣ ጽድቅን የሚያደርግ ጻድቅ ነው [ኃጥያትን ማድረግ በመቀጠሉ እንደ ጻድቅ የማይቆጠር ሰው]። ኀጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፤ ምክንያቱም ዲያብሎስ ከመጀመሪያ አንሥቶ ኀጢአትን የሚያደርግ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ የተገለጠውም የዲያብሎስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ ነው* (1 ዮሐንስ 3፥7-8)።

*ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኀጢአትን በመለማመድ አይቀጥልም፤ የርሱ ዘር በውስጡ ይኖራልና፤ ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደም ኀጢአትን ሊያደርግ አይችልም* (1 ዮሐንስ 3፥9)።

*ትእዛዞቹንም የሚጠብቁ ሁሉ በርሱ ይኖራሉ፤ እርሱም በእነርሱ ይኖራል። በእኛ መኖሩን በዚህ፣ ይኸውም እርሱ በሰጠን መንፈስ እናውቃለን* (1 ዮሐንስ 3፥24)። *[በክርስቶስ ነኝ የሚል ሰው የእግዚአብሔርን ህግ ደጋግሞ ከሚጥስ ሕይወት ሊኖረው አይችልም። ]*

*እግዚአብሔርን ስንወድድና ትእዛዞቹን ስንፈጽም የእግዚአብሔርን ልጆች እንደምንወድድ በዚህ እናውቃለን፤ እግዚአብሔርን መውደድ ትእዛዞቹን መፈጸም ነውና* (1 ዮሐንስ 5፥2-3)። *[መታዘዝ በእውነተኛ ፍቅር ውስጥ የሚነሳሳ ሲሆን፤ አለመታዘዝ በሕይወታችን ፍቅር እንደሌለ ማሳያ ነው። ]*

*ምክንያቱም ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋል [ፈተናው እና መንፈሱ] ዓለምን የሚያሸንፈውም እምነታችን ነው* (1 ዮሐንስ 5፥4)።

ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኀጢአት እንደማያደርግ፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚጠብቀው [ጠባቂዎች]፣ ክፉውም እንደማይነካው እናውቃለን (1 ዮሐንስ 5፥18)።

► በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ግልጽ የሆነው የአንድ አማኝ መለያ ባሕርይ የትኛው ነው?

ከእነዚህ ጥቅሶች የአማኙ መለያ ባሕርይ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ የሚኖር መሆኑ ግልጽ ሆኖ ተቀምጧል። የአማኝ ትልቁ ስልጣን/ privilege የፍቃድ ኃጢያትን ማሸነፍ/ ድል መንሳት ነው።

## የ1ኛ ዮሐንስ 1፥8 መግለጫ

አንዳንድ ጊዜ አማኝ የፍቃድ ኃጢያትን በማሸነፍ መኖር እንደሚችል የሚክዱ ሰዎች 1 ዮሐንስ 1፥8 "ኀጢአት የለብንም ብንል፣ ራሳችንን እናስታለን፤ እውነቱም በእኛ ውስጥ የለም" የሚለውን ይጠቅሳሉ። ነገር ግን ኃጢያት አለብን ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ማለት አማኞች እንኳን ኃጢያት መሥራታቸውን ቀጥለዋል ማለት ነው? ይህ ደግሞ ከላይ ከተጠቀሱት የ1 ዮሐንስ 3 መግለጫዎች ጋር የሚስማማ አይሆንም። ዮሐንስ ቀደም ሲል "እያንዳንዱ ሰው፣ አማኝን ጨምሮ ኃጢያት መሥራቱን ቀጥሏል" ብሎ ከተናገረ፣ በምዕራፍ 3 ላይ እነዚህን ቃላት ሊናገር የሚችለው እንዴት ነው? ይህ ትርጉም አይሰጥም።

የተጻፈበት አውድ ትርጉሙን ይገልጻል። በ 1 ዮሐንስ 1፥7 መሰረት ከኃጢያት መንጻት ቃል ተገብቶልናል። ይህ መንጻት የተሰጠው በብርሃን ለሚመላለሱ ነው፤ ይህ ማለት ደግሞ ለእውነት የሚኖሩና ለእግዚአብሔር ለሚታዘዙ ነው። እግዚአብሔርን እየታዘዙ እየኖሩ ያሉ በክርስቶስ ደም ካለፈ ኃጢያታቸው ነጽተዋል።

ነገር ግን ሃጥያት እንደሰሩና መንጻት እንደሚያስፈልጋቸው የሚክዱ አንዳንድ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚያ ሰዎች ሃጥያት የለብንም ብለው ራሳቸውን የሚያስቱ ናቸው። በፍጹም ኃጢያት እንዳልሰሩ ወይም የኃጢአት ችግራቸውን ያለ ክርስቶስ እንደፈቱ ይናገራሉ።

በድጋሚ በ1 ዮሐንስ 1፥9 ይቅር መባል እና ከኃጢያት መንጻት ቃል ተገብቷል። በ1 ዮሐንስ 1፥10 ኃጢያት አልሰራንም የሚሉ ከእግዚአብሔር ከራሱ ጋር እንደሚቃረኑ ጸሃፊው በድጋሚ ይገልጻል።

ዮሐንስ በክርስቶስ የቀረበውን መንጻት እና ይቅር መባል እንደሚያስፈልጋቸው ያላሰቡትን፤ መዳንም አያስፈልገንም ለሚሉ ስህተታቸውን ለማስተካከል የጻፈው ነበር። አማኞች እንኳን ኃጢአት መሥራታቸውን ቀጥለዋል እያለ አልነበረም፤ ምክንያቱም በዚህ ደብዳቤ ላይ ካለው ዋና አጽንዖት እና ቀጥተኛ መግለጫዎች ጋር ይቃረናል።

## የእግዚአብሔር ጸጋ ድል ለሚነሳ ህይወት

የተወረሰ ውድቀት እና በሰው ልጅ ድክመት ምክንያት ድል የሚነሳ ህይወት መኖር ሁልጊዜ ቀላል አይደለም። በዚህ ምክንያት ብዙ ሰዎች የፍቃድ ኃጢአት ሳይሠሩ መኖር የማይቻል እንደሆነ ያምናሉ። ግን የእግዚአብሔር ጸጋ ለሁለቱም ችግሮች መልስ አለው።

► የተወረሰ ውድቀት ምንድን ነው?

***የተወረሰ ውድቀት*** የሰው ልጅ ከተወለደ ጀምሮ ወደ ኃጢአት እንዲያዘነበል የሚያደርግ የተፈጥሮ ሞራል መበላሸት ነው። አማኝ ከዳነ በኋላ ከዚህ የኃጢአት ዝንባሌ ጋር ይታገላል። ነገር ግን እግዚአብሔር ጸጋን የሚያቀርበው ለዕለት ተዕለት ድል ብቻ ሳይሆን ከውርስ ሃጥያት ለማጽዳትም ነው (ሐዋርያት ሥራ 15፥9፤ 1 ተሰሎንቄ 5፥23፤ 1 ዮሐንስ 1፥7)።

የኃጢአተኛ ተፈጥሮ ለምድራዊ ሕይወታችን በሙሉ መገዛት ያለብን ቅድመ ሁኔታ አይደለም። አንድ አማኝ በድል ለመኖር ያለ ምንም ገደብ ልቡን ለእግዚአብሔር አሳልፎ የሚሰጥበት ደረጃ ላይ መድረስ አለበት (ሮሜ 12፥1)። አማኙ በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ እንዲወድ ያስችለዋል።

▶ የሰው ድክመት ምንድን ነው?

***የሰው ድክመቶች*** አካላዊ ወይም አዕምሯዊ ውስንነቶች ወይም ጉድለቶች ናቸው። አዳም በኃጢአት በመውደቁ እና የሰው ልጅ ቀጣይነት ባለው ኃጢአት በመውደቁ ምክንያት፣ እግዚአብሔር እንድንሆን ካደረገን በአእምሮ፣ በአካል እና በስሜት ደካሞች ነን።

ድክመቶች ስሕተት እንድንሠራ ያደርጉናል። በአንድ ሁኔታ ውስጥ ማድረግ ያለብንን ትክክለኛ ነገር አናውቅ ይሆናል። ስለ አንዳንድ ሰዎች ወይም ብሄረሰቦች የተሳሳቱ አመለካከቶች ሊኖሩን ይችላሉ። አንድ ሰው ሲድን የተሳሳቱ አመለካከቶቹ ወድያውኑ አይስተካከሉም። የተሳሳቱ ሃሳቦች የተሳሳቱ ድርጊቶችን ያስከትላሉ፤ ምክንያቱም አንድ ሰው ምን ማድረግ እንዳለበት ከተሳሳተ፤ የተሳሳተ ነገር ያደርጋል።

አንድ ሰው ድክመቶቹ በተለያዩ ምክንያቶች ሊያስቸግሩት ይችላሉ። ምናልባት መጽሃፍ ቅዱሳዊ መርሆችን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት አልተማረ ይሆናል። ምናልባትም ስሜቶቹን ለመቆጣጠር የሚረዳውን ስርአት አላዳበረም ይሆናል። ምናልባትም ጠንካራ ሆኖ እንዲቀጥል የሚረዱት የዕለት ተዕለት ልምምዶች የሉት ይሆናል። ምናልባትም በመንፈስ የመመላለስን አስፈላጊነት አልተረዳ ይሆናል።

> "ሰዎች ወደ ቅድስና አይሳቡም። በጸጋ ከሚደረግ ጥረት በቀር ሰዎች እግዚአብሔርን ወደመምሰል፣ ለጸሎት፣ ቃሉን ለመታዘዝ፣ ወደ እምነት እና በጌታ ደስ ወደመሰኘት አይሳቡም። ወደ ድርድር እንሄድና መቻቻል እንለዋለን፤ ወደ አለመታዘዝ እንገዛና ነፃነት ብለን እንጠራዋለን፣ ወደ አጉል እምነት እንገዛና እምነት ብለን እንጠራዋለን። ራስን የመግዛት ዲሲፕሊን ማጣት እናከብርና መዝናናት ብለን እንጠራዋለን፤ ወደ ጸሎተ-አልባነት እንሻገርና ከህጋዊነት አምልጠናል ብለን ራሳችንን እናታልላለን። ወደ አምላክ የለሽነት ተንሸራተን ነፃ እንደወጣን እራሳችንን እናሳምነዋለን።
>
> ዲ.ኤ.ካርሰን

ሌሎች በፈቃድ/ አውቀው/ ኃጢአት እየሰሩ እንደሆነ ሁልጊዜ ማወቅ ስለማንችል በሌሎች ላይ ለመፍረድ መቸኮል የለብንም። ብዙውን ጊዜ ሰዎች የሚሳሳቱት እውቀትና መንፈሳዊ ብስለት ስለሌላቸው ነው።

ሌላ ማንም ሰው መቼም ሊያጋጥመው አይችልም ብለው ያሰቡት ፈተና አጋጥሞዎት ያውቃል? በኃጢያት ላይ ሙሉ በሙሉ በድል መኖር በእርግጥ ይቻል ይሆን ብለው ጠይቀው ያውቃሉ? አምላክ በፈተናዎች ውስጥ ድክመታችንን እንድንቋቋም የሚያስችል የበለጠ ጸጋን እንደሚሰጠን ቃል ገብቶልናል።

> *በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም፤ እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገሥ እንድትችሉ፣ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል* (1 ቆሮንቶስ 10፥13)።

► ከዚህ ጥቅስ የምናውቃቸው አንዳንድ ነገሮች ምንድናቸው?

ይህ ጥቅስ ብዙ አስፈላጊ ነገሮችን ይነግረናል።

1. **ፈተና የሚመጣው በሰውነታችን ምክንያት ነው።** ይህ ማለት የሚያጋጥምህ ትግሎች ለአንተ ልዩ አይደሉም ማለት ነው።

2. **እግዚአብሔር ገደባችንን ያውቃል።** ምን ያህል መቋቋም እንደምንችል ይረዳል። እኛ ምን ያህል መቋቋም እንደምንችል አናውቅም፤ እሱ ግን ያውቃል።

3. **እግዚአብሔር ወደ እኛ የሚመጡትን ፈተናዎች ገደብ ያበጃል።** በድል እንድንኖር ይፈልጋል። በዚህ ጥቅስ መሰረት ሁል ጊዜ ድል ማድረግ ይቻላል።

4. **እግዚአብሔር በድል እንዲንኖር የሚያስፈልገንን ይሰጣል።** ማምለጫ መንገዱን ያዘጋጃል፤ የእግዚአብሔር ሃሳብ በድል የተሞላ ህይወት እንድንኖር ነው። ለድል ህይወት ጸጋን ይሰጣል።

## በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ መኖር

► ሮሜ 8 አውጡና በዚህ ክፍል ውስጥ የተጠቀሱትን ጥቅሶች ተመልከቱ።

ሮሜ 8 መንፈስ በአማኙ ሕይወት ውስጥ ስለሚሰራው አስደናቂ ሥራ መግለጫ ይሰጣል። ሮሜ 8፥26 መጸለይ እንደሚገባን እንዴት መጸለይ እንዳለብን እንኳን እንደማናውቅ ይነግረናል፤ ግን መንፈስ ቅዱስ በእኛ በኩል ይጸልያል።

ይህ ምዕራፍ የድል ሕይወት እንዴት መኖር እንደሚቻል ይነግረናል። ከሥጋ ይልቅ መንፈስን የምንከተል ከሆነ አንኮነንንም (ሮሜ 8፥1፣ 4)። የመንፈስ ኃይል በእኛ ውስጥ ስለሚሠራ እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀውን ጽድቅ ማሟላት እንችላለን (ሮሜ 8፥4)።

> "ለእግዚአብሔር አስፈላጊ መሆን አለበት፤ ምክንያቱም እሱ ራሱ እንዲህ ብሎናል። 'ያለ ቅድስና ማንም ጌታን ማየት አይችልም' (ዕብራውያን 12፥14)። ቅድስና የአድርጉና አታድርጉ ዝርዝር አይደለም፤
>
> ከዚህ ይልቅ ክርስቶስን መምሰል ነው።"
>
> -ጂም ሲምባላ

አንድ ሰው በኃጢአተኛ ተፈጥሮው ቊጥጥር ሥር ከሆነ እግዚአብሔርን ማስደሰት አይችልም (ሮሜ 8፥8)፤ ይኮነናል (ሮሜ 8፥1) እንዲሁም በእግዚአብሔር ይፈረድበታል (ሮሜ 8፥13 ላይ "ሞት")። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እና ምሪት የኃጢአትን ስራ ማስወገድ እንችላለን (ሮሜ 8፥13-14)።

## በክርስቶስ መኖር

በዮሐንስ 15፥1-10 ላይ ስለ ወይኑና ቅርንጫፎቹ የሚገልጸው ታዋቂ ምሳሌ ይገኛል፤ ለአንዳንድ አስፈላጊ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል።

በክርስቶስ የምንኖረው እንዴት ነው? "ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ" (ዮሐንስ 15፥10)። በክርስቶስ መኖር ማቆም ማለት አንድ ሰው እርሱን መታዘዙን አቁሟል ማለት ነው። ቀጣይ ምን ይከሰታል?

“በእኔ የማይኖር ተጥሎ እንደሚደርቅ ቅርንጫፍ ነው፤ እንዲህ ያሉት ቅርንጫፎች ተለቅመው ወደ እሳት ይጣላሉ፤ ይቃጠላሉም” (ዮሐንስ 15፥6)። አንድ ሰው መታዘዙን ካቆመና በዚህም በክርስቶስ መኖሩን ካቆመ ይጣላል። ። የተቃጠሉ ቅርንጫፎች ምሳሌ ሙሉ በሙሉ መጣላቸውን ያሳያል።

“በእኔ ኑሩ፤ እኔም በእናንተ እኖራለሁ። ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ካልሆነ በቀር ብቻውን ፍሬ ሊያፈራ አይችልም፤ እናንተም በእኔ ካልኖራችሁ ፍሬ ልታፈሩ አትችሉም” (ዮሐንስ 15፥4)። “በእኔ ያለውን፣ የማያፈራውን ቅርንጫፍ ሁሉ ቈርጦ ይጥለዋል” (ዮሐንስ 15፥2)። በክርስቶስ በመታዘዝ ካልኖርን ፍሬ ማፍራት አንችልም። ፍሬ ማፍራት ማለት የተለወጠ፣ የተባረከ እና በእግዚአብሔር ጸጋ የሚመራ ሕይወት መኖር ማለት ነው። እግዚአብሔርን የማይታዘዝ ሰው እርሱ ከሚያቀርበው የሕይወት ፍሰት ራሱን ይለያል፤ እንዲሁም ከእንግዲህ የእግዚአብሔርን ጸጋ መጠቀም አይችልም። ፍሬ የማያፈራ ሁሉ ይጣላል።

ክርስቶስ እንደ ወይን ግንድ ሕይወትን የሚሰጠን ነው (ዮሐንስ 15፥6)። መዳን የሚጠበቀው በግንኙነት ነው። ከክርስቶስ መለያየት ከድነት መለየት ነው። እግዚአብሔርን በመታመንና በመታዘዝ ከክርስቶስ ጋር ያለንን የድነት ትስስር እንጠብቃለን (ዮሐንስ 15፥10)።

የመብራት አምፖሎች እና ኤሌክትሪክ ተመሳሳይ ጽንሰ-ሀሳብ ያለው ዘመናዊ ምሳሌ ናቸው። አንድ አምፖል የኤሌክትሪክ ኃይል ወደ ውስጥ ሲፈስ ብርሃን ይኖረዋል። አምፖሉ ከኃይል ምንጩ ከተለየ ብርሃኑን ማቈየት አይችልም። በተመሳሳይም ከክርስቶስ ጋር ባለን ግንኙነት የዘላለም ሕይወት አለን (ዮሐንስ 17፥3)። የእርሱ ሕይወት በእኛ ውስጥ ይፈስሳል። ይህን ህይወት ራሳችንን ከእርሱ ከለየን መጠበቅ አንችልም።

### መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስጠንቀቂያ

አንዳንዶች አንድ ስም በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ከተፃፈ በኋላ ሊሰረዝ የሚችልበት ምንም መንገድ እንደሌለ ይናገራሉ። ይሁን እንጂ አንድ ስም ሊሰረዝ የሚችልበት ቢያንስ አንድ መንገድ አለ:-

> ማንም በዚህ የትንቢት መጽሐፍ ከተጻፈው ቃል አንዳች ቢያጐድል፣ እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ ዕድሉን ያጐድልበታል (ራእይ 22፥19)።

ከራእይ መጽሐፍ ክፍል በመሰረዝ ጥፋተኛ የሆኑ በጣም ጥቂት ሰዎች አሉ። ይሁን እንጂ አንድ ሰው ስሙ ከሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ሊሰረዝ እንደሚችል ተገልጿል።

እየሱስ እንዲህ ሲል ተስፋና ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል:- “ድል የሚነሣም እንደ እነርሱ ነጭ ልብስ ይለብሳል፤ ....ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስስም” (ራእይ 3፥5)።

ጳውሎስ የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች እምነታቸውን ሊተዉ እንደሚችሉ በማሰብ ተጨንቆ ነበር። እንዲህ ቢሆን ኖሮ ለእነሱ ያከናወነው የወንጌል ድካም ከንቱ ይሆን እንደነበር ተናግሯል (1 ተሰሎንቄ 3፥5)። ይህ የሚያሳየው አንድ አማኝ እምነቱን ሙሉ በሙሉ ጥሎ የቀድሞ ድነቱን ዋጋ ቢስ ሊያደርገው ይችላል።

በ2 ጴጥሮስ 2፥18-21 ውስጥ ጌታችንና መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስን በማወቃቸው የዓለምን ርኵሰት ያመለጡ አንዳንድ አማኞችን የሚያስቱ የሐሰት አስተማሪዎች እናገኛለን። እነዚህ የቀድሞ አማኞች የጽድቅን መንገድ አውቀው

የተዉ ናቸው። ይህ ክፍል ኃጢአተኛ ወደሆነ የአኗኗር ዘይቤ ከመመለስ ይልቅ መንገዱን ፈጽሞ ባያውቁ ይሻላቸው እንደነበር ይናገራል። ይህ ጥቅስ አንድ ሰው ወደ ኃጢአት በመመለስ ድነቱን ሊያጣ እንደሚችል ያሳያል። አንድ ሰው ድነቱን ሊያጣ ባይችል ኖሮ አንድ ሰው ከመዳኑ በፊት ከነበረው የከፋ ሁኔታ ውስጥ ሊገባ አይችልም ነበር።

ልጅነት ሊለወጥ ይችላል። በአንድ ወቅት የዲያብሎስ ልጅ (ዮሐንስ 8፥44) እና የቊጣ ልጆች (ኤፌሶን 2፥3) ነበርን። ነገር ግን ያ ልጅነት በእግዚአብሔር ልጅነት ተቀየረ (ሮሜ 8፥15)። አባካኙ ልጅ ከአባቱ ተለይቶ በነበረበት ወቅት የልጅነት መብቱን ሁሉ አጣ። በተመለሰ ጊዜ ግን አባቱ እንደ ሞተ ቆጥሮት እንደነበር ተናግሯል (ሉቃስ 15፥32)።

እግዚአብሔር አማኞች ደኅንነት እንዲሰማቸው ይፈልጋል፤ ግን ስሜታቸውን በሐሰተኛ ማረጋገጫ ላይ በመመስረት እራሳቸውን አደጋ ላይ እንዲጥሉ አያደርጋቸውም። እግዚአብሔር ቃል ያልገባውን ነገር ለአማኞች ቃል መግባት የለብንም። ማንኛውንም ነገር ብናደርግ ድነታችንን እንደማናጣ ዋስትና አይሰጠንም። ነገር ግን ኃጢአትን ድል በማድረግ እንድንኖር እንደሚመራንና እንደሚያስችለን ቃል ገብቷል። ይህም ከፍርሃት ነጻ እንድንሆን በቂ ማረጋገጫ ነው።

አንዳንድ ጊዜ አማኞች ስለመዳናቸው ጥርጣሬ ይኖራቸዋል። በአንድ ወቅት እንደዳኑ እርግጠኛ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ሆኖም አሁንም ከእግዚአብሔር ጋር የሚያድን ግንኙነት እንዳላቸው ይጠራጠራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ አስፈላጊ ጥያቄ ላይ ጥርጣሬ ውስጥ አይተወንም። የእግዚአብሔር ፈቃድ አማኙ በመዳኑ እርግጠኛ ሆኖ ለመጨረሻ ሑነቶች ድፍረት እንዲኖረው (1 ዮሐንስ 4፥17) እንጂ የእግዚአብሔርን ምርመራ ማለፍ/ አለማለፍ ላይ እንዲጠራጠር አይደለም።

አንድ አማኝ ጥርጣሬ ሲኖረው በአንድ ወቅት እንደዳነ እርግጠኛ ስለሆነ በቀላሉ ችላ ሊላቸው አይገባም። በእምነት መሆናችሁን ለማወቅ ራሳችሁን መርምሩ (2 ቆሮንቶስ 13፥5)። የሚለው ተገቢ ነው። አንድ ሰው ለመዳን የሚያስፈልጉትን መጽሃፍ ቅዱሳዊ እርምጃዎች በመከተል እንደዳነ የሚያውቅ ከሆነና በታዛዥነት በመመላለስ በክርስቶስ ውስጥ እንደሚኖር የሚያውቅ ከሆነ መንፈሳዊ ሕይወት እንዳለው እርግጠኛ መሆን ይችላል።

### ማስወገድ ያለብን ስህተት፥ ዝቅተኛ መጠበቅ

*ለክፍሉ መሪ ማስታወሻ- ሁለት የክፍሉ አባላትን ይህንን እና የሚቀጥለውን ክፍል ያስረዱ።*

ለሰዎች ኃጢአትን ማሸነፍ በሁለት ነገሮች ምክንያት የማይቻል ይመስላል፤ በሰው ድክመት እና የተወረሰ ውድቀት። እግዚአብሔር በሰው ልጅ ውሱንነት እንደማይፈርድብን ማስታወስ አለብን። ፈቃዱን እንፈጽም ዘንድ እግዚአብሔር በመንፈሱ ኃይል ይሰጠናል። ድካም መኖሩ ኃጢአት አይደለም፤ እንዲሁም ማንም ሰው በድካም ምክንያት ኃጢአት ሊሠራ አይገባም።

የተወረሰ ውድቀት ተጽዕኖ ከድነት በኋላም ይቀጥላል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ለመንጻት የሚሆን ጸጋን ይሰጣል። ከተወረሰ ውድቀት ጋር በመወለዳችን አይፈረድብንም፤ ነገር ግን በተፅዕኖው ስር ከቀጠልን ጥፋቱ የእኛ ነው። ስለዚህ የሰው ድካምም ሆነ የተወረሰ ውድቀት በድል የመኖር ተስፋችንን እንድናጣ ሊያደርገን አይገባም።

በክርስቶስ በማመን ከእርሱ ጋር አንድ ሆነናል። በሞቱና በትንሣኤው ከእርሱ ጋር ተባብረናል፤ ይህ ማለት ለእኛ ለኃጢአት መሞት እና ለአዲሱ ሕይወት ትንሣኤ ማለት ነው (ሮሜ 6፥3-11)። እርሱ በእኛ ውስጥ ነው፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ነን። የክርስትና ሕይወት የተቻለንን ሁሉ ማድረግ የእርሱን ምሳሌ ለመከተል መሞከር ብቻ አይደለም። የክርስትና ሕይወት ክርስቶስ በእኛ ውስጥ የሚኖረው ነው። እርሱ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ በኃጢአት ላይ ድል ነስቷል፤ አሁንም በእኛ ውስጥ በድል ይኖራል።

## አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

በታላቋ ከተማ ጐዳና አንድ ጥግ ላይ አንዲት ድሀ ሴት ቡትቶ ለብሳ ተቀምጣለች። ፀጉሯ በቆሻሻ ተጨማልቆ እስርስር ያለ ነው። ቆዳዋ ቆሻሻና ሚከረፋ ነው። በተስፋ መቍረጥ ውስጥ ተቀምጣለች። ድንገት ታላቅ ሁከት ሆነ፤ በአንዱ ጥግ የመንግሥቱ ታላቁ ልዑል ከባለሥልጣኖቹ ጋር ይጓዛል። ልዑሉ ቈንጆ፣ ጠንካራ እና ደግ ነው! ሰረገላው ቆሸሽ ብላ በተቀመጠችበት ሴት በኩል ሲያልፍ ልዑሉ ለአሽከርካሪው “አቁም!” ብሎ ጮኸ። ሰረገላው ሲቆም ልኡሉ ለአገልጋዮቹ " በመንገድ ዳር የተቀመጠችው ሴት ማግባት የምፈልጋት ሴት ናት!” አላቸው።

አሁን ቦታው ትቀይሯል፤ በቤተ መንግሥቱ የሠርግ ቀን ላይ። ምን እናያለን? በቡትቱ ልብሷና ከነቆሻሻ ጸጉሯ የተቀመጠች ቁሽሽ ያለች ሴት ነበረች። የግል አገልጋዮቿ የሰርግ ልብስ፣ ሳሙናና ሽቶ ይዘው በዙሪያዋ ናቸው፤ ሙሽራዋ ግን ለሠርጓ ቀን ራሷን ለማዘጋጀት ፍላጐት የላትም። አንደኛው አገልጋይ "እመቤቱ ለሠርጉ መዘጋጀት አትፈልጊም?" ብላ ጠየቀቻት። ሙሽራይቱም "እሱ ሲያየኝና ሊያገባኝ ሲፈልግ እንዲህ ነበርኩ፤ ስለዚህ አሁንም ምንም ብመስል ለውጥ አያመጣም ብዬ እገምታለሁ" ብላ መለሰችላት።

እኛም በእንደዚህ ዓይነት አቋም እንደነግጥ ነበር። ልኡሉ ስለሚወዳት በነበረችበት ሁኔታ እንድትቆይ አይፈልግም። ልዑሉ የምትማርክ ባልነበረችበት ጊዜ ስለወደዳት ፤ እሷም ለእሱ ምርጥ ሆኖ ለመታየት መፈለግ ይኖርባታል።

እግዚአብሔር ኃጢአተኞች ሆነን ሳለን ይወደናል፤ ይህ ማለት ግን ኃጢአት ምንም ለውጥ አያመጣም ማለት አይደለም። እርሱ ስለሚወደን ሁኔታችንን ለመለወጥ ይፈልጋል። እርሱ ስለሚወደን እርሱን የሚያስደስት መልክና ባህሪ ለመልበስ መፈለግ አለብን።

## በድል አድራጊነት ለመኖር የሚረዱ ተግባራዊ መርሆች

በዓለም ዙሪያ የክርስትና እውነት ከአጉል እምነት ጋር እየተቀላቀለ ነው። አንዳንዶች በተደጋጋሚ ጸሎት፣ በስሜት ተኮር ልምምዶች፣ ክፉ መናፍስትን (የተወሰኑ ኃጢአቶች መንስኤ ናቸው ተብለው በሚታሰቡ) በመገሰፅ፣ ራስን በመጉዳት በሚደርስ ሥቃይ፣ የተወሰኑ ክታብ በማድረግ፣ በቤት ውስጥ መንፈሳዊ ምልክቶችን በማስቀመጥ ወይም ሰውነትን በልዩ ዘይት በመቀባት ኃጢአትን ማሸነፍ እንደሚቻል ያስተምራሉ። በመንፈሳዊ ተአምራት አማካኝነት ድል እናገኛለን ብሎ መጠበቅ ስሕተት ነው።

አንዳንዶች ደግሞ ኃጢአትን ድል ማድረግ አቅልለው ያስተምራሉ። የድነት ልምዶች እና በመንፈስ መሞላት የኃጢአትን ኃይል በቋሚነት ያስወግዳል ይላሉ። የመንፈሳዊ እድገት፣ ስነ ስርአት እና የማያቋርጥ ንቃት አስፈላጊነት ላይ አጽንዖት አይሰጡም።

በዓለምና በኃጢአት ላይ የማያቋርጥ ድል ማግኘት ያልቻሉ ራሳቸውን በቅንነት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቃቸው ተገቢ ነው:-

1. **በእውነት ዳግመኛ ተወልጄአለሁን?** ለቀድሞ ሕይወቴ ሞቼአለሁን? ንስሐ ገብቼ ትቼዋለሁን? በክርስቶስ አዲስ ሕይወት አለኝን:- አዲስ አመለካከት፣ አዲስ ምኞት፣ ለእግዚአብሔር ነገሮች አዲስ ፍላጐት አለኝን (2 ቆሮንቶስ 5፥17)?ክርስቶስ በልቤ ውስጥ ለመኖር የመጣው በመንፈስ ቅዱስ በኩል ነውን? ኃጢአትን ለማሸነፍ በሰው ፈቃድ ኃይል እየሞከርኩ ነው ወይስ በውስጤ በሚኖረው በእግዚአብሔር ኃይል ነው የምደገፈው (ገላትያ 2፥20)?

2. **የአምላክን ቃል በልቤ ውስጥ እያኖርኩ ነው?** መዝሙረኛው "አንተን እንዳልበድል፣ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ" (መዝሙር 119፥11) ብሎ መስክሯል። ልክ አዲስ የተወለደ ሕፃን የእናቱን ወተት በጉጉት እንደሚመገብ የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ አለብን (1 ጴጥሮስ 2፥2)።

3. **ለኃጢአት የሞተ እንደሆንኩና ለእግዚአብሔር ሕያው እንደሆንኩ አድርጌ እቈጥራለሁ?** "እንደዚሁም ለኀጢአት እንደ ሞታችሁ፣ ነገር ግን በክርስቶስ እየሱስ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቍጠሩ" (ሮሜ 6፥11)። ፈተና በእኔ ላይ ሥልጣን እንደሌለው በመተማመን ፈተናውን እቃወማለሁ?

4. **ለማሸነፍ በእግዚአብሔር ላይ እደገፋለሁ?** ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ የተወለደ ሁሉ ዓለምን እንደሚያሸንፍ ሐዋርያው ዮሐንስ ገልጿል። "ዓለምን የሚያሸንፈውም እምነታችን ነው" (1 ዮሐንስ 5፥4)። ሐዋርያው ጳውሎስ ከእየሱስ መስቀል በቀር በምንም ነገር ላይ እምነት እንደሌለው ተናግሯል፤ ምክንያቱም ዓለማዊ ነገሮች እኛን ለመሳብና ለመቈጣጠር ያላቸውን ኃይል የሚያጡት በመስቀሉ አማካኝነት ነው (ገላትያ 6፥14)። የጽድቅ ሁሉ ምንጭ የሆነውን እየሱስን የምንረሳ ከሆነ የፀና የድል ሕይወት መኖር አንችልም።

5. **ሁልጊዜ ጌታ እየሱስን በእምነት እየለበስኩ ኃጢአትን እድል ፈንታ እያሳጣሁ ነው?** በክርስቲያና ጉዞአችን የትም ብንሆን ድል ወድያው የሚመጣ አይደለም። ኃጢአትን በተመለከተ የእየሱስን አመለካከት በንቃት ማዳበርና ምሳሌውን መከተል ይኖርብኛል። (ሮሜ 13፥14፣ ኤፌሶን 4፥24)

6. **የእግዚአብሔርን መንፈሳዊ የጦር እቃ እየተለብስኩ ነው?** በሕይወት ውጊያ ሜዳ ላይ ብዙ አማኞች መንፈሳዊ መከላከያዎቻቸው ላይ ጥንቃቄ ባለማድረጋቸው ብቻ በሰይጣን የእሳት ፍላጻዎች ተጎድተዋል (ኤፌሶን 6፥11)።

7. **ራስን የመግዛት ባሕርይ እያዳበርኩ ነውን?** በእምነታችን የቱንም ያህል ብስለት ቢኖረን ራስን የመግዛት ባሕርይ ማዳበር ያስፈልገናል። ሰውነቴን እያሠለጠንኩ በስርአት ውስጥ እያስገባሁት ነው? ተፈጥሯዊና ከእግዚአብሔር የተሰጡ ፍላጐቶቼን (እንደ ምግብ፣ እንቅልፍ ወይም ፆታዊ ግንኙነት)፤ አዲስ የተወለደው ነብሴን አላማ ያገለግሉ ዘንድ አስገዛለሁ። ሰውነቴ በኃጢአት ስለተበላሸ ስለሆነ ምኞቶቹ ሚዛናዊ አይደሉም። ሰውነት እንዲገዛ ሊፈቀድለት አይገባም፤ መንፈስን ማገልገል አለበት። ጳውሎስ መንፈሳዊ መስሎ የተጣለ ሰው እንዳይሆን ሰውነቱን እንደሚጎስምና እንዲገዛለት እንደሚያደርግ ተናግሯል (1 ቆሮንቶስ 9፥25-27)። ይህ ተግሣጽ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን አስፈላጊ ነው።

8. **ታዛዥ በመሆን እየኖርኩ ነው?** "በብርሃን ብንመላለስ" የሐዋርያው ዮሐንስ ምክር ነው (1 ዮሐንስ 1፥7)። ወደ መንግስተ ሰማይ በሚወስደው መንገድ ላይ ብዙ ወጥመዶች፣ መሰናክሎች እና አደገኛ ቦታዎች ስላሉ ሁል ጊዜ በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን (መዝሙር 119፥105) እና በመንፈስ ቅዱስ መገኘት (ዮሐንስ 14፥ 26)ውስጥ መመላለስ አለብን። ወደ ብርሃን መንገድ ለመመለስ ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች በጨለማ ውስጥ መመላለሳቸው እንዲሰናከሉ፣ እንዲወድቁና በመጨረሻም እንዲሞቱ ያደርጋል።

► የእምነት መግለጫውን ቢያንስ ሁለት ግዜ አብራችሁ አንብቡ።

**የእምነት መግለጫ**

እያንዳንዱ አማኝ ድል አድራጊ የሆነ ክርስቲያናዊ ሕይወት የመኖር መብት እና ግዴታ አለው። አማኙ ከክርስቶስ ጋር ባለው ግንኙነት ሕይወት አለው። እምነት ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኘን ነው፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የማይቀበል እና ወደ ኃጢአት የሚመለስ አማኝ ይህን እምነት ሊያዳክምና ጨርሶ ሊያጠፋውም ይችላል። አማኝ እያንዳንዱን ፈተና ማሸነፍ እንዲችል እግዚአብሔር የሚያበረታ ጸጋን ይሰጣል።

## **ትምህርት 9 የቤት ስራዎች**

(1) **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የቤት ስራ፡-** ከታች ከተዘረዘሩት ዘርፎች መካከል እያንዳንዱን ተማሪ አንድ ይመደብ። ከሚቀጥለው ክፍለ ግዜ በፊት ክፍሉን አንብባችሁ በትምህርቱ ውስጥ ካለው ሃሳብ ላይ ምን እንደሚናገር በአንድ አንቀፅ ፃፉ።

- ማቴዎስ 13፥18-23
- ዕብራውያን 10፥23-39
- ያዕቆብ 1፥21-27
- 2 ጴጥሮስ 1፥1-11
- ራእይ 3፥14-22

(2) **ፈተና፡-** የሚቀጥለው ክፍለ ግዜ የምትጀምሩት በትምህርት 9 ፈተና ነው። ለፈተና ዝግጅት እንዲሆን የፈተና ጥያቄዎችን አጥኑ።

(3) **የማስተማር የቤት ስራ፡-** ከክፍል ውጪ የማስተማርያ ግዜን ቀጠሮ መያዝ እና ማስተማራችሁን ሪፖርት ማድረግ አስታውሱ።

## **ትምህርት 9 ፈተና**

(1) የ1ኛ ዩሐንስ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

(2) 1ኛ ዩሐንስ በአንድ አማኝ ሕይወት ውስጥ ይበልጥ አጽንኦት የሰጠው ባህሪ የቱ ነው?

(3) ከ1 ቆሮንቶስ 10፥13 ላይ የምናገኛቸው አራት ነገሮች ምንድን ናቸው?

(4) አማንያን በክርስቶስ መሆን/ ከክርስቶስ ጋር መጣበቅ የሚቀጥሉት እንዴት ነው?

(5) በክርስቶስ ያልንን የድነት ግንኙነት በምን መጠበቅ እንችላለን?

# ትምህርት 10

# መንፈስ ቅዱስ

## የትምህርቱ አላማ

(1) ተማሪው የሚከተሉትን ማስረዳት ይችላል

- በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ባህርያት
- ከመጽሐፍ ቅዱስ በመነሳት ስለመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት እና ስብዕና ማስረዳት
- የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት እና ስብዕና ለምን መሰረታዊ የክርስትና ትምህርት እንደሆነ መግለጽ
- የመንፈስ ቅዱስ ሚና በታሪክ ውስጥ እና በዚህ ዘመን
- ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ህብረት ያለው አማኝ ያለውን ተግባራዊ የህይወት ልምምድ መረዳት
- ስለመንፈስ ቅዱስ ክርስቲያናዊ የእምነት መግለጫ

(2) ተማሪው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በተመለከተ ያሉ መመሪያዎችን ይተገብራል።

## መግቢያ

► መዝሙር 139 አብራችሁ አንብቡ። ይህ ክፍል ስለ እግዚአብሔር መንፈስ ምን ይነግረናል?

አንዳንድ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ስሜትን የሚቀሰቅስ፣ ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ኃይል፣ ማንነት የሌለው ወይም ዝም ብሎ መገኘት ብቻ እንደሆነ ያስባሉ። ለምሳሌ የይሖዋ ምስክሮች “መንፈስ ቅዱስ በራሱ ስብዕና ያለው የሥላሴ አካል ሳይሆን እግዚአብሔር ፈቃዱን ለመፈፀም የሚጠቀምበት ኃይል ነው፤ በተወሰነ መልኩ ከኤሌክትሪክ ኃይል ይመሳሰላል”[20] ብለው ያምናሉ።

► ይህ የይሖዋ ምስክሮች ግንዛቤ የተሳሳተ የሆነው ለምንድነው?

> “ከአብና ከወልድ ጋር በሚሰገድለትና በሚከበር፣ ከአብና ከወልድ በሚሠርጽ፣ በነቢያት በተነገረ፣ የሕይወት ጌታና ሰጪ በሆነ፣ በመንፈስ ቅዱስም አምናለሁ።”
>
> የኒቂያ የእምነት መግለጫ 325 ዓ.ዓ

የይሖዋ ምስክሮች መንፈስ ቅዱስን በራሱ ስብዕና የሌለው ኃይል አድርገው ያዩታል። ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ አረዳድ ስለሌላቸው ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ህብረት ሊኖራቸው አይችልም።

እየሱስ የመንፈስ ቅዱስ ስራን በንፋስ መስሎታል። ፤ ድምፁንም ትሰማለህ፣ ነገር ግን ከየት እንደመጣ፣ ወዴት እንደሚሄድም አታውቅም (ዮሐንስ 3፥8)። ስለመንፈስ ቅዱስ እያንዳንዱን ነገር ልንረዳ እንችላለን ብለን መጠበቅ የለብንም። ነገር ግን ስለእርሱ ልናውቃቸው የምንችላቸው ነገሮች አሉ። እነዚህም ከእግዚአብሔር ጋር ላለን ህብረት በጣም አስፈላጊ ናቸው።

---

[20] Should You Believe in the Trinity? (New York፥ The Watchtower Bible and Tract Society, 1989)

*መንፈስ ቅዱስ ከቤተክርስትያን ጋር ስላለው መስተጋብር በጥልቀት የሚነግረን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ነው። ይህ መጽሐፍ የመጀመሪያዋ ቤተክርስትያን ለመንፈስ ቅዱስ የነበራትን ምላሽ ያሳየናል። ይህም:-*

1. *የመጀመሪያዎቹ አማኞች የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት አክብረዋል። (ሐዋርያት ሥራ 5፥3-4ን አንብብ)።*
2. *ለመንፈስ ቅዱስ መገኘት፣ ምሪት እና እንቅስቃሴ እውቅና ይሰጡ ነበር። (ሐዋርያት ሥራ 15፥28ን አንብብ)።*
3. *የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚደገፉና ለእርሱም ምላሽ የሚሰጡ ነበሩ። (ሐዋርያት ሥራ 4፥24፣31ን አንብብ)።*

> *በህግ በተናገረው፣ ነብያት ስለእርሱ ባስተማሩት፣ በዮርዳኖስ በወረደው፣ በሐዋርያት በተናገረው እና በቅዱሳን በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን። እርሱ ቅዱስ መንፈስ መሆኑን፤ የእግዚአብሔር መንፈስ፣ ፍጹም መንፈስ፣ ረዳት፣ ያልተፈጠረ፣ ከአብ የሚሰርጽ፣ በወልድ የሚሰጥ መሆኑን እናምናለን።*
>
> *-የኢጲፋነስ የእምነት መግለጫ 374 ዓ.ዓ*

*እኛም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ይህንን የመሰ ህብረት እንዲኖረን መለኮትነቱን እና ስብዕና ያለው አካል መሆኑን መረዳት ይኖርብናል።*

### መንፈስ ቅዱስ አካል/ መደብ አለው

*መንፈስ ቅዱስ ልክ እንደእየሱስ የሚዳሰስ ስጋ ያለው አካል ባይኖረውም ስብዕና ግን አለው። የእውነተኛ አካልነት/መደብ መገለጫዎች እውቀት (ሃሳብ)፣ ፈቃድ እና ስሜት ናቸው። መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ አለውን? እንደፈቃዱ መጠን ለቤተክርስቲያን ስጦታዎችን ይሰጣል (1 ቆሮንቶስ 12፥11)። መንፈስ ቅዱስ እውቀት (ሃሳብ) አለውን? "መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር እንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራል" (1 ቆሮንቶስ 2፥10)። መንፈስ ቅዱስ ስሜት አለውን? በኤፌሶን 4፥30 ላይ "ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ" ተብለናል። መንፈስ ቅዱስ የሚያዝን ከሆነ ስሜት አለው ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ እውቀት፣ ፈቃድ እና ስሜት ስላለው ስብዕና እንዳለው እንረዳለን።*

*► መንፈስ ቅዱስ አካል እንደሆነ መረዳት ለምን ይጠቅመናል?*

*ስብዕና ያለው አካል ከሌሎች ጋር ህብረት ማድረግ ይችላል። መንፈስ ቅዱስ ስብዕና የሌለው ኃይል ብቻ ቢሆን ኖሮ ከእርሱጋር ህብረት ማድረግ አንችልም ነበር። ነገር ግን በፊልጵስዩስ 2፥1 እና 2 ቆሮንቶስ 13፥14 መሰረት መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር ህብረት ያደርጋል፤ ስለዚህም ስብዕና አለው ማለት ነው።*

*ለክፍሉ መሪ ማስታወሻ- ስለመንፈስ ቅዱስ ስብዕና ተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ለማግኘት ወደመጨረሻ የሚገኘውን "ስለመንፈስ ቅዱስ ስብዕና የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች" በሚል ርዕስ ስር ያለውን ትምህርት ይመልከቱ።*

### መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው

*መንፈስ ቅዱስ ሁሉን አዋቂ፣ ሁሉን የሚያይ እና በሁሉም ስፍራ የሚገኝ አምላክ ነው። የአናንያንና የሰጲራን ታሪክ ታስታውሳላችሁ? በሐዋርያት ሥራ 5፥3-4 አናንያ ከመቀሰፉ በፊት ጴጥሮስ "መንፈስ ቅዱስን ትዋሽና…ሰይጣን*

ልብህን ለምን ሞላው?...የዋሸኸው እኮ እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አይደለም” ብሎት ነበር። ከዚህም መንፈስ ቅዱስን መዋሸት እግዚአብሔርን መዋሸት መሆኑን እንረዳለን። ይህም መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር መሆኑን ያሳያል።

***መንፈስ ቅዱስ ሁሉን አዋቂ ነው።*** በ1 ቆሮንቶስ 2፥10-11 መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ነገር ሁሉ እንደሚያውቅ እናነባለን። ይህ ልዕለ ተፈጥሯዊ ምጡቅ እውቀት ይፈልጋል። መንፈስ ቅዱስ የትንቢት መጽሐፍትን ጨምር ቅዱሳት መጽሐፍት እንዲፃፉ አነሳስቷል፤ ይህም ሁሉን አዋቂነቱን ያስረዳል። (2 ጴጥሮስ 1፥21 ይነበብ)። ቅዱሳት መጽሐፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዳለባቸው 2 ጢሞቴዎስ 3፥16 ይናገራል። ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው።

***መንፈስ ቅዱስ በሁሉም ስፍራ ይገኛል።*** መዝሙር 139፥7-10 ሰው ከእግዚአብሔር መንፈስ የሚያመልጥበት ስፍራ እንደሌለ ይነግረናል። ሮሜ 8፥9 መንፈስ ቅዱስ ከሁሉም አማኝ ጋር እንደሚገኝ ይነግረናል። የክርስቶስ መንፈስ የሌለው የክርስቶስ ወገን አለመሆኑን ያስረዳናል። ከዓውዱ እንደምንረዳው የክርስቶስ መንፈስ የተባለው መንፈስ ቅዱስ ነው።

***መንፈስ ቅዱስ ኃያል ነው።*** መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ሁሉ ያደርጋል። ዓለምን ስለ ኀጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ይወቅሳል (ዮሐንስ 16፥8)። ይህን ለማድረግ የእያንዳንዱን ሰው ህሊና መድረስና ለእያንዳንዱ እውቀት እውነትን ማስረዳት መቻል አለበት። ለእያንዳንዱ አማኝም የውስጥ ጥንካሬን ይሰጣል (ኤፌሶን 3፥16ን አንብብ)። በዓለም ዙሪያ ባሉ አማኞች ሕይወት ውስጥም ሑሉ የመንፈስ ፍሬ እንዲፈራ የሚያደርገው እርሱ ነው (ገላትያ 5፥22-23ን አንብብ)። ይህንን ከመለኮት በቀር ሌላ ማድረግ የሚችል የለም።

በሉቃስ 12፥10 ላይ መንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብን ቃል የሚናገር ሲል ስድብን ለማመልከት የተጠቀመበት ቃል እግዚአብሔርን ማቃለልን ለመግለጽ ብቻ የሚውልን ቃል ነው። ይህም መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር መሆኑን ያስረዳል።

***መንፈስ ቅዱስ ዘላለማዊ ነው*** (ዕብራውያን 9፥14)።

ሰውነታችን የእግዚአብሔር መቅደስ የተባለው መንፈስ ቅዱስ በዚያ ስለሚያድር ነው (1 ቆሮንቶስ 3፥16)።

ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች እንደምንረዳው፣ መንፈስ ቅዱስ ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ሲሆን፣ እርሱም በመለኮታዊ ሥላሴ ውስጥ ሦስተኛው አካል ነው።

► በመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት ማመን የሚገባን ለምንድነው?

የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት መረዳት ለእርሱ የሚገባውን ክብር እና አምልኮ እንድንሰጠው ይረዳናል። ስለዚህ ምነፈስ ቅዱስን አለማምለክ ከባድ ነገር ነው።

**መንፈስ ቅዱስ ከአብ እና ከወልድ ይለያል**

ይህን ስንል አንድ ሰው ከሌላው እንደሚለየው እንደዚያው መንፈስ ቅዱስ ከአብ እና ከወልድ ይለያል እያልን አይደለም። የሥላሴ አካላት አንዳቸው በሌላቸው ውስጥ ይኖራሉ፤ ሶስቱ አካላት አንድ እግዚአብሔር ነው። ነገር ግን እርስ በእርሳቸው ይነጋገራሉ፣ ይዋደዳሉ እንዲሁም በመካከላቸው ህብረት አለ።

በሥላሴ ውስጥ ስላለው ልዩ ልዩ አካል መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ለምሳሌ በዮሐንስ 14-16 እየሱስ ወደአብ ሲሄድ ስለሚልከው ረዳት (አጽናኝ) ደጋግሞ ያነሳል። (ዮሐንስ 14፥16-17ና 26፣ ዮሐንስ 15፥26፣ዮሐንስ 16፥7ና 13-15ን አንብብ)። ይህ ረዳት ደቀመዛሙርትን የሚያስተምርና የሚመራ እንደሆነም ይናገራል። እየሱስ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ቢሆን ኖሮ ስለሌላ ረዳት ማውራት ትርጉም አይኖረውም ነበር። በዚህ ክፍል እየሱስ ስለሌላ አካል እያወራ እንደሆነ መረዳት እንችላለን።

መንፈስ ቅዱስ የሚናገረው ከራሱ እንዳልሆነ፤ ክርስቶስ ከአብ የተቀበለውን የክርስቶስን ነገር እንደሚገልጥ እየሱስ ተናግሯል (ዮሐንስ 16፥13-15)። አብና ወልድ ከመንፈስ ቅዱስ የማይለዩ ቢሆኑ ኖሮ ይህ የእየሱስ አባባል ትርጉም አይሰጥም ነበር።

በእየሱስ ጥምቀትም የምንመለከተው ሶስቱ የሥላሴ አካላት በአንድ ጊዜ ግን በተለያየ ሁኔታ መገኘታቸውን ነው። ማርቆስ 1፥10-11 አብ ከሰማይ "የምወድድህ ልጄ አንተ ነህ፣" ሲል መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በእርግብ አምሳል በእየሱስ ላይ አርፏል።

ከዘላለም ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ በልዩ የሥላሴ አካልነት ከአብና ከወልድ ጋር ነበረ። እግዚአብሔርም በመካከላቸው ባለው የፍቅር ህብረት ውስጥ እንድንካፈል ፈጥሮናል። ከጥንት ጀምሮ እያንዳንዱ የሥላሴ አካል ከሌሎች ጋር ኅብረት እንዳለው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ባለን ህብረት እንድንደሰት ይፈልጋል (1 ዮሐንስ 1፥3-4)። (ዮሐንስ 17፥22-23ን አንብብ። )

**መንፈስ ቅዱስ ይሰራል**

ከዓለም ፍጥረት አንስቶ መንፈስ ቅዱስ በስራ ላይ ነው። በዓለም መፈጠር ውስጥ ሲሰራ ነበር (ዘፍጥረት 1፥2ና 26)። ለልዩ ተልዕኮ ለተጠሩ ሰዎች ልዩ ችሎታን ይሰጣል (ዘፀአት 35፥30-31፤ መሳፍንት 3፥9-10፤ መሳፍንት 15፥14-15)። ለነብያት መልዕክትን ይሰጣል (ኢሳይያስ 61፥1)፣ ቅዱሳት መጽሐፍት እንዲፃፉ አነሳስቷል (2 ጴጥሮስ 1፥21)፣ ሁልጊዜ ሰዎች ወደእግዚአብሔር እንዲመለሱ በልባቸው ይሰራል (ሐዋርያት ሥራ 7፥51)።

የህይወት መንፈስ ተብሎ ተጠርቷል (ሮሜ 8፥2ን አንብብ)። እኛን የፈጠረንና እንትንፋስ የሰጠን ይህ መንፈስ ነው። ይህ ቅዱስ መንፈስ ባይኖር ኖሮ ህያው የሆነ አንዳችም ነገር በምድር ላይ አይገኝም ነበር፤ ሰውም ወደአፈር ይመለስ ነበር (ኢዮብ 33፥4፣ ኢዮብ 34፥14-15)።

አዲስ ኪዳን ልዩ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስን ስራ ያስተዋውቀናል። መጥምቁ ዮሐንስ እየሱስ ሰዎችን በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቅ ተናግሯል (ማቴዎስ 3፥11)። እየሱስም ለደቀመዛሙርቱ በአብ ቃል የተገባውን የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት እንዲጠባበቁ ነግሯቸው ነበር፤ ይህም በበዓለ ሃምሳ ተፈፅሟል (ሐዋርያት ሥራ 1፥4-5፣ 8)።

መንፈስ ቅዱስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር እንደሚኖር እና እየሱስ በምድር ሳለ ያስተማራቸውን እንደሚያስታውሳቸው ወደ እውነትም እንደሚመራቸው እየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ነግሯቸው ነበር (ዮሐንስ 14፥26ና ዮሐንስ 16፥13)። እየሱስ መንፈስ ቅዱስ ሌላ አጋዥ መሆኑን ተናግሯል (ዮሐንስ 14፥16ና 26፣ ዮሐንስ 15፥26፣ ዮሐንስ 16፥7)። እየሱስ የተጠቀመው የግሪኩ ቃል "ከእኛ ጋር የሚኖር"፣ "የሚያፅናና" እና "የሚረዳ" የሚለውን ሃሳብ ይይዛል። "ተወካይ" የሚል ትርጓሜም አለው። መንፈስ ቅዱስ እየሱስን በመወከል የእርሱን ቃል ያስታውሰናል። [21]

► መንፈስ ቅዱስ የሚያከናውናቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?

ሁሉንም የመንፈስ ቅዱስ ስራዎች ጠቅሰን ባንጨርስም የተወሰኑትን መዘርዘር እንችላለን።

1. ስለኃጢአት ይወቅሰናል (ዮሐንስ 16፥8፤ 1 ቆሮንቶስ 2፥4፤ 1 ተሰሎንቄ 1፥5)። ይህ ካልሆነ ሰው ኃጢአቱን መረዳትና ንስሃ መግባት አይችልም።
2. በኃጢአት ለሞተው ሰው በዳግም ልደት ህይወትን ይሰጣል (ቲቶ 3፥5፤ ኤፌሶን 2፥1፤ ዮሐንስ 3፥5)።
3. ለአማኝ ስለመዳኑ የውስጥ ማረጋገጫ ይሰጠዋል (ሮሜ 8፥16)።
4. በእያንዳንዱ አማኝ ህይወት ውስጥ ይኖራል (ሮሜ 8፥9፤ 1 ቆሮንቶስ 6፥19)።
5. የእግዚአብሔርን እውነት እንድንረዳ ማስተዋልን ይሰጣል (1 ቆሮንቶስ 2፥9-10፣ 13-14፤ 2 ቆሮንቶስ 3፥14-17፤ ኤፌሶን 6፥17)።
6. ሰዎችን ለልዩ አገልግሎት ይጠራል፤ አገልግሎቱንም ይመራል (ሐዋርያት ሥራ 13፥2-4፣ ሐዋርያት ሥራ 15፥28፣ ሐዋርያት ሥራ 16፥6-10)።
7. ይቀደሱ ዘንድ የአማኞችን ልብ ያጠራል (ሐዋርያት ሥራ 15፥8-9፤ 1 ጴጥሮስ 1፥2)።
8. ከኃጢአት በላይ በድል ለመኖር የሚያስችልን አቅም ይሰጣል (ሮሜ 8፥1፣ 5፣ 13፤ ገላትያ 5፥16)።
9. በአማኝ ህይወት ውስጥ መንፈሳዊ ፍሬ እንዲፈራ ያደርጋል (ገላትያ 5፥22-23)።
10. ለአገልግሎት የሚሆንን መንፈሳዊ ስጦታ ይሰጣል (1 ቆሮንቶስ 12፥4-10፣ 28-30፤ ሮሜ 12፥6-8፤ 1 ጴጥሮስ 4፥10-11)።
11. ለአገልግሎት ልዩ ቅባት ይቀባል (ሐዋርያት ሥራ 1፥8፣ ሐዋርያት ሥራ 13፥9፤ ገላትያ 3፥5፤ 1 ጴጥሮስ 1፥12)።
12. አማኝ እንደእግዚአብሔር ፈቃድ መፀለይ እንዲችል ይረዳል (ሮሜ 8፥26-27፤ ኤፌሶን 6፥18)።
13. አማኝ እንደእግዚአብሄር ፈቃድ መፀለይ እንዲችል ይረዳል (ሮሜ 8፥26-27፤ ኤፌሶን 6፥18)።
14. በቤተክርስቲያን ውስጥ አንድነትን እና ህብረትን ይፈጥራል (ኤፌሶን 4፥3፤ ፊልጵስዩስ 2፥1)።

[21] እዚህ ጋር በ1 ዮሐንስ 2፥1 ላይ እየሱስ ከአብ ዘንድ ጠበቃችን መሆኑን የሚገልፀው ተመሳሳይ ቃል ነው።

### *የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በተመለከተ አንዳንድ መመሪያዎች*

*ለክፍሉ መሪ ማስታወሻ-* የክፍሉ አባል ይህንን ክፍል ማስረዳት ይችላል።

1. *መንፈስ ቅዱስ በተለያዩ ስጦታዎች፣ አገልግሎቶችና አሰራሮች ይሰራል* (1 ቆሮንቶስ 12፥4-6)።
2. *መንፈሳዊ የጸጋ ስጦታዎች እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ እንጂ እንደ መንፈሳዊ ዕድገት ልክ የሚሰጥ አይደለም* (1 ቆሮንቶስ 12፥11፣ 1 ቆሮንቶስ 4፥7)።
3. *እያንዳንዱ አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ተሰጥቶታል* (1 ቆሮንቶስ 12፥7)።
4. *ከእያንዳንዱ አማኝ የተወሰነ ስጦታ መጠበቅ አይቻልም* (1 ቆሮንቶስ 12፥8-11፣ 14-30)።
5. *ስጦታዎች ሁልጊዜ ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው ሌሎችን ለማገልገል ነው፤ በዚህም እግዚአብሔር እንዲከብር ነው* (1 ቆሮንቶስ 12፥21-22፣ 25፤ 1 ጴጥሮስ 4፥10-11)።

### *በልሳን የመናገር ስጦታ*

*በልሳን መናገርን አስመልክቶ በሁሉም ክርስቲያኖች ዘንድ ወጥ አቋም የለም። አንዳንድ ክርስቲያኖች ሁሉም አማኝ መንፈስ ቅዱስን ሲቀበል በልሳን መናገር ይችላል ብለው ያምናሉ።*

*ሌሎች ደግሞ በልሳን የመናገር ስጦታ በሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ ሰዎች መልዕክት ለመናገር እንደተሰጠ ያምናሉ። ይህንንም የሚያምኑት በሐዋ ሥራ* 2፥6 *ላይ በበዓለ ሃምሳ ቀን ከተለያየ ቦታ የመጡ የልዩ ልዩ ቋንቋ ተናጋሪ ሰዎች በልሳን የተናገሩ ሰዎችን መረዳት ስለቻሉ ነበር። እግዚአብሔር በልሳን መናገርን ጨምሮ የተለያዩ ስጦታዎችን እንደወደደ እንደሚሰጥም ያምናሉ* (1 ቆሮንቶስ 12፥4-11)። *ሁሉም ሰው ሊኖረው የሚገባ አንድ ስጦታ እንዳለ አይቀበሉም* (1 ቆሮንቶስ 12፥29-30)፤ *በዚህም ምክንያት ሁሉም አማኝ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ቢኖርም* (ሮሜ 8፥9) *ስጦታው መኖሩ ስለአማኙ መንፈሳዊነት ምንም አይናገርም* (1 ቆሮንቶስ 14፥22)።

*በአንዳንድ አገልግሎቶች ውስጥ በአማኞች ዘንድ የተለያየ አመለካከት መኖሩ በአንድነት ለማገልገል እንቅፋት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን አማኞች አንዳቸው ሌላቸው ላይ በዚህ የአመለካከት ልዩነት ምክንያት ሊፈርዱ አይገባም።*

### *መንፈስ ቅዱስ ከአማኞች ጋር ህብረት ያደርጋል*

*ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ካለን ከመንፈስ ቅዱስ ጋርም ህብረት እያደረግን ነው። ከአንዱ የሥላሴ አካል ጋር ህብረት እያደረጉ ከሌላው ጋር አለማድረግ አይቻልም* (ኤፌሶን 2፥18፤ ዮሐንስ 6፥44ን አንብብ)።

*አንድ ሰው እንዲድን ትምህርተ-መንፈስ ቅዱስን መረዳት አይጠበቅበትም። ደቀ መዛሙርቱ ስለመንፈስ ቅዱስ ብዙም ሳይረዱ መንፈስ ቅዱስን እንደሚያውቁትና እርሱም ከእነርሱ ጋር እንደሆነ እየሱስ ነግሯቸው ነበር* (ዮሐንስ 14፥17ን አንብብ)።

*መንፈስ ቅዱስን በትክክለኛው መንገድ መረዳት ከእርሱ ጋር በትክክለኛ መንገድ ህብረት እንድናደርግ እና እርሱም በህይወታችን የበለጠ እንዲሰራ ያደርጋል። እርሱ ስብዕና እንዳለው መረዳታችን ከእርሱ ጋር ህብረት ማድረግ*

እንድንችል ያደርገናል። እኛ እናወራዋለን፤ እርሱም ይመልስልናል። በጆሮ የምናደምጠው ዓይነት ድምጽ ባያሰማንም የእግዚአብሔርን ፍቃድ እና ፍቅሩን ያስረዳናል። የእግዚአብሔርን ፍቃድ ለማድረግ ከወሰንን እኛ ባናስተውለው እንኳን እእሱ ይመራናል።

ማንነት ያለው አካል መሆኑን ማወቅ ዝም ብሎ ኃይል ብቻ ወይም ደግሞ ስሜት ብቻ አለመሆኑን ያስረዳናል። እግዚአብሔርን ስናመልከው ማንነቱንም እያሰብን ነው እንጂ ያለማስተዋል የሆነ ከንቱ ስሜት ውስጥ እየገባን አይደለም። ስንፀልይም ትርጉም ባላቸው ቃላት ሲሆን ፈቃዱንም ለመረዳት ጥረት እናደርጋለን እንጂ በሌሎች ሃይማኖቶች እንደሚታየው ትርጉም የማይሰጡ ወይም አስማታዊ የሆኑ ቃላትን አንደግምም።

መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር እንደሆነ ማወቃችን እርሱን በአክብሮት እንድናመልከው ያደርገናል። ስንፀልይ እና በህይወታችን መሪነቱን ስናስተውል፤ የሚወደን አምላክ፣ ሁለንተናችንን የሚያውቅ፣ ነጋችንንም የሚያውቅ እንደሆነ ልናስተውል ይገባል። እርሱ ልንታዘዘው የሚገባ ባለሙሉ ስልጣንም ነው።

እርሱ ሁልጊዜም ከእኛ ጋር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ ልንሞላ እና በእርሱም ልንመላለስ እንደሚገባ ይነግረናል (ገላትያ 5፥25)። ቤተክርስቲያን ስንመጣ ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜም በእርሱ መገኘት ውስጥ እንዳለን እያስተዋልን መኖር አለብን። ከእኛ ጋር ያለ ብቻ ሳይሆን በእኛ ውስጥ የሚኖርም ነው። ስለዚህም ቅዱስ እና ንፁህ የሆነ ኑሮ ልንኖር ይገባል። (1 ቆሮንቶስ 6፥19 ይነበብ)።

የመንፈስ ቅዱስ ቀዳሚ ትኩረት ለምናምን ለእኛ በኃጢአት ላይ ድል መስጠት እና ልባችንን ማጥራት መሆኑን ማስተዋል አለብን (ሮሜ 8፥13፣ ገላትያ 5፥16፣ ሐዋርያት ሥራ 15፥8-9)። ዋና ትኩረቱን ሳናስቀድም ስለሌሎች ነገሮች ልንፀልይ አይገባንም። በፍጹም ሊቀድሰን እንደሚችል አምነን በእምነት እንፀልይ። (1 ተሰሎንቄ 5፥23ን አንብብ)።

በህይወት ውጣ ውረዶች ውስጥ የምናልፍበትን የውስጥ ጥንካሬ ይሰጠናል (ኤፌሶን 3፥16)። እኛን እና ያለንበትን ሁኔታ ይረዳል፤ የሚያስፈልገንንም ይሰጠናል።

በአገልግሎታችን ውስጥ ምሪት ለመቀበል፣ ቃሉን በኃይል ለመናገር እና በሰዎች ልብ ውስጥ መንፈሳዊ ውጤትን ለማምጣት በመንፈስ ቅዱስ ላይ መደገፍ አለብን። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ይህንን በሰፊው እናያለን። የትኛውም የሰው ችሎታ መንፈስ ቅዱስን ሊተካው አይችልም።

በመንፈስ የተሞላን እንኳን ብንሆን በየዕለቱ ከእርሱ ጋር ህብረት ማድረግ አለብን። በመንፈስ ተመሉ የሚለው ትዕዛዝ ሁልጊዜ የምናደርገው ነገር ነው። ያለማቋረጥ በመንፈስ ልንሞላ ይገባናል፤ ይህም ከእርሱ ጋር ባለን ህብረት ውስጥ የሚከናወን ነው (ኤፌሶን 5፥18 ይነበብ)።

► የእምነት መግለጫውን ቢያንስ ሁለት ግዜ አብራችሁ አንብቡ።

## የእምነት መግለጫ

*መንፈስ ቅዱስ ከአብ እና ከወልድ ጋር የሥላሴ አካል ነው። ስለኃጢአት ይወቅሳል፣ በእያንዳንድ አማኝ ውስጥ በመኖር ያድሳል፣ በኃጢአት ላይ ድልን ይሰጣል እንዲሁም ልብን ያነፃል። በመንፈስ ፍሬ እና ለአገልግሎት የሚሆንን መንፈሳዊ ስጦታ ለቤተክርስቲያን የሚሰጥ፣ የቤተክርስቲያንም የአንድነት መሰረት መንፈስ ቅዱስ ነው።*

## ስለመንፈስ ቅዱስ ስብዕና የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች

*ለክፍሉ መሪ ማስታወሻ- ከዚህ በታች ያለው ክፍል የግድ መጠናት የለበትም። ተማሪዎች ከፈለጉ ግን እንደተጨማሪ ማብራሪያ መጠቀም ይቻላል።*

አንዳንድ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ከኤሌክትሪክ ወይም ከመሬት ስበት ኃይል ጋር በማመሳሰል ስብዕናውን አይቀበሉም። ነገር ግን ስብዕና የሌለውን አካል መጽሐፍ ቅዱስ ስለመንፈስ ቅዱስ በሚያወራበት መንገድ መግለጽ ከባድ ነው። ኤሌክትሪክ አያወራም ማመዛዘንም አይችልም፤ የመሬት ስበትንም መዋሸት አይቻልም። እውቀት የሌለው ኃይል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሊረዳ አይችልም።

አንዳንድ ሰዎች እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት በሰውኛ ዘይቤ ስብዕና ለሌለው አካል የተገለጸ እንጂ ስብዕና ስላለው አካል የተጻፈ አይደለም ይላሉ። ሆኖም ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለመንፈስ ቅዱስ ሲያወራ የራሱ ማንነት እንዳለው አካል ሲሆን ሰዎችም እንደዚያው ሲመልሱለት እናያለን። በአንዳንድ ስፍራዎች መንፈስ ቅዱስ እንደግዑዝ አካል ተጠርቷል፤ ለምሳሌ በሐዋርያት ሥራ 2፥17 ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ይፈሳል በማለት ተገልጿል። መጽሐፍ ቅዱስ ብዙውን ጊዜ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገረው እንደ አካል በመሆኑ ይህ ምሳሌዓዊ ዘይቤ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል።

ስለመንፈስ ቅዱስ ስብዕና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች:-

- በ ማቴዎስ 28፥19 በአብ፥ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንድናጠምቅ ታዘናል፤ ይህም ሦስቱም ስልጣን እንዳላቸው ያመለክታል።
- 2 ቆሮንቶስ 13፥14 ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ህብረት ስለማድረግ ይጠቅሳል፤ ይህም ትርጉም ያለው ትባቦትን የሚጠይቅ ነው።
- በ ማርቆስ 13፥11 በስደት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች መናገር እንደሚገባቸው እንዲናገሩ አቅም እንደሚሰጣቸው ተስፋ ተሰጥቷል።
- በዮሐንስ 14፥17፣ 26 መንፈስ ቅዱስ እውነትን ስለሚያስተምርና ስለሚያስታውስ የእውነት መንፈስ ተብሏል።
- በዮሐንስ 16፥7-11 መንፈስ ቅዱስ ዓለምን ስለኃጢአት፣ ስለጽድቅ እና ስለፍርድ ይወቅሳል፤ ይህ ትርጉም ያለው መግባባትን የሚጠይቅ ነው።

- ዮሐንስ 16፥13-15 እንደሚነግረን መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ የሆነውን እንጂ ከራሱ አይናገርም።
- በ1 ቆሮንቶስ 12፥11 መሰረት መንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች እንዴት መሰጠት እንዳለባቸው ይወስናል።
- የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ለመንፈሳችን ይመሰክርልናል (ሮሜ 8፥16)።
- ስለእኛ በአብ ፊት ይማልዳል፤ ይህም የእግዚአብሔር አብን ፍቃድ ለመረዳት እንደሚችል ያሳያል (ሮሜ 8፥26-27)።
- በኤፌሶን 4፥30 መሰረት ሊያዝን ይችላል፤ ይህም የሚረዳ እና ስሜት ያለው መሆኑን ይነግረናል።
- ሊዋሽ ይችላል፤ ይህም ማለት ንግግራችንን እና ሃሳባችንን ይረዳል (ሐዋርያት ሥራ 5፥3)።
- ይናገራል፣ አቅጣጫ ያሳያል፤ እንዲሁም ልናከብረው የሚገባ ጽቃድ አለው (ሐዋርያት ሥራ 13፥2-4)።
- ሐዋርያትን በሚሽነሪ ጉዟቸው ውስጥ ይመራቸው ነበር፤ አንዳንድ ጊዜም ለመሄድ ያሰቡበት ቦታ እንዳይሄዱ ይከለክላቸው ነበር (ሐዋርያት ሥራ 16፥6)።

## ትምህርት 10 የቤት ስራዎች

(1) የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የቤት ስራ፦ ከታች ከተዘረዘሩት ዘርፎች መካከል እያንዳንዱን ተማሪ አንድ ይመደብ። ከሚቀጥለው ክፍለ ግዜ በፊት ክፍሉን አንብባችሁ በትምህርቱ ውስጥ ካለው ሃሳብ ላይ ምን እንደሚናገር በአንድ አንቀፅ ፃፉ።

- ሐዋርያት ሥራ 1፥4-8
- ሮሜ 8፥1-14
- 1 ቆሮንቶስ 2፥9-16
- 1 ቆሮንቶስ 12፥1-13
- ገላትያ 5፥22-26

(2) ፈተና፦ የሚቀጥለው ክፍለ ግዜ የምትጀምሩት በትምህርት 10 ፈተና ነው። ለፈተና ዝግጅት እንዲሆን የፈተና ጥያቄዎችን አጥኑ።

(3) የማስተማር የቤት ስራ፦ ከክፍል ውጪ የማስተማርያ ግዜን ቀጠሮ መያዝ እና ማስተማራችሁን ሪፖርት ማድረግ አስታውሱ።

## ትምህርት 10 ፈተና

(1) የመጀመርያዋ ቤተ-ክርስቲያን ለመንፈስ ቅዱስ የነበራት ምላሽ ሦስት ባህሪያት ዘርዝሩ?

(2) መንፈስ ቅዱስ ዕላዌ እንደሆነ በምን እናውቃለን?

(3) መንፈስ ቅዱስ መለኮት እግዚአብሔር እንደሆነ የምናውቅበትን አምስት መንገድ ዘርዝሩ።

(4) ዘጠኝ የመንፈስ ቅዱስ ስራዎችን ዘርዝሩ።

(5) የመንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን በዋናነት ቅድሚያ የሚሰጠው ስራው ምንድን ነው?

# ትምህርት 11
# ክርስትናዊ ቅድስና

## የትምህርቱ አላማዎች

(1) ተማሪው የሚከተሉትን ማስረዳት ይችላል

- ቅዱስ የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱሳዊ አጠቃቀም
- የእግዚአብሔር ቅድስና ለክርስቲያን ቅድስና መሠረት እንደሆነ
- ቅድስና ለአምልኮና ከእግዚአብሔር ጋር ላለው ግንኙነት ያለው ጠቀሜታ
- ስለ መቀደስ የሚገልጹ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌዎች
- ለመንፈሳዊ ብስለት የሚረዱ ልምዶች
- ስለ ክርስትናዊ ቅድስና ክርስቲያናዊ የእምነት መግለጫ

(2) ተማሪው በሚኖርበት ዓለም የእግዚአብሔር ጸጋ ቅዱስ እንደሚያደርገው እምነት ይኖረዋል።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል

ቅድስና ተብሎ የተተረጐመው የዕብራይስጥ ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከ600 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል። ቅዱስ ተብሎ የተተረጐመው የዕብራይስጥና የግሪክ ቃላት በዋነኝነት የሚያመለክቱት መለየት ወይም ለአንድ ዓላማ የተሰጠ መሆንን ነው። አንድ የተቀደሰ ነገር ቀደሞ ከሚያገለግልበት ነገር ተነጥሎ ለአዲስ ለተለየ ዓላማ ይለያል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተሰጡ እና እንደ ቅዱስ የሚታዩ በርካታ ነገሮችን ልብ ይበሉ።

- **የተቀደሰ መሬት**- እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር የመገናኛ ቦታ አድርጎ ለይቶታል (ዘፀአት 3፥5)።

- **የመገናኛው ድንኳን እና ቤተመቅደስ** -ብዙ ቅዱስ ነገሮች ከመገናኛው ድንኳን እና ከቤተመቅደስ ጋር የተያያዙ ነበሩ፤ የክህነት ልብሶችን ጨምሮ (ዘሌዋውያን 16፥32)፣ ቂጣ (ዘፀአት 29፥34) እና ዕቃዎች (ዘጸአት 40፥9)። እነዚህ ለእግዚአብሔር አምልኮ የተለዩ ነበሩ።

- **የተቀደሱ ቀናት**- የሰንበት ቀን እንደ ቅዱስ ተለይቶ ነበር (ዘፍጥረት 2፥3፤ ዘፀአት 20፥8)። እንደ የስርየት ቀን ያሉ ሌሎች የአይሁድ በዓላት እንዲሁ ልዩ ነበሩ (ዘሌዋውያን 23፥26-29)። እነዚህ ቀናት ለእረፍት፣ ለማሰላሰል እና ለአምልኮ ተለይተዋል።

- **ቅዱስ አምላክ**- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የቅድስና ትልቁ ምሳሌ እግዚአብሔር ራሱ ነው። የእግዚአብሔር ሁሉ ነገር ቅዱስ ነው። ስሙ ቅዱስ ነው (ዘሌዋውያን 22፥2)፤ ቃሉ ቅዱስ ነው (ኤርምያስ 23፥9)፤ መንገዱ ቅዱስ ነው (መዝሙር 77፥13)። ቅድስና ማለት እግዚአብሔር ለመለኮታዊ ማንነቱ እና ቦታው ተገቢ ካልሆነ ከማንኛውም ኃጢአተኛ፣ ርኩስ፣ የታወቀ፣ ተራ ነገር ሙሉ በሙሉ ተለይቷል ማለት ነው።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ እየሱስ ቅዱስ (ዮሐንስ 17፥19፤ ሐዋርያት ሥራ 4፥27፣ 30) እና ያለ ኃጢአት (2 ቆሮንቶስ 5፥21) ተብሎ ተጠርቷል። መላእክት (ማርቆስ 8፥38) እና ሐዋርያትና ነቢያት (ኤፌሶን 3፥5) እንደ ቅዱሳን ተገልጸዋል። እነዚህ ሁሉ ለልዩ ዓላማ ተለይተዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ህዝቦችን ቅዱስ እንዲሆኑ ይጠራቸዋል (ዘሌዋውያን 11፥44-45፤ 1 ቆሮንቶስ 1፥2፤ 1 ጴጥሮስ 1፥15-16)። ይህ ትምህርት እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀውን ቅድስና ያብራራል።

## የእግዚአብሔር የሚያመልኩ ቅዱሳን

► *መዝሙር* 119፥33-40 አብራችሁ አንብቡ። ይህ ክፍል ስለ እግዚያብሔር አማኝን ስለሚቀይርበት መንገድ ምን ይነግረናል?

እግዚአብሔር ራሱን መግለጥ ሲጀምር የመጀመሪያ ዓላማው ምን ዓይነት አምላክ እንደሆነ ማሳየት ነበር። እግዚአብሔር እራሱን በዋነኝነት ቅዱስ ብሎ ገልፆታል። አብዛኛውን ጊዜ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን "የእስራኤል ቅዱስ" ብሎ ጠርቶታል።

የአምልኮ ጭብጥ የእግዚአብሔር ቅድስና ነበር፥-

> ታላቁንና አስፈሪውን ስምህን ይወድሱ፤ እርሱ ቅዱስ ነው። አምላካችንን እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ አድርጉት፤ በእግሩ መርገጫ ስገዱ፤ እርሱ ቅዱስ ነውና (*መዝሙር* 99፥3፣ 5)።

የእግዚአብሔር ቅድስና ከሰው የሚጠይቀው መሰረታዊ ነገር ነው። እርሱ ቅዱስ ስለሆነ የሚያመልኩት ቅዱሳን እንዲሆኑ ይጠራቸዋል። "እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ" (ዘሌዋውያን 11፥44-45፣ ዘሌዋውያን 19፥2፣ ዘሌዋውያን 20፥26፣ ዘሌዋውያን 21፥8) ይላል።

የእስራኤል አምላክ ከአረማውያን የሐሰት አማልክት የተለየና የተለየ አምልኮ የሚጠይቅ ነበር።

> ወደ እግዚአብሔር ተራራ ማን ሊወጣ ይችላል? በተቀደሰ ስፍራውስ ማን ይቆማል? ንጹሕ እጅና ቅን ልብ ያለው፤ ነፍሱን ለሐሰት ነገር የማያስገዛ፤ በውሸት የማይምል (*መዝሙር* 24፥3-4)።

እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ "እግዚአብሔር የማንን አምልኮ ይቀበላል?" የሚያመልኩ ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን አምላኪ ናቸው ማለት አይደለም። እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ቅዱሳን መሆን አለባቸው።

እግዚአብሔር የሚጠብቀው ቅድስና ሥነ ስርዓታዊ ወይም ማስመሰል አይደለም፤ እውነተኛ ቅድስና ነው። እግዚአብሔርን ለሚያመልኩ የቅድስና መስፈርት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተደጋግሟል።

> ነገር ግን የጠራችሁ እርሱ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተም በኑሯችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ፤ ምክንያቱም "እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ" ተብሎ ተጽፏል (1 ጴጥሮስ 1፥15-16)።

ፀባይ ማለት የአንድ ሰው ባህሪ እና አጠቃላይ የአኗኗር ዘይቤ ነው። እግዚአብሔር አምላኪዎቹ በሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ብቻ ቅዱስ መስለው እንዲታዩ፣ ወይም ደግሞ በእውነት ቅዱሳን ሳይሆኑ ቅዱሳን ተብለው እንዲጠሩ ብቻ አይፈልግም። ከዚህ ይልቅ አገልጋዮቹ ቅዱስ ሕይወት እንዲመሩ ይፈልጋል።

► ቅድስና ከአምልኮ ጋር የተያያዘባቸው አንዳንድ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

ቅድስና ለአምልኮ አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም

1. **እግዚአብሔርን እንወደዋለን እንዲሁም እርሱን መምሰል እንፈልጋለን-** እግዚአብሔርን ማምለክ እርሱ እጅግ አስደናቂ መሆኑን ማየት እና እንደ አምላክነቱ መውደድ ነው። የማንነቱን ባህሪያት ማድነቅ ማምለክ ነው። የእግዚአብሔር ማንነት በመሠረቱ ቅዱስ ነው። ስለሆነም የእግዚአብሔርን ተፈጥሮ በእውነት የምንወድ ከሆነ፣ ምንም እንኳን በራሳችን ውስጥ ብናየውም ኃጢአትን እና ርኵሰትን እንጠላለን።

2. **እግዚአብሔርን እንወደዋለን እንዲሁም እርሱን ደስ ማሰኘት እንፈልጋለን-** እውነተኛ አምልኮ ምን እንደሆነ ከተገነዘብን አምላክ ከእኛ የሚጠብቀው ነገር አያስገርመንም። እግዚአብሔርን የምናመልከው በፍርሃት ወይም እኛን ስለባረከን ብቻ ሳይሆን ስለምንወደው ነው።

## መቀደስ በድነት ወቅት

መጽሐፍ ቅዱስ በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ውስጥ የሚከናወነውን ነገር ለማመልከት ቅድስና የሚለውን ቃል ይጠቀማል። ጳውሎስ "በቆሮንቶስ ላለችው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፤ በክርስቶስ እየሱስ ተቀድሰው...ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት" (1 ቆሮንቶስ 1፥2) ብሎ ጽፏል። ጳውሎስ "...በጌታ በእየሱስ ክርስቶስ ስምና በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል" (1 ቆሮንቶስ 6፥11) ብሎ ጽፏል። በቆሮንቶስ የነበሩ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ብስለት ያላደጉና በክርስቶስ ውስጥ እንዳሉ ልጆች ገና ስጋውያን ቢሆንም ቀድሞውኑ ተቀድሰዋል (1 ቆሮንቶስ 3፥1)።

*መቀደስ* በቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ውስጥ ጠቅለል ባለ ሁኔታ የተገለፀ ቃል ነው። እነዚህ የቆሮንቶስ ሰዎች ከኃጢአትና ከዚህ ዓለም ወጥተው ለእግዚአብሔር የተለዩ ነበሩ። እነዚህ ሰዎች በቅድስና ረገድ የበሰሉ ባይሆኑም ከቀድሞ ህይወታቸው ተለይተው አሁን የአምላክ ቤተሰብ አባል ሆነዋል።

ከእግዚአብሔር ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ስንገናኝ፤ ኃጢአት ከእርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት የሚያስተጓጉል መሰናክል ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ንስሐ እስካልገባን፣ ይቅር እስካልተባልን እና አዲስ ልብ እስካልተሰጠን ድረስ መጀመር የማንችለው ለዚህም ነው።

> አንድ የሂንዱ አዛውንት ኤሚ ካራማይክልን "ብዙ ስብከቶችን ሰምተናል፤
>
> የጌታሽን የእየሱስን ሕይወት ልታሳዩን ትችያለሽ?" ብሎ ጠየቃት።

ከእግዚአብሔር ጋር በታረቅን በዚያ ሰዐት እንለወጣለን (ቲቶ 3፥5)። በመንፈሳዊም አዲስ ፍጡራን ሆነናል። ከኃጢአት ኃይል ነጻ ወጥተናል፤ እናም እግዚአብሔርን ለማስደሰት እንፈልጋለን። የክርስቲያን ቅድስና የሚጀምረው ሲድን ነው።

ድነት ወድያውኑ ወደ ቅድስና ሕይወት እንደሚመራ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። መዳን የሚያመጣው የእግዚአብሔር ጸጋ በአሁኑ ዘመን ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ፣ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት እንድንኖር ያስተምረናል (ቲቶ 2፥11-12)። የድነት ዓላማ ከኃጢአት ነፃ ሊያወጣንና ቅዱሳን ሊያደርገን ነው፤ ይህም ከእግዚአብሔር ጋር በግንኙነት እንድንኖር ነው (ሉቃስ 1፥74-75፣ ሮሜ 6፥2፣ 11-16)።

## በቅድስና ማደግ

ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት ስንኖር የእርሱን እውነት የበለጠ ስንረዳ በቅድስና ማደጋችንን እንቀጥላለን። በብርሃን መመላለስ ማለት የእርሱን እውነት የበለጠ በመረዳት ውስጥ እግዚአብሔርን መታዘዛችንን መቀጠል ማለት ነው (1 ዮሐንስ 1፥7)። እርሱን ደስ የሚያሰኘውንና የማያስደስተውን ነገር በተሻለ ስናውቅ፤ የእርሱ እውነትና የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይለውጠናል።

እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው ሙሉ ለሙሉ ቅዱስ መሆን ይፈልጋል። ድርጊቱን ብቻ መቀየር አይፈልግም። ፍላጐቱ ሙሉ ለሙሉ ንጹሕ እንዲሆን ይፈልጋል። ዳዊት በኃጢአት ላይ ሙሉ ድል በመቀዳጀት መኖር እንዲችል ጸለየ፤ ከዚያም ቃላቱና የልቡ ማሰላሰል እንኳ እግዚአብሔርን ደስ እንዲያሰኙ ጸለየ። (መዝሙር 19፥12-14 ይህንንም ይመልከቱ መዝሙር 119፥7፣ 34፣ 36፣ 69፣ 80፣ እና 112። )

የመንፈሳዊ ብስለት ሂደት በአጠቃላይ መቀደስ ይባላል። መቀደስ እየጨመረ የሚሄድ ከኃጢያት እና ከአለም የመለየት እንዲሁም ለእግዚአብሔር የመሰጠት የህይወት ዘመን ሂደት ነው። ይህ ጳውሎስ የዓለምን ምሳሌ ስለመከተል የሰጠው ማስጠንቀቂያና [ያለማቋረጥ] በአእምሯችሁ መታደስ ተለወጡ” (ሮሜ 12፥2) በሚለው ማሳሰቢያ ውስጥ ተገልጿል። በአንድ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ከዓለም መለየት እና በእውቀት መለወጥ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚጠናቀቁ ልምዶች አይደሉም። አማኙ ከጌታ ጋር ሲራመድ፤ ብልፅናና እድገትን ያለማቋረጥ ይለማመዳል። ይህ ሁሉ መቀደስ በሚለው ቃል ውስጥ ተካትቷል።

## የተወረሰ ውድቀት እና ቅድስና

***የተወረሰ ውድቀት*** የሰው ልጅ ከተወለደ ጀምሮ ወደ ኃጢአት እንዲያዘነበል የሚያደርግ የተፈጥሮ ሞራል መበላሸት ነው። የነገረ-መለኮት ሊቃውንት አንዳንድ ጊዜ "የመጀመሪያው ኃጢአት" ብለው ይጠሩታል፤ ምክንያቱም በአዳም ኃጢአት ምክንያት የተወለድነው በተፈጥሮአችን ኃጢአተኛነት ነው።

እያንዳንዱ ሰው የሚወለደው ራስ ወዳድ እና ለኃጢአት ካዘነበለ ፈቃድ ጋር ነው። እግዚአብሔር ፍላጎቱን እና ጥንካሬን ካልሰጠን በቀር ፍቃዳችን ትክክለኛውን ለመምረጥ ነጻ አይደለም (ሮሜ 6፥16-17)። የተወረሰ ውድቀት እንደ ኩራት፣ ምቀኝነት፣ ጥላቻ እና ይቅር አለማለትን ያሉ ውስጣዊ ኃጢአቶችን ያነሳሳል። የኃጢአት ድርጊቶችንም ያነሳሳል።

► አንድ ሰው ከዳነ በኋላ የተወረሰ ውድቀት ይኖረዋል?

የዳነ ሰው በውርስ ውድቀት ቁጥጥር ስር አይደለም። አሁንም በእርሱ ቁጥጥር ሥር ቢሆን ኖሮ በኃጢአት ውስጥ ይኖራል እንጂ አይድንም። መጽሐፍ ቅዱስ በሥጋ አእምሮ የሚመራ ሰው እንደሚኮነን ይነግረናል (ሮሜ 8፥6-8፣ 13)። የዳነው ሰው በውርስ ውድቀት ቁጥጥር ስር አይደለም፤ እናም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ኃጢአትን ድል አድርጎ መኖር ይችላል (ሮሜ 8፥1፣9፣ 13)።

ነገር ግን የዳነ ሰው እስኪነጻ ድረስ በውስጡ የውርስ ውድቀት ተጽእኖ አለው። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ አማኞች ምንም እንኳን ድነት ቢያገኙም ሥጋዊ ሰዎች እንደነበሩ እና እንደ ዓለም ሰዎች ያለ አመለካከት እንዳላቸው ነግሯቸዋል።

(1 ቆሮንቶስ 3፥1-3ን አንብብ)። አዲስ ክርስቲያን እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ መግባቱ የተለመደ ነገር እንደሆነ አሳይቷል። *ሥጋውያን መሆን* በክርስቶስ ገና ሕፃን እንደመሆን ነው ብሏል።

በዚህ ሁኔታ ያለ አማኝ እግዚአብሔርን ይወዳል፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን በፍጹም ልቡ፣ ነፍሱ፣ ሃሳቡ እና ኃይሉ መውደድ አይችልም (ማቴዎስ 22፥37)። እሱ እንደ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ጥሪ የመከተል አንድ ሃሳብ እንዳለው ሊናገር አይችልም (ፊልጵስዩስ 3፥13-15)። አንዳንድ የልቡ ማሰላሰሎች በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንደሌላቸው ያውቃል (መዝሙር 19፥14)።

እግዚአብሔር በዚህ ሁኔታ ውስጥ አይተወንም። በጥንት ዘመን እንኳን እግዚአብሔርን በፍጹም ልባቸው እንዲወዱት የሚያደርግ የጸጋ ሥራ እንደሚሠራ ለእስራኤላውያን ቃል ገብቶላቸዋል። (ዘዳግም 30፥6ን አንብብ)።

ዳዊት ከይቅርታ በላይ የሆነ የጸጋ ሥራ ለማግኘት ጸለየ። በኃጢአት ወድቆ ነበር፤ ይህም በልቡ ውስጥ ባለው ችግር ምክንያት እንደ ሆነ ተገነዘበ። ኃጢአት በተፈጥሮ ውስጥ እንዳለ ያውቅ ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ፍጹሞ ቅዱስ እንዲሆን እንደሚፈልግም ያምን ነበር። ሙሉ መንጻትን ለማግኘት ጸለየ። (መዝሙር 51:5-10ን አንብብ። )

> "መቀደስ እግዚአብሔር እንዲያደርግልኝ የምፈልገው የእኔ ሀሳብ አይደለም፤ መቀደስ እግዚአብሔር ለእኔ ሊያደርግልኝ የሚፈልገውን ሃሳብ ነው፣ እናም ወደ ትክክለኛው
>
> ሃሳብ እና መንፈሳዊ አመለካከት ሊያስገባኝ ይገባል፤ ለዚህም በማንኛውም ዋጋ ሙሉ በሙሉ እንዲቀድሰኝ እፈቅድለታለሁ።"
>
> - ኦስዋልድ ቻምበርስ

የአዲስ ኪዳን አማኞች ከድነት በኋላ ወደ ሌላ ልዩ ክስተት ተጠርተዋል። የተሰሎንቄ አማኞች ወንጌልን የተቀበሉ፣ ከጣዖት አምልኮ የተመለሱ፣ ስደትን የተቋቋሙ፣ በመንፈስ ቅዱስ ደስ የሚላቸው እና የእየሱስን መምጣት የሚጠባበቁ ድንቅ የአማኞች ምሳሌ ነበሩ (1 ተሰሎንቄ 1፥6-10)። ግን በእምነታቸው ውስጥ ገና የጎደለ ነገር ነበር። በረጅም ሂደት ወይም በሞት ጊዜ የሚቀርበው ነገር አልነበረም፤ ምክንያቱም ጳውሎስ ወደ እነርሱ በሚያደረገው ጉብኝት ሊከሰት እንደሚችል ተናግሯል። (1 ተሰሎንቄ 3፥10ን አንብብ)።

> የሰላም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁ፣ ነፍሳችሁና ሥጋችሁ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ ያለ ነቀፋ ይጠበቁ። የጠራችሁ የታመነ ነው፤ እርሱም ያደርገዋል (1 ተሰሎንቄ 5፥23-24) ብሎ ፀልዩአል።

ጳውሎስ እነዚህ አማኞች ሙሉ በሙሉ እንዲቀደሱ ጸለየ። ውጤቱም ጌታ በሚመለስ ጊዜ አማኞች በሥጋ፣ በነፍስ እና በመንፈስ ነውር የሌለባቸው ይሆናሉ።

> "ቤተ ክርስቲያን በዙሪያችን ካለው አለም ጋር በተያያዘ ድርብ ሃላፊነት አለባት። በአንድ በኩል በአለም ውስጥ መኖር፣ ማገልገል እና መመስከር አለብን። በሌላ በኩል በአለም ከመበከል መራቅ አለብን። ስለዚህ ከዓለም በማምለጥ ቅድስናችንን ለመጠበቅ ወይም ዓለምን በመምሰል ቅድስናችንን ለመሠዋት መፈለግ የለብንም።
>
> - ጆን ስቶት

የእየሱስ ደቀ መዛሙርት በጴንጤቆስጤ ዕለት ልዩ የሆነ የጸጋ ሥራ አይተዋል። እየሱስ ከዓለም እንዳልሆኑ፣ የእርሱና የአብ እንደ ሆኑ፣ ስሞቻቸውም በመንግስተ ሰማይ እንደ ተጻፈ ስለተናገረ ከዚያን ጊዜ በፊት እንደዳኑ እናውቃለን (ዮሐንስ 15፥3፣ ዮሐንስ 17፥14፣ 9-10፤ ሉቃስ 10፥20)። ነገር ግን ራስ ወዳድና

የእግዚአብሔርም ቅድሚያ ሰጪነት አልነበራቸውም። እየሱስ ስለኃጢአተኛ አመለካከታቸው በተደጋጋሚ ገስጿቸዋል። (ማርቆስ 9፥33-34፤ ማርቆስ 10፥35-41፤ ሉቃስ 9፥54-55ን አንብብ። )

እየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ፣ ወደ ሰማይ ከመመለሱ ጥቂት ቀደም ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ለዓለም የእርሱ ምስክሮች እንደሚሆኑ ነገሯቸዋል። ነገር ግን በመጀመሪያ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ ብሏቸው ነበር። (ሉቃስ 24፥49፤ ዮሐንስ 20፥22፤ ሐዋርያት ሥራ 1፥2-5፣ 8ን አንብብ)። አስቀድሞ በርካታ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ በተለይም በዮሐንስ 14-16 ነግሮአቸዋል።

በበዓለ ሃምሳ ቀን ደቀ መዛሙርቱ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ (ሐዋርያት ሥራ 2፥4)። ይህ መሞላት ተነሳሽነታቸውን፣ ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ነገሮች እና ድርጊቶቻቸውን ቀይሯል። በቀሩት የአዲስ ኪዳን ክስተቶች አለመግባባቶች እና ስህተቶች ቢሰሩም የክርስቶስን አይነት አስተሳሰብ እና ቅድሚያ የሚሰጡትን አሳይተዋል። በጴጥሮስ እና በዮሐንስ የተጻፉት መልእክቶች የክርስቶስን መልእክት እና ልብ ያንፀባርቃሉ። በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸው ጌታ አምላካቸውን በፍጹም ልባቸው፣ ነፍሳቸው፣ ሃሳባቸው እና ኃይላቸው እንዲወዱ እና ባልንጀሮቻቸውን እንደራሳቸው እንዲወዱ አስችሏቸዋል (ማቴዎስ 22፥37-39)። ሙሉ በሙሉ ለመንፈስ ቅዱስ ስለተሰጡ ልክ በክርስቶስ እንደ ኖረ በእነርሱ በኩል ኖረ (ሉቃስ 4፥1፣ 14፣ 18፤ ሐዋርያት ሥራ 2፥22)።

አንዳንድ ክርስቲያን አስተማሪዎች በቅድስና ሂደት ላይ ያተኩራሉ፤ ሌሎች ደግሞ ወሳኝ የውሳኔ ምዕራፍ ላይ ያተኩራሉ። ሰዎች ካዩአቸው የተለዩ የመቀደስ ክስተት መካከል የጴንጠቆስጤ እና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ልምምድ ምሳሌ ነው። አንድ ነገር ጨርሶ ሙሉ መሆን መቻሉ በአንድ ጊዜ መደረጉን ያሳያል። በአንድ የእምነት ቅጽበት እና ሙሉ ለሙሉ እጅ መስጠት እንኳን ወንጌል መስራት የሚችለውን እንዲሰራ አለመገደባችን አስፈላጊ ነው (ሮሜ 12፥1-2)። እየሱስ በሞቱና በትንሳኤው ያቀረበው ሁሉ ለሚከተሉት ለሁሉም ይገኛል፡-

1. ከእየሱስ ጋር ለኃጢአት እንደሞቱ አድርገው ለቆጠሩ (ሮሜ 6፥11)
2. ኃጢአት በሥጋቸው እንዲነግሥ ለማይፈቅዱ (ሮሜ 6፥12)
3. ሰውነታቸውን የጽድቅ ዕቃ አድርገው ላቀረቡ (ሮሜ 6፥13)

በታሪክ ውስጥ ታላላቅ ክርስቲያኖች በመንፈስ ወደተሞላ ህይወት እና ከእግዚአብሔር ጋር ጥልቅ ግንኙነት የገቡበትን ጊዜ መስክረዋል። ከነዚህ ወንዶች እና ሴቶች መካከል እንደ ጆን ቡኒያን፣ ሁድሰን ታይለር፣ ድዋይት ኤል። ሙዲ፣ ሳሚ ሞሪስ፣ ኦስዋልድ ቻምበርስ፣ ፍራንሲስ ሪድሊ ሃቨርጋል እና ኤሚ ካርማይክል ይካተታሉ።[22]

እግዚአብሔር በቅጽበት ማድረግ የሚችለውን አለመገደባችን አስፈላጊ ቢሆንም፤ በሂደት የሆነውን የመንፈስ ቅዱስን ሥራም መዘንጋት የለብንም። አንዳንድ ጊዜ ይህ ዓይነቱ ቅድስና እንደ ተጠናቀቀ ምንም እንኳን ቢገለጽም፣ ካሉበት ደረጃ ተጨማሪ እድገት ሊኖር እንደማይችል አያመለክትም። ለምሳሌ ፈረንሳይኛ መናገር የተማረ አንድ ሰው የተሻለ ፈረንሳይኛ ለመናገር መማር አይችልም ማለት አይደለም። ፈፅመው የተቀደሱትም ከዚህ በፊት ያልተለማመዱትን

[22] ብዙዎቹን ታሪኮች በShepherds Global Classroom *Doctrine and Practice of the Holy Life* የሚለውን ኮርስ ማንበብ ትችላለህ።

ቅድስና ማየት/ መለማመድ ችለዋል። ይሁን እንጂ ይህ ፈፅሞ የፍፁምነት ቅድመ ሁኔታ አይደለም። አማኝ እያደገ የሚሄድበት የቅድስና ሕይወት ነው።

## መቀደስ እና ክርስቲያናዊ ብስለት

መጽሐፍ ቅዱስ ስለበሰለ አማኝ ሕይወት ይገልጻል። መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ሕይወት ውስጥ ክርስቲያናዊ ባሕርያትን ለማሳደግ ይሠራል። የመንፈስ ሥራ ልዩ የሆኑ የማንጻት ወይም የመቀባት እንዲሁም ቀስ በቀስ የሚከናወኑ ሂደቶችን ያካትታል። አንድ አማኝ መጽሐፍ ቅዱሳዊው የሆነ የበሰለ አማኝ መግለጫ ጋር የማይመጥን መንፈሳዊ ሕይወት መርካት የለበትም።

የዕብራውያን ጸሐፊ አንዳንድ አንባቢዎቹ አሁንም እንደ ሕፃናት እንደነበሩ ተናግሯል (ዕብራውያን 5፥12)። ዕብራውያን 6፥1"ስለ ክርስቶስ የተሰጠውን የመጀመሪያ ትምህርት ትተን ወደ ብስለት እንሂድ" ሲል አሳስቧቸዋል።

ሐዋርያት ለአማኞች ያቀረቡት ጸሎት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያሳየናል።

### ፍቅር

ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጸለየ፥- “እኛ ለእናንተ ፍቅር እንዳለን ሁሉ እርስ በርስ ያላችሁን ፍቅርና ለሌሎችም ያላችሁን ፍቅር ጌታ ያብዛላችሁ...” (1 ተሰሎንቄ 3፥12-13)። ለኤፌሶን ሰዎችም እንዲህ ሲል ጸለየ፥-

> ደግሞም ሥር ሰድዳችሁ፣ በፍቅር ታንጻችሁ፣ የክርስቶስ ፍቅር ስፋቱ፣ ርዝመቱ፣ ከፍታውና ጥልቀቱ ምን ያህል እንደ ሆነ፣ ከቅዱሳን ሁሉ ጋራ የመገንዘብ ኀይልን እንድታገኙ ነው። እስከ እግዚአብሔር ሙላት ሁሉ ልክ ደርሳችሁ እንድትሞሉ፣ ከመታወቅ በላይ የሆነውን የክርስቶስን ፍቅር ታውቁም ዘንድ ነው (ኤፌሶን 3፥17-19)።

ጳውሎስ እነዚህ አማኞች እንዲበዙና በፍቅር እንዲሞሉ ይፀልይ ነበር። በ1 ቆሮንቶስ 13ላይ ጳውሎስ ይህ ፍቅር በበሰለ አማኝ ውስጥ ምን መምሰል እንዳለበት ገልጿል። የመቀደስ ሕይወት በቀላሉ እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ፣ ነፍስህ፣ ሃሳብህ እና ኃይልህ መውደድ እና ባልንጀራህን እንደ ራስህ መውደድ ነው (ሉቃስ 10፥27)። ቅዱሳን ሰዎች ከእግዚአብሔር እና ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት እንደዚህ ያለ ነው።

### ነቀፋ አልባነት

ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች በ1 ተሰሎንቄ 3፥12-13 "ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ...በአምላካችንና በአባታችን ፊት ነቀፋ የሌለባችሁና ቅዱሳን ሆናችሁ እንድትገኙ ልባችሁን ያጽና" ብሎ ፀልዮአል። ከሁለት ምዕራፎች በኋላም ሙሉ በሙሉ ይቀደሱ ዘንድ "ነፍሳችሁና ሥጋችሁ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ ያለ ነቀፋ ይጠበቁ" (1 ተሰሎንቄ 5፥23) ብሎ ጸልዩል። *ያለ ነቀፋ* ማለት በሁሉም መንገድ ፍፁም መሆን ማለት አይደለም። ነቀፋ የሌለበት ሰው ስህተት ይሠራል፤ ነገር ግን ሊኖረው የሚገባው ባህሪ እና ፀባይ አለው።

**ውስጣዊ ጥንካሬ**

ጳውሎስ የኤፌሶን አማኞችን በኤፌሶን 3፥15-16 "በውስጥ ሰውነታችሁ እንድትጠነክሩ፣ ከክብሩ ባለጠግነት በመንፈሱ በኩል ኀይል እንዲሰጣችሁ እጸልያለሁ" ሲል ጸለየ። አንድ ሰው በእምነት ሲያድግ ውስጣዊ ባህሪው እየጠነከረ ይሄዳል። ውስጣዊ ጥንካሬ ትክክለኛ ምርጫዎችን የማድረግ እና የተሳሳቱ ውሳኔዎችን የመቃወም አቅም ነው።

**የክርስቶስ በእኛ ማደር**

ጳውሎስ **ክርስቶስ በልባቸው እንዲያድር** ሲል የኤፌሶንን ጸሎት መጸለይ ቀጥሏል (ኤፌሶን 3፥17)። በዚህ ክፍል ውስጥ “እንዲያድር” ተብሎ የተተረጎመው ቃል በጊዜያዊነት በአንድ ቦታ መቆየት ሳይሆን በቋሚነት መኖር ማለት ነው። ይህ አነጋገር እየሱስ እኛን መጎብኘት ብቻ ሳይሆን ከእኛ ጋር መኖር እንደሚፈልግ ያሳያል። ክርስቶስ የተጠበቀ/ ቀጥነት ያለው መንፈሳዊ ህይወት በሚኖሩ ምቾት እና እርካታ ይሰማዋል።

**የእግዚአብሔር ሙላት**

ጳውሎስ የኤፌሶን ጸሎት የልመና ክፍሉን "እስከ እግዚአብሔር ሙላት ሁሉ ልክ ደርሳችሁ እንድትሞሉ" (ኤፌሶን 3፥14-19)። በሚል ጸሎት አጠቃሎታል። ይህ መንፈሳዊ እውነታን ለመግለጽ አካላዊ ምሳሌን መጠቀም ነው። እግዚአብሔር ሁሉ ነገራችንን፣ አእምሯችንን፣ ፈቃዳችንን፣ ስሜታችንን፣ እንቅስቃሴያችንን፣ አመለካከታችንን፣ ፍላጎታችንን እና ምላሻችንን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ይፈልጋል ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙት የቅዱስና ሕይወት መግለጫዎች ሁሉ ይህ ከሁሉ የላቀ ሊሆን ይችላል—በዚያ ምንም ለአምላክነት ተቃራኒ የሆነ ክፋት እስከማይኖር ድረስ እግዚአብሔርን መምሰል ነው።

የሚቀጥሉት ሁለት ጥቅሶች ይህንን ጸሎት ይደመድማሉ፥-

> እንግዲህ በእኛ ውስጥ እንደሚሠራው እንደ ኀይሉ መጠን፣ ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ በላይ እጅግ አብልጦ ማድረግ ለሚቻለው፣ በቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በክርስቶስ እየሱስ፣ በዘመናት ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ለርሱ ክብር ይሁን! አሜን (ኤፌሶን 3፥20-21)።

> "ርካሽ ጸጋ ለራሳችን የምንሰጠው [ምናባዊ] ጸጋ ነው። ርካሽ ጸጋ ንስሐን ሳያስፈልገው የይቅርታ ስብከት፣ ያለ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ጥምቀት፣ ያለ ንስሃ ቁርባን ነው... ርካሽ ጸጋ ያለ ደቀ መዝሙርነት ጸጋ፣ ጸጋ ያለ መስቀል፣ ጸጋ ያለ እየሱስ ክርስቶስ፣ የሚኖርና ሥጋ የለበሰ ነው።
>
> — ዲያትሪክ ቦንሆፈር

ይህ ቡራኬ እግዚአብሔር ከምንጠይቀው ወይም ከምናስበው በላይ ማድረግ እንደሚችል ይናገራል። ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ስለገንዘብ ብልፅግና ሳይሆን ስለ መንፈሳዊ ሕይወት ነው። የቅድስና እና የብስለት ደረጃዎችን እንድንደርስ ሊረዳን የሚችለውን በውስጣችን የሚሠራው ኃይል አቅልለን መመልከት የለብንም።

## ክርስቲያናዊ ልምምዶች

አዲስ ኪዳን ወደ ቅድስና እና ብስለት የሚያሳድጉትን ልምምዶችን ይሰጠናል።

***በጎ ህሊና ይኑርህ።*** ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ መልካሙን ገድል እንድትጋደል (የድል አድራጊ ክርስቲያን ሕይወት ምሳሌ) መንገዱ እምነትና በጎ ኅሊናም ይኑርህ (1 ጢሞቴዎስ 1፥18-19) ብሎ ነገረው።[23] ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ 24፥16 "በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ንጹሕ ኅሊና እንዲኖረኝ ሁልጊዜ እጥራለሁ" ብሎም ተናግሯል። ሕሊናችንን ማዳመጥ ንስሐ እንድንገባ፣ እንድንመልስ፣ ሰው ጋር እንድንታረቅ ወይም ባሕርያችንን እንድንቀይር ሊያደርገን ይችላል። በጎ ሕሊና መኖር ማለት ሰዎች ኃጢአት መሥራታቸውን ሲገነዘቡ ኃጢአታቸውን ይናዘዛሉ እንዲሁም ንስሃ ይገባሉ ማለት ነው።

***ራስህን ለእግዚአብሔር ስጥ።*** በሮሜ 12፥1 ላይ ባለው ጠንካራ ምክር ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል:- "እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ ይህም እንደ ባለ አእምሮ የምታቀርቡት አምልኳችሁ ነው። " የሮሜ አማኞች በተለወጡ ጊዜ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር አቅርበው ነበር፤ ሆኖም እዚህ ላይ ጳውሎስ ለእግዚአብሔር የበለጠ ሙሉ በሙሉ መስጠትን አሳስቧል።

***ከአለም ጋር አትመሳሰል*** (ሮሜ 12፥2)። አለምን መምሰል ማለት በማያምን ማህበረሰብ እይታ መቀረፅ፣ እሴቶቹን እስከመጋራት እና እንደማያምኑት አይነት ባህሪ ማሳየት ነው። የዓለም ሰዎች በራስ ወዳድ፣ በኢፍትሐዊና በኃጢአት መንገድ የሥጋን ምኞት በሚሟላታቸው ማመካኛ ይፈልጋሉ። አማኝ የተለየ ነው (2 ቆሮንቶስ 10፥3-4)።

***አእምሮህን አድስ።*** ጳውሎስ የሮሜን ምክር እንዲህ ሲል ቀጥሏል፥-

> …መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሯችሁ መታደስ ተለወጡ (ሮሜ 12፥2)።

አንድ ሰው የአለምን አስተሳሰብ በመቃወም እና የእግዚአብሔርን አስተሳሰብ በተቀበለ ቁጥር እሱ ወይም እሷ የበለጠ እየተለወጠ ይሄዳል።

***በብርሃን ተመላለስ።*** ዮሐንስ እንዲህ ሲል ጽፏል:- "ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ እኛም በብርሃን ብንመላለስ፣ እርስ በእርሳችን ኅብረት አለን፤ የልጁም የእየሱስ ደም ከኀጢአት ሁሉ ያነጻናል" (1 ዮሐንስ 1፥7)። ብርሃን ለእውነት ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። ስለዚህ በብርሃን መመላለስ ማለት እውነትን መማር እና መከተል መቀጠል ማለት ነው።

***መከራን በእምነት ታገሥ።*** በ1 ጴጥሮስ 5፥10 ላይ ያለው የጴጥሮስ ቡራኬ የታደሰ፣ ጠንካራ እና የተረጋጋ አማኝ የመሆንን የከበረ አላማ ይጠቁማል፤ ግን ወደዚያ የሚያደርስ ይልቁንም ደስ የማይል መንገድን ይገልጻል። "የጸጋ ሁሉ አምላክ፣ ለጥቂት ጊዜ መከራ ከተቀበላችሁ በኋላ እርሱ ራሱ መልሶ ያበረታችኋል፤ አጽንቶም ያቆማችኋል" (1 ጴጥሮስ 5፥10)። መከራ አመለካከታችንን የምናጠራበት እና ባህሪያችንን የምናስተካክልበት መንገድ አለው።

---

[23] ጳውሎስ በተለይ መጋቢዎች ንጹሕ ሕሊና እንዲኖራቸው አሳስቦ ነበር፤ ይህንን ጉዳይ በተለይ ለመጋቢ ጢሞቴዎስ በጻፈው የመጋቢ መልእክቱ ውስጥ ለሦስት ተጨማሪ ጊዜ አጽንኦት ሰጥቷል። እነዚህም "በጎ ኅሊና" (1 ጢሞቴዎስ 1፥5) እና "ንጹሕ ኅሊና" (1 ጢሞቴዎስ 3፥8-9፤ 2 ጢሞቴዎስ 1፥3) ናቸው።

እግዚአብሔር እኛን የሚያሳድገንን መከራን ይፈቅዳል። ልንቀበለው እና እግዚአብሔር የሚያስተምረንን ለመማር መሞከር አለብን (2 ቆሮንቶስ 12፥7-10)።

► የእምነት መግለጫውን ቢያንስ ሁለት ግዜ አብራችሁ አንብቡ።

## የእምነት መግለጫ

የክርስቲያን ቅድስና የሚጀምረው አንድ ኃጢአተኛ ንስሐ ሲገባ እና በእግዚአብሔር ጸጋ ሲለወጥ ነው። አማኙ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመረዳት ሲያድግ እና መታዘዙን ሲቀጥል መንፈሳዊ እድገት ያሳያል። መቀደስ አማኙን አንጽቶ ወደ ተቀደሰ ባሕርይና ሕይወት የሚያመጣበት የእግዚአብሔር ሥራ ነው።

## ትምህርት 11 የቤት ስራዎች

(1) የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የቤት ስራ፦ ከታች ከተዘረዘሩት ዘርፎች መካከል እያንዳንዱን ተማሪ አንድ ይመደብ። ከሚቀጥለው ክፍለ ግዜ በፊት ክፍሉን አንብባችሁ በትምህርቱ ውስጥ ካለው ሃሳብ ላይ ምን እንደሚናገር በአንድ አንቀፅ ፃፉ።

- ኢሳይያስ 6፥1-8
- ሐዋርያት ሥራ 2፥1-18
- 1 ቆሮንቶስ 10፥1-13
- 1 ተሰሎንቄ 5፥14-24
- ቲቶ 2፥11-14

(2) ፈተና፦ የሚቀጥለው ክፍለ ግዜ የምትጀምሩት በትምህርት 11 ፈተና ነው። ለፈተና ዝግጅት እንዲሆን የፈተና ጥያቄዎችን አጥኑ።

(3) የማስተማር የቤት ስራ፦ ከክፍል ውጪ የማስተማርያ ግዜን ቀጠሮ መያዝ እና ማስተማራችሁን ሪፖርት ማድረግ አስታውሱ።

## ትምህርት 11 ፈተና

(1) የቅድስና መሰረታዊ ትርጉሙ ምንድን ነው?

(2) እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ማለት ምን ማለት ነው?

(3) ቅድስና ለአምልኮ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

(4) ክርስቲያናዊ ቅድስና መች ይጀምራል?

(5) በብርሃን መመላለስ ማለት ምን ማለት ነው?

(6) የሕይወት ዘመን ውስጥ ያለውን የቅድስና ሂደት ውስጥ አማኝ ሲያልፍ በሕይወቱ ምን ይሆናል?

(7) የተወረሰ ውድቀት ምን ማለት ነው?

(8) አንድ አማኝ በሥጋ፥ በነፍስ እና በመንፈስ ነውር የሌለበት ሆኖ እስከእየሱስ መመለስ ድረስ እንዴት መገኘት ይችላል?

# ትምህርት 12

# ቤተክርስቲያን

**የትምህርቱ አላማዎች**

(1) ተማሪው የሚከተሉትን ማስረዳት ይችላል

- የቤተክርስቲያን መነሻ
- ቤተክርስቲያን እንደ ህያው ተቋም
- ቤተክርስቲያን እንደ ህያው አጥቢያ
- የአለም አቀፋዊቷ ቤተክርስቲያን የአንድነት መሰረት
- የአጥቢያ ቤተክርስቲያን የአንድነት መሰረት
- ዋና ዋና የክርስቲያን ሀይማኖት ስነ-ስርአቶች በቤተክርስቲያን
- የቤተ ክርስቲያን አላማ
- ስለ ቤተክርስቲያን ክርስቲያናዊ የእምነት መግለጫ

(2) ተማሪዎች በየአጥቢያ ቤተክርስቲያናቸዉ የሚጠበቅባቸዉን ሃላፊነት ይረዳሉ።

**የቤተክርስቲያን መነሻ**

► ኤፌሶን 3፥3-10 አብራችሁ አንብቡ። ይህ ክፍል ስለ ቤተክርስቲያን ምን ይነግረናል?

ከአዲስ ኪዳን በቀደሙት ክፍለ ዘመናት ቤተክርስቲያን ሚስጥራዊና በሙላት ያልተገለጠች ነበረች። የእግዚአብሔርን ፀጋን የተለማመዱና ከእግዚእብሄር ጋር ህብረት የሚያረጉ ሰዎች ነበሩ (ሮሜ 4፥1-8)። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን አልተመሰረተችም።

► ቤተክርስቲያን መች ተጀመረች?

ቤተክርስቲያን የጀመረችዉ በእየሱስ ህይወት እና አስተምሮ ላይ ነዉ። ቤተክርስቲያን የተመሰረተችዉ በተደረገልን ድነት ስራ ላይ ነዉ (ማቴዎስ 16፥16-18)። የጴንጤቆስጤ ቀን የቤተ ክርስቲያን ዘመን ጅማሮ ነዉ። ከዛ ጊዜ ጀምሮ ቤተክርስቲያን ክርስቶስ በምድር መመላለስ ሳያስፈልገው በመንፈስ ቅዱስ ጉልበት ቀጥላለች (ዮሐንስ 16፥7)።

እየሱስ ለደቀ መዛሙረቱ ትምህርቱን በመላዉ አለም እንዲያደርሱ ስልጣንን ሰጥቷቸዋል (ማቴዎስ 28፥18-20)። መንፈስ ቅዱስ ወደ እዉነት ሁሉ እንደሚመራቸው ቃል ገብቶላቸዋል (ዮሐንስ 16፥13)። ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት ተብላ ልትጠራ ትችላለች፤ ምክንያቱም የሐዋርያት አስተምሮ የቤተክርስቲያን ትምህርት መሰረቶች ናቸዉ። ከነዚህ ትምህርቶች በተቃርኖ የሚቆም ሁሉ ክርስቲያን ሊባል አይችልም።

የቤተክርስቲያን መነሻዎች፥

1. የእየሱስ አገልገሎት
2. የክርስቶስ የድህነት ስራ
3. የጴንጤቆስቴ ቀን ክስተት
4. የሐዋርያት ትምህርቶች ማደግ

**ቤተክርስቲያን እንደ ህያው ተቋም**

ቤተክርስቲያን ከቤተሰብ ጋር በንፅፅር መቅረብ ትችላለች፤ እግዚአብሔር እንደ አባት፣ አማኞች ደሞ ወንድምና እህት ናቸዉ (ማቴዎስ 12፥48-50፣ ቈላስይስ 1፥2)። ቤተ ክርስቲያን አንድ ምንጭና ዘር የሌላት መንግስት ናት (1 ጴጥሮስ 2፥9-10)። ቤተክርስቲያን እንደ አካል ብትመሰል ክርስቶስ ራስ ነው (ኤፌሶን 4፥15-16፣ ኤፌሶን 5፥30)። ምእመኖች ደሞ አብረው የሚሰሩና የሚተጋገዙ ናቸው (1 ቆሮንቶስ 12፥14፣ 26)።

ክርስቲያን እንደ ቤተ ክርስቲያን አካልነቱ እራሱን የመነጠል እሳቤ ሊኖረዉ አይገባም። እርሱ ሌሎች ወንድሞችን ይፈልጋል፥ ለሌሎች ወንድሞችም ያስፈልጋል (1 ቆሮንቶስ 12፥21)። ከቤተ ክርስቲያን ተነጥሎ መንፈሳዊ ህይወትን መምራት ልክ አይደለም።

ከቤተክርስቲያን መነጠል ክርስቶስ በምድር ከሚያደርገው መነጠል ነው። አልፎም ቤተ ክርስቲያንን አለማክበርና አለመውደድ ፥ ክርስቶስን አለማክበርና አለመውደድ ነው።

**ቤተክርስቲያን እንደ ህያው አጥቢያ**

ቤተክርስቲያን አለማቀፋዊ ነች፥ በውስን ቦታም በየአጥቢያዎቹም ትገኛለች። ክርስቲያኖች በአካል በያሉበት ካልተገናኙ ቤተ ክርስቲያን መቀጠል አትችልም። ጳውሎስ ለቆሮንጦስ አማኖች የክርስቶስ አካሎች እንደሆኑ ነግሮአቸዋል (1 ቆሮንቶስ 12፥27)፥ ይህም እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተክርስቲያን የአንድ ክርሰቶስ አካል እንደሆነ ይነግረናል።

እግዚአብሔር አጥቢያ ቤተክርስቲያናት የእምነት ቤተሰብ እንዲሆኑ ነዉ የሰራቸው

1. በመንፈሳዊ ሰጦታዎች የሚያገለግሉ የአለማቀፋዊ ቤተክርስቲያን አካሎች
2. አለማዊም/ስጋዊ ሆነ መንንፈሳዊ ፍላጎቶችን መተጋገዝ
3. የእግዚአብሔርን ጥበብ በሕይወት መንገዶች ሁሉ መግለጥ
4. ያላመኑት እንዲቀየሩ እና ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብነት እንዲቀላቀሉ መጋበዝ

እውነተኛ ሕብረት ኢኮኖሚንም ይጨምራል ምክንያቱም ሕብረት ህይወትን በጋራ መካፈልና ስለ ሌሎች ፍላጎቶች መጨነቅንም ይጨምራል (ያዕቆብ 2፥15-16፣ ያዕቆብ 1፥27)። በክርስቶስ ወንድምና እህት የሆኑትን ያ አባል በቤተክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ተሳታፊ እስከሆነና አቅሙ በሚፈቅደው መጠን ኃላፊነቱን እየተወጣ እስካለ ድረስ መፈለግ የቤተክርስቲያን ሀላፊነት ነው በሚቻለዉ ሁሉ መተጋገዝ ግዴታ ነው።

የአጥቢያ ቤተክርስቲያናት እንዲመሰረቱ እና እንዲዐኑ እግዚአብሔር መንፈሳዊ ስጦታዎችንና ጥሪዎችን ይሰጣል (ኤፌሶን 4፥11-12)።

የአጥቢያ ቤተክርስቲያናት ማህበረሰብን ያገለግላሉ። ተቀዳሚ አላማቸው ግን መንፈሳዊ አገልግሎት፥ የወንጌል ሰበካና የእግዚአብሔርን አውነት ለሰዎች ሁሉ ማድረስ ነው። ቤተክርስቲያን በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ ቁሳዊ ፍላጎቶችን የምታሟላ ቢሆንም፥ ቅድሚያ የምትሰጠው ግን በቤተክርስቲያኗ መንፈሳዊ ኅብረት ውስጥ ላሉት ሰዎች ነው። (ገላትያ 6፥10)።

## የቤተክርስቲያን ፍፁምነት

እየሱስ ለእንከን አልባና ንፅህ ቤተ ክርስቲያን ራሱን ሰጥቷል (ኤፌሶን 5፥27)። ቤተክርስቲያን ሁልጊዜ ይቅር ለማለት ዝግጁ መሆን አለባት እንጂ ኃጢአትን በፍፁም ማስተናገድ የለባትም። መሪዎችም ለመንፈሳዊ ሕይወት ምሳሌ መሆን አለባቸው (1 ጢሞቴዎስ 3፥2-3)። አንድ ምእመን በሃጢአት ቢወድቅ በመሪዎች ንስሃ እንዲገባ ሊጠየቅ ይገባል፥ ነገር ግን ፈቃደኛ ባይሆን ከህብረቱ ይገለላል (1 ቆሮንቶስ 5፥11-13)።

► ለምንድነው ቤተክርስቲያን ፍፁም ያልሆነችው?

ቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሰዎች ፍፁም ሊሆኑ አይችሉም። ቤተክርስቲያን ወንጌል ሰባኪ ስለሆነች ንስሀ ያልገቡ ሰዎች በቤተክርስትያን ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ። ካመኑት መሃልም የገባቸውን እውነት እንዴት መኖር እንዳለባቸው የማያወቁ ይኖራሉ። ክርስትና የመንፈሳዊ እድገት ሂደት ስለሆነ በሳል የሚባሉ ክርስትያኖችም ሊፈተኑ ይችላሉ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ያለማቋረጥ ማስተማር እና ወደ ወንፈሳዊ እድገት ከፍታ መምራት ይጠበቅባታል (ኤፌሶን 4፥11-16፤ 2 ጢሞቴዎስ 3፥16-17)።

## የቤተክርስቲያን ምንነት

**አለማቀፋዊቷ የቤተክርስቲያን በሁሉም ቦታና ጊዜ የሚገኙ አማኞችን የሚያጠቃልል ነው።** ይችን ቤተክርስቲያን የሚያስተዳድር ወይም የአባላቶቿ ዝርዝር ያለው ምድራዊ ድርጅት ስለሌለ የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ትባላለች።

**አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ማህበረሰብ የሚገኙ በአካል መገናኘት የሚችሉ አባሎችን ይዛ የክርስቶስ አካልነት ሚናዋን የምትወጣ ናት።** ይህ ስብስብ ሌላ አላማ ካለዉ ቤተ ክርስቲያን ሊባል አይችልም።

የሚከተለው ጠለቅ ያለ ማብራሪያ ወይም ት ርጉም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ከሌሎች የቡድኖች ዓይነቶች ለመለየት የሚረዳው ነው። “የተጠመቁ አማኞች ስብስብ ሲሆን ለአምለኮ፥ ለመነቃቃት፥ ለአገልግሎት፥ ለህብረትና ለወንጌል ስርጭት የተሰባሰቡ ናቸው። በተጨማሪም በመንፈሳዊ መሪነት የሚያመኑ፥ ባላቸው የፀጋ ስጦታ በየትኛውም የማህበረሰብ ተሳተፎአቸው የሚመሰክሩ እና ዘወትር ትእዛዛትን የሚጠብቁ ናቸው። ”[24]

[24] David Dockery, *Southern Baptist Consensus and Renewal፥ A Biblical, Historical, and Theological Proposal* (Nashville፥ B&H Publishing Group, 2008), 127

## የአለም አቀፋዊቷ ቤተክርስቲያን አንድነት

ለሁሉም ጊዜና ቦታ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ነው ያለችው። እየሱስም አለ "ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፣" (ማቴዎስ 16፥18) ቤተ ክርስቲያኖቼን አላለም። ጳውሎስም እንደፃፈው አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ እና አንድ ተስፋ አንድ ጌታ፣ አንድ እምነትና አንድ ጥምቀት አለ (ኤፌሶን 4፥4-6)።

የጥንት ክርስትና የእምነት መግለጫ የሚያያዘው ክካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋር ነው። ይህ ግን የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን በአለም ላይ ያሉ ሁሉንም እውነተኛ ክርስትያኖችን ነው።

> ''የኔ ልብ ካንተ ጋር እንደሆነው ሁሉ አንተም ልብህን በኔ ላይ ከጣልክ፥ በጥልቅ ስሜት ዉደደኝ፥ ከወንድም ይልቅ እንደሚቀርብ ጓደኛ፥ በክርስቶስ በሆነ ወንድማማችነት፥ የአዲሲቷ እየሩሳሌም ህብረት እንደሆነ ዜጋ፥ ለአንድ ጦር እንደተሰለፈ ወታደር፥ ለደህንነት አንድ መሪ እንዳለው፥ ለአንዲት መንግስት እንደሚያብር፥ ክርስቶስን በፅናትና በትዕግስት እንድሚጠብቅ፥ በጋራ የክብሩም ወራሽ እንደሚሆን ዉደደኝ''
>
> ጆን ዌስሊ፥ ከስብከቱ አጥሮ የተወሰደ "ካቶሊክ ስፒሪት"

የአለም አቀፋዊቷ ቤተ ክርስቲያን አንድነት አንድ ወጥ ተቋምና አመራር ያላት አይደለችም ይህ ደሞ ክርስቶስ ዳግም ክመምጣቱ በፊት የሚሆን አይደልም። ብዙዎች እንዲሆን ቢመኙም የእግዚአብሔር ፍቃድ ግን አይደለም ምክንያቱም እየሱስ ደቀ መዛሙርቶቹ ከህብረታቸው ዉጪ የሆነ ሰው መመስከር የለበትም ብለው ሲያስቡ አስተካክሏቸዋል (ሉቃስ 9፥49-50)። እየሱስ አለም አቀፋዊቷ ቤተ ክርስቲያን አንድ አመራር እንዲኖራት ቢፈልግ ራሱ በምድር ላይ ቆይቶ ይመራት ነበር። ነገር ግን እየሱስ በምድር ላይ ቢቆይ የመንፈስ ቅድስ ልዩ ልዩ ስራ አይኖርም ብሎ አሰበ (ዮሐንስ 16፥7)።

► የአለም አቀፋዊቷ ቤተክርስቲያን አንድነት መሰረቱ ምንድነው?

የአለም አቀፋዊቷ ቤተክርስቲያን አንድነት መሰረት የሚከተሉት ናቸው፤

1. የሐዋርያት አስተምህሮ/ዶክትሪን
2. ከክርስቶስ ጋር በመሆን መለወጥ የሚችል ህብረት

አስተምህሮአዊ አንድነት ስንል ሁሉም ክርስትያኖች በሁሉም ጉዳይ ላይ ይስማማሉ ማለት አይደለም። በወሳኝ ጉዳዮች ሳይቀር ልዩነቶች አሉ። አስተምህሮአዊ አንድነት ስንል ስለ እግዚአብሔርና ክርስቶስ ማንነት እንዲሁም ስለ ወንጌል የጋራ አቋም አላቸው፤ ያለበለዚያ አንድ አምላክን ማምለክም ሆነ ፀጋውን መካፈል አይችሉም።

አስተምህሮ ብቻውን ለክርስትያናዊ አንድነት አያግዝም፤ በተጨማሪም ከክርስቶስ ጋር ያለ ህብረትን የሚለውጥ ክርስትያናዊ ህብረትን ያጠናክራል። ንስሃ ስለገቡ፥ እምነታቸውን በክርስቶስ ላይ ስለ ጣሉና መንፈስ ቅዱስ አብሮአቸዉ ስላለ በመሃላችው ለዩ ህብረት አለ። በተለያየ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ቢሆኑም እርስበርሳቸው ይተዋወቃሉ።

> ''በእውነት የተባረከ ልብ ከራሱ አብልጦ ስለሌሎች መዳን አብዝቶ እንደሚጨነቅ እየተረዳው መጥቻለው። ''
>
> ዴኒስ ኪንሎው

## የአጥቢያ አብያተ ክርስትያናት አንድነት

ማንኛውንም ሰው ክርስትያን ነው ለማለት በወሳኝ የክርስትና አስተምሮት ማመን አለበት፤ በተጨማሪም ከክርስቶስ ጋር ያለ የሚለውጥ ህብረት ሊኖረው ይገባል። ነገር ግን አጥቢያ አብያተ ክርስትያናት ጠለቅ ያለ የአስተምሮ ትንታኔ ያስፈልጋቸዋል።

አጥቢያ አብያተ ክርስትያናት አብረው የሚያመልኩ፥ ወንጌልን የሚሰብኩ፥ ማህበረሰብ የሚያገለግሉና በኑሮአቸው ምሳሌ መሆን የሚችሉ ሰዎች ስብስብ ናቸው። ይህንን አላማ ለማሳካት ጠለቅ ባሉ የአስተምህሮት ጉዳይ ላይ መስማማት አለባቸው።

ለምሳሌ፥ በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስትያን ያለ ሰው ወጣቶችንና አዲስ አማኞችን ለልሳን ፀጋ እንዲፀልዩ ሊነግራቸው ይችላል፤ የቤተ ክርስትያን መሪዎች እና ሽማግሌዎች ደሞ የልሳን ፀጋ ለሁሉ የተገባ እንዳልሆነ ሊያምኑ ይችላሉ። የእግዚአብሔር ፈቃድ ባልሆነ ልምምድ ውስጥ ሆነው መንፈሳዊ ግራ መጋባት ውስጥ እንዳይሆኑ ይሰጋሉ። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ባንዲት ቤተ ክርስትያን ውስጥ አብረው መሆን ይከብዳቸዋል። መሪዎች እንደ አማኝ ቢያዩአቸውም ግርታ የሚፈጥር ነገር እንዲሰበኩ አይፈቅዱላቸውም።

የአጥቢያ አብያተ ክርስትያናት የጋራ ኑሮአቸውንና አገልግሎታቸውን የሚነኩ ጉዳዮች ላይ በአስተምሮ መስማማት አለባቸው። ይህንንም በፅሁፍ ቢያሰፍሩ ጥሩ ነው። የሚጠቅመውም አማኝን ከማያምን ለመለየት ሳይሆን የትኛው አስተምሮ አማኞችን የማቀራረብና ለዘወትር አምልኮ እንዲሁም አገልግሎት አንድ እንደሚያደርጋቸው ያሳያል።

## የቤተክርስትያን ስርአቶች

እየሱስ ሁለት ስርአቶች ለቤተክርስትያን ሰቷል።

**ጥምቀት** የክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ምልክት ነው (ሮሜ 6፥3-4)። ጥምቀት አማኞች በሀጢያት ሞትን እና በክርስቶስ ደሞ ትንሳኤን ማግኘታቸውን የሚያረጋግጡበት ነው። ጥምቀት አያድንም። ጥምቀት መለወጣችንን በይፋ የምናሳይበት ነው (ዮሐንስ 3፥7-8)።

**የጌታ ራት/ቅዱስ ቁርባንን** የጀመረው እየሱስ ነው። ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ከመሰቀሉ በፊት ያለው የመጨረሻው ራት ነው (1 ቆሮንቶስ 11፥23-25)። ዳቦውና ወይኑ ለመዳናችን የተከፈለውን የእየሱስን ደምና ስጋ ይወክላል። ለስጋችን ምግብን ስንበላ ለነፍሳችን ደሞ በሱ መስዋዕትነት ላይ እንደገፋለን (ዮሐንስ 6፥53-58)።



የቤተ ክርስትያን ስርአቶች ‘’የፀጋ መንገዶች’’ ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ። ያለ እምነትና መታዘዝ ከተከወኑ ግን ፀጋን አያድሉም። እግዚአብሔር የሰጠን ስርአቶች ናቸው። በእምነት ከተደረጉ ፀጋን ያሰጣሉ።[25]

► የቤተክርስትያን አላማ ምንድነው?

---

[25] ምስል፥ "The Lord's Supper" በAllison Estabrook ኦክቶበር 14፣ 2022 ከhttps፥//www.flickr.com/photos/sgc-library/52476662295/, licensed under CC BY 4.0.

**በአዲስ ኪዳን መጽሐፍት የሚገኙ አንዳንድ የቤተ ክርስትያን አላማዎች**

> "እግዚአብሔር የቤተክርስትያን ህይወታችን ህንፃና አገልግሎት ላይ ብቻ እንዲያተኩር ይፈልጋል ብዬ አላምንም፥ እግዚአብሔር ለቤተክርስትያን የሚፈልገው በየትኛውም አይነት ስብስብ ዉስጥ የነቃ የደቀ መዝሙር ህይወት፥ ተልእኮና ህብረትን መጠበቅ ነው።"
>
> ፍራነሲስ ቻን

**ቤተክርስትያን የሚከተሉትን ማድረግ አለባት**

1. *ወንጌል መስበክ* (*ማቴዎስ* 28፥18-20)
2. *በህብረት ማምለክ* (1 *ቆሮንቶስ* 14፥26)
3. *አስተምሮን መጠበቅ* (1 *ጢሞቴዎስ* 3፥15፤ *ይሁዳ* 1፥3)
4. *አገልጋዮችን በገንዘብ ማገዝ* (1 *ጢሞቴዎስ* 5፥17-18)
5. *የወንጌል መልእክተኞችን (ሚሽነሪዎችን) መላክ፣ ማገዝ* (*ሐዋርያት ሥራ* 13፥2-4፤ *ሮሜ* 15፥24)
6. *አባሎችን በሚያስፈጋቸው ነገር ማገዝ* (*ሮሜ* 12፥13፤ 1 *ጢሞቴዎስ* 5፥3)
7. *በሃጢያት የወደቁትን ማስተካከል* (1 *ቆሮንቶስ* 5፥9-13)
8. *ጥምቀትንና ቅድስ ቁርባንን መፈፀም* (*ማቴዎስ* 28፥19፤ 1 *ቆሮንቶስ* 11፥23-26)
9. *አማኞችን ወደ መንፈሳዊ ብስለት መምራት* (*ኤፌሶን* 4፥12-13)
10. *ማህበረሰብን በሚችሉት ሁሉ ማገዝ* (*ገላትያ* 6፥10፤ *ኤፌሶን* 4፥28፤ *ዕብራውያን* 13፥16)

አብዛኞቹ ከላይ ያሉት ክንውኖች በአንድ ሰው ብቻ የሚሰሩ አይደሉም። የአማኞችን ትብብርና የአመራር መዋቅር ይፈልጋል።

እግዚአብሔር አማኞች በአቅራቢያቸው በሚገኝ አጥቢያ እንዲተጉና ቤተ ክርስትያኗ ምድራዊ ግቧን እንድታሳካ ይፈልጋል። በቤተ ክርስትያን የማያገለግል አማኝ የክርስቶስ አካልነት ግቡን አያሳካም።

**ማስወገድ ያለብን ስህተት፥ መንፈሳዊ ግለኝነት**

*ለክፍሉ መሪ ማስታወሻ- የክፍሉ አባል ይህንን ክፍል ማስረዳት ይችላል።*

አንዳንድ ሰዎች በአጥቢያ አብያተ ክርስትያናት መሳተፍን አይመርጡም። ለእሁድ አምልኮ የፈለጉበት ቦታ ሄደው ማምለክ ይፈልጋሉ። ቤተክርስትያንን በተልእኮዋ ሊያግዙ አይችሉም ምክንያቱም ቤተክርስትያን በእነሱ ጥገኛ ልትሆን አትችልም። መንፈሳዊ ህብረትን ለማርገም ሆነ ሃላፊነት ለመውሰድ የሚያበቃ ግንኙነት የላቸውም። ሁሉም ክርስትያን ይህን ካረገ ቤተክርስትያን አትኖርም።

► የእምነት መግለጫውን ቢያንስ ሁለት ግዜ አብራችሁ አንብቡ።

**የእምነት መግለጫ**

ክርስቶስ አንዲት ቅድስት አለማቀፋዊት ቤተክርስትያን ገንብቷል፤ በየአጥቢያ ቤተክርስትያን እንደ ክርስቶስ አካል የምትገለፅ። ቤተክርስትያን የሐዋርያትን አስተምህሮ ትከተላለች ሁሉንም እውነት ተጠብቃለች። ቤተክርስትያን

በህብረት ለሁሉም ፍላጎቶች የምታገለግል የእግዚአብሔር ቤተሰብ ነች። ቤተክርስትያን እግዚአብሔርን ታመልካለች፥ ወንጌል ትሰብካለች፥ አማኞችን ደቀመዝሙር ታረጋለች።

## ትምህርት 12 የቤት ስራዎች

(1) የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የቤት ስራ፦ ከታች ከተዘረዘሩት ዘርፎች መካከል እያንዳንዱን ተማሪ አንድ ይመደብ። ከሚቀጥለው ክፍለ ግዜ በፊት ክፍሉን አንብባችሁ በትምህርቱ ውስጥ ካለው ሃሳብ ላይ ምን እንደሚናገር በአንድ አንቀፅ ፃፉ።

- 1 ቆሮንቶስ 5፥1-13
- 1 ቆሮንቶስ 6፥1-8
- 1 ቆሮንቶስ 12፥14-31
- ኤፌሶን 4፥11-16
- ያዕቆብ 2፥1-9

(2) ፈተና፦ የሚቀጥለው ክፍለ ግዜ የምትጀምሩት በትምህርት 12 ፈተና ነው። ለፈተና ዝግጅት እንዲሆን የፈተና ጥያቄዎችን አጥኑ።

(3) የማስተማር የቤት ስራ፦ ከክፍል ውጪ የማስተማርያ ግዜን ቀጠሮ መያዝ እና ማስተማራችሁን ሪፖርት ማድረግ አስታውሱ።

## ትምህርት 12 ፈተና

(1) የቤተ-ክርስቲያን ዘመን መች ጀመረ?

(2) ቤተ-ክርስቲያን ሐዋርያዊት ተብላ መጠራት የምትችለው ለምንድን ነው?

(3) የቤተ-ክርስቲያን መሰረት አራት ገጽታዎችን ምንድን ናቸው?

(4) አለማቀፋዊቷ ቤተ-ክርስቲያን ማን ነች?

(5) አጥቢያ ቤተ-ክርስቲያን ምንድን ነው?

(6) ካቶሊካዊት ቤተ-ክርስቲያን የሚለው ሃሳብ የመጀመርያ ትርጉሙ ምን ነበር?

(7) አለም አቀፋዊቷ ቤተ-ክርስቲያን አንድንት የሚሰጡ ሑለት ነገሮች ምንድን ናቸው?

(8) ቤተ-ክርስቲያን የምትጋራው የእምነት መግለጫ ሊኖራት የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

(9) የአጥቢያ ቤተ-ክርስቲያን ስድስት አላማዎችን ዘርዝሩ።

# ትምህርት 13

# ዘላለማዊ እጣ

**የትምህርቱ አላማዎች**

(1) ተማሪው የሚከተሉትን ማስረዳት ይችላል

- የመንግስተ ሰማይ ተቀዳሚ ተግባር
- በቅዱስ መፅሃፍት የተገለጠችው መንግስተ ሰማይ ባህሪ
- በቅዱስ መፅሃፍት የተገለጠው ዘላለማዊ ቅጣት ባህሪ
- ዘላለማዊ ቅጣትን የካዱ ሀይማኖቶች መሳሌ
- የዘላለማዊ ቅጣት ፍትሃዊነት
- ስለ ዘላለማዊ እጣ ክርስቲያናዊ የእምነት መግለጫ

(2) ተማሪዎች አንዳንድ ድርጊቶች የማይመለስ ዘላለማዊ መዘዝ እንደሚያመጣባቸው ይረዳሉ።

**ክፍል 1፥ የአማኞች ዘላለማዊ እጣ**

► ራእይ 21 አብራችሁ አንብቡ። ይህ ክፍል ስለ አማኞች እጣፈንታ ምን ይነግረናል?

ሁሉም ፍጥረት ለእግዚአብሔር ክብር ተፈጥሯል፥ ነገር ግን መንግስተ ሰማይ እግዚአብሔር በአምሳሉ በፈጠራቸው ፍጥረታቶች በሙላት የሚመለክበት ማእከላዊ ስፍራ ናት (ራእይ 5፥11-14 አንብቡ)። የእግዚአብሔር ክብር በሙላት ብርሃን በመሆን በከተማው ላይ ይገለጣል (ራእይ 21፥23)። እግዚአብሔር ፊቱን የምናይበትም ቦታ ነው (ራእይ 22፥4)።

በመንግስተ ሰማይ አማኞች እግዚአብሔርን በማምለክ ፍስሃና ሙላትን የሚያገኙበት ነው። መዝሙር 16፥11 "በአንተ ዘንድ የደስታ ሙላት፣ በቀኝህም የዘላለም ፍሥሓ አለ። " ይላል። ፍስሀና እና አምልኮ ይስማማሉ። እግዚአብሔር ማንነቱን ተረድተን ማንነቱ በሚገባው መጠን እንድናመልከው በመልኩ ፈጥሮናል። እንድናመልከው ስሜት፥ የማፍቀር አቅምና ብልሀት ተሰጥቶናል።

እየሱስ ለሐዋርያት ይህን ብሎ ነበር፥

> ልባችሁ አይጨነቅ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፤ በእኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ ይህ ባይሆንማ ኖሮ እነግራችሁ ነበር፤ የምሄደውም ስፍራ ላዘጋጅላችሁ ነው። ሄጄም ስፍራ ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ፣ እኔ ባለሁበት እናንተም ከእኔ ጋራ እንድትሆኑ ልወስዳችሁ ዳግመኛ እመጣለሁ (ዮሐንስ 14፥1-3)።

የእየሱስ ስለ መንግስተ ሰማያት የሚነግረን አለ። ዋናው ነገር መንግስተ ሰማያት የእግዚአብሔር ቤት እንደሆነ፥ እሱስም የአባቴ ቤት በሎታል። ሌላው ዋና ነገር አንድ ቀን በዛ እንደምንኖር ነው።

የመንግስተ ሰማያት ተስፋ በምድር እንዴት መኖር እንዳለብን ይመራናል። በመንግስተ ሰማያት እሳቤ የሚኖር ሰው በምድር መልካምን ያረጋል። ሰማያዊ በረከትን የሚጠብቅ ሰው በፈተናዎች የፀናል የእግዚአብሔርንም ፍቃድ ይፈፅማል። እየሱስም ዋጋ ስለሚከፍሉ ሰዎች ይህንን በኋል "በሰማይ የምትቀበሉት ዋጋ ታላቅ ስለ ሆነ ደስ ይበላችሁ፤ ሐሤት አድርጉ" (ማቴዎስ 5፥12)።

**የመንግስተ ሰማያት ባህርያት**

► ስለ መንግስተ ሰማያት ምን ምን እናውቃል?

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የሚፈልጉትን አይነት ቤት በምድር ላይ መግዛት አይችሉም ወይም ያላቸውን እንደሚፈልጉት ማርግ ላይችሉ ይችላሉ፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ገደብ የሌለው ሀይልና ሀብት አለው። ስለዚህ የሱ ቤት እንደሚፈልገው እንደሆነ እናወቃለን። ይህ ድሞ መንግስተ ሰማያት ከእግዚአብሔር ተፈጥሮ ጋር የማይጣረስ መልክ እንዳለው ያረጋግጥልናል።

በመንግስተ ሰማያት ሀጥያት የለም። በመንግስተ ሰማያት ያሉ ፍጡራን ሰው፥ መላአክ ወይም ሌላ ሁሉም ቅዱስ ናቸው። (ራእይ 21፥8፤27 ይነበብ።)

መንግስተ ሰማያት ከሀዘን፥ ህመም፥ ግጭት ወይም አደጋ ከመሳሰሉ የሀጢአት ፍሬዎች ነፃ ነች (ራእይ 21፥4 ይነበብ)። ማርጀት፥ ሞትን የመሳሰሉ እርግማኖች አይኖሩም (ራእይ 22፥3 ይነበብ)።

የመንግስተ ሰማያት ውበት በቃላት ከሚገልፀው በላይ ነው። በመፅሀፉ ስለ ኢያስጲድ ቅጥር፥ የእንቁ ደጅ፥ ከከበረ ድንጋይ የተሰራ መሰረት እና የወርቅ ጎዳና በዝርዝር ተፅፏል (ራእይ 21፥18-21 ይነበብ)።

> ''የትኛውም ምድራዊ ልምምድ እንደማያረካኝ ካወቅኩ ልሰጠው የምችለው ማብራሪያ ለዚች ምድር አለመፈጠሬን ነው። ምድራዊ ደስታ ለፍፁም እርካታ አይሆን ይሆናል፥ ሊያነቃው ወይም ወደ እውነተኛ ሊመራ ይሆናል፤ ወደሌላኛው የሚመራ ማንቂያ ደውል ነው፤ ሌሎችንም ወደዛ የሚመራ። ''
>
> ሲኤስ ሌዊስ፤ ሜር ክርስቲያኒቲ

**ማን እና መቼ?**

መንግስተ ሰማያት ንስሃ ለገቡና እየሱስን እንደ አዳኝ ላመኑ ናት (ዮሐንስ 3፥16)። መጽሐፍ በዘላለማዊ እሴቶች የምንኖር ከሆነ በሰማይ የማይጠፋና አስተማማኝ የሆነ ዘላለማዊ መዝገብ ማከማቸት እንደምንችል ይነግረናል (ማቴዎስ 6፥20 ይነበብ)። መንግስተ ሰማያት በሚሊዮን የሚቆጠሩ በተቤዡ ሰዎችና መላአክት የተሞላች ነች (ራእይ 5፥8-11)።

መች ነው ወደ መንግስተ ሰማያት የምንገባው? እየሱስ አብሮት የተሰቀለውን ወንበዴ በገነት በዛው ቀን አበረው እንደሚሆኑ ነግሮታል (ሉቃስ 23፥43)። ጳውሎስም ከስጋ መለየት ከጌታ ጋር መሆን መሆኑን ነግሮናል (2 ቆሮንቶስ 5፥8)፤ ስለዚህ አማኝ በስጋ እንደሞተ ወደ መንግስተ ሰማያት እንደሚገባ እናውቃለን። በጌታ ምፅአት በስጋ ያልሞቱ ሞትን ሳያዩ ወደ መንግስተ ሰማያት ይገባሉ (1 ቆሮንቶስ 15፥51-52፤ 1 ተሰሎንቄ 4፥13-18 ይነበብ)።

**ክፍል ሁለት፥ የማያምኑ ዘላለማዊ እጣ ፈንታ**

*ምድራዊ ቅጣት የሆነ ቀን ማበቃቱ አይቀርም፤ ምንም እንኳን ተቀጪው ሲሞት ቢሆንም። ነገርግን እየሱስ ዘላለማዊ ቅጣትን እንደዚህ ገልፆታል፥*

> *እናንተ የተረገማችሁ፤ ለዲያብሎስና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው የዘላለም እሳት ከእኔ ተለይታችሁ ሂዱ... እነዚህም ወደ ዘላለም ፍርድ፣ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ (ማቴዎስ 25፥41፣ 46)።*

*እየሱስና ሀዋርያት ዘላለማዊ ቅጣት፥ የእሳት ባህርና ሲኦል መኖራቸውን አረጋግጠውልናል። እየሱስ ከዚህ ጥፋት እንድንተርፍ አስጠንቅቆናል። የእየሱስ እና ሀዋርያት ቃል የሚከተለው ነው፥*

> *በዓለም መጨረሻም ልክ እንደዚሁ ይሆናል፤ መላእክት መጥተው ኀጢአተኞችን ከጻድቃን በመለየት፣ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት ወደ እቶን እሳት ይጥሏቸዋል (ማቴዎስ 13፥49-50)።*

*ለፈሪሳውያን እየሱስ አላቸው "እናንተ እባቦች፤ የእፉኝት ልጆች! ከገሃነም ፍርድ እንዴት ልታመልጡ ትችላላችሁ?" (ማቴዎስ 23፥33)።*

*በሌላ ጊዜ እየሱስ ከፈሪሳውያን ጋር ሲያወራ ሞቶ ወደ ሲኦል የገባን አንድ ሰው ሥቃይ እንዲህ ሲል ገልጾታል፥*

> *በሲኦልም እየተሠቃየ ሳለ ቀና ብሎ ከሩቅ አብርሃምን አየ፤ አልዓዛርንም በዕቅፉ ይዞት አየ። እርሱም፣ 'አብርሃም አባት ሆይ፤ ራራልኝ፤ በዚህ ነበልባል እየተሠቃየሁ ስለ ሆነ፣ አልዓዛር የጣቱን ጫፍ ውሃ ነክሮ ምላሴን እንዲያቀዘቅዝልኝ እባክህ ላክልኝ' እያለ ጮኸ (ሉቃስ 16፥23-24)።*

*ሀዋርያው ጳውሎስ እንደዚህ ፅፋአል*

> *ይህም የሚሆነው ጌታ እየሱስ በሚንበለበል እሳት ከኀያላን መላእክት ጋራ ከሰማይ በሚገለጥበት ጊዜ ነው። በዚያ ጊዜ እግዚአብሔርን የማያውቁትንና ለጌታችንም ለእየሱስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል። እነርሱም ከጌታ ፊትና ከኀይሉ ክብር ተወግደው በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ (2 ተሰሎንቄ 1፥7-9)።*

*ጴጥሮስም ፃፈ*

> *እግዚአብሔር ኀጢአት የሠሩትን መላእክት ሳይራራላቸው ወደ ገሃነም ከጣላቸውና በጨለማ ጕድጓድ ለፍርድ ካስቀመጣቸው (2 ጴጥሮስ 2፥4)።*

*ዮሀንስም ፃፈ*

> *ያሳታቸው ዲያብሎስም፣ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፤ እነርሱም ቀንና ሌሊት ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሠቃያሉ... ስሙ በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘ ሁሉ ወደ እሳት ባሕር ተጣለ (ራእይ 20፥10፣ 15)።*

*ስፍራው የተገለፀበትን ቃላት አስተውሉ፤ እሳት፥ የስቃይ ስፍራ፥ ጥፋት፥ ጨለማ፥ ጕድጓድ፥ ፍርድ፥ ለቅሶና ጥርስ ማፉአጨት።*

እየሱስ አለ፥

> *ቀኝ ዐይንህ የኀጢአት ሰበብ ቢሆንብህ፣ አውጥተህ ወዲያ ጣለው፤ ሰውነትህ በሙሉ ወደ ገሃነም ከሚጣል ከሰውነትህ አንዱን ክፍል ብታጣ ይሻልሃል። ቀኝ እጅህ ቢያሰናክልህ ቈርጠህ ወዲያ ጣለው፤ ሰውነትህ በሙሉ ወደ ገሃነም ከሚጣል ከሰውነትህ አንዱን ክፍል ብታጣ ይሻልሃል (ማቴዎስ 5፥29-30)።*

*እየሱስ ይህን ሲናገር አካል መቆረጥን እያበረታታ አይደለም ነገር ግን ወደ ሲኦል የሚያስገባንን ማንኛውንም ድርጊት ምንም ያህልም ቢያጓጓንም መተው እንዳለብን ለማስገንዘብ ነው።*

► *ስለ ሲኦል የተሳሳተ አስተምህሮ ያላቸው ሀይማኖቶች የትኞቹ ናቸው?*

*መጽሐፍ ቅዱስ ሞት የሰውን ልጅ በግዜ የተገደበ ዕድልን መጨረሻ ሲሆን እና ሲኦልም* (1) *ዘላለማዊ፥* (2) *መመለስ የማይቻልበት እና* (3) *ጣር እንደሆነ። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል በኢ-አማንያን (ኤቲስት) ተቀባይነት የለውም። ከሞት ቦሃላ ህይወት የለም ይላሉ በተጨማሪም በጆሆቫ ዊትነስ፥ ሞረሞኖች፥ እና ዩኒቨርሳሊስትስ ሁሉም ሲኦል የለም ብለው ያመናሉ። ሞት የሰውን ልጅ ከክብሩ እስከመጨረሻው እንዳወረደው የሮማን ካቶሊክ አትቀበልም፤ እጣ ፈንታ ከሞት ቦሃላ መለወጥ ይችላል ብላ ታምናለች።*

*ፍትሀዊ አይደለም በሚል ሲኦል የሚባል ነገር የለም ብለው የሚክዱ ሰዎች አሉ። በውስን ጊዜ ለሚፈጠር የሀጢአት ስህተት ዘላለማዊ ቅጣት ፍትሀዊ አይደለም ብለው ይከራከራሉ። ቅዱስ ኦገስቲን የወንጀልኛ ህግን ተመርኩዞ ምላሽ ሰቷል፤ ዝርፊያ በጥቂት ደቂቃ ውስጥ ከተከወነ ቅጣቱም ደቂቃ ብቻ መፍጀት አለበት ማለት ነው? ብሎ ይጠይቃል። በቅጽበት የሚፈጸም ግድያ ዳግም መመለስ የማይችል ጥፋትን ያስከትላል።በመፅሃፍ ቅዱስ ዘላለማዊና ኤልሻዳይ እግዚብሄር ላይ ለተሰራ ሀጢአት ዘላለማዊ ቅጣት እንደሚጠብቀን ይናገራል።*

► *ሲኦል ለምን ዘላለማዊ ሆነ?*

*ሲኦል ዘላለማዊ የሆነበት ምክንያት፥*

1. *ሀጢአት ኤልሻዳይ እግዚአብሔር የተሰራ ወነጀል ነው*
2. *ንስሃ ያልገቡ ሀጢአተኞች ለእግዚአብሔር ሊያቀርቡ የሚገባቸውን ዘላለማዊ አገልግሎት ክደዋል*
3. *እኛ ዘላለማዊ ፍጡሮች ነን ከእግዚአብሔር ከተለየን ሌላ የምንሄድበት ስፍራ የለም*

*በምድር ሳለን በምድር ላይ ውሳኔዎቻችንን መለወጥ በመቻላችን ደስ ይለናል። ምርጫውም ዘላለማዊ ቆይታችንን መወሰን መቻሉ በጣም ከባድ ይመስላል። አሁን ሆን ብለን ምርጫ ብናደርግ እንኳ፤ ከምድራዊ ህይወት በኋላ ድጋሚ እድል እንዲሚሰጠን እናስብ ይሆናል። ሆኖም እግዚአብሔር የመፈተኛ ጊዜያችንን በአንድ የሕይወት ዘመን ብቻ ቢገድበው ምክንያታዊነት የጎደለው አይደለም።*

*አንዳንዶች እግዚዓብሔር የፍቅር አምላክ ስለሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ወደሚነግሩን አሰቃቂ ወደሆነ ወደዚህ ቦታ ሰዎችን ይልካል ብለው ማመን ይከብዳቸዋል። ማወቅ ያለብን ነገር እግዚአብሔር ወደ ጥፋት እንድንገባ አይፈልግም ነገር ግን ንስሃ እና ድህነትን እንድናገኝ ይፈልጋል። ይህም ነገር በመፅሃፍ ቅዱስ በብዙ ስፍራ ተጠቅሶ ይገኛል* (2 *ጴጥሮስ* 3፥9፤ 1 *ጢሞቴዎስ* 2፥4፤ *ሐዋርያት ሥራ* 17፥30 *ይነበብ)። ወደ ሲኦል የሚሄዱት እነዚያ*

ወደዚያ አስፈሪ ስፍራ የሚያደርሷቸውን ምርጫዎች ያደረጉ ናቸው። ማንም በድንገት ወደ ሲኦል አይገባም የእግዚአብሔርን ቅድስናና ድህነት የካዱ ሰዎች ወደዚህ አስፈሪ ቦታ ይገባሉ።

መልካም የሆነ ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር ከሆነ፤ እግዚአብሔርን መተው መልካም ነገሮችን ሁሉ መተው ነው። ሰላም፣ ከፍርሃትና ከሥቃይ ነፃ መሆን፣ እንዲሁም ምቾት ያለው ስፍራ መልካም ነገሮች ናቸው ይህን ደሞ በሙላት ማቅረብ የሚችለው እግዚአብሔር ነው። ከእግዚአብሄር መለየት መልካም ነገሮችን ሁሉ ያሳጣናል ሲኦል ማለት ደሞ ይህ ነው።

ለእግዚአበሄር ክብር ይሁንና በእየሱስ የማዳን ስራ ከሚመጣው ቁጣ ድነናል (1 ተሰሎንቄ 1፥10)። ከአስፈሪዊ ሲኦል ተላቀን በደጎንነታችን ደስታና በሰማይ ድንቅ ነገሮች ተካፋዮች ሆነናል። በክርስቶስ አምነን የንስሃን መንገድ ስንመርጥ ዘላለማዊ መዳረሻችን መንግስተ ሰማያት ይሆናል (ፊልጵስዩስ 3፥20፣ ሐዋርያት ሥራ 20፥21)

> ‘’ በስተመጨረሻ ስለ ሲኦል ያለው ተቃውሞ ወደ አንድ ጥያቄ መምጣት አለበት፤ ‘እግዚአብሔር ከዚህ በላይ ምን እንዲያደርግ ነው የምትፈልገው?’ ሀጢያታቸውን እንዲሽር፥ አዲስ ሕይወት እንዲሰጣቸው ነውና ተአምራዊ እገዛ እንዲያደርግላቸው ነው? ግን እኮ የሄን አድርጓል፤ ሰዎች ግን ምህረትን እምቢ አሉ ፤ ለራሳቸው ፍላጎት እንዲተዋቸው? ወይኔ፥ አዝናለው ይህንንም አድርጓል።
>
> ሲኤስ ሌዊስ
> “ዘ ፐሮብለም ኦፍ ፔይን” ከሚለው በለውጥ የተወሰደ

## ማስወገድ ያለብን ስህተት፥ ዘላለማዊ መዘዝን መርሳት

በምድር ህይወት ውሳኔዎቻችን የሚዘልቁ አይመስለንም። በቂ ጊዜ እያለን ብዙ ጥፋቶችን ማርም እንችላለን። ብዙ ውሳኔዎች ዘላለማዊ መዘዝ እንዳላቸው መርሳት የለብንም። መቼ እንደምንሞትና የምህረት ጊዜያችን መቼ እንደሚያበቃ አናውቅም። ከሞት በኋላ የራሳችንን ዘላለማዊ ዕጣ ፈንታ የወሰኑም ሆነ ሌሎች በውሳኔያቸው ላይ ተጽዕኖ እንዲያሳርፉ ያደረግናቸውን ድርጊቶቻችንን መለወጥ አንችልም።

► የእምነት መግለጫውን ቢያንስ ሁለት ግዜ አብራችሁ አንብቡ።

## የእምነት መግለጫ

ሲኦልም ሆነ ገነት ሁሉም ሰው ዘላለማዊ መዳረሻ አለው። መንግስተ ሰማይ አማኞች በደስታ እግዚአብሔርን እያመለኩ የሚኖሩበት የእግዚአብሔር ቤት ነው። በመንግስተ ሰማይ ሀጢያትም ሆነ የሀጢያት ፍሬ የለም። ሲኦል በክርስቶስ አማካኝነት ከኃጢአታቸው ላልዳኑ ሁሉ የተዘጋጀ ዘላለማዊ፥ ሊወጣበት የማይችል እጅግ ሥቃይ የበዛበት የቅጣት ስፍራ ነው። ሲኦል ወሰን በሌለው አምላክ ላይ በፈቃድ ለሚፈጸም ኃጢአት የሚሰጥ ፍትሃዊ ቅጣት ነው።

## ትምህርት 13 የቤት ስራዎች

(1) የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የቤት ስራ፦ ከታች ከተዘረዘሩት ዘርፎች መካከል እያንዳንዱን ተማሪ አንድ ይመደብ። ከሚቀጥለው ክፍለ ግዜ በፊት ክፍሉን አንብባችሁ በትምህርቱ ውስጥ ካለው ሃሳብ ላይ ምን እንደሚናገር በአንድ አንቀፅ ፃፉ።

- ኢሳይያስ 5፥11-16
- ማቴዎስ 5፥27-30
- ሉቃስ 16፥19-31
- ራእይ 22፥1-5
- ራእይ 22፥10-17

(2) ፈተና፦ የሚቀጥለው ክፍለ ግዜ የምትጀምሩት በትምህርት 13 ፈተና ነው። ለፈተና ዝግጅት እንዲሆን የፈተና ጥያቄዎችን አጥኑ።

(3) የማስተማር የቤት ስራ፦ ከክፍል ውጪ የማስተማርያ ግዜን ቀጠሮ መያዝ እና ማስተማራችሁን ሪፖርት ማድረግ አስታውሱ።

## ትምህርት 13 ፈተና

(1) የመንግስት ሠማያት ዋና ተግባር ምንድን ነው?

(2) በመንግስ ሠማያት የማይኖሩ አራት ነገሮችን ዘርዝሩ።

(3) መንግስተ ሠማያት የሚገባው ማን ነው?

(4) አማንያን መቼ ነው መንግስተ ሠማያት የሚገቡት?

(5) በመጽሐፍ ቅዱስ ስለሲኦል የሚነግረን ሦስት ነገሮች ምንድን ናቸው?

(6) እየሱስ አንድ ሰው እጁን መቁረጥ አለበት ሲል ምን ማለቱ ነው?

(7) ሲኦል ዘላለማዊ የሆነበትን ሦስት ምክንያቶች ዘርዝሩ?

# ትምህርት 14
# የመጨረሻ ሑነቶች

## የትምህርቱ ግቦች

(1) ተማሪው የሚከተሉትን ማስረዳት ይችላል

- ስለ መጨረሻ ሑነቶች በሚመለከቱ ርዕሰ ጉዳዮች ውስጥ ያሉ የአስፈላጊነት ደረጃዎች
- የክርስቶስ መምጣትና ለአማኝ ያለው ጠቀሜታ
- የሰው ልጆች ሁሉ ከሞት መነሳትና የሥጋዊ አካል ዋጋ
- የመጨረሻው የፍጥረታት ሁሉ የህሊና ፍርድ
- ዘላለማዊቷ የእግዚአብሔር መንግስት
- ስለ መጨረሻ ሑነቶች ክርስቲያናዊ የእምነት መግለጫ

(2) ተማሪዎች ምድራዊ ህይወትን በዘላለማዊ ህይወት መነፅር የማየትን ጥቅም ይረዳሉ።

## መግቢያ

► ዳንኤል 7፥9-14 አብራችሁ አንብቡ። ይህ ክፍል ስለ ወደፊቱ ምን ይነግረናል?

በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ የትንቢት ምልክቶች፤ የአውሬው ምልክት፥ ቀንደ መለከት፥ ታላቁ መከራ፥ ፀረ ክርስቶስ፥ ሰባቱ አመት፥ 1000 አመት፥ ነጩ ዙፋን፥ የምትመጣዋ አዲሲቷ ከተማ፥ የእሳት ሀይቅ ያጠቃልላሉ።

► ስለመፅሃፍ ቅዱስ የትንቢት ጉዳዮች ምን ታስባላችው?

## የአስፈላጊነት ደረጃዎች

በትንቢት ላይ ያሉ ውይይቶች ከመሠረታዊ እውነቶች ይልቅ ብዙ ጊዜ ትንንሽ ሀሳቦች ላይ ያተኩራሉ። በትንቢት ላይ ያሉ ሀሳቦች ሁሉም እኩል ጠቀሜታ የለውም። ስለዚህ በዚህ ትምህርት ሁሉንም ርእስ አንሸፍንም።

የአውሬው መልክ ምን ሊመስል እንደሚችል እንዳንድ ሰዎች በመደነቅ ያስባሉ። ሀሰተኛው ክርስቶስ ከየት ይነሳል? እነዚህን ጥያቄዎቸወ መፅሃፍ ቅዱስ በሙላት አይመልስም ስለዚህ እነዚህ ጥያቄዎች ላይ ጊዜ መፍጀት ትርጉም የለዉም።

መፅሃፍ ቅዱስ ይበልጥ የሚያብራራቸው ሀሳቦች አሉ። ለምሳሌ እየሱስ ከመከራ በፊት፥ በመከራው ጊዜ ወይም ከመከራው በሃላ ነው የሚመጣው? የሚሊኒየም ዘመኑ እንደተባለው 1000 አመት ብቻ ነው? ነገር ግን እነዚህ ሀሳቦች ለወንጌል ወሳኝ አይደሉም። በነዚህ ጉዳዮች ላይ ባለመስማማት ህብረትን ማበላሸት ልክ አይደለም።

ከመፅሃፍ ቅዱስ ትንቢቶች ይበልጥ የሚጠቅሙና ማንም ሊርዳቸው የሚችል አሉ። እነዚህ ትንቢቶች አኗኗራችንንና አጠቃላይ የክርስትና አስተምሮአችንን ይነካሉ። 4 ይበልጥ የሚጠቅሙንን የመፅሃፍ ቅዱስ ትንቢቶች ስለመጨረሻው ፍርድ እንመለከታለን።

### የእየሱስ በአካል ዳግም መምጣት

ምንም እንኳን በመንፈስ ከአማኞች ጋር ቢሆንም እየሱስ በአካል ወደ ምድር ይመጣል። ለሁሉም እየታየ በክብር ይመጣል። (ራእይ 1፥7ን አንብብ)።

► እየሱስ ሲመጣ ምን ይፈጠራል?

የእየሱስ መምጣት በምድር ታሪክ ትልቅ ጡዘት ነው። የአለም መንግስት የክርስቶስ መንግስት ይሆናል። ለሱ የታመኑ ክብርና ሞገስን ያገኛሉ። ከእርሱ ያልሆኑት ይጣላሉ። በተቃዋሚዎቹ ሁሉ ላይ ስልጣን ይኖረዋል። (ማቴዎስ 26፥64ን አንብብ)። ጉልበት ሁሉ ለርሱ ይሰግዳል፤ ምላስ ሁሉ ምስጋናን ያመጣል (ፊልጵስዩስ 2፥10-11)።

የሞቱ ክርስትያኖች ከክርስቶስ ጋር ለመምራት ይነሳሉ (2 ጢሞቴዎስ 2፥12)። የተነሱት እና በጊዜው በህይወት ያሉት አማኞች ክርስቶስን ለማግኘት ይነሳሉ (1 ተሰሎንቁ 4፥16-17)።

የእየሱስ መምጣት የተባረከ የክርስትያኖች ሁሉ ተስፋ ነው (ቲቶ 2፥13 ይነበብ)። ይህ ለኛ ምን ማለት እንደሆነ አስቡት። የመከራ፥ የስቃይና የሀዘን ማብቂያ ነው። ከተወደዱና ከቅዱሳን ጋር የምንገናኝበት፥ እምነታችን ባዶ እንዳለሆነ የምናረጋግጥበት ነው። የክርስቶስ መልክ፥ የመንግስተ ሰማያት መግቢያና የዘላለማዊ የእግዚአብሔር መንግስት ሙላት ነው። እነዚህ ሁሉ ነገሮች መምጣቱ ላይ እንጂ የመምጫው ጊዜ ላይ የተደገፉ አይደሉም።

> ‘’ከሞት በሃላ ያለን ትንሳኤ በደስታ የማይጠብቅ በክርስቶስ ትምህርት ቤት ብዙ አልተራመደም። የጌታን መምጣት በትእግስት እንጠብቅ ምክንያቱም ትልቅ ደስታ የሚፈጥር ነገር ነው። ይመጣል ይቤዠናል፥ ወደ ክብሩና መንግስቱ ይመራናል።‘’
>
> ከጆን ካልቪን የተወሰደ፣ ኢንስቲትዩትስ ኦፍ ዘ ክርስቲያን ሪሊጅን

እየሱስ በክብርና በስልጣን እንደሚምጣ ተናግሮአል (ማቴዎስ 24፥30)። መጥቶ የራሱን ሰዎች እንደሚወስድ ቃል ገብቷል (ዮሐንስ 14፥3)። መልአክትም ወደ ሰማእ ሲወጣ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል ብለዋል (ሐዋርያት ሥራ 1፥11)። ሐዋርያት ለዚህ ዓለም ያለውን የእግዚአብሔርን የመጨረሻ ዕቅድ እስኪመሰርት ድረስ መምጣቱን በንስሃ መጠበቅ እንዳለብን ሰብከዋል። (ሐዋርያት ሥራ 3፥19-21ን አንብብ)። እየሱስ በክብርና በስልጣን እንደሚመጣ በአዲስ ኪዳን ትምህርቶች ዉሰጥ ተደጋግሞ አለ።[26]

የእየሱስን መምጣት የሚጠቁሙ ምልክቶች ቢኖሩም ትክክለኛወ ጊዜን ማውቅ አይቻልም። ይህ ለአማኞች ነቅተው እንዲጠብቁ ይረዳል (ማርቆስ 13፥33-37)።

► እየሱስ ለምን ይመጣል?

---

[26] 1 ተሰሎንቁ 4፥15-16፤ 2 ተሰሎንቁ 1፥7፣ 10፤ ቲቶ 2፥13፤ ዕብራውያን 9፥28፤ ያዕቆብ 5፥7-8፤ 1 ጴጥሮስ 1፥7፣ 13፤ 2 ጴጥሮስ 1፥16፣ 2 ጴጥሮስ 3፥4፣ 12፤ 1 ዮሐንስ 2፥28

ብዙ ሰዎች ከእግዚአበሄር በተቃራኒ ያሉበት አለም ላይ ነው የምንኖረው። ፍጥረታት ሁሉ በሀጢያት እርግማን ይሰቃያሉ። አለም ፖለቲካ ተግባር፥ በማህበረሰብ ተሀድሶ፥ በትምህርት ወይም በኢኮኖሚ የሚስተካከል አይደለም። እየሱስ ሲመጣ ሁሉን ያሰተካክለዋል።

ሁሊም ሃጢአተኛ ነው ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመምጣት ፍቃደኛ ለሆነ ሁሉ ግን ከጥፋት ይድናል። የእግዚአብሔር መንግሥት ንስሐ በሚገቡና በሚያምኑ ሰዎች መካከል አሁን እየሠራች ትገኛለች (ማርቆስ 1፥14-15፤ ማርቆስ 9፥1)። መንግስቱም በእየሱስ መምጣት ሙሉ ይሆናል።

► እየሱስ እንደሚመጣ እያወቅን እንዴት እንኑር?

የቀድሞ ክርስትያኖች ቅድሚያ የሚሰጡትን ነገር መርሳት የለብንም። እምነታችንን እንድንጠብቅና እስከ መጨረሻው እንድንፀና ተጠርተናልና (1 ቆሮንቶስ 16፥13) (ማቴዎስ 24፥13)። የአለም ጉዳይና ሀሴት የክርስቶስ መምጣትን ሊያሰረሳን አይገባም (ሉቃስ 21፥34-36)። አላፊውን የምድርን ነገር ትተን የዘላለሙን ማስቀደም አለብን (2 ጴጥሮስ 3፥11-13)። ወደ ሰማይ እያየን ሳይሆን በመንፈስ ነቅተን እንድንጠብቅ ተነግሮናል (ማርቆስ 13፥33-37)። እሱን እንድንመስል ለንፅህናና ለንፁህ ሂይወት መፀለይ ይገባናል (1 ዮሐንስ 3፥3)።

ክርስቶስ እንደማይመጣ አስበው የዛሬን ብቻ የሚኖሩ ነቅተው ሊጠብቁ አይችሉም። የእየሱስ መምጣት እንደ መብረቅ ያለ ነው (ማቴዎስ 24፥27፤ 1 ቆሮንቶስ 15፥52)፥ ስለዚህ ከመጣ ቦሃላ ማንም ነገሮችን ለመቀየር ጊዜ አይኖረውም። 1 ተሰሎንቁ 5፥1-6 የሚነግርን በጨለማ በዚህ አለም የሚመላለሱ ሰዎች በመምጣቱ የደነግጣሉ። ለነሱ መማጣቱ እንደሌባ ነው። ላመኑት ግን ሙሽራዋን እንደምትጠብቅ ሙሽሪት ደስታን የሚያመጣ እንጂ ፍርሀት የሚፈትር አይደለም (ዮሐንስ 14፥2-3)።

እየሱስን የምንጠብቀው፤

1. የሰማዩን በማስቀደም
2. በንፅህና በመኖር
3. በፀሎት በመትጋት

## የሰዎች ሁሉ አካለዊ ትንሳኤ

ሁሉም ሰው በአካል በትንሳኤ እንደሚነሳ መጽሐፍ ይነግረናል ስለዚህ አካላችን ዘላለማዊ እንደሆነ እናወቃለን። የትንሳኤ አስተምሀሮ አስፈላጊ ነው። ሐዋርያው ፓውሎስ በ1 ቆሮንቶስ 15 ስለዚህ ጉዳይ ነግሮናል። ይህንንም ሲያበራራ ትንሳኤን መካድ ወንጌልን መካድ ነው ብሎናል። ትንሳኤ ከሌለ እየሱስ ባልተነሳ ነበር (1 ቆሮንቶስ 15፥13)። እየሱስ ደሞ ከሞት ካልተነሳ ወንጌል ዉሸት ይሆናል ማንም ሰው መዳን አይችልም (1 ቆሮንቶስ 15፥17)።

ሁሉም ሰው በትንሳኤ ይነሳል ግን ባንድ ጊዜ አይደለም፥ በምፅአት ቀን ክርስቲያኖችን ሁሉ ወደ ራሱ ይወስዳቸዋል በስጋ የሞቱም ይነሳሉ (1 ተሰሎንቄ 4፥16-17፤ ራእይ 20፥6)። በመጀመሪያው ትንሳኤ በሀጥያት የሞቱት አይነሱም። ከጊዜ በኋላም ለፍርድ ሰአት ይነሳሉ (ራእይ 20፥13)።

ክርስትያኖች በክብር ከእየሱስ ጋር ይነሳሉ (1 ዮሐንስ 3፥2)። ከዛ በሃጢያት የወደቁት ውደ ዘላለም ጥፋት ይገባሉ (ዮሐንስ 5፥28-29)።

► በትንሳኤ አካል አለማመን ምን ለውጥ ያመጣል?

ስለ ትንሳኤ ማመናችን አኗኗራችን ላይ ተፅእኖ ይፈጥራል። የአስተምህሮቱን ተፅእኖ በማያመኑት ላይ በተግባር ማየት እንችላለን። በቆሮንቶስ ጉባኤ ውስጥ የነበሩ አንዳንድ ሰዎች የሰው አካል ከሞት እንደሚነሳ ይክዱ ነበር። በዚህ ጉዳይ ለሁለት ወገን ተከፍለው ነበር።

አንዳንዶች ‘’ስጋ ስለማይነሳ ዋናው መንፈስ ነው’’ ይላሉ። ይህ ማለት የምንሰራው ሀጢያት ያን ያክል ችግር አይፈጥርም በለው ያስባሉ። የሚጣል ሰውነት ሰላለን ዝሙት ብንፈፅም ችግር የለውም ይላሉ።

> ‘’ሞት ሆይ መውጊያህ የታለ? ሲኦል ሆይ ድል ማረጊያህ የት አለ? ክርስቶስ ተነስቷል፥ አጥፍቶሃል ክርስቶስ ተነስቷል፥ ዲያቢሎስ ወድቋል፤ ክርስቶስ ተነስቷል፥ መላእክት ተደሰቱ፤ ክርስቶስ ተነስቷል፥ ሕይወት ነፃ ወጣች፤ ክርስቶስ ተነስቷል፥ መቃብር ባዶ ሆኗል ፤ ለክርስቶስ ከሞት መነሳት ላንቀላፉት የመጀኛ ምክንያት ሆነ፤ ክብርና ስልጣን ከዘላለም እስከ ለዘላለም አሜን
>
> ክሪሲስቶም፣ “ኤስተር ሆምሊ”
> ኤስተር ስቶም

አንዳንድ ቆሮንቶሳውያን “ምግብ ለሆድ ነው፤ ሆድም ለምግብ ነው፤” የሚል መፈክር ነበራቸው ይህም ማለት ሰውነት ከሥጋዊ ፍላጎቶች ማርኪያነት ውጭ ሌላ ፋይዳ የለውም ማለት ነው። ጳውሎስም ለሰውነታቸው ክብር ስላልሰጡ እንደሚጠየቁ ነግሯቸዋል (1 ቆሮንቶስ 6፥13)። እርሱም ሰውነታችን የጌታ ነው በትንሳኤ ቀን ከክርስቶስ ጋር እንደሚነሳ ነግሯአዋል (1 ቆሮንቶስ 6፥14)።

ሌሎች ደሞ “ሰውነታችን ትንሳኤ ስለሌለው የረከሰና ጥቅም አልባ ነው ስጋዊ ፍላጎታችንን መገደብ አለብን በተጨማሪም ደስታ ከሚሰጥ ነገር መቆጠብ አለብን በለው ያምናሉ፤ ጣፋጭ የሆኑ ምግቦችን አለመብላት ወይም በትዳር ሕይወት አለመደሰት ይኖርብናል ይሉ ነበር።

እነዚህ ሁሉ ስህተቶች የሚመጡት ትንሳኤን ከመካድ ነው። ትንሳኤን መካድ ለሰውነታችን ያለንን ከብር ያሳጣናል። በክርስትና አስተምህሮ ግን ትነሳኤ ለሰውነታችን የምንሰጠውን ክብር ይጨምራል።

► 1 ቆሮንቶስ 6፥14፤ 15፤ 19-20ን አንብብ

እነዚህ ጥቅሶች የክርስትያን አካል/ሰውነት ዋጋ እንዳለው የሚነግሩን ናቸው። ምክንያቱም፤

- የተቤዠን ነን
- የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነን
- የክርስቶስ አካል ነን
- በክብር በትንሳኤ እንነሳለን

የትንሳኤ ትምህርት ለምን አስፈለገ

- እየሱስ ከሞት ተነስቷል
- ሁሉም ሰው ከስጋ ሞት ይነሳል

- ሰውነት ዘላለማዊ ዋጋ አለው
- ወንጌል እውነት ነው

## ፍርድ

የመጨረሻ ሑነቶች ስማቸው በሕይወት መዝገብ ለሌለ የመጨረሻ ነው። የህልውና ሳይሆን የመምረጥ እድል መጨረሻ። ከዚያ በኋላ በሚቀጥለው የዘላለም ሕይወት ውስጥ በፍጹም የማይመለስ ውሳኔአቸውን ይኖራሉ።

ፍርድ ምርጫችንን ከአፋጣኝ ውጤቶቻቸው በላይ ትርጉም ይሰጠዋል። አንዳንድ ሰዎች ለነጠላ ድርጊታቸው ውጤት ሀላፊነት ከቻሉ ለሌላው ነገር መጨነቅ እንደሌለባቸው ያስባሉ። ኃጢአታቸው ጉዳት እስካላደረሰ ድረስ ክፉ እንዳልሆነ አድርገው ማመን ይፈልጋሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ ኃጢአት ሁሉ ጎጂ ነው። ነገር ግን በምድር ከባድ መዘዝ ባያመጣም በመጨረሻ ሑነቶች ግን ዋጋ ያስከፍለናል። የእግዚአብሔር ቃል ሰዎች ለስራቸው ፍርድን እንደሚቀበሉ ይነግረናል። (2 ቆሮንቶስ 5፥10፤ ሮሜ 2፥6-11ን አንብብ)።

በፍርድ ጊዜ የተወሰኑት ለዘላለማዊ ቅጣት የተወሰኑት ደግሞ ለዘላለማዊ ሽልማት ይመረጣሉ። መጽሐፍ ንስሐ ያልገቡ ኃጢአተኞች ለሠሩት የኃጢአት ሥራ የኩነኔ ፍርድን ለመቀበል ከሙታን ተለይተው የሚነሱበትን አንድን የፍርድ ትዕይንት ይገልጻል። (ራእይ 20፥11-15 ይመልከቱ)። ለክርስትያኖች ደግሞ ሌላ እንደ ትጋታቸው ለዘለቀ ውጤቶቻቸው የሚሸለሙበት ፍርድ አለ። (1 ቆሮንቶስ 3፥14-15ን አንብብ)።

ከፍርድ ቦሃላ ሀጢያት አይኖረም። አለምን ያለ ሀጢያት ማሰብ ቢከብድም አንድ ቀን በእግዚአብሔር ላይ ያመፁ ሁሉ የጠፋሉ።

እግዚአብሔር በፍርሃት እንድንኖር ወይም ፍርሃት ቅን ሕይወትን ለመኖር ምክንያታችን እንዲሆን አይፈልግም። ነገር ግን ስለ ፍርድ ነቅቶ መጠበቅ ሕይወታችንን የሚመራ ትልቅ የሀላፊነት ስሜት ነው።

እነዚህን አራት ነገሮች ለመረዳት ስለ ፍርድ ማወቅ ይኖርብናል፤

1. የሀጢያት ተፅእኖ
2. ለእግዚአብሔር ያለን ሀላፊነት
3. የምርጫችን ጠቀሜታ
4. የሀጢያቶች ሁሉ ማብቂያ

## የእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግስት

በአንዳንድ ፍልስፍና እና እምነቶች ጊዜ የሚሄደው መጀመሪያና መጨረሻ በሌለው በዘላለም ሁደት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ግን ጊዜ መጀመሪያ አለው ክስተቶችም በጊዜ የሚመጣ መደምደሚያ አላቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ከፍጥረት ጀምሮ፥ ስለ ሰው ልጅ ውድቀት፥ከዚያም እግዚአብሔር በሰው ልጅ የታሪክ ዘመናት ውስጥ እየሠራ ስላለው የማዳን እቅድ ይነግረናል።

በዘፍጥረት 3 የሀጢያት ጅማሮን እናያለን። በራእይ ደግሞ ሀጢያት ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ ከተማ እንደማይኖር ይነግረናል (ራእይ 21፥27)። በዘፍጥረት የህይወት ዛፍ ውድቀትን የሞት ፍርድን ሲነግረን (ዘፍጥረት 3፥22-24)።

በራእይ ደግሞ የህይወት ዛፍን መመለስ፥ የህይወት መዝገብንና የህይወት ውሃ የምታፈሰውን ወንዝ ይነግረናል (ራእይ 22፥1-2፣ 19)።

የምትመጣው ምሉዕና ዘላለማዊ የእግዚአብሔር መንግስት የእግዚአብሔርን እቅድ የምታሟላ ናት። እግዚአብሔር ሁልጊዜም የአጽናፈ ዓለሙ ንጉስና ባለቤት ነው። ነገር ግን የሰው ልጅ ከወደቀበት ጊዜ ጀምሮ በእግዚአብሔር መንግስት ላይ እያመፅ ይገኛል። ያ ዓመፅ በድንገት ያበቃል። እግዚአብሔርም ያለ ተቀናቃኝ ፍጥረቱን ይገዛል። ልክ እንደ ሰማይ ምድር እግዚአብሔር እንደሚፈልጋት ፍጹም ትሆናለች።

## ማስወገድ ያለብን ስህተት፥ ምድራዊ ህይወት ላይ ማተኮር

በሰዎች መሀል መድራዊ ህይወትን ለዘላለም ማስቀጠል የመፈለግ እሳቤ አለ። ሁኔታዎችን በማመቻቸትና ችግሮችን በመፍታት እና እርካታ የሚሰጠንን አካባቢ በመፍጠር ሙከራ ብዙ መቆየት የምንችል ነው የሚመስለን ነገር ግን እንደ አብርሀም ነው እንድንሆን ነው የሚፈለገው በድንኳን እየኖርን ዘላለማዊ ህይወትን መናፈቅበ (ዕብራውያን 11፥8-10፣ 14-16)። የምንገነባቸው ነገሮች፣ ያሉን ንብረቶችና የምንፈጥራቸው ሁኔታዎች ሁሉ ጊዜያዊ መሆናቸውን ማስታወስ ይኖርብናል ይህንንም አስበን ለማይጠፋው የዘላለም ቤት መትጋት ይኖርብናል።

► የእምነት መግለጫውን ቢያንስ ሁለት ግዜ አብራችሁ አንብቡ።

## የእምነት መግለጫ

እየሱስ እንደ ቃሉ ይመጣል የሞቱትን ሊያስነሳ፥ ያመኑትን ወደ መንግስቱ ሊወስድ። የሰው ልጅ ሁሉ ካንቀላፋበት ነቅቶ ስለስራው ለፍርድ ይቀርባል የዘላለም ክብር ወይም የዘላለም ቅጣት ይፈረድበታል። የእግዚአብሔር መንግሥት በሙላት ትመጣለች እግዚአብሔርም ለዘላለም ይነግሣል።

## ትምህርት 14 የቤት ስራዎች

(1) **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የቤት ስራ፦** ከታች ከተዘረዘሩት ዘርፎች መካከል እያንዳንዱን ተማሪ አንድ ይመደብ። ከሚቀጥለው ክፍለ ግዜ በፊት ክፍሉን አንብባችሁ በትምህርቱ ውስጥ ካለው ሃሳብ ላይ ምን እንደሚናገር በአንድ አንቀፅ ፃፉ።

- ዳንኤል 2፥31-45
- ማቴዎስ 25፥31-46
- 1 ቆሮንቶስ 15፥51-58
- 2 ጴጥሮስ 3፥1-14
- ራእይ 20፥11-15

(2) **ፈተና፦** የሚቀጥለው ክፍለ ግዜ የምትጀምሩት በትምህርት 14 ፈተና ነው። ለፈተና ዝግጅት እንዲሆን የፈተና ጥያቄዎችን አጥኑ።

(3) **የማስተማር የቤት ስራ፦** ከክፍል ውጪ የማስተማርያ ግዜን ቀጠሮ መያዝ እና ማስተማራችሁን ሪፖርት ማድረግ አስታውሱ።

## ትምህርት 14 ፈተና

(1) ስለ መጨረሻ ሑነቶችን ያሉ አራት አስፈላጊ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ምንድን ናቸው?

(2) በእየሱስ ዳግም ምጽዓት በሆነ ግዜ አማኞች ምን ይሆናሉ?

(3) የእየሱስን መመለስ በምን መንገድ መጠበቅ አለብን?

(4) ስለትንሳኤ ያለን አስተምሮ ለምን አስፈላጊ ሆነ?

(5) ስለፍርድ በሚገባ በማወቃችን አራት የምንረዳቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

# ትምህርት 15

# ጥንታዊ የእምነት መግለጫዎች

## የትምህርቱ አላማዎች

(1) ተማሪው የሚከተሉትን ማስረዳት ይችላል

- እንደ የእምነት መግለጫ የእምነት መግለጫ ዓላማ እና አጠቃቀም
- አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የእምነት መግለጫዎች ምሳሌዎች
- የሶስት ታሪካዊ የእምነት መግለጫዎች አመጣጥ እና ይዘት
- ለምን የዘመናችን ክርስቲያኖች ታሪካዊ ክርስትናን አጥብቀው መያዝ አለባቸው
- ስለ እምነት መግለጫዎች ክርስቲያናዊ የእምነት መግለጫ


(2) ተማሪው የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን መሰረታዊ እምነቶችን እንደ የመጀመሪያ የክርስትና እምነት አድርጎ ይመለከታል።

## መግቢያ

► 2 ዮሐንስ አብራችሁ አንብቡ። ይህ ክፍል ስለጥንቷ ቤተክርስቲያን አስተምህሮዎች አስፈላጊነት ምን ይነግረናል?

### የእምነት መግለጫዎች አመጣጥ

የእምነት መግለጫ የክርስቲያን አስፈላጊ እምነቶች ማጠቃለያ ነው። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ማጠቃለል እንደሚያስፈልግ ተመልክታለች።[27]



*አትኔሺየስ ካ. 296-373, በ" ኦን ዘ ኢንካርኔሽን" ታዋቂ ድርሰት ጽፏል። በዚህም የእየሱስ ምሉእ መለኮት እና ሙሉ ሰውነት ለክርስትና እምነት ለምን በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ገልፆ ነበር። እሱ የኒቂያ የሃይማኖት መግለጫ ከወጣበት በኒቂያ ምክር ቤት ውስጥ ተፅእኖ ነበረው።*

► ቤተ ክርስቲያን ለምን የእምነት መግለጫ አስፈለጋት? መጽሐፍ ቅዱስ በቂ አልነበረም?

መጽሐፍ ቅዱስን እናምናለን የሚሉ አሁንም መጽሐፍ ቅዱስን የሚቃረኑ ትምህርቶችን የሚያስተምሩ ሁልጊዜ አሉ። ቤተ ክርስቲያን እውነተኛውን ክርስትና ከሐሰት ትምህርቶች የሚለይ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ መግለጫዎችን አዘጋጅታለች።

---

[27] ምስል፥ S. Athanasius"፣ ከBibliothèque Sainte-Geneviève Images, https፥//archive.org/details/EST84RESP8A, public domain.

ከመጀመሪያዎቹ የአስተምህሮ መግለጫዎች አንዱ **"እየሱስ ጌታ ነው"** የሚለው እየሱስ አምላክ ነው ማለት ነው። ቃሉ፣ *ጌታ **እየሱስ ክርስቶስም*** የሚሉት ቃላት እየሱስ መሲሕ (*ክርስቶስ*) እንደሆነ እና እርሱ አምላክ እንደሆነ ተናግሯል። እየሱስ ጌታ ነው ለማለት ወይም *ጌታ እየሱስ ክርስቶስ* የሚለውን ቃል ለማለት የሚቃወም ሰው አማኝ አልነበረም።

በኋላም ክርስቲያን ነን የሚሉ ነገር ግን **እየሱስ በርግጥም ሰው እንደነበር** የማያምኑ ሰዎች ነበሩ። ለዚህም በ1 ዮሐንስ መልእክት ውስጥ "እየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የሚቀበል መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤ እየሱስን የማይቀበል መንፈስ ግን ከእግዚአብሔር አይደለም" (1 ዮሐንስ 4፥2-3) የሚለውን የእምነት መግለጫ እናገኛለን። ሐዋርያው ደግሞ አንድ ሰው አስፈላጊ የሆነውን የክርስቶስን ትምህርት ቢክድ ኃጢአት እየሠራ ነው እንጂ ከእግዚአብሔር እንዳልሆነ ተናግሯል (2 ዮሐንስ 1፥9)።

ብዙ መግለጫዎችን የሚሰጠው የመጀመሪያው የእምነት መግለጫ በ1 ጢሞቴዎስ 3፥16 ይገኛል።

> [እግዚአብሔር] እርሱ በሥጋ ተገለጠ፤ በመንፈስ ጸደቀ፤ በመላእክት ታየ፤ በአሕዛብ ዘንድ ተሰበከ፤ በዓለም ባሉት ታመነ፤ በክብር ዐረገ።

በ1 ጢሞቴዎስ ውስጥ ያለው የእምነት መግለጫ የሚመለከተውን ሁሉንም ጉዳዮች አናውቅም፣ ነገር ግን እግዚአብሔር በሥጋ ተገለጠ ሲል የእየሱስን አምላክነትና ሰውነት ያጎላል።

> "ስለዚህ ሌላ የዘላለምን ደኅንነት ለማግኘት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋ መገለጽ በእውነት ማመን አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ትክክለኛው እምነት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ አምላክም ሰውም መሆኑን ማመን አስፈላጊ ነው።"
>
> - አትናስያን የሃይማኖት መግለጫ

እነዚህ አጫጭር የእምነት መግለጫዎች አላማ ነበራቸው። አንድ የጥንት ክርስቲያን በእየሱስ አምናለሁ የሚል ሌላ ሰው ቢያገኝ ክርስቲያኑ "እየሱስ ጌታ እንደሆነ ታምናለህ?" ወይም "እየሱስ በሥጋ የመጣ አምላክ እንደሆነ ታምናለህን?" ብሎ ሊጠይቅ ይችላል። ግለሰቡ "አይ" ካለ ሰውዬው እየሱስና ሐዋርያቱ ያስተማሩትን እንዳልተገነዘበ ወይም እንዳልተቀበለ ያውቃል።

ከበዓለ ሃምሳ በኋላ በነበሩት የመጀመሪያዎቹ ጥቂት መቶ ዓመታት ቤተ ክርስቲያን ስለ ሥላሴ፣ ስለ ክርስቶስ በሥጋ መገለጥ እና ስለ መንፈስ ቅዱስ ማንነት ግልጽ መግለጫዎችን መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝታዋለች። ከመናፍቅነት ለመጠበቅ የአስተምህሮ መስፈርቶችን አዘጋጅተዋል። የእምነት መግለጫዎቹ እያንዳንዱ ክርስቲያን የሚያምንባቸውን መሠረታዊ እውነቶች ማጠቃለያ እንዲሆን ታስቦ ነበር።

የእምነት መግለጫዎቹ ሁሉንም ጉዳዮች ሊሸፍኑ አይችሉም፤ ነገር ግን አንድ ሰው በእነዚያ ቀደምት የእምነት መግለጫዎች ውስጥ ምንም ነገር ቢክድ እንደ ክርስቲያን አይቆጠርም ነበር። የክርስትናን እምነት ለመግለጽ የተሞከረበት ነው።

ሦስቱ የቤተክርስቲያን ቀደምት የእምነት መግለጫዎች እዚህ አሉ።

## የሐዋርያት የእምነት መግለጫ

የሐዋርያት የእምነት መግለጫ በሐዋርያት የተጻፈ አይደለም፣ ነገር ግን በሁለተኛው ክፍለ ዘመን የሐዋርያትን ትምህርት ለመግለጽ የተጻፈ ነው።

> እኔ ሁሉን በሚችል ሰማይና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ።
>
> ደግሞም በአንድ ልጁ በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፣ ከድንግል ማርያም በተወለደ፣ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን መከራ በተቀበለ፣ በተሰቀለ፣ በሞተ፣ በተቀበረ፣ ወደ ሴኦል በወረደ፣ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን በተነሣ፣ ወደ ሰማይ በወጣ፣ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በተቀመጠ፣ በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ከዚያ በሚመለስ፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ።
>
> ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ በአንዲት ቅድስት የሓዋርያት ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳን አንድነት፣ በኃጢአት ስርየት፣ በሥጋ ትንሣኤ፣ በዘላለም ሕይወት አምናለሁ። አሜን።

ይህ የእምነት መግለጫ እየሱስ በእርግጥም ሰው እንደነበር እና ከድንግል እንደተወለደ የካዱትን ሰዎች ስህተት ለማጋለጥ የታለመ ይመስላል። እየሱስ በእውነት እንደሞተ ወይም በሥጋ ከሞት መነሣቱን የሚክዱም ነበሩ።

በሐዋርያት የእምነት መግለጫ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተነገረው በጣም ጥቂት ነው። ይህ የሆነው ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ ማን እንደሆነ ስላላወቀች አይደለም፣ በማንነቱ ላይ የተነገሩ ኑፋቄዎች ቤተ ክርስቲያንን ገና እየተፈታተኑ ስላልነበሩ ነው።

"የኃጢአት ይቅርታ" ከሥራ ወይም ከሥርዓት ይልቅ በጸጋ መዳንን ያመለክታል።

## የኒቂያው የእምነት መግለጫ

የኒቂያው የእምነት መግለጫ የተቋቋመው በ 325 በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ሲሆን ዓላማውም የክርስቶስንና የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት አስተምሮን ለማስጠበቅ ነበር። በ 381 በሌላ ምክር ቤት ጥቂት መግለጫዎች ተጨምረዋል። ይህ የእምነት መግለጫ ከዚህ በፊት ያልተነሱ አንዳንድ ጉዳዮችን ይመለከታል።

> ሁሉን በሚችል ሰማይንና ምድርን፣ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ አንድ አምላክ በሚሆን በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ።
>
> እርሱ ብቻ የአብ ልጅ በሚሆን፣ ዓለም ሳይፈጠር ከአብ በተወለደ፣ ከአምላክ በተገኘ አምላክ፣ ከብርሃን በተገኘ ብርሃን፣ ከእውነተኛ አምላክ በተገኘ እውነተኛ አምላክ፣ በህልውናው ከአብ ጋር አንድ የሆነ፣ በተፈጠረ ሳይሆን በተወለደ፣ ሁሉ በእርሱ በሆነ፣ ስለ እኛ ስለ ሰዎች ስለ ደህንነታችንም ከሰማይ በወረደ፣ በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማርያም ስጋ ነስቶ ሰው በሆነ፣ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ በተሰቀለ፣ መከራ በተቀበለ፣ በሞተ፣ በተቀበረም፣ በቅዱሳት መጻሕፍትም እንደተጻፈ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ በተነሣ፣ ወደ ሰማይም በወጣ፣ በአብ ቀኝ በተቀመጠ፣ በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ዳግመኛ በክብር በሚመጣ፣ ለመንግሥቱም ፍጻሜ በሌለው በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ።

ከአብና ከወልድ ጋር በሚሰገድለትና በሚከበር፣ ከአብና ከወልድ በሚሠርጽ፣ በነቢያት በተነገረ፣ የሕይወት ጌታና ሰጪ በሆነ፣ በመንፈስ ቅዱስም አምናለሁ።

የሁሉም በሆነች በአንዲት ቅድስት የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንም አምናለሁ።

ለኃጢአት ማስተስረያ በአንዲት ጥምቀትም አምናለሁ።

የሙታንን ትንሣኤና ገና የሚመጣውን ዓለም ሕይወትም እጠባበቃለሁ። አሜን።

► በዚህ መግለጫ ውስጥ በሐዋርያት የእምነት መግለጫ ውስጥ ያልነበሩ አንዳንድ ነገሮች የትኞቹ ናቸው?

እዚህ ላይ ስለ ሦስቱም የሥላሴ አካላት መግለጫዎቹ ሲሰፉ እንመለከታለን። እየሱስ አምላክ ነው ብለው ከሚያምኑ ግን ከአምላክነቱ አንሷል ከሚሉት ለመጠበቅ የክርስቶስ ሙሉ አምላክነት ላይ አጽንዖት ተሰጥቶታል። እርሱ ዘላለማዊ ነው (ከዘመናት በፊት የነበረ)፣ አልተፈጠረም፣ እና አብ የያዘውን ሁሉ ያቀፈ ነው። እየሱስ አምላክ ተብሎ ሊጠራ የሚገባው አብ አምላክ ተብሎ በሚጠራባቸው ተመሳሳይ ምክንያት ነው።

መንፈስ ቅዱስም ልክ እንደ አብና ወልድ ሊመለክ የሚገባው ነው፤ ይህም አምላክ መሆኑን ያረጋግጣል።

## የኬልቄዶኒያ የእምነት መግለጫ

**የኬልቄዶንያ የእምነት መግለጫ** በ 451 ተፃፈ። ዓላማውም የክርስቶስን በሥጋ የመገለጥ አስተምሮን ለማስጠበቅ ነበር። የፀሐፊዎቹ ያሳሰባቸው የክርስቶስን ፍፁም አምላክነት እና ፍፁም ሰውነት አስተምህሮ ያለምንም መቀናነስ መጠበቅ ነበር፣

በመጨረሻ ጸሐፊዎቹ እነዚህን አስተምህሮዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ትውፊታዊ እንደሆኑ አድርገው ይመለከቷቸዋል ብለዋል። አዳዲስ አስተሳሰቦችን እያዳበሩ ሳይሆን ቤተክርስቲያኒቱ ሁልጊዜ የምታምንበትን ይሚገቱ ነበር።

ስለዚህም ቅዱሳን አባቶችን በመከተል አንድ ልጅ የሆነውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መናዘዝ እንደሚገባን ሁላችንም በአንድነት አስተምረናል።

ያው ሰው በመለኮት ፍፁም የሆነ እና ደግሞም በሰብአዊነት ፍፁም የሆነ ፤

በእውነት አምላክ እና

ምክንያታዊ ነፍስ እና አካል ያለው።

እርሱ እንደ አምላክነቱ ከአብ ጋር አንድ አይነት ነው።

እርሱም እንደ ሰውነቱ ከእኛ ጋር አንድ ነው።

በነገር ሁሉ እንደ እኛ ሆንን ግን ያለ ኃጢአት።

ከጥንት ጀምሮ እንደ አምላክነቱ ከአብ ተወለደ።

በመጨረሻው ዘመን፣ ለእኛ እና ለእኛ መዳን ፣

እንደ ሰውነቱ ከእግዚአብሔር እናት ከድንግል ማርያም ተወለደ።

እሱ አንድ እና አንድ ክርስቶስ ነው ፣ ልጅ ፣ ጌታ ፣ አንድያ ልጅ ፣

በሁለት ተፈጥሮ የሚታወቅ

እርስ በእርሳቸው የማይታለሉ፣ የማይለወጡ፣ የማይነጣጠሉ እና የማይነጣጠሉ ናቸው።

የባሕርይው ልዩነት በኅብረታቸው ምክንያት ጨርሶ አልጠፋም።

በምትኩ ፣ የእያንዳንዱ ተፈጥሮ ባህሪዎች ተጠብቀዋል ፣

እና በአንድ ሰው እና በአንድ ሕልውና ውስጥ በተመሳሳይ ጊዜ ይከሰታሉ፣

ያልተነጣጠሉ ወይም ለሁለት ያልተከፋፈሉ፣

እርሱ ግን አንድ እና አንድ ልጅ ነው፣ እና አንድያ ልጅ ነው።

እግዚአብሔር ቃል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ።

ነቢያት ከጥንት ጀምሮ ስለ እርሱ የተናገሩት እንዲህ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስም ራሱ አስተምሮናል።

የአባቶች ጉባኤም እምነትን ለእኛ አስረክቦናል።

► በዚህ የእምነት መግለጫ ውስጥ በተለይ ትኩረት የተደረገባቸው አንዳንድ ነገሮች ታያለህ?

የክርስቶስ አምላክነት እየሱስ በሰማይ ብቻ የነበረው ነገር ግን በምድር ላይ ያልነበረው አይደለም። የጥንቶቹ ክርስቲያኖች እየሱስ በእውነት አምላክ በሥጋ እንደሆነ ያምኑ ነበር። በምድር በነበረበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔርንና የሰውን ባሕርያት በአንድነት ይዞ ነበር። ይህንን የክርስቶስን ተፈጥሮ ለአዳኝነቱ ልዩ መመዘኛ አድርገው ቆጠሩት።

## የዛሬ የእምነት መግለጫዎች

ቤተክርስቲያን ከጀመረች ዘመናት አለፉዋል። አለም በብዙ መልኩ ተለውጣለች። ብዙ ሃይማኖታዊ እምነቶች መጥተዋል።

አንዳንድ ሰዎች ትምህርቶች ተመሳሳይ ሆነው መቀጠል የለባቸውም ብለው ያስባሉ። ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው ቢጠሩም የፈለጉትን ለማመን ነፃነት ይሰማቸዋል።

► የቤተ ክርስቲያንን ቀደምት የእምነት መግለጫዎች ማመን አስፈላጊ ነውን?

በቀደሙት የእምነት መግለጫዎች የተገለጸው የመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አይለወጥም። የጥንት ክርስቲያኖች አምላክ ያዳናቸው ስለእምነታቸው እንደሆነ ያውቁ ነበር። እነዚህ ስለ እግዚአብሔር ማንነት እና ስለ መዳን መንገዶች የተነገሩት ከመጀመሪያም የነበሩ መሠረታዊ ክርስትና ናቸው።

> "ነገር ግን ማንኛውም አዲስ ትምህርት የተሳሳተ መሆን አለበት፤ ምክንያቱም አሮጌው ሃይማኖት ብቸኛው እውነት ነው፤ ከመጀመሪያው የነበረው ተመሳሳይ ካልሆነ በስተቀር የትኛውም ትምህርት ትክክል ሊሆን አይችልም።"
>
> - ጆን ዌዝሊ፣ "ኦን ሲን ኢንብሊቨርስ" ስብከት የተወሰደ

አንድ ሰው እነዚህን ሁሉ ትምህርቶች ሳያውቅ ወይም በትክክል ሳይረዳው መዳን ይቻላል። ሁሉም ትምህርቶች ለወንጌል አስፈላጊ አይደሉም። አንድ ሰው እውነት እንደሆነ የሚያውቀውን ነገር መካድ እና አሁንም ክርስቲያን መሆን አይችልም። ነገር ግን በአንዳንድ ነገሮች ሊሳሳት ይችላል።

በዚህ ትምህርት ውስጥ ያሉት ጥንታዊ የእምነት መግለጫዎች ስለ አስፈላጊ አስተምሮዎች ብቻ ይናገራሉ። ቤተክርስቲያን ከእነዚህ አስፈላጊ ነገሮች የተለየ የእግዚአብሔር እይታ ካላት፤ የተለየ የድኅነት መንገድ መፍጠር አለባት። ይህ ደግሞ ሌላ ወንጌል ነው። ይህን ካደረጉ ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው መጥራት የለባቸውም፤ ምክንያቱም አዲስ እምነት እየፈጠሩ ነው።

እርግጥ ነው፣ እያንዳንዱ ሰው የፈለገውን የማሰብ ነፃነት አለው፤ ነገር ግን የክርስትና እምነት ከሌለው እውነተኛ የእየሱስ ተከታይ አይደለም።

በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ክፍለ ዘመናት እንደ ዛሬ ቤተ እምነቶች አልነበሩም፤ አንድ ቤተክርስቲያን ነበረች። ስለዚህ የእምነት መግለጫዎቹ የመላው ቤተክርስቲያን መግለጫዎች ነበሩ። በዛሬው ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን የሚያከብሩ አብያተ ክርስቲያናት በሌሎች በርካታ ጉዳዮች ላይ ባይስማሙም የእምነት መግለጫዎችን እምነት ይይዛሉ።

የጥንቷ ቤተክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር ያላት ግንኙነት ከሁሉም በላይ አስፈላጊ እንደሆነ ታውቃለች። ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት እንደዳኑ ያውቁ ነበር። አምላክ ምን እንደሚመስል ማወቃቸውን ማረጋገጥ ለእነሱ በጣም አስፈላጊ የሆነው ለዚህ ነው።

የይሁዳ መጽሐፍ በመጀመሪያ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠን እምነት መጠበቅ እንዳለብን ያስጠነቅቀናል (ይሁዳ 1፥3)። ወንጌልን በመስበክ፣ ምእመናንን ደቀመዝሙር ስናደርግና ወደ አገልግሎት የሚጠራቸውን በማሰልጠን በታማኝነት ስናገለግል እግዚአብሔር የእርሱን እውነት ይቀባ።

### ማስወገድ ያለብን ስህተት፥ የቤተ እምነት ትምክህት

በአንድ ድርጅት ውስጥ የተዋሃዱ የአብያተ ክርስቲያናት ቡድን ቤተ እምነት ይባላል። ክርስቲያን ነን የሚሉ በሺዎች የሚቆጠሩ ቤተ እምነቶች አሉ። የየትኛውም ቤተ እምነት አካል ያልሆኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ገለልተኛ አብያተ ክርስቲያናትም አሉ።

አንዳንድ ጊዜ ቤተ እምነቶች በስብከተ ወንጌል ይጀምራሉ። በአንድ ክልል ውስጥ ብዙ አማኞች ካሉ እና እነሱን የሚከታተል ቤተ እምነት ከሌለ አዲስ ቤተ እምነት ሊቋቋም ይችላል። በአንድ ሀገር ውስጥ ቤተ እምነት ከሚስዮን ድርጅት ሥራ ሊጀምር ይችላል።

አንዳንድ ጊዜ ቤተ እምነት የሚነሳው አንድ አስፈላጊ አስተምህሮ ተክዷል ወይም ተረስቷል ብለው በሚያምኑ ቡድኖች ስብስብ ነው። በአስተምህሮ ትክክል ለመሆን በማሰብ አዲስ ቤተ እምነት ይጀምራሉ። ትምህርቶቻቸውን በጊዜ ሂደት ማዳበርን ይቀጥላሉ። መጽሐፍ ቅዱስን ከሌሎች የክርስቲያን ቡድኖች በተለየ መንገድ ስለሚረዱ፤ አንዳንድ ትምህርቶቻቸው ከሌሎች ቤተ እምነቶች የተለዩ ናቸው።

ቤተ እምነቶች የአምልኮ ሥርዓቶችንና ክርስቲያናዊ አኗኗርን የሚመለከቱ ስርአቶችም ይቀርፃሉ። ቤተ እምነቶች በስርአቶቻቸው ይለያያሉ።

አብዛኞቹ የክርስቲያን ቤተ እምነቶች እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን እኛ ብቻ ነን አይሉም። አንድ ድርጅት በምድር ላይ ያለች የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን በሙሉ ነኝ ብሎ ቢደመድም ሊታመን አይገባም።

ብዙ ጊዜ የማያምኑ ክርስትናን የሚቃወሙት በመከፋፈሉና በልዩነቱ ነው። የማያምኑት የተለያዩ የክርስትና ቡድኖች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስላቸዋል። ብዙ የዓለም ሰዎች በክርስቲያኖች መካከል ትንሽ አንድነት እንደሌለ ያስባሉ።

በእውነት ክርስቲያን የሆነ ቤተ እምነት ወይም አጥቢያ ቤተክርስቲያን የጥንት የክርስትናን የእምነት መግለጫዎች አስተምህሮ ያምናል። ይህ በሁሉም የክርስቲያን ድርጅቶች መካከል ያለው የአስተምህሮ አንድነት ነው። በትንንሽ አስተምህሮ ጉዳዮች እና ስርአቶች ላይ ብዙ ልዩነት አለ፤ ነገር ግን በእነዚህ ልዩነቶች ምክንያት ቤተክርስቲያን እውነተኛ ክርስቲያን አይደለችም ልንል አይገባም።

### ማስወገድ ያለብን ስህተት፥ የግል እምነቶች ላይ ያለ አለመግባባት

አንድ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት ሲኖር፣ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት የመረዳት ችሎታውን ያሳድጋል። ሁልጊዜ ሌሎች ወደሚሰጡት መደምደሚያ ላይ አይደርስም። እውነትን በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ሲጠቀም፤ ሌሎች ክርስቲያኖች ከሚያደርጉት የተለየ መሠረታዊ ሥርዓቶችንና መመሪያዎችን ለራሱ ያዘጋጃል።

አንድ ግለሰብ ስለ እምነቱ ሲያስብ፣ ክርስቲያን እንደማይሆን እስካልወሰነ ድረስ፣ የጥንት ክርስትና መሠረታዊ ትምህርቶችን ለመቃወም ነፃነት ሊሰማው አይገባም።

አንድ ክርስቲያን በቤተክርስቲያኑ ላይ የተቀመጠውን አስተምሮ ማመን መቻል አለበት። የቤተ ክርስቲያኑ አስተምህሮ ስህተት ነው ብሎ ካመነ፣ እንደ አባል በእውነት ለቤተክርስቲያን መሰጠት ከባድ ነው።

አንድ ክርስቲያን በግለሰብ ደረጃ በቤተክርስቲያኑ አስተምሮ ይመራል። ነገር ግን ከሌሎች የቤተክርስቲያኑ አባላት የሚለይ የግል እምነት ሊኖረው ይችላል። የግል እምነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቀጥታ የተገለጸ ነገር አይደለም፤ አንድ ሰው የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ የሚጥርበት ነው።

እያንዳንዱ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ባለበት ሁኔታ ላይ በታማኝነት ሊጠቀምበት ይገባል፤ ሆኖም በራሱ መደምደሚያ በሌሎች ለመፍረድ መፍጠን የለበትም። ሁሉም ክርስቲያኖች የቀደሙትን የእምነት መግለጫዎች እንዲይዙ መጠበቅ ተገቢ ነው፣ እናም የቤተክርስቲያኑ አባላት የቤተክርስቲያናቸውን አስተምሮ እንዲይዙ መጠበቅ

ተገቢ ነው። ነገር ግን አንድ ክርስቲያን ሌሎች ሰዎች ከሁሉም የግል እምነቶቹ ጋር እንዲስማሙ መጠበቅ ትክክል አይደለም።

► የእምነት መግለጫውን ቢያንስ ሁለት ግዜ አብራችሁ አንብቡ።

## የእምነት መግለጫ

ቅዱሱ መጽሐፍ የመጀመሪያዎቹን የክርስትና አስተምህሮዎች እንድንይዝ እና እንድንከላከል ይነግረናል። የጥንት ክርስቲያኖች ለወንጌል እና ከእግዚአብሔር ጋር ላለን ግንኙነት አስፈላጊ የሆኑትን እምነቶች ገለፀዋል። እነዚያ መግለጫዎች አሁንም አስፈላጊ የሆነውን ክርስትናን ይገልጻሉ።

## ትምህርት 15 የቤት ስራዎች

(1) የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የቤት ስራ፦ ከታች ከተዘረዘሩት ዘርፎች መካከል እያንዳንዱን ተማሪ አንድ ይመደብ። ከሚቀጥለው ክፍለ ግዜ በፊት ክፍሉን አንብባችሁ በትምህርቱ ውስጥ ካለው ሃሳብ ላይ ምን እንደሚናገር በአንድ አንቀፅ ፃፉ።

- 1 ጢሞቴዎስ 3፥16
- 1 ጢሞቴዎስ 4፥1-7
- ቲቶ 1፥7-14
- 1 ዮሐንስ 4፥1-3፣ 14-15፤ 1 ዮሐንስ 5፥12
- ይሁዳ 1፥3-13

(2) ፈተና፦ የሚቀጥለው ክፍለ ግዜ የምትጀምሩት በትምህርት 15 ፈተና ነው። ለፈተና ዝግጅት እንዲሆን የፈተና ጥያቄዎችን አጥኑ።

(3) የማስተማር የቤት ስራ፦ ከክፍል ውጪ የማስተማርያ ግዜን ቀጠሮ መያዝ እና ማስተማራችሁን ሪፖርት ማድረግ አስታውሱ።

## ትምህርት 15 ፈተና

(1) የእምነት መግለጫ ምንድን ነው?

(2) ስለ እየሱስ ያሉትን ሑለት የመጀመርያ የእምነት መግለጫ ዓርፍተ ነገሮችን ጻፉ።

(3) ብዙ መግለጫዎችን ላሉት ለመጀመርየው የእምነት መግለጫ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማጣቀሻው ምንድን ነው?

(4) የሐዋርያት የእምነት መግለጫ አላማ ምንድን ነው?

(5) የኒቅያ የእምነት መግለጫ አላማ ምንድን ነው?

(6) የቀልቄዶን የእምነት መግለጫ አላማ ምንድን ነው?

# የሚመከሩ ምንጮች

**በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ስለተገለጹት ርዕሶች የበለጠ ለማጥናት እባክዎ የሚከተሉትን ምንጮች ይመልከቱ።**

Oden, Thomas C. *Classic Christianity፥ A Systematic Theology*. New York፥ HarperOne, 2009.

**የእግዚአብሔር መጽሐፍ**

Dockery, David S. *Christian Scripture*. Nashville, Broadman and Holman, 1995.

**የእግዚአብሔር ባህሪያት**

Purkiser, W.T., ed. *Exploring Our Christian Faith*. Kansas City, MO, Beacon Hill Press, 1960.

Tozer, A. W. *The Knowledge of the Holy*. New York, Harper and Row, 1961.

**ሥላሴ**

Reeves, Michael. *Delighting in the Trinity፥ An Introduction to the Christian Faith*. Downers Grove፥ IVP Academic, 2012.

Sanders, Fred. *The Deep Things of God፥ How the Trinity Changes Everything*. (2nd ed.) Wheaton፥ Crossway, 2017.

Sanders, Fred. "The Triune God of the Bible፥ Seeing the Trinity in Scripture" (lecture) available at www.youtube.com/watch?v=7w3FJLGgxKs

**ሰው**

Purkiser, W.T., ed. *Exploring Our Christian Faith*. Kansas City, MO, Beacon Hill, 1978. (See Chapter 10, "What is Man?")

**ኃጥያት**

Wesley, John. "The Doctrine of Original Sin," in *The Complete Works of Wesley. Vol. 9*.

Wilcox, Leslie. *Profiles in Wesleyan Theology*. Salem, OH, Schmul Publishing, 1985. (See Chapter 7, "Origin and Nature of Sin," 141-170.)

**መናፍስት**

Lewis, C. S. *The Screwtape Letters*. New York, Macmillan Co., 1968.

Wesley, John. "Satan's Devices." *Wesley's 52 Standard Sermons*. Salem, OH, Schmul Publishing, 1988.

**ክርስቶስ**

Strobel, Lee. *The Case for Christ*. Grand Rapids, Zondervan, 1998.

Torrance, Thomas F. *Incarnation፥ The Person and Life of Christ*. Edited by Robert T. Walker. Downers Grove፥ IVP Academic, 2008.

Wellum, Stephen J. *The Person of Christ፥ An Introduction.* Edited by Graham A. Cole and Oren R. Martin. Wheaton፥ Crossway, 2021.

**ድነት**

Purkiser, W. T., ed. *Exploring Our Christian Faith*. Kansas City, MO, Beacon Hill Press, 1960. (See Chapter XI and XII, "Man's Predicament," and "The Doctrine of Atonement.")

Wilcox, Leslie. *Profiles in Wesleyan Theology*. Salem, OH, Schmul Publishing, 1985. See Chapters 9-10, "Atonement" and "Conditions of Reconciliation," 171-214.

Wiley, H. Orton and Culbertson, Paul T. *Introduction to Christian Theology*. Kansas City, MO, Beacon Hill Press, 1946.

**በድነት ዙርያ ያሉ ጉዳዮች**

Shank, Robert. *Life in the Son*. Minneapolis, Bethany House Publishers, 1989.

Wiley, H. Orton and Culbertson, Paul T. *Introduction to Christian Theology*. Kansas City, MO, Beacon Hill Press, 1946.

**መንፈስ ቅዱስ**

Carter, Charles. *The Person and Ministry of the Holy Spirit, A Wesleyan Perspective*. Grand Rapids, Baker Book House, 1974.

Murray, Andrew. *Andrew Murray on the Holy Spirit*. New Kensington, Whitaker House, 1998.

**ቤተክርስቲያን**

Noll, Mark. *Turning Points*. Grand Rapids, Baker Academic, 1997.

Oden, Thomas. *Life in the Spirit*. Peabody, Prince Press, 2001.

**ዘላለማዊ እጣ**

Lewis, C. S. "The Weight of Glory," in *The Weight of Glory and Other Addresses*. New York, Macmillan Publishing, 1980.

Purkiser, W.T., ed. *Exploring Our Christian Faith*. Kansas City, MO, Beacon Hill Press, 1967. (See Chapter XXVIII, "The Future Life.")

Wesley, John. “The Great Assize.” *Wesley’s 52 Standard Sermons*. Salem, OH, Schmul Publishing, 1988.

### የመጨረሻ ሑነቶች

Ladd, George Eldon. *The Blessed Hope*. Grand Rapids, Eerdmans, 1992.

Wiley, H. Orton & Culbertson, Paul T. *Introduction to Christian Theology*. Kansas City, MO, Beacon Hill Press, 1949.

### ጥንታዊ የእምነት መግለጫዎች

Gonzalez, Justo L. *The Story of Christianity, Vol. I*. New York, Harper, 2010.

Noll, Mark. *Turning Points, Decisive Moments in the History of Christianity*. Grand Rapids, Baker, 2012.

# የቤት ስራዎች መዝገብ

**የተማሪ ስም**____________________________________________

**እያንዳንዱ የቤት ስራ ሲጠናቀቅ ምልክት ያድርጉበት። ተማሪው ፈተናዎቹ** 70% **ወይም ከዚያ በላይ ነጥብ ሲያመጣ እንደ “የተሟላ” ይቆጠራሉ። ከ**Shepherds Global Classroom **ሰርተፍኬት ለመቀበል ሁሉም ስራዎች በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቅ አለባቸው።**

| ትምህርት | ክፍል | ፈተና |
|---|---|---|
| 1 | | |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |
| 6 | | |
| 7 | | |
| 8 | | |
| 9 | | |
| 10 | | |
| 11 | | |
| 12 | | |
| 13 | | |
| 14 | | |
| 15 | | |

| ከክፍል ውጪ የማስተማርያ | |
|---|---|
| ቀን | ቦታ |
| | |
| | |
| | |

**የምስክር ሰርተፍኬት ማመልከቻ በ**Shepherds Global Classroom**፣ በድረ-ገጻችን** www.shepherdsglobal.org **ላይ ሊጠናቀቅ ይችላል። የምስክር ወረቀቶች በተማሪ (ዎች) ስም ማመልከቻውን ለሚሞሉ አስተማሪዎች እና አስተባባሪዎች ከ**SGC **ፕሬዝዳንት በዲጅታዊ መንገድ ይተላለፋሉ።**